

To Kill a Generation: The Red Terror in Ethiopia በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፎ የነበረውን መጻሕፌን ወደ አማርኛ የመለሰው ዝናሮው ታጋይ ፀጋዬ ገብረ መድኅን ነው። የቅኔና የሥነ ጽሑፍ ችሎታው በብዙዎች ዘንድ ተደናቂነት የነበረው ፀጋዬ ገብረ መድኅን በ፲፱፻፷ ዎቹ ዓመታት የተማሪ ማኅበር መሪ፡ የኢሕአፓ መሥራች አባልና የአመራር አባል ነው። በሥነ ጽሑፍና በግዕዝ ችሎታው ጎምቱና ወጻፎቹ ይብተራው ብለው ይጠሩታል።

ፀጋዬ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ፡ ሰላም፡ እኩልነትና ፍትኅ እንዲሰፍን ሰረጅም ጊዜ ታግሏል። ፀጋዬ ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ በገጠሩ ትግል ውስጥ በመቆየት ከፍተኛ መስዋእትነትን የከፈለ ሲሆን በ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጎንደር ከናሶ ሀገር ልዩ ስሙ ሳንኪሳ በተባለ ቦታ በወያኔ ሙር ተይዞ ከተመሰደ በኋላ እስከሁን መጻረሻው ሳይታወቅ ቀይቷል። የፀጋዬና የጓደኞቹ የደረሱበት መጥፋትና እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች ብዙ ሰዎች እየተገደሉ እየታፈኑና እየተሰቃዩ መሆናቸው የአሁኖቹ መረዎች የእገዛ ዘይቤ ከፈተኞቹ ብዙ እንደደማይለይ ያሳያል። እንደ ደርጉ ጊዜ "ቀይ" የሚል ስም ባይሰጠውም በወያኔ እገዛም መጠኑ ትንሽ ይልቁን ሽብር እየተባባደ መሆኑ አጠራጣሪ አደደለም። "አንድ ትውልድ ለመምተር ፡ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ " የተጻፈው ተመሳሳይ የትውልድ አልቂት በኢትዮጲያ እንዳይደገም ለመከላከል ነበር። ሽብር እያካሄዱ ላሉት የአሁኖቹ መረዎች የመጸሐፉ መልእክት ትምህርት የሆናቸው አደመስልም።

ባቢሌ ቶላ
፲፱፻፺፱ ዓ. ም.

አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ



አንድ ትውልድ ለመምተር
ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ

አባቢሌ ቶላ
ትርጉም
ከፀጋዬ ገብረመድህን

አንድ ትውልድ
ለመምተር

ቀዩ ሽብር
በኢትዮጵያ

በባቢሌ ቶላ

ፍሪ ኢትዮጵያ ፕሬስ

ትርጉም

ጸጋዬ ገብረመድኅን

ይህ የመጽሐፌ የእግርኛ ትርጉም በወያኔ እስር ቤት ለሚገኙት

ለጸጋዬ ገብረመድኅን፣
ለይስሐቅ ደብረጽዮን
ለሥዩታው ሁሴን
ለበለጠ እምሐ
እና
ሌሎቹም።

እንዲሁም ከኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ለሀገርና ለወገን ሲታገሉ ቆይተው በወያኔ ለተገደሉት

ለኝለብ ዳፍላ
ኃይሌ እባይና
ገብረ እግዚአብሔር ወልደሚካኤል (ጋይም)
ለሌሎቹም
መታሰቢያ እንድትሆን አበርክቻለሁ።

ባቢሌ ቶላ

© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

© copyright 1997

ለአማርኛው ትርጉም መግቢያ

ስለቀይ ሽብሩ በእንግሊዝኛ የተጻፈውን ፀጋዬ ገብረድኅን ከተረጉመው የቆየ ቢሆንም በልዩ ልዩ ችግሮች የተነሳ ላይታተም ዘገየ። በመሀሉ ያለደራሲው ፍቃድ አሳትሞ መሸጥ ልምድ በሆነባት ሀገራችን አንድ ግለሰብ መጽሐፉን ተርጉመው ለሽያጭ አቀረቡ። ይባስ ብለውም (ተገደው ሊሆንም ቢቻል) የመጽሐፉን ትርጉም መታሰቢያነት "ለኢሕአዴግ" ሰጡ። የበደል በደል!

የጸጋዬ ገብረድመኅን ትርጉም የመጽሐፉን መልዕክት በደረቁ ሳይሆን በውበት የሚያቀርብ ነው። የጸጋዬም ሆነ የመጽሐፉ ዕጣ የቀይ ሽብር ጣጣ ገና እንዳላከተመ ያመለክታሉ።

ደጋግመን እንደገለጽነው ቀይ ሽብር በማንኛውም ሥርዓት ሊወለድ የሚችል በመሆኑ የመጽሐፉ ዋነኛ ዓላማ ይህ ቅሥፈት/እርግማን ዳግም እንዳይወለድ ለማድረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነቅቶ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ እንዳለበት ለመጠቆም ለማሳሰብ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳለፈውን አሰቃቂ የመከራ ዘመን ለማዕዳን ማሳወቁም አስፈላጊ ሆኖ መጽሐፉ በእንግሊዝኛ ቢወጣም ይህን ቋንቋ የሚያውቁት በርካታ የሀገራችን ምሁሮች በእንባቢ ደረጃ የታሰቡ ነበሩ።

ቀይ ሽብሩ በፋሽስቱ መንግሥት ቢካሄድም በሂደቱ ተሳታፊው ለጉዳቱ ተጠያቂው በእሱ ብቻ የሚወሰን አልነበረም። የጠቆመ፣ ያጋለጠ፣ ጐረቤቱ ወገኑ ሲረሽን አላየሁም ያለው፣ ወጣት በጠራራ ፀሐይ ሲደፋ ፀጥ ያለ፣ ለእምባገነን አረመኔ ሥርዓት ያጐበደደ፣ ወዘተ ሁሉ ራሱን መጠየቅ፣ ኅሊናውን መመርመር ይገባዋል፤ ቀይ ሽብሩ

የደራሲው ማስታወሻ

በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸመው የሽብርና የግፍ ታሪክ በአንድ መጽሐፍ ቅጽ ተወስቶ የሚያልቅ አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥት «ቀይ ትርሺት» ብሎ መተራቱን የመረጠው፣ ያ ሽብር ጭሎ ያለፈውን የጎሊና ቁስልና በልዩ ልዩ ገጽታው ያስከተለውን መዘዝ ተንትኖ ለማቅረብ እንዲሁም በዓይነ ምክር የተደገፉ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠናከር አያሌ የመጻሕፍት ቅጾች ይጠይቃል።

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ወደር የማይገኝለትን ያን የሚዘገንን የመንሱት ወቅት በተሟላ መልኩ ማቅረብ ይቻል ዘንድ የሽብሩን መራራ ጽዋ የተጐነጩት አሁን በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የየራሳቸውን ታሪክ በማውሳት እንዲተባበሩ ደራሲው ተሥፋ ያደርጋል።

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የሽብሩ ቀጥተኛ የዓይን ምስክር የሆኑትን ብዙዎችን ያነጋገርኩ ሲሆን በተቻለበት ሁኔታ ሁሉ ሽብሩ ዋነኛ ዒላማ ያደረጋቸውን የኢሕአፓን አባላትም ጠይቂያለሁ። እስከተቻለ ድረስ የታሪኩን ምንጮች ጠቅሻለሁ። በጽሁፍ የዓይን ምስክርነታቸውን የሰጡኝ ፅሁፍተኛ መጠሪያ ስማቸው እንዳይገለጽባቸው ከማሳሰብ ጋር በመሆኑ፥ እኔም ማሳሰቢያቸውን አክብሬላቸዋለሁ፣ ተዘርዝረው የተጻፉ ሙሉ ስሞች ሁሉ እውነተኛ መጠሪያ ስሞች ሲሆኑ የመስካሪዎችን ሙሉ ስም ማስታወስ ባለቻሉበት ሁኔታ ግን ያባት ስም መጠቀስ አልተቻለም::

የሽብሩ አሰቃቂነት ዲካው እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመገመት የሚቻለው በወቅቱ ከነበረው ሁኔታና ከተቃርኖው ባህርይ አንጻር እንደመሆኑ መጠን ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ስንነሣሣ በታሪኩ ውስጥ ገናና ቦታ በያዙት (ግለትም በወታደራዊዉ መንግሥት፣ በመኢሶንና በኢሕአፓ) መካከል በእንጻድ መሠረታውያን ነጥቦች ላይ የነበራቸውን ልዩነት በአጭሩም ቢሆን ተችቶ ግለፉ የግድ ሆኗል፤ ሆኖም እኔህ የልዩነት ነጥቦች እኔ እዚህ ካቀረብኩት ይበልጥ በተጋሳና የተሰነዘረው በሚጆቹ ላይ (እነሱግ ሞቱ አበታ) ሳይሆን በቀረው ላይ ነበር።

በባርነት ካልተገዛችሁ፣ ካላጨበጨባችሁ ግራ እጅ እንስታችሁ ይውደም ካላላችሁ ወዘተ ... ታልታላችሁ ለማለት። የሽብሩ ጊዜ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን፣ ልኩን መፈተሸው ወቅት ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም። እርገጤ ተሸመ፣ ለገሠ መሳኩ ብሎ ከመኮነን ባሻገር የሁላችን ሚና ምን ነበረ ብለን መጠየቅ አለብን ያልነውም ለዚህ ነው። ገዳዩን መቅጣት አንድ ነው፤ ነፍሰገዳይ እግሎ በሺ ደረጃ ሊጨፈንና ለምን ተውነው፤ ዝም አልነው ብሎ መጠየቅ ደግሞ የበለጠ ጠቃሚ ነው። የርግማኑን መንስኤ ማወቅና ማስወገዱ በረዢሙ ፍሬያማ ስለሆነ።

መጽሐፉ የወቅቱ ባለሥልጣኖችና አጋፋሪዎቻቸው ለራሳቸው ሊጠቀሙበት ጥረዋል። በቀይ ሽብሩ በራሱም የፖለቲካ ችርቻሮን ለማካሄድ አየያፌ ሽብረብ ሲካሄድ ታዝበናል። እንደነና የሥልጣን ጥሜት ያሳበዳቸው ሽብርን አርግዘው ሊወልዱ ሲፍጨረጨሩም እያየን ነው።

የመጽሐፉ ተገቢው ትርጉም መውጣቱ የሽብሩ ተጠቂ ለነበሩትና በአዲሶቹ ባለነፍጠኞች መከራ እዩ ሳሉት ለፈረደባቸው ታሪክ ለማይረሳቸው ለዓይነታ ፀረሽብር የኢሕአፓ ልጆች መታሰቢያነት መቅረቡም የግድ በመሆኑ እንሆ!

ባቢሌ ተሳ።

ዘርዘር ባለ መልክ መቅረብ እንደሚያሻቸው ግልጽ ነው።

ይሄ መጽሐፍ ዕውን ይሆን ዘንድ ተመክሮቻቸውን ለደራሲው በማካፈል፣ የምስክርነት ታሪኮን በማሰባሰብ፣ ረቂቁን በማንበብና ጠቃሚ ትችት በማቅረብ ብዙ ሰዎች አስተዋጽዖ አድርገዋል፤ ስማቸው እንዲጠቀስ ግን ማንኛቸውም አልጠየቁም። ይህም ሆኖ ለት.ቆ.፣ ፍ.ኢ.፣ ቤ፣ አ.ናስርና ይ. እምሐ ልዩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የመጠኩትን ከግብ አደርስ ዘንድ ያበረታቱኝ "ሽ" እና "ተ"ንም አመሰግናለሁ። በርግጥም ይህ መጽሐፍ የተባበረ ጥረት ውጤት ሲሆን ከፍካሬውም (Intepretation) ሆነ ከትንታኔው ለሚመጣ ስህተት ሓላፊነቱን በሙሉ የሚወስደው ደራሲው ነው።

በመጨረሻም የሽብሩ ሰለባ ሁነው ለወደቁት፣ ከሽብሩም ለተረፉት አሁንም ከሽብሩ ኃይላት ጋር በትንንቅ ላይ ለሚገኙት፣ እንዲሁም በኢትዮጲያ ውስጥ በሠፈነው የሰብአዊ መብት መረገጥ ተቄርጽሪነቱን በማሳየት ለዚሁ መብት መከበር የታገሉትንና የሚታገሉትን ላበረታታው ለዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት (Amnesty international) ይህን መሕፍ አምሐ አድርጌ አቀርባለሁ።

ባቢሌ ቶላ።

አንድ ትውልድ ለመምተር ቀዩ ሽብር በኢትዮጵያ

ማውጫ

መቅድም 1

ክፍል አንድ፤ የሽብር ዋዜማ

፩ ኃያላን ያስገብራሉ 3
፪ የንጉሥ ነገሥቱ መውደቅ፣ የማን አብዮት? 15
፫ ኩሽኩ ሽብር፣ አዲሱ አምባገንነትና ሕዝቡ 33
፬ ምን ምርጫ? ምን ግትርነት? 57

ክፍል ሁለት፤ የይፋው ሽብር

፩ እርከን አንድ፣ ሂላማው ታወጀ 75
፪ ለምን ፲፱፻፷፱? 81
፫ የሽብሩ መጋበርት 85
፬ ከእርከን አንድ እስከ ቀይ ሽብር 91
፭ "አቫቶቹ" 101
፮ የሶቪየት ዝምድና 135

ክፍል ሦስት፤ ቀይ ሽብር ሲተረጉም

፩ የሽብሩ "አርበኞች" 155
፪ ምን ያህል? 185
፫ የተፈጻፀሙ ይናገሩ 191

ክፍል አራት፤ መደምደሚያ

ቀዩ ሽብር ዋጋው የከበደ ድል 237

መቅድም

«ገናናው ልዑል ሆይ» አለ እምላክ
«እውነቱን እናገራለሁ»

ሳሙኤል ጆንስን፣ ራስሌላስ፣
መሥፍን ኢትዮጵያ፣ ለንደን 1759

ዕድሜው አሁን ወደሃያ ቤት ማገባደጃ ላይ የሆነውን «ዬ» የተባለውን ጉልማሳ ታሪክ እንውሰድ። ከወገቡ በታች ሽባ ነው፤ አንድ ዓይኑን አጥቷል፤ ሁለት ጣቶች ከቀኝ እጁ ጉድለዋል፤ አስጨናቂ ሕልም አሁንም አሁንም እየተመላለሰ መንፈሱን ያምሰዋል፤ አብዛኛውን ጊዜም ቀውስ ውስጥ ይከተዋል፤ ምንብ የሚቀምሰው ላመል ነው። ታዲያ ተመልካቾን ወዬ! ያሰኛል።

በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ዬ የደስ ደስ ያለው፣ እወጣ እወጣ የሚል ደልደል ያለ ሰውነት ያለውና የሠመረ ሕይወት ለመኖር ተስፋው ብሩኅ የሆነ ወጣት ነበር፤ ግን መቼ ለዚህ ቢያድለው? አንድ ዕለት ማታ በመጋቢት ውስጥ በአንድ የመኢሶን ካድሬ የሚመሩ ስድስት የቀበሌ ዘበኞች እሱን ሲሉ መጡ። ከፖለቲካ ጋር ምንም አግባብ የሌለው «ዬ»ም ለጊዜው ደንገጠና እየተሩፋፋ በነበረው ፖለቲካና ወታደራዊ ግብግብ ውስጥ ምንም ተሣትፎ እንዳልነበረው አጋቾቹ ሲረዱ ወዲያውኑ እንደሚለቁት ተማመነ። ታሉን ለሚቀበሉት ምንም ውስጥ ስለሌለ በስሕተት የተያዘ መሆኑን፣ የኢሕአፓ አባል የነበረው ታላቅ ወንድሙም የት ሊገኝ እንደሚችል እንደማያውቅ ነገራቸው።

«ዬ» ያላወቀው ግን አጋቾቹም ሆኑ ቃል ተቀባዮቹ እውነቱን እየነገራቸው መሆኑ ላይ ጥርጥር እንዳልነበራቸው

ነው። በተይዞው ማኅስት «ዬ»፣ ከርሩቱ ወደሚያውድ ከፍል ተወስዶ ከታላቅ ወንድሙ ጋር ፊት ለፊት እንዲገናኝ ተደረገ። እሱንቱን ለመለየት እስከሚያስቸግር ድረስ ብርቱ የሆነ ግብረ ሰቆቃው* በዚያች ዕለት ተፈጽሞበት ነበር ያገኘው። በዚያች ዕለት ከዚያም በኋላ በተደጋጋሚ ጊዜ «ዬ» እዚያው በታላቅ ወንድሙ ፊት በእሥቃቂ ሁኔታ ግብረ ሰቆቃው ይፈጸምበት ገባ። እሪ ይላል፤ ነፍሰም ላይዘራ የሚቆይባቸው ጊዜያት ነበሩ፤ እንደፍላጉታቸው የተባለ ወንጀል ሁሉ ፈጽሚያለሁ ብሎ ሊለፈልፍላቸው ፈቃደኛ ይሆናል። ግን እኒያ የሰቆቃው አበጋዞች ለሱ ቃል ደንታ አልነበራቸውም። ፍላጉታቸው የታላቅ ወንድሙን ጽኑዕ መንፈስ ለመስበር ነበርና። እሱ ግን (ወንድሙ) «ዬ» አሥር ቢማለልና ቢማጠነው መች ፍንክች ቢል!

ከሳምንት በኋላ ደግሞ፥ ዕድሜያቸው ወደ ስድሣ እየተጠጋ የነበረው እናታቸው እንዲመጡ ተደረገ። እነርሱኑ ሁለት ልጆቻቸውን ለማሳደግና ለማስተማር ብዙ ቁም ስቅል ያዩ ሴት ነበሩ። ባላቸው ከሞቱ በኋላ ጸግመኛ እንዳለማግባተቸው መጠን የሚተዳደሩት ጠላ በመሸጥ ነበር። ሁለቱ ልጆቻቸውን እንዳልሆኑ ሆነው ባዩ ጊዜ የድንጋጤና የኀዘን ፍላጻ ሰንጥቆ ሲጥላቸው ጩኸታቸውን ለቀቁት። ያም የመከራቸው ምዕራፍ መክፈቻ ሆነ። በሁለቱ ልጆቻቸውና በስድስት የግብረ ሰቆቃው ሙያተኞች ፊት ልብሳቸውን እንዲያወልቁና እርቃናቸውን እንዲሆኑ ተገደዱ። እዚያው አልጾቻቸው ፊት ግብረ ሰቆቃው ተፈጸመባቸው፥ ተዋረዱ። ያም ሆኖ ያ ትልቅ ወንድም እንዳችም ትንፍሽ ያለው መረጃ አልነበረም፤ ፋሽስት ውሾች እያለ የሚሰነጨፍባቸውን ጩኸት አፍኖ ለማስቀረት እሱንም ከእናቱ ጋር ደርበው ግለታታቸው ለኒያ የዐመፃ ክንዶች አልፈየደም።

በመጨረሻም የግብረ ሰቆቃው ሙያተኞች እባለ ዘሩን ሰልበው በትንንሹ ከክታተፉት በኋላ እኒያን እናት አስገድደው አበሏቸው። እሳቸውም ከዚያ በኋላ ልቡናቸው ተለያቸው፤ በዚያው ሩታቸውን ስተው ከእሥር በተለቀቁ በዚያኑ ዕለትም ሕይወታቸውን በገዛ እጃቸው አጠፉ።

ይኸው በእምቢተኛነት የጸናው ትልቁ ልጃቸው በፒያኖ ሽቦ ታንቆ እንዲገደል ተደርጎ የቀይ ሽብር ትዕይንታቸው አካል ይሆን ዘንድ ከአውራ ጉዳና ወጥቶ ተጣለ። ዬ ግን ከዚያ በኋላ ሦስት ዓመታት ታሥሮ በ1972 ዓም ተለቀቀ።

የተድሞ ስብእናውን ቀር ብቻ ይዞ፣ ድውይ ሽባ ሆኖ አትቱ ላይ የኑሮ ዕጣ፣ የመንፈስ ሽክም ሆነ።

ይህ ታሪክ ወይ ጉድ ተበሎ የሚታለፍ የተናጠል ታሪክ አይደለም፤ ከዚህ በጣም የሚሰቀጥጡ፣ ይበልጥም የሚዘገንኑ፣ ለማመንም የሚያዳግቱ ድርጊቶች በመላ ኢትዮጵያ ተፈጽመዋል። ይህንና ይህን የመሳሰለው፣ በወታደራዊው መንግሥት ከ፲፱፷፰ እስከ ፲፱፸፫ ዓ.ም የተካሄደው ገደብ ያልነበረው ጭፍን የጅምላ ግድያ ተካትቶ ነው ሽብር የሚባለው። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተፈጻይተው ሞቱ፤ ከዚያ በላይ የሚሆኑ ደግሞ ፀዮትወ – ሰቆቃው ተፈራርቆባቸው ወደወህኒ ቤት ተጣሉ። እንዲህ ብለው ሲናገሩት ግን ባዶ ቃል ሆኖ ይሰማል፤ ደረቅ ስታቲስቲክ፣ በጣምም አጠቃላይ ይሆንና የሽብሩን አስከፊ ገጽታ ፍንትው አድርጎ ለማሳየት አይሆንለትም። መግደል፣ መሞት የተለመዱና የአዘቦት ቃላት መሆናቸው ያሳዝናል። ሞተ፤ ተገደለ፤ ሲባል በዚያች ቅጽበት እንግላ እየሆነ ማስደንገጡ ባይቀርም እሱንም ቢሆን እየለመድነው መጥተናል። ሰውን፣ የራሱን ሥጋ መትሮ ማብላት፣ ጥፍሮቹን መንቀል፣ በፈላ ዘይት ውስጥ መዝፈቅ፣ ሽንትና ሠገራ የጠጣ ጨርቅ አፍ ውስጥ መጭመስ፣ እፍንጫውን በጢንላ ቦጭቆ መጣል፣ በሴት ብልት ውስጥ ጠርሙስ መጠርመስ፣ የጡቶቿን ውልቂልቢት መቁረጥና መላ ጡቶቿን መቁረጥ፣ የሚያፈቅሩትን ተመልካች አድርጎ ካሰቃዩ በኋላ እንገቱን መቅላት፣ ወይም በፒያኖ ሽቦ አንቆ መግደል በተለምዶ እንደሚጠራው፣ ግድያ ብቻ ሊባል አይችልም፤ ቀይ ሽብር እንኺ ይህ ነው።

በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ በአካያነት ሊታይ የሚችለው የካቲት ፲፬፻፸፰ ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ የተፈጸመው የግራዚያኒ ጭፍጨፋ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ የሞሶሎኒ ልዩ መልዕክተኛ በአዲስ አበባ፣ ማርሻል ግራዚያኒ፣ አብርሃ ደቦቄና ምኅሥ አስገዶም የተባሉት ወጣት አርበኞች የእጅ ቦንብ ወርውርውበት ከሞት የተረፈ ሲሆን፤ በዚያ ከበብ ማርሻሉ ለምፅዋት አሰባስቧቸው የነበረው የከተማይቱ ነዳያን፣ ለበቀል መወጫ ወዲያውኑ ተረሸኑ። ከዚያም ለ፫ ቀናት «ብላክ ሽርትሽ» ተብለው የሚታወቁት ወታደሮች እገሌ ተእገሌ ሳይሉ ይገድሉ ዘንድ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ላይ መረን ተለቀቁ፤ በብዙ ሺህ የሚቁጠር ሰው አለቀ፣ ከዚህም ውስጥ በቡዙ መቶ የሚቁጠሩ የሀገሪቱ

ምሁራን ይገኙበታል። ይህች ዕለት እስካሁን በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታስባ ትውላለች።

ባሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች፣ ሽማግሌዎችም ሆኑ ወጣቶች ይህን ወታደራዊ መንግሥት ፋሺስት ይሉታል። የሌተና መንግሥቱ እንዱ ቅጽል ስም ግራዚያኒ ነው። የሆነ ሆኖ፣ የ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ጭፍጨፋ ቀይ ሽብሩ ጋር ሊወዳደር አይታጣውም። ያለቀው ሰው ብዛት፣ በመንፈስ ላይ አሥምሮ ያለፈው የሰቀቀን ሰንበር ሊታሰብ፣ በማንኛውም የግፍና የጭካኔ መለኪያ ቀይ ሽብር የበላይነቱን ይይዛል። እንድ ወጣት ትውልድ ያልምንም ማጋነን ከህገሪቱ ምድረ ገጽ እንዳልነበር ሆኗል። ዕድሚያችው ከአሥር ዓመት በታች የነበር ያልባለቱ ልጆችን፣ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን ሽብሩ አላለፋቸውም። ትንሽ ትልቅ ላይል ከተማዎችን ሁሉ ደቧቸዋል። ይህ ሁሉ የተፈጸመው እገር በቀል በሆነና ሕዝባዊ ኑኝ በሚል መንግሥት መሆኑ ስሜት ላይ የፈጠረውን ቁስል ይብልጥ የሚያንገበግብና ይብልጥም የሚከነክን አድርጎታል። ቀዩ ሽብር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ካሉ አስከፊ ምዕራፎች ጉልሁን ምዕራፍ ይይዛል።

ይህን ምዕራፍም ነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማቅረብ የምንሞክረው። የጓለት ዲሞክራሲና ነጻነት ቀርቶ በምትኩ ሽብርና ሞት እነሆ ስለተባለ ሕዝብ አሳዛኝ ታሪክ ነው የምናወሳው። ሽብሩ፣ የሕዝብን እምነትና ድጋፍ ለማግኘት የተነሳው ምንግሥት ይሁንኝ ብሎ ዓልሞ የተነሳበት የጥረገው ፖሊሲ ነበር። ሽብሩ ያስፈለገበት ምክንያት ፖለቲካዊ ተቃውሞን ለማፋፈን፣ ለትግል የተነሳሣ ሕዝብን ፍርሐት ረዓድ ውስጥ በመክተት ሰጥ ብሎ የሚገዛ ግዑዝ ፍጥረት ለማድረግ ይቻል ዘንድ ዓይነተኛና ቀልጣፋ ውጤት የማያሳይ ዘዴ ነው ተብሎ ስለታመነበት ነው። የወታደራዊው መንግሥትና ጭፍን ኢሰብአዊ ስሜት ጎሊናቸውን የሰወረው ባለሟሎች በቃሳት ጉንጉን፣ በንግግር ፈሊጥ አሽሞንሙነው ሊያቀርቡት የሚሞክሩት ገጽታ፣ የተሸሞነሞነበት ግልባብ ሲገፈፍ ፈጥጠ የሚቀርበው ሀቅ ይኼው ነው። የቀይ ሽብሩን ትክክለኛ ታሪክ ማወቁ የሚረዳው፣ በሕዝብ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ግድያ ለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን፣ ሀገሪቱ በዚህ ቀን ይቆማል በማይባል የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ለምን እንደተዘፈቀችም ለመረዳትም ጭምር ነው። ከዚህ ሌላም ደግሞ፣ ይህ ታሪክ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለበት፣ ውድ ተመክሮ የተገበየበት እንደመሆኑ መጠን በእንዲህ

ዓይነት ተመሳሳይ ሁኔታ ሊወድቁ ለሚችሉ ሌሎች ሕዝቦች ዓይነተኛ መምህር በመሆን ታሪካቸው በእንዲህ ዓይነት ፀፀትወ መከራ እንዳይቀልም መዘከር ሊሆናቸው ስለሚችል ነው።

በመጨረሻም ይህን ታሪክ የምናወሳው፣ ለቀይ ሽብሩ ስለባ ሆነው ለወደቁቱ፣ ለሞቱቱ ሁሉ ሰንበሩን ለተሸከሙቱ፣ በወሀኒ ቤትም ለሚገኙቱ፣ መሥዋዕትነታቸው እንዳልተረሳ ከልብ ለመግለጽ ነው። በእዋሽና በአሰበ ተፈሪ ለተገደሉት ሳብ አደሮች ከተገጠመው ታዋቂ ግጥም የሚከተሉትን ስንኞች እዚህ ላይ ያስታውሷል፤

«የደምም ድምፅ አለው የንጉጓድ ጮኽት፣
ብራቅ ነው ይሉኝል የሳብ አደሩ ሞት፤»

ክፍል አንድ

የሽብር ዋዜማ

ኃያላን ያስገብራሉ

«ነፃ ምርጫዎች በመርዝና በጩቤ፣ ውይይት
በጥይትና በሥቅላት የተተኩበት ፣ ሥልጣን
ለመጨበጥ (ወይም በሥልጣን ላይ ለመቆየት)
እጅግ ጭካኔ የተመላበትን ዘዴ ብቻ
የምታውቅ ሀገር ነው ኃይለሥላሴ የገዛው።»

ከ«ንጉሠ ነገሥቱ፤ የፈላጭ ቆራጭ ነጋሲ አወዳደቅ»
The Emperor
Down Fall of an Autocrat
በኔር ካፑቺንስኪ
ቪንቲጅ ቡክስ፣ ኒውዮርክ፣ 1984 ገጽ101

በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት መቼም መች ግለት ይቻላል ኃይል ላይ የተመሠረተ ነበር። የሀገሪቱ በርካታ ታሪክ ነጸኞና ምዕራፍ የተሞሉት ባለሥልጣኖች ሕዝቡ ላይ ባደረሱት ግፍና ጭፍጨፋ ነው። ገዥዎችም እርስበርሳቸው መጋጨታቸው አልቀረም፤ ሁኖም ግን «በዝኖናኝ ጠብ፣ በመሃሉ የሚጐዳው የሚረጋግጡት ሣር ነው» እንደተባለው እነሱ በተጋጩ ቁጥር የሚረገጥ፣ የሚጨፈጨፈው ምስኪኑ ተራ ሕዝብ ነበር። ፈጨዳላቂት ኢትዮጵያ ጠመንጃን ያመለክች፣ ለሱም ስትሰግድ የነበረች እንደመሆኗ መጠን ግድያ የዘወትር ክሥተት ነበር፤ አረመኔነትም እንደቁራጠኝነት ይቁጠር ነበር። ይህም ደግሞ ገዥዎች እንከተላለን ከሚሉት ሕገ ክርስትናና ክርስቲያናዊ

ሥነምግባር ጋር ሲጓረር ከቶ አይታያቸውም።

እንደሌሎች ብዙ ሀገሮች ሁሉ ኢትዮጵያም የተቈረቈረችው በኃይል ነበር። ቅድመ ምኒልክ ዘመን (ማለትም ቅድመ 1889) በፈውዳላዊ መሣፍንትና መኳንንት እንዲሁም በዙፋን ተፎካካሪዎች መካከል ያልተቋረጠ ጦርነቶችን የሚያሳይ ገጽታ ነበረው። ጦርነቶች ብዙ መንደሮች የሚደመሰሱባቸውን ሀብት፣ ንብረት የሚወድምባቸው፣ የብዙ ሺህ አርሶአደሮች ሕይወት የሚጠፋባቸው የእልቂት ወቅቶች ነበሩ። ፈውዳላዊዉ ጅር ወይም ሠራዊት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ከሕዝብ መዝረፍ የተገባው፣ የሚጠበቅበትም እንደሆነ በጽሁፍ ባይደነግግም፣ የዚያኑ ያህል የተረጋገጠ ነበር ለማለት የሚቻል ወይንም «የተፈጥሮ» /የተለመደ የሆነ ሕግ ነበር። የዘረፋው ክፉ ዕጣ ሠራዊቱ ከሚነሳበት ነቋጣ ሬቅ ብለው የሚገኙ መንደሮች ሁሉ ይደርስባቸዋል። ወደማዕርግ ዕድገት ማሻቀቢያው ጎይል ጉልበት ብቻ ነበር። ከተራ ሰው ደረጃ ተነሥተው በጎይል በጉልበታቸው ዙፋን ላይ ለመውጣት የቻሉት ወዜ ቴዎድሮስ በዓይነተኛ ምሳሌነት ይቀርባሉ። ጎያላን ይገዛሉ፣ ጎያላን ያስገብራሉ፤ ይህ ነበር ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ሕግና ደንብ ሁኖ የቈየው።

የዛሬዉይቱን ኢትዮጵያ ዳር ድንበር በመደካት ወቢይ ሚና የነበራቸው ዳግማዊ ወዜ ምኒሊክ ወደደቡብና ወደሌሎች አካባቢዎች ያስፋፉት ያካባቢውን ሕዝብ ዕብሪትና ትምክህት ለተመላበት ኃይል እንዲንበረከክ በማድረግ ሲሆን ተቃውሞው በመነከረ መጠንም ዕልቂቱም በዚያው ልክ ጨምሮ ነበር፤ ብዙ ተቃውሞ ያላሳዩትም ቢሆኑ የሚደርስባቸው ዘረፋ ለክት አለነበረውም። ጉራጌዎች፣ ወላይታዎች፣ ኦሮሞዎች ... ወዘተ የተዘውተረ ጭፍጨፋ ደርሶባቸዋል። ትምህርት ያልቀሰሙ ለዘረፋ የተሠለፉ ከአማራውና ከትግራይ አካባቢ የተሰባሰቡ መንጋ ነፍሰገዳዮች እድራጉታቸው እንደጀግንነት ተቈጥሮላቸው፣ ነፍጠኞች ተብለው በዘረፉ ሲሞገሱ፣ በጥቃ ሲወደሱ፣ ንጉሡ ደግሞ ከዚያው ከተያዘው መሬት ጋሻ መሬት በመሸለም ርስተኛ ጉልተኛ እያደረጓቸው፣ ያካባቢው አርሶ አደር ግን አስከፊ ከሆነ የግዙነት ደረጃ ወደቀ። የዚያን ጊዜው ፍትሕ ማጣትና በዚያን ጊዜ የበቀል ጥላቻ እስከዛሬ ድረስ ሥር እንደሰደደ ነው። (1)

ያለፉት የኢትዮጵያ ገዥዎች የተወለኑ የእምነት ልምዶቻቸው ከክርስተና እምነት ጋር ጉልህ በሆነ መንገድ መፃረራቸው

እንዳለ ሁኖ ለክርስትና እምነት ሬሳቸውን ያስገዙ መሆናቸውን ምንጊዜም ያረጋገጡ ነበሩ ማለት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ግን ሃይማኖታቸው መጅም ቢሆን የተግባራቸው መመሪያ አልሆነም። ለሰንበት ቅዳሴ እረፈድኩኝ ብሎ እበሰኩ ገበርኩ፣ እዩዩ የሚል የመሬት ከበርቴ፣ ሙሉ የአርሶ አደር ቤተሰብ ሲገድል ትንሽም ኅሊናውን አይሰቀጥጠውም። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ዐቢይ ያም (ሁዳዴ) የሻረውን፣ ሰው ሁሉ ፊት ቢኖሰው መንገደኛን ግዙን ለመዝረፍ፣ ወይም መፃሪያውን ለመንጠቅ ሰው የገደለውን ግን አፍ አውጥቶ የሚያነውረው የለም። በ፲፱፻፺ዎቹ ዓ.ም ውስጥ ከታሳሳቆቹ ፈውዳላዊ መሣፍንት እንዱ የነበረው ራስ መሥፍን ልጁ የሽንጥ ተኩስ ሲለማመድ ዒላማ የሚያደረገው አርሶ አደሩን ነበር። ታዲያ ይህ ጀሬ ተብሎ ይጠራ የነበረው ነፍሰ ገዳይ በፈውዳሎች አካባቢ በ«ወንድነቱ» በተኳሽነቱ መደነቅን ነው ያተረፈው። ለነገሩማ ሕዝብ እንዲጨፈጭፍ ትእዛዝ የሚሰጡት ነገሥታት ነበሩ። «የሃይማኖት ጠባቂ» ተብለው ይጠሩ የነበሩት።

ዋናው አስምረንበት ለማለፍ የምንፈልገው፣ ግድያ አመጽፅ እየተዋረሰ ከመጣው ብሔራዊ ግዕዘ ልቡናና ማኅበራዊ ባህል ጋር የሠመረ እንደነበር ነው። ይህን ስንል ደግሞ ኢትዮጵያውያን በተፈጥሯቸው የእመፃ ሰዎች ናቸው የሚል እንድምታ ለመስጠት አይደለም፤ ኢትዮጵያውያን የትም ቦታ እንደሚገኘው ሕዝብ ሁሉ ሰላም ወዳዶች ናቸው። ልናሳይ የምንፈልገው ነጥብ፣ በገዥዎቹና በሕዝቡ መካከል የነበረው ግንኙነት በአብዛኛው መልኩ በጎይል ላይ የተመሠረተ እንደነበር ነው። በህብታምና በድኃው፣ በባልና በሚስት፣ በወላጅና በልጆች መካከልም የነበረው ገንኙነት ጎይልን ምርኩዝ ያደረገ ነበር። ወዜ ኃይለሥላሴ ሚኒስተሮቻቸው ስህተት ሲፈጽሙ፣ አባት ልጁን እንደሚቀጣው ገለል አድርገው በግርፋት ይቀጡ ነበር። የሚገረፉቱ ክፉ ስላደረጉ ሳይሆን «ልካቸውን እንዲያውቁ» እንጂ። ሳይታሰብ፣ ባስፈለገ ጊዜ ጎይልን ማሳየት፣ ደካማው፣ ተገዢ «ጌታ ማን እንደሆን እንዳይዘነጋው ያስታውሰዋል።» ባህልና ሃይማኖት (ሕጉም ጭምር) ተገዥዎች ይህን እንደዕድል ፈንታቸው እንዲቀበሉት ያዝዟቸዋል። የወዜ ኃይለሥላሴ ሕገ መንግሥት «የንጉሠ ነገሥቱ ሰውነት ከቡር ንኡድ ነው፤ ሥልጣኑም እይነሥም» ብሎ ይደነግጋል። ፅጵ ሳቱም «ሥዩመ እግዚአብሔር» ሳይ ለማመፅ የሚደፍራትን ፈጥነው ለማውገዝ ነቅተው ይጠብቃሉ።

ውይይት፣ ማኅበባት፣ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ መቻል ይህም ትክክልና ተገቢም መሆኑን መቀበል ጨርሶ የሚታወቅ አልነበረም። ሰጥ፣ ለጥ፣ ያዝ፣ ጠበቅ፣ አድርጎ የማይገዛ ገዥ፣ የራሱን ድቀት የሚጠራ ነው። እባት ሲፈራ እንደደካማ ከመቁጠሩም በላይ ልጆቹን ያባልጋል ይባላል። ሠይፍና ከዘራ የሥነሥርዓት መከሠቻዎች ሁነው አማራጭ የሌላቸው የእዝ ተዋረድ ማስጠበቂያዎች ነበሩ። ቤተሰብ ጠንካራ አባት ያስፈልገዋል።፤ ሀገርም ፍጹም ሥልጣን ያለው ገዥ። ፈውዳላዊ ሥርዓት በተንሠራፋባት ኢትዮጵያ ደግ፣ መሐሪ የሆነ ገዥ በጥርጣሬ ዓይን ሲታይ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ግን የደንቡ ነው። እሜን ብሎ መቀበልም የዘወትር ልምድ ነው። ቅጣት የግድ ጭካኔ የተመላበት መሆን እንዳለበት ይታመንበታል። ቤት የሚያውክ ሙሌ ኩታራ ቁልቁል ተሰቅሎ በርበሬ ይታጠናል። ያመፀ በሰም ተንከር በእሳት ሲጋይ የመሬት ከበርቴዎች በእንከርና በእርካታ ይመለከቱታል።

ብዙ ምዕራባውያን "ዘመናዊ ዐዋቂና አስተዋይ" ይሏቸው የነበሩት ኃይለሥላሴ ይህን በመሰለች ኢትዮጵያ ላይ ነው የነገሡት። በእርግጥም በዚያ መንገድ ልትገዛ የምትችል እንደዚያ ያለች ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች። ዐፄ ኃይለሥላሴ ሕጎች ቢደነግጉም፥ ስለኋላቀር አገሮች ያሳቸው ግምገማ ግልብነት የሚያጠቃውን የውጭ ተመልካቾችን አስተያየት ለማለዘብ የታለሙ ከመሆናቸው በቀር ከወረቀት አልፈው በግብር ላይ የሚውሉ አልነበሩም። የ፲፱፻፶፩ ዓ.ምሕረቱ ሕገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ መብቶችን -የንግግር ነፃነትን ጨምሮ- ያረጋገጠ ሲሆን፥ ስነር ያምበላሰሰው ሰው መንግሥት (መንግሥትና ንጉሥ ተወራራሾች ናቸው) ላይ ሳያስበው የሚወረወረው ነቀፋ በክብረነክ ወንጀል ከአምስት አስከሰባት ዓመታት እስራት እንዲከናነብ ያደርገዋል። ዐፄ ኃይለሥላሴ በከፋፍለህ ግዛ መርህና በፈውዳላዊ ተንኮል የተካኑ ሆነው ሳል፥ በተጨባጩ የገዙት ግን ሰጥ፥ ለጥ ያዝ ረገጥ በማድረግ ነበር። ወደዘፋንም የወጡት ተንኮል ሠርተው ልጅ እያሱን በመገልበጥ በኋላም እንደሚነገረው ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው የነበሩትን ንግሥት ዘውዲቱን በመርዝ በመግደል እንደነበር መች ይረሳል?

እኒሁ «ዐዋቂና አስተዋይ» ንጉሠ ነገሥት በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. አራአና ፋላቺ ለተባለችው የጣሊያን ጋዜጠኛ በሰጡት ቃል፤ «የኔጋሲ ዘር እንደመሆናችን መጠን ሥልጣን የባሀርይ ግንዘባችን ነው። አንድ ንጉሥ በኃይል በመጠቀሙ ሊፀፀት አይገባውም፤ ... ቄራጥ እርምጃ ለመውሰድ ወደኋላ ብለን አናውቅም። ለሕዝቡ የሚበጀውን የሚያውቅ ንጉሠ ነው፤ ሕዝቡ ራሱ እያውቀውም» ይህ እንግዲህ በንጉሣዊ ትምክህት የተገፈፈና የተጠናከረ ዓይን ያወጣ ጭካኔ ነው። መጨከን አለመጨከን አለመቻል የደካማነት ምልክት ነው። ደግ፣ ይቅር ባይ መሆን አመፅን ይወልዳል። የተገኘ ፈቃድ አይጠየቅም፤ ሞኝ ደንቆሮና ወይንም አሁን የተወለደ ጨቅላን ማን ምክር ወይም ሐሣብ ይጠይቀዋል? ባንድ ቃልም ሕዝብ የሚበጀውን የማወቅ ተውህቦውን ተገፍፎ በእግዚአብሔር የተቀባው ንጉሥ እንዳፈተተው የሚያደርገው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን ላይ፣ የሚያምፅ እንደኑሩቴ ይቁጠርበታል። መናፍቃንን የመቅጣት ጉዳይ ሲመጣ ደግሞ የኢትዮጵያ ገዥዎች ከሲፖኞቹ የመናፍቃን ምርመራ (The Inquistion) አበጋዞች የሚግሩት ምንም አልነበራቸውም።

በንጉሠ ነገሥቱ ረጅም የግዛት ዘመን በመንግሥት ትእዛዝ በግልጽ በሕዝቡ ላይ የአመፃ በትር ወርዶበታል። የሕዝብ አመፆች (በጉጂም፣ በባሌ፣ በትግራይ) ጭካኔ በተመላበት መንገድ ተደምስሰዋል። ሰላማዊ ሰልፈኞች በቆመጥ ተደብድበዋል፤ በጋዝ ጠስ እንብተዋል፤ ተገድለውማል። (የ፲፱፻፶ምቹ መጨረሻና ፲፱፻፷ምቹ መጀመሪያ የተማሪዎች ሰላማዊ ሠልፎች) የተቃዋሚ ግለሰቦች ግድያ በእነር ውስጥም በውጭም በልዩ ልዩ ስኳዶች (እፉኝ ዓይኖች) ይካሄድ ነበር፤ (ለምሳሌ ካርቱን ከበደ፣ ካርቱም ውስጥ፣ ሌሎችም ሞቃዲሾና ሳና ውስጥ) የኤርትራ ሽምቅ ውጊያ በመንደሮች ላይ ከፍተኛ ግፍ እንዲፈጸም በር የከፈተ ሲሆን የደረሰው የሰው እልቂት የዓለምን ሕዝብ ጆሮ ለመኩርኩር ከሚችልበት ደረጃ ደርሶ ሊስተጋባ ባለመቻሉ «ደጉ ንጉሥ» እንዲያውም «የአፍሪቃ አባት» የሚለውን ስያሜ የተቀጸሉትን የፈላጭ ቆራጩን ንጉሥ ገጽታ አላቀለመውም። ባጭሩ ዐፄ ኃይለሥላሴ በሥልታቸው የተሬቀቁ ይሁን እንጂ ካሳፉት ፈላጭ ቆራጭ ነገሥታት የሚለያቸው ነገር ከቶ አልነበረም። ቴዎድሮስም፣ ዮሐንስም፣ ምኒልክም ቢሆኑ የግዛት ዘመናቸው ግድያ የተትረፈረፈበት ነበር። እንደኃይለሥላሴ ማኪያቬሊን እንኖኖውም ያነበቡ ባይሆኑም በተለያየ ደረጃ በፈውዳል ተንኩል ውስጥ የተዘፈቁና በኃይልም ከሀሊነት የሚያምኑ ነበሩ። እርሶ እደሩ ለሁሳቸውም ያው ገባር ነው፤

የሚጉነበስላቸው፣ የሚንበርላቸው፣ የሚያገለግላቸው፣ የሚሞትላቸውም፤ ... ሁሉም፣ ኃይለሥላሴም ጭምር በእርሶ እደሩና፣ ምርቱን ለመሬት ከበርቴው ጭኖ በሚያመጣቸው የቤት እንስሳት መካከል የነሳ ልዩነት አይታያቸውም ነበር ብሎ መናገር ማጋነን አይሆንም።

የግብረ ሰቆቃው መፈጸም ላለፉት ነገሥታት እንግዳ አልነበረም። ዐፄ ኃይለሥላሴ ግን በሥልጣኔ፣ በተራመዱት በአሜሪካና በእሥራኤል መንግሥታት እርዳታና መምህርነት ሊያራቅቁት በቅተዋል። ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች ጠበብት እንዲመጡ ተደረገ፤ ኢትዮጵያውያንም ወደቴላቪቭና ዋሽንግተን ወደሚገኘው ኢንተርናሽናል ፖሊስ አካዳሚ ተልከው ጉልዳፋ የነበሩት ሥልቶች ርቀትና ጥበት እግኙተው እረመኔያዊነታቸው የላቀ ሆነ። እንዲህ ዓይነቱን ጥበብ የቀመሱት ተማሪዎች የእሁኑን የኩሎኔል መንግሥቱን ወታደራዊ መንግሥትም ማገልገላቸውን የቀጠሉ ሲሆን በዚህኛው ዙር ደግሞ ሶቭዬት፣ ኪዩባ፣ ምሥራቅ ጀርመን ላበረከቱት ትምህርት ምሥጋና ይግባቸውና በጥበብ ላይ ጥበብ እንዳከሉ መጠቀስ ያለበት ነው።

የእጅ ጣቶችን በጮጋሰ ቦጭቆ መጣል፣ እሸዋ ወይም ወጋ የተሞላ ጠርሙስ ከቄለጥ ላይ በማንጠልጠል ከጥቅም ውጭ እንደሆነ ማድረግ፣ እጅ እግር ሽባ ማድረግ፣ ውስጥ እግርን መግረፍ፣ ቁሻሻ ወጋ ውስጥ መዝፈቅ፣ ከባድ እግረሙት እግር ላይ አስገብቶ ከጪለመ ምድር ቤት ውስጥ ማሠር፣ ማስራብ፣ የብረት ሠንሰለት እንደልዓም ከአፍ ውስጥ አስገብቶ ጥርሶችን ለመስበር ወደኋላ መሳብ፣ መድፈር፣ ... ወዘተ ወዘተ ... የኃይለሥላሴ እሥረኞችና ተቃዋሚዎች ይደርስባቸው የነበረ ነው። እንዱ የሥቃይ ጉረኖ የሆነው ከአፍሪቃ እንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ቢጣሩ በሚሰማ ርቀት ላይ ያለው ማዕከላዊ ወህኒ ቤት «ዓለም በቃኝ» (ዕውነትም ዓለም በቃኝ! ፈውዳሎች ነውረኛ ፈዝ እያውቁም ማን አለ?) ይባል ነበር። (ዓለም በቃኝ አሁንም አለ) እንድ የማይካድ ነገር፣ ዐፄ ኃይለሥላሴ ሽብርን የተጠቀሙበት በነሲብ አልነበረም፤ ሆኖም መጠቀሙን ተጠቅመዋል። ኤርትራ ውስጥ የተማረኩ ሽምቅተዋጊዎች ግብረ ሰቆቃው ከተፈጸመባቸው በኋላ ይገደሉ ነበር፤ ባሌ ውስጥ ወላጆቻቸውን አስፈራርቶ ለማንበርከክ ሲባል የሕፃናት ጆሮ ተቁርጧል። ምናልባት በግርግር ውስጥ የተፈጸመ የወታደሮች እድራጎት ነው ሊባል ቢችልም

እድራጉቱ እንደወንጀል ስላልተወሰደ በዚህ ለፍርድ የቀረበም፣ የተቀጣም አልነበረም።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ እዬ ኃይለሥላሴ ከፍርሐት የተነሣ የሚፈሩ፣ የሚከበሩ፣ ሥልጣናቸው የማይጠየቅ ንጉሥ ነበሩ። የግርማዊነታቸው ሮልስ ሮይስ መኪና አውራ ጎዳናው ላይ ብቅ ባለ ጊዜ ባለህበት ቆመህ መኪናው ሲያልፍ ዝቅ ብለህ እጅ መንሣት አለብህ። እንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች ይህንን እድራጎት ንጉሥ ነገሥቱን ከማፍቀር እንደመነጨ እድርገው ያዩታል። እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ለመድረስ ሲቸኩሉ የማያዩት ግን ንጉሣዊውን መኪና ከኋላው የሚያጅቡትን የታጠቁ ወታደሮች ነው። ቁም እጅ የማይነሣ፣ በክብረ ነክ ተወንጅሎ ይቀጣል። ይህንን ሕዕናቱም ያውቁታል። ከዚህ የባሰ ደግሞ ንጉሥ ነገሥቱ በአምልኮ ባዕድ የተለከፉ ናቸው፤ ሰውነቱ ላይ ጭረት የሌለበት ልጅ ቄሪጥ ለተባለው ቢሸፍቱ ሐይቅ ውስጥ ለመሸገው ሲይጣን መሥዋዕት ያቀርባሉ ብሎ ሕዝቡ ያምናል። የተማሩ የሩቅ ሰዎች ይህ ሁሉ፣ ኋላቀር ሕዝብ በምናቡ የሚያውጠነጥነው ፍሬ ከርስኪ ነው ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ምናልባት ግን ስለኢዲ አሚንና ቦካሳ የሰሙ ከእንዲህ ዓይነት አስተያየት ይቁጠቡ ይሆናል። ኢትዮጵያውያን ግን ንግሥት ዘውዲቱ « ዕድሜያቸው እንዲረዝም» በሰው ደም ይታጠቡ እንደነበር ያውቃሉ። እንዳንድ ያካባቢ ፍንጮችም ንጉሥ ነገሥቱም ከእንዲህ ዓይነቱም ተግባር ያልራቁ እንደነበሩ ያመለክታሉ። እዚህ ላይ ዋናው ነጥብ፣ ሕዝቡ ይህ እንደሚፈጸም በርግጥ አምኖ ብዙ ወላጆች ልጆቻቸውን ለቄሪጥ ለሚቀርበው መሥዋዕት ተገቢ ሆነው እንዳይገኙ ጆሯቸውን መብሳታቻው ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሊኒን የታወቀውን የመንግሥት ትርጓሜ ባያውቀውም፣ መንግሥት ግለት ኃይል መሆኑን አሳምሮ ያውቀዋል። ለአብዛኛው ሕዝብ፣ መንግሥት ባይተዋር የሆነና ኃይሉን ባስፈለገው ጊዜ የሚጠቀም፣ ከሕዝብ በጣም ርቆ የሚገኝ አካል ነው። ገዥው ማን ነው?ጠመንጃ የያዘ። ነገሥታቱ አንድ ጊዜ ቁንጮው ላይ ከደረሱ በኋላ ለራሳቸው ግብ የተስማማ ይሆን ዘንድ ታሪክን ይጠመዝዛሉ፤ በአፈታሪክ ከሚታወቁት ከንግሥተ ሳባና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር በማያያዝ አዲስ የትውልድ ሀረግ ይመዛሉ። ሥልጣን ላይ ለመውጣት በኃይል፤ እዚያው ላይ ለመቈየት ደግሞ ይበልጥ የዐመፃ ሥራ መፈጸምን ነው የኢትዮጵያ ነገሥታት

የታሪክ ገጽታ የሚያሳየው። በዚህ ሁሉ መሐል ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ታላቅ የጦርነት ፊልም ውስጥ ዝቅተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሚንጋጋውና ሲጨፈለቅ፣ በጦር ሲወጋ፣ እጅ እግሩ ሲቁራረጥ፣ ሲተኩሰበት፣ ሲሞት እንደሚታየው ማንነቱ ሳይታወቅለት፣ ሳይታዘንለት፣ ሳይለቀስለት ወድቆ እንደሚቀረው አልባሌ ተዋናይ ነው። ከልደት እስከሞት የፍዳ ቋት። ያለው ሁኔታ የያዘውን ሥርዓት ጠብቆ መቀጠሉ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ የተቀደሰ እንደሆነና በወዲያኛው ዓለም እንደሚካሥ እምና እስከዚያው በዕድል ማማረር «ብዕዓን ትሑታን ልብ» ሊላም ሊላ።

ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ ሲወሰዱ በጠመንጃ ያመልካሉ በግለት ፈርጠም ብለው የሚያቀርቡቱ ይህንን የኢትዮጵያውያን ታሪክና ዕውነታ የሚያንፀባርቀውን ጎልቶ የሚታይ ገጽታ ይረሳሉ። ስለሌሎች ሕዝቦችም እንዲሁ መናገር ይቻላልI ለምሳሌ የጠመንጃ ፍቅር ያላቸውን የኤን.አር.ኤ (NRA) ጠንካራ አባላት የሆኑትን አሜሪካኖችንም ለምሳሌ መውሰድ እንችላን። ግን ይህ ነጥቡን ባጠቃላይ መሳት ይሆናል። ኢትዮጵያዊው እንደግለሰብ ዐመፅ ያገበረው እይደለምI ግን ዐመፅ የበከለው አየር በሚያውድበት፣ የአንድ ሰው የክብሩ መግለጫ፣ ኃይል፣ ጉልበት በሆነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ነው የሚኖረው። በዚህ ሁኔታ ጠመንጃ፣ ከሃሊነትን፣ ወንድነትን «ትዕብናን» ዋጋ ግምትን ያሳያልI የራስ መከላከያም ነው። አንድ የታታ ብረት የሌለው (ወይንም መቀማት ያልቻለ) ሰው ከአባብ ወይም ከተናካሽ ውሻ ለመከላከል በሚል ሰበብ በትር ይይዛልI ውስጣዊ ምክንያቱ ግን ሌሎች ለጥቃት የሚያስቡትን መሣሪያ አልባ ሰዎች ለማስፈራሪያ ወይም ለመቆጣጠሚያ ነው። ብረት ያልታጠቀ ሰው የማንም መጫወቻ ነው።I ወይም በልሳነ ትምክህት ሽፍታ ወይም ቀማኛ ለመሆን እንኳ የማይቻለው ሌት ተብሎ ይጠራል። የታጠቀ ሰው እምቢኝ ወይም እጅ ለመስጠት ምርጫ አለው። ምርጫው ጠባብ ቢሆንም የጠመንጃው መኖር የሚለጠው ልዕልና ልዩነት ያመጣል።

በኢትዮጵያውያን ወግ ውስጥ ሽፍታ ከፍተኛ ቦታ አለው። ብዙውን ጊዜ ሽፍታ በባለሥልጣኖች ላይ ያመፀ የአካባቢው አርሶአደር ነው። ሽፍቶች (በይፋም ባይሆን) ይደነቃሉ፤ ይወራላቸውማልI ብዙዎቹ እንደሮቢንሁድ ከሀብታም እየነጠቁ

ለድኃ የሚሰጡ ሳይሆኑ ድኃውን የሚቀሙI አርሶአደር ወገናቸውን የሚያሸብሩ ናቸው። ሆኖም በቦታው ካሉ ባለሥልጣኖች አኳያ ሲታዩ ዓመፃቸው፣ ተራው ሰው ቢመኝ የማያገኘውን ሳት ብሎ የሚታይ ከሂሎትን ያቀጻጸቸዋል። ለሌሎች ቢባ በመሆን ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም ነው የIፀIያምቹና የIፀIጅምቹ ዓ.ም አብዮታውያን እንግዳ ነገር ሆነው የታዩት። አርሶ አደሩ ፣ እኒህ ሰዎች ዓላማቸው ምንድን ነው? ምንስ ጥቅም ያገኙበታል እያለ መልስ ለማግኘት ሲያውጠነጥን ረጅም ጊዜ የፈጀበት። ባጭሩም በፊውዳላዊት ኢትዮጵያ ኑፍሰገዳይ ነገሥታት እረመኔ የመሬት ከበርቴዎች፣ ስግብግብ ገዥዎችና ተራ ሽፍቶች ጀግኖች ይሰኙ ነበር።

ምናልባትም እዚህ ላይ መጥቀስ የሚገባን አንድ ነገር፣ ይህ ባህል ወደጥቂቶቹ ዘመናውያን የሽምቅ ተዋጊ ድርጅቶች ወግ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ነው ለካላሽንኮቭ (AK 47) ጠመንጃዎቻቸው ጥውም ታና ያላቸው። የፍቅር ዘፈን እንደሚዘፈንላቸው ነው። ለነገሩ ግን ለጠመንጃቸው ያላቸው ፍቅር «የፖለቲካ ሥልጣን ከአፈ ሙዝ ይሠርፃል» ከሚባለው ከማኦ ብሂል እንደመጣም የሚናገሩ አሉI ይህ ግን ሁሉንም የሚያጠቃልል አይደለም። ከነዚህ ድርጅቶች በአንዳንዶቹ ላይ የሚንፀባረቀው የወታደራዊነት ዝንባሌ፣ ከአርሶ አደሩ ጋር ያላቸው የፊውዳል ግንኙነት (መቼም የሚቀርቡት ለውጭው ሰው እንዲጥም በዲሞክራሲያዊና በተራማጅ ቃላት ተበጃጅተው ነው) ማንአህሎኝነታቸውና በኃይል ላይ ያላቸው ጭፍን ዕምነት ሲታይ፣ ሁኔታዎች የተለወጡ ይምሰሉ እንጂ በተጨባጭ ግን እንደቀድሞው በነበሩበት እንዳሉ ያመለክታል። ያ ያለፈ የገለማ ባህል፣ የፊውዳሎች ወግና አሠራር እኒሁ ፈውዳሊዝምን ለማውደም ቁርጥኝንታችውን በመሐላና በመገዘት የሚገልጹቱ፣ ጫንቃ ላይ፣ ከብደቱን እንደጣለባቸው ያለ ይመስላል። ኃይለሥላሴ ሞተዋልI ግን ደግሞ ኃይለሥላሴ አሁንም ሕያው ናቸው ማለት ይቻላል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያዊን ተራማጅ ጫር ጫር ቢያደርጉት ከቆዳው ሥር ለመሬት ከበርቴነት ያቄበቆበ እካል ብቅ ይላል።

ይህን ሁሉ ስንል በምንም ዓይነት መንገድ የደርግን እሥቃቂ ወንጀል ለአንባቢው ዓይን አትልሎ ለማትረብ አይደለም። እንዲያውም በተቃራኒው ደርግ ሲወርድ ሲኖረድ

የመጣውን የዓመፃና የፈላጭ ቆራጭነት ሥርዓት ከፍጻሜ ለማድረስ የተንሣሳውን ሕዝባዊ አብዮት በማጨናገፉ እንደአረመኔያዊና ኢሰብአዊ ኃይል ጎልቶ የሚታይ ነው። የ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የየካቲቱ አብዮት በዓመፃ አገዛዝ ላይ የታበየና ለሕግና ሥርዓት ለዴሞክራሲ ለሰላም፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰው ሰውነቱ ትክክለኛውን ትርጉምና ተገቢውን ቦታ እንዲያገኝ ሠፊው ሕዝብ የነበረውን ግልጽ የሆነ ምኞት ያስተጋባ ነው። ሕዝቡ ለመብቱ ጮኸ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከየትኛውም ማኅበራዊ ዕርከን ይምጣ ተገቢውን ክብር ማግኘት አለበት ሲል ጠየቀ፤ መንግሥታዊ ዕመፃና ከሁሉም በላይ የሐሳብ ልዩነትን ማፈን አወገዘ። በሌላ አንጋገር የየካቲቱ አብዮት የጠመንጃን የበላይነት፣ ሽብርንና ዓመፃን ሲታወም የያዘው ደርግ ግን ይህን ተፃርሮ ቆመ። ይዘቱን ሳይቀይር የቅርፅ ለውጥ ብቻ አድርጎበጉቱ የአገዛዝ ሥልት መቀጠሉን መረጠ። አብዮቱ ተጨናገፈ፣ ሽብር ነገሠ። ብዙ ነገር ተለዋወጠ፤ ማንኛውም ነገር ሆነ፣ በሕዝብና በመንግሥት መካከል የነበረው ግንኙነት ግን ቀድሞ ከተስተናበረበት ሁኔታ ምንም ያህል አልተቀየረም።

በየካቲቱ አብዮት መጀመሪያ አካባቢ ለእያሌ ዓመታት እኒያ የጠፉ ሰዎች ማለትም በጨለማ ቤትና ሽታቸው በማያስጠጋ እሥር ቤቶች ውስጥ ተቈልፎባቸው የነበሩ ተጋዦች ከምኅብ ማነስ አጥንታቸው ገጦ፣ የፀሐይ ብርሃን ከማጣት ቆዳቸው ወይቦ፣ በከፊል የታወሩ፣ እስከናካቴውም የታወሩ፣ ሰውነታቸው የበደነ፣ ወይም ሽባ ሆነው፣ ባለ እእምሮዎችና፣ እእምሮ የነሣቸው ሁሉ ሆነው ኀብረተሰቡ ፊት እነሆኝ ብለው ጉች አሉ። የፊውዳሉ አገዛዝ ወንጀል በሕዝቡ ፊት ገኃድ ሆኖ ቀረበ። ሕዝቡም «ይህ ግፈኛ መንግሥት ይውረድ» የሚል ጮኸት አሰማ። አብዮቱ እየተቀጣጠለ በመሄድ የዚያ ኢሰብአዊ ሥርዓት ቡታ ነጋሪ ሆነ። ይህንን፣ ያንን እናሻሽላለን እየተባለ ይገባ የነበረ ቃልኪዳን ሁሉ የሕዝቡን ቁጣ ሊያቀዘቅዝም ሆነ ንጉሣዊ አገዛዝን ከድቀቱ ሊያድነው አልተቻለውም። በዚህ ጊዜ ነበር ደርግ ጣልቃ የገባው።

ወታደራዊ መኰንኖችን የመረጣቸው የለም፤ ግንም በሕዝቡ ላይ እንዲሠለጥኑ ቃል የሰጣቸው የለም። ሥልጣንን በኃይል የራሳቸው በማድረግ በዚያው በጥንቱ የአገዛዝ ሥልት ቀጠሉ። ሕዝቡ ትግሉን እንዲያቆም በማዘዝ፣ ነገሥታት

ይገዛሉ፣ ሕዝብም ይታዘዛል ብለው በማስታቀር እኒያ የቀድሞ ነገሥታት ይሉት የነበረውን አስተጋቡ። በእርግጥም ሕዝብ በትምህርት ሳቅ ባለ ሕብረተሰብ ውስጥ በሰብአዊ ፍጡር ትርጓሜ ላይ ትንታኔ እቅርቦ ሊቅነቱን ሊያስመስክር ለሚፈልግ ጸሐፊ በሚያረካው ደረጃ ቁልጭ አድርጉ አበጃጅቶ ጥያቄውን እያቅርብ እንኚ ለዴሞክራሲ፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለእኩልነት፣ ዕመታ እንዲቆም፣ የሽብርና የዓመፃ አውታሪት እንዲፈርሱ ለሕዝባዊ ሥልጣን ጮኹቱን አሰምቷል። የሕዝባዊ ሥልጣን ዋነኛ ጥያቄ የጊዜያዊ መንግሥት ሕዝባዊ ጥያቄ ውስጥ የተካተተ ነበረ። ደርግ፣ ይህንን ሁሉ ተቃውሞ በእሻፈረኝ ባይነት ቆመ። በኃይሉ ሥልጣን ወለድ (እንደነገሥታቱ) እዚያው ሥልጣን ላይ ለመቈየትም ደግሞ ኃይል መጠቀም ነበረበት፤ (አሁንም ልክ እንደነገሥታቱ) ተቃውሞውን ሳሰማ አብነቱ ዕመታና ሽብር ነው አለ።

ለዚህም ነው የ«ቀይ ሽብሩ»ን እሥቃቂነት ለመረዳት የየካቲቱን አብዮትበነባራዊ መልኩ መመርመር የሚያስፈልገው። በአብዮቱ ውስጥ ሕይወትን፣ ኑሮን በሚመለከት ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ተጋጩ፤ ስለቀድሞውና ስለወደፊቱ ሁለት የተለያዩ ትንታኔዎች ተሳተሙ። እንደኛው፣ የሕዝቡና የተራማጅ ምሁራን የሆነው፣ የቀድሞውን ዓመፃ፣ በኃይል የመጠቀምን ባህል በማውገዝ ይህንን ሥርዓት ለማፍረስና ተራው ሰው የሚከበርበት፣ የወደፊት ዕድሉ የሚሠምርበት ሥርዓትን ለመፍጠር ሲሆን፣ ሁለተኛው የደርግና የደጋፊምቹ የሆነው ደግሞ የቀድሞውን በዓመፃ የቀለመ ገጽታ ተቀብሎ፣ በዚሁም ተመሥርቶ ይበጀኛል ያለውን ሥርዓት ለመቀየስ ነበር። ሕዝቡ ሰላምንና መሠረታዊ ለውጥን የፈለገ ቢሆንም ያን ለማግኘት መታገል ነበረበት። ደርግም ሥልጣን ለመጨበጥ፣ የሕዝባዊ ትግሉንም ፍሬ ለመቀማት ኃይልን መጠቀም ነበረበት። ከራስም ጠላይ ስንነሣ ያለአግባብ ያገኘውን ይዞ ለመቆየት በኃይል ላይ ከመተማመን ሌላ ምርጫም አልነበረውም። ከዚህም ስንደረደር «ቀዩ ሽብር» የጊዜ ጉዳይ እንጂ የግድ ቀኑን ቈጥሮ መወለድ የነበረበት ነበር።

ግን ይህን ግለት የሽብሩን አረመኔያዊነት ቅንጣት ታህልም የሚቀንሰው አይደለም። ዐመፅ ለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ እንግዳ ነገር አልነበረም።፤ ለምዶበታል ግለት በጊዜው የነበረው መንግሥት በኢትዮጵያውያንላይ የፈጸመውን ጭፍጨፋ ትክክለኛ ወይም ተገቢ አያደርገውም።

የንጉሠ ነገሥቱ መውደቅ
የማን አብዮት?

«ስለእመፅ እንጨነቅም፤ ወይም ከሚገባው በላይ እያሳሰበንም፤ እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች በአንድ ሀገር ታሪክ ውስጥ ዘወትር የሚከሠቱ ናቸው። ሁልጊዜም የሚንቀሳቀስ የሚብላላ ነገር አለ። የትም ቦታ የሥልጣን ጥመኞች አሉ፤ ተንኰለኞች አሉ፤ በነሱ ላይ በድፍረትና በቊርጠኛነት እርምጃ መውሰድ ብቻ ነው አማራጩ። ከማንታት፣ ከደካማነት ወይም ከሚጋጩ ስሜቶች መጠንቀቅ ያስፈልጋል፤ ወደቸንፈት ይመራሉና። እኛ እራሳችን እዚህ ወጥመድ ውስጥ ገብተን እናውቅም። ኃይል በኃይል ነው መመለስ ያለበት።»

ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
ለኦርያና ፉላቺ ከሰጡት ቃለ ምልልስ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

በእርግጥም ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ እንድ ነገር እየተብላላ ነበር፤ ንጉሠ ነገሥቱም እንደወትሮው አድርገው እንዳይመለከቱት ማስጠንቀቂያ በሆናቸው ነበር፤ ግን የገዛ ራሳቸው ግትር አመለካከት እሥረኛ ከመሆናቸው በላይ እየጸጸም ነበሩ። ያም ሆኖ

ለፍፁም ሥልጣን የነበራቸው ፍትወት ምንም ያልቀነሰ በመሆኑ በወቅቱ ሥርዓት ያለው አስተዋርሶ መንግሥት የሚመከናወንበትን መንገድ ለማስያዝ እንቅፋት ሆነባቸው። ንጉሠ ነገሥቱ ሥርወ መንግሥታቸው እንዲቀጥልላቸው ዝግጅት አላደረጉም፤ በልጃቸው በእልጋ ወራሹ ብዙ መተማመን አልነበራቸውም፤ (እሱም ቢሆን ሽባ ሆኖ ለንደን በሕክምና ላይ ነበር) እኔው በዕድሜ የገፉ ንጉሥ ነገሮችን በአስተሀቅሮ ከመመልከታቸውም ጋር ማንኛውንም ሞገድ «እንደወትሮው ሁሉ» ባላቸው ሥልጣንና ኃይለ ለመቋቋም በራሳቸው ላይ በትምክህት የተሞላ መተማመን ነበራቸው። ይህም የተሳሳተ ግምት ዙፋናቸውንም ሕይወታቸውንም እንዲያጡ አደረጋቸው።

ኢትዮጵያ፣ አብዮት እጅግ የዘገየባት፣ ፍጹም ሥልጣን በተቀዳጀ ነጋሢ የምትገዛ፣ በዓለም ላይ መናጢ ድኃ ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ ነበረች፤ የፖለቲካ ሥልጣኑ በጥቅሉ የተያዘው በኃይለ ሥላሴ ሲሆን ፓርላማው ለይስሙላ የቆመ የዲሞክራሲያውያን ተቋማት አፍአዊ ምስል ነበር። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት የሚሾሙት በንጉሠ ነገሥቱ ሲሆን (ሁሉም ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ነበሩ) ፓርላማው በታሪኩ ውስጥ የአባላቱን ደሞዝ ለማስጨመር ካደረገው በስተቀር አንድም ነገር ከራሱ አመንጭቶ ሕግ አድርጎ ያሳለፈው ነገር አልነበረም። የሕግ ምንጭ ራሳቸው ንጉሡ ነበሩ። ዲሞክራሲያውያን መብቶች የተገደቡ ሲሆኑ የተፈቀደለት የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም። ልዩነትን መግለጽ ከወንጀል፥ ተቃዋሚ መሆን ከክህደት ሲቆጠር፥ የሃይማኖት(የእስልምና) ጭቆናም እንደፖሊሲ በወግ የተያዘ ነበር። መገናኛ ብዙኃን በመንግሥት ሥር ከመሆናቸውም ጋር ሳንሱሩ ደግሞ የሚያሳውስ አልነበረም።

በሥርዓተ ማህበር ተዋረድ፣ ከራስጌ ንጉሠ ነገሥቱ፣ ንጉሣውያን ቤተሰብ፣ መሣፍንቱና መኳንንቱ፣ ታላላቅ የቢሮ ከበርቴዎችና ከፍተኛ የቤተክህነት አለቆች ሲሆኑ፣ ከግርጌ ደግሞ ሠፊው ሕዝብ ነበር፤ ከእነዚህም አብዛኛው መሬት የሌለው ጢሰኛና ድኃ አርሶ አደር ሲሆን፣ በተደነገገ ሕግ ከምርቱ ሲያውን ለመሬት ከበርቴው እንዲሰጥ ይጠየቃል። ኢኮኖሚው መሠረት ያደረገው በዋና መልኩ ኋላቀርና ከእጅ ወደአፍ ከሆነ የምርት ደረጃ ላይ ያለ እርሻን ነበር። የንፍስ ወከፍ አማከይ የዓመት ገቢ ስላ የአሜሪካ ዶላር (መቶ ሀያ የኢት. ብር) ላይ ረግጦ የቆመበት፣ የሕፃናት

ሞት መጠን ከስልሳ በመቶ በላይ እያንጃበበ የነበረበት፣ ከሕዝቡ ዘጠና ምስት በመቶ መሃይም የሆነበት፤ የአንድ ሰው አማካይ ዕድሜ ከሠላሳ ምስት ዓመት በላይ ሊዘል ያልቻለበት፤ የገጠሩ አካባቢ ዶክተሮች አይቶ የማያውቅበት፤ ንዳድ አሥር ከመቶ እጁን የሠራተኛ ኃይል ከጥቅም ውጭ ያደርግበት የነበረው ሁኔታ፤ የገዥዎቹ ቅጥ ያጣ የምቾትና የተድላ ደስታ ኑሮ በአንፃሩ ገጠ እንዲወጣ አድርጎታል። ይህን መልክ ነበር ኢትዮጵያ የምታሳየው።(2)

በእንዳንዶች(3) ሥልጣኔን ያመጣ የነገሥታት አገዛዝ የተባለላቸው ኃይለሥላሴ የገዙት እንዲህ ባለች ኢትዮጵያ ላይ ነበር። በእንዳራዊ መልክ ሲታይ ንጉሡ ተራማጅ ሚና የተጫወቱበት ጊዜ ቢኖር ባጭሩ የተቀጨ እንጂ ነበር። የተበታተኑትን ፊውዳላዊ የሥልጣን ማዕከላት በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሥር ለማምጣት የነበረው ጎራት፤ ማዕከላዊ የጦር ኃይል ለመመሥረት ማዕከላዊ የአስተዳደር አውታራትን ለመዘርጋት፣ የትምህርት ቤቶች ለመከፈት ... ወዘተ እንሣሽ ምክንያት ሆነ። ገናናው ንጉሥ በምዕራባውያን ድጋፍ ተጠቅመዋል፤ በተለይም አሥመራ ውስጥ ቃኘው የተባለ ትልቅና ዋነኛ የሆነ የግንኙነት ቤዝ ከነበረው ከአሜሪካ ጋር እሥራኤልም ለፀረአብነቱ ውልውል ባልነበረው የልብ ወዳጅ በሆነ ንጉሥ ጎን ለእርዳታ ተሠልፋለች። ይህም ወዳጅነት ንጉሠ ነገሥቱ በአንጻራዊ ደረጃ ዘመናዊ ሊባል የሚችል የጦር ኃይልና ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን በሚገባ ለማስጠበቅ የረዳቸውን የሲኩዩሪቲ አውታር ለመገንባት ዕድሉን ሰጣቸው። በሌላ ደረጃ ደግሞ ይኸው ወዳጅነት አንድ የካፒታሊስት ኃይለ ኃያላን ከአንድ ኋላቀር፣ ፀረዲሞክራሲ ከሆነ ኃይል ጋር የሠመረ ግኑኝነት ጠብቆ አብሮ መኖሪያት እንደሚችል አረጋገጠ።

እንደንጉሠ ነገሥቱ ሁሉ ማንም ማን እግዚአብሔር የመረጠኝ ነኝ ቢልም እንኳ፣ ጊዜ አንድ ቦታ ላይ ፀጥ ብሎ ቆሞ አይጠብቅምና የጎበረተሰቡ እድገት ምንም እንኳ እንደቀንድ አውጣ ቢንቁረሰስም የራሱም የሆነ የለውጥ ሂደትና የራሱም የሆነ ውጤት ነበረው። ኢትዮጵያ ለውጭ ዓለም በሯን መክፈቷም ተጽዕኖ እምጥቷል። በእፍሪታ ላይ የነፈሰው የለውጥ ነፋስ በኢትዮጵያም ላይ ሽው በማለቱ እስከዚያን ጊዜ ድረስ የንጉሠ ነገሥቱ ተወዳጅ ልጆች የነበሩት ምሁራን መቃነጥነጥ ጀመሩ። ከአበቃቀሉ ሊከለስ ያለና የጥገና ለውጥ ቅኝት የያዘ የህውከት ዘር ከአዲስ

አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጽር ግቢ መታየት ጀመረ። በመንግሥቱ አስተዳደር ውስጥ ባሉ የቢሮ ከበርቴዎችና በባህል ሲገዙ በኖሩት በፈውዳላዊ መሳፍንት መካከል የነበረው መፈራረቅ ንጉሥ ነገሥቱን የነላጋይ ሚና ስለሠጣቸው ይህም በእንጻሩ ፍጹም ሥልጣናቸውን አጠናከረላቸው

በታህሣስ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም መንግሥቱ ነዋይ የመራው በከብር ዘበኛ የተሞከረ መፈንቅለ መንግሥት መናጋትን አመጣ። የመፍንቅለ መንግሥቱ ዋነኛው ጠንሳሽ፣ የከብር ዘበኛ ዋና አዛዥ የነበረው ወንድሙንና በጣም ይፈራ ለነበረው የሲኪዩሪቲ መሥሪያ ቤት ዋና አዛዥ የነበረውን እንዲሁም የፖሊሱንም አዛዥ ሊያገባባ የቻለው ገርግሚ ነዋይ የተባለው አሜሪካ የተማረ ምሁር ነበር። ፈውዳላዊ ሥርዓቱንና ሥልጣኑ የይግደጠየቀውን ንጉሣዊ አገዛዝ ይቃወም የነበረው ገርግሚ ከብሔራዊ ስሜት የመነጨ ተራማጅ ሐሣቦች ነበሩት። መፈንቅለ መንግሥት ያደረጉቱ ሥልጣኑ በሕገ መንግሥት ተመጥኖ በተሠጠው ንጉሠ ነገሥት (በዚያው በኃይለ ሥላሴ ልጅ በእልጋ ወራሹ) ሥር አገዛዙ ለዘብ ያለ ሥርዓት ለማቋቋም ነበር አሳባቸው። መፈንቅለ መንግሥት የተሞከረው ንጉሠ ነገሥቱ ለሀገር ጉብኝት ወደብራዚል ሄደው በነበረበት ጊዜ ሲሆን የጦር ሠራዊቱ በታማኝነቱ ስለቆመ መፈንቅለ መንግሥቱን የሞከሩትን በማቸነፍ በሦስት ቀናት ውስጥ እንዲከሽፍ አደረገ። አሜሪካ መፈንቅለ መንግሥቱን በማከሸፍ ረገድ ወሳኝ የሆነ ሚና ነበረው የሚል ስሞታ አለ፤ ሆኖም ከቴከኒካዊ ጉድለቶች፣ በደንብ ካለማቀድ፣ መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎቹ ቄራዋ ውሳኔ ሚጠይቅ ሰዓት ከማመንታታቸውም በመነጨ ሁኔታ ከሽፎም ሊሆን ይችላል። ወደመፈንቅለ መንግሥቱ ማከተሚያ አካባቢ ጥቂቶቹ የመሣፍንቱ ወገንና ሚንሲትሮች በመፈንቅል አድራጊዎቹ ተገድለዋል።

ኃይለ ሥላሴ መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎቹን በሥቅላት ቀጡ። (ራሳቸውን በራሳቸው የገደሉት እንኳን ላይቀሩ አረሳቸው በአደባባይ ተሠቀለ) ከዚያም ሥልጣናቸውን እንደገና ማረጋገጥ ጀመሩ። ሆኖም አጠቃላይ ሁኔታ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የአዲስ ምዕራፍ በር ከፋች ሆነ። ያ የማይገሠስ የፍጹም ሥልጣንም አፍአዊ ግርማ የቀድሞው ሞገሡን አጣ፤ ፍጹም ታዛዥነት የሚለው አስተሳሰብ ጥያቄ ምልክት ወደቀበት። ሴላ አማራጭ እንደሚያስፈልግ ለሕዝቡ ብዥ ብሎ ይታየው ጀመር።

መንግሥቱ ነዋይ ላይ የታየው ረጋ ያለና ክብሩን የጠበቀ ስብእና በሕዝብ ዘንድ አክብሮት አተረፈለት፤ በእደባባይ ሲሰቀልም ሕዝቡ በፀጥታ፣ በጽሞናና በተመሰጠ ተመለከተ። ... መፈንቅለ መንግሥት ሞካሪዎቹ አልተሳካላቸውም፤ መልእክታቸውን ለሕዝብ ቀደም ብለው ለማስተላለፍ እንኳን አልቻሉም። ሆኖም ግን የለውጥ ዘር ከሕዝቡ መንፈስ ውስጥ እንዲዘራ፣ ቢያንስ ጥርጣሬ እንዲያድር ለውጥ የሚመጣበትን የተሻለና ፍቱን የሆነ መንገድ ማንሰላሰል ማስፈለጉን አሳይተዋል።(4)

ይህን ሁሉ ነገር በሚገባ ለማጣጣም የተሻለው ዕድል የነበራቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበሩ። መፈንቀለ መንግሥቱን ደግፈዉ ነበረና የንጉሥ ነገሥቱና የመሬት ከበርቴዎች የቁጣ ወጀብ አላለፋቸውም። «የጃንሆይ ልጆች» መሆናቸው ቀረ። በዩናቨርሲቲው ቅጥር ግቢ «አዞዎች» ተብለው የሚጠሩ የሥር ነቀል ለውጥ አመለካከት የነበራቸው ተማሪዎች ሥርዓቱን ለመቃወም ውስጥ ውስጡን መደራጀት ጀመሩ። በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ተማሪዎች በፈውዳላዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ድብሉቅልቁን ሊያወጡ ከሚችሉት መፈክሮች እንዱን «መሬት ለአራሹ» የሚለውን ይዘው ሰላማዊ ሠልፍ አደረጉ፤ ሠላማዊ ሰልፉን ፖሊሶች ኃይል በመጠቀም ቢተኑት፤ ጥቂት የተማሪ መሪዎችም ከዩኒቨርሲቲው እንዲባረሩ ተደረገ።(5) ሆኖም ከዚያ በኋላ ተማሪዎች ያንኑ ፈለግ በመከተል በያመቱ ከፍተኛ ትርምስ የሚፈጥሩ መፈክሮችን በማከታተል ከፖሊስ ጋር ይጋፈጡ ገቡ። ከፖሊስ ጋርም በሚደረገው ግጭት ወላጆችንና የከተማውን ሕዝብ ስሜት እየቀሰቀሰ መጣ። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ተሣታፊ እየሆኑ መምጣታቸው መልእክቱ በርቀትና በሥፋት እንዲሠራጭ አደረገ። ፲፱፻፷ ዓ.ም ሲገባግ ተማሪዎች አጠቃላይ ሥርዓቱ በሥር ነቀል ለውጥ እንዲገረሰስና በምትኩም ሕገሣዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እንዲቋቋም መጠየቅ ጀምረው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱና አጫፋሪዎቻቸው፣ እንዲሁም አሜሪካውያን አማካሪዎቻቸው በዚህ ሁሉ ውስጥ የሚታያቸው «የኮሚኒዝም መቅሠፍት» ሆነ። ታዲያም ዕመቃው ተጠናከረ። የተማሪ መሪዎች ታሠሩ፤ ተገደሉም፤ ግን እንቅስቃሴው አልረገበም።

ከሕዝቡ አብዛኛው የሆነው አርሶ አደሩ : ምንም እንኳ እንደምሁራን አርቆ ማስተዋልና ባልተዘበጠ መንገድ አመለካከቱን መቃኘት ባይሆንለትም ዝም ብሎ ተመልካች

አልሆነም፤ የዘመናት የፈውዳል ባህልና፣ ፍዳ መከራን እንደዕድል ፈንታ አድርጎ የመቀበል እምነት እንደመርግ ቢጫነውም፣ ግብታዊ በሆነና በደንብም ባልተደራጀ መንገድ መገንፈሉ አልቀረም። የአግሬውና የትግሬው ባህል፣ የሃይማኖት ... ወዘተ በደቡብ ኢትዮጵያ በብሔርና በሃይማኖት ላይ ያደረሰው ጭቆና በኢኮኖሚ ደረጃ ካለው ጭቆና ጋር በመጣመሩ፣ ዐመፁ የብሔርና የምርት ጥያቄን አወሳስቦ መያዙ የግይቀር ነበር። በባሌ አርሶአደሮች ከመንግሥት ጋር ያደረጉት ጦርነት ከ፲፱፻፶፫ እስከ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ተጥሏል። በ፲፱፻፷ ዓ.ም የጉጂም አርሶአደሮች የአርሻ ገቢ ታክስን በመቃወም መንግሥት ላይ ጠመንጃ እንሥተው ከባድ ውጊያ በኋላ ዐመፁ ተደምስሷል።(6) በሌሎች አካባቢዎችም ትንሽም ትንሽ የማይባሉም የአርሶ አደር ዓመፆች እየተነሡ፣ በኃይል፣ በክፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ፣ በመደለልም፣ በማስፈራራትም ሊበርዱ ችለዋል። ሆኖም እዚህ ላይ ጠቅሰን ማለፍ ያለብን፣ ምንም እንኳ የአርሶ አደሩ ዓመፆች የለውጥ ፍላጎትን ያንፀባረቁ ቢሆኑም ያ ፍላጎታቸው በዚያው በሚዋጉት ሥርዓተ መንግሥት ከልል ውስጥ የታጠረ እንጂ ከዚያ ወጣ ብሎ የማተረ አልነበረም። ስለዓላማቸው ግልጽ የሆነ ርዕዮትም ሆነ ያሉበት የግዙነት ሁኔታ ከአጠቃላይ የሥርዓቱ ባህርይ የመነጨ ስለመሆኑ ግንዛቤ አልነበራቸውም። እንዲሁም ግብታውያን የአርሶአደደር ዓመፆች ሁሉ የእነዚህም የቸንፈት መሠረት ይኸው ነበር።

ሠራተኞችም እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። ቁጥራቸው አነስተኛ የነበረ ቢሆንም (በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ሙያተኞችን ጨምሮ በኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር (ኢሠአማ) የተመዘገቡት አንድ መቶ ሺህ ነበሩ) የማህበር መብቶችንና የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ለማግኘት በዓመታት ውስጥ በየጊዜው ትግሎች አካሂደዋል። የመጀመሪያ የሠራተኛ ማህበር በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም በፍራንኮ ኢትዮጵያ ባቡር ጣቢያ የተቋቋመ ሲሆን፣ መንግሥት አጠቃላይ የማህበር መብቶቻቸውን እውቅ ኢሠአማ በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም እስኪመሠረት ድረስ የሠራተኞች መሪዎች እየታሠሩ፣ እየተገደሉ፣ የሥራ ማቆም አድማዎች በጭካኔ እንዲበተኑ እየተደረገ ብዙ ዓመታት ማለፍ ነበረባቸው። የኢትዮጵያ መንግሥትና የበላይ ጠባቂው የነበረው የአሜሪካ መንግሥት የኢሠአማን የበላይ አመራር ለመቆጣጠር የቻሉ ሲሆን ከአይ.ሲ.ኤፍ.ቲዩ. እና ከኤ.ኤፍ.ኤል – ሲ.አይ.ኦ. ጋር ትሥስር እንዲኖረው

አድርገዋል። ሆኖም ሌሎች መሪዎችና የበታች ማኅበራት ሥልጣኑን «ከተሸሙት» ከነበሩን ሰሎሞን፣ ዓለም አብዲ፣ ፍሥሐ ጽዮን ተከኤ (እንደቅደም ተከተላቸው የኢሠአማ ፕሬዚዲንት፣ ምክፕሬዚዲንት፣ ዋና ፀሐፊ) እጅ ፈልቅቆ ለማውጣትም ብቻ ሳይሆን የሥራ ሁኔታ እንዲሻሻል፣ ለበቂ የመነሻ ደሞዝ፣ ለማኅበራዊ ቤኩዩሪቲ ጥቅሞች .. ወዘተ ዋስትና የሚሰጣቸውን የሠራተኛ ሕግ እንዲወጣ ለማስደረግ እንዲያስችላቸው ትግላቸውን ቀጠሉ። አብዛኞዎቹ ኩባንያዎች በውጭ አገር ሰዎች ባለቤትነት ሥር የነበሩ ሲሆኑ፣ በእንዳንዶቹ ውስጥ በደች.ኤች.ቪ.ኤ. ባለቤትነት ሥር እንደነበረው እንደወንጂ ስኳር ባሉት ውስጥ ነጮቹ ሥራ አስኪያጆችና ተቆጣጣሪዎች ዘረኞች ነበሩ። በሀንዶች፣ በንጉሣውያን ቤተሰብና በሚንስትሮች የጋራ ባለቤትነት ሥር በነበረው በኢንዶ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ ዕድሚያቸው ለጋ የሆነ ልጆችን ማሠራት በሥፋት ይታይ ነበር። የሥራ ሁኔታውም ልክ በኢንዱስትሪያዊው አብዮት ጊዜ በአውሮፓ ውስጥ እንደነበው ዓይነት ነበር። በአጠቃላይ ሠራተኞችን ብዝበዛው እንገሸገሻቸው፤ በጉ፤ ታገሉም። ሲል ሲልም በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በማህበር በተደራጁት ሠራተኞችና በተራግጅ ተማሪዎች መካከል ምሥጢራዊ ግንኙነት እየተዘወተረ መጣ።

የተማሪው እንቅስቃሴ ሊራመድ የሚችልበት ደረጃ የተወሰነ፣ ከልሉም የጠበበ መሆኑን የተረዱ፣ በሥር ነቀል ለውጥ የሚያምኑ ምሁራን በሚያዝያ ወር ፲፱፻፷፰ ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታ ፓርቲን (ኢሕአፓ) ለመመሥረት በምሥጢር ተሰባስበው ጉባኤ አደረጉ። የነበረውንም መንግሥት በትጥቅ ትግል ለመገርሰስ ይቻል ዘንድ የሽምቅ ተዋጊ ኃይል ለማሠልጠንና ለማስታጠቅ እርምጃዎች ተወሰዱ። ባሉትም ሕዝባዊ ንቅናቄዎችና ማህበራት ውስጥ መልክ ባለው መንገድ ለመሥራት ዕቅድ ወጣ። ሥር ነቀል ለውጥ በሚሉት ምሁራን መካከል የነበው የሐሳብ ልዩነት ግለትም ፓርቲ ለመመሥረትም ሆነ የትጥቅ ትግል ለመጀመር ጊዜው ገና ነው ይሉ በነበሩትና (ኋላም መኢሶን የተባለ ድርጅት ባቋቋሙት) በፓርቲ ተደራጅቶ ለመታገል ጊዜው ይፈቅዳል በሚሉት መካከል የነበረው ልዩነት ጨርሶ ከለየለት ደረጃ የደረሰው ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ከዚሁ ዕለት ጀምሮ ነበር። [8]

ደግሞም የኤርትራ የሽምቅ ውጊያ ጦርነት ነበር።

የኤርትራ ነፃ አውጪ ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም ያወጣው በ1963 ዓ.ም የትጥቅ ትግል ከጀመረ ከአሥር ዓመት በኋላ ቢሆንም በዚያን ጊዜ በአንጻራዊ ደረጃ እጅግ ተደራጀቶ የነበረው ይኸው የኤርትራውያን የሽምት ውጊያ ነበር። የኤርትራውያን የትግል ባህርይ ምን ነበር የሚል ትንተና ውስጥ መግባት የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ባይሆንም ጦርነቱ በንጉሡ ነገሥታዊው መንግሥት ላይ የራሱ የሆነ ጫና እንደነበረው መናገሩ በቂ ይሆናል። በአገር ውስጥ ተራማጅ አመለካከት የነበራቸው ምሁራን ይኸው የኤርትራው ትግል የሽምት ውጊያን ለመጀመርና ለመቀጠልም ይቻላል የሚለው እምነታቸውን የሚያረጋግጡበት ሆነላቸው። ጥቂቶች ደግሞ የዋኃን ከመሆናቸው የተነሣ፣ የሽምት ተዋጊዎች በወቅቱ ከቶውንም የማይገባቸውን የተራማጅነት ካባ አከናንቧቸው። በዓውደ ጦርነቱ ላይ ደግሞ መመጣጠን አልነበረም፤ የንጉሡ ጦር የበላይነቱን ይዞ ሽምት ተዋጊዎቹ በዕዕዋት ከተራቆተው ከበረሃማው አካባቢ መወሰን ነበረባቸው። ተሐኤ፣ አስላማዊና ወንዜ፣ ሰበካዙ በሚል የሚያደላ ድርጅት ነው እየተባለ ይለጠፍበት የነበረውን ለመፋቅና ብዙ ከርስቲያናውያን ኤርትራውያንን ከደጋው ክፍል ለመሳብ ተስኖት ነበር። እንዲያውም በሃይማኖትና በጐሣ ላይ የተመሠረቱ ውስጣዊ ግጭቶች በጅምሩ ዓ.ም ድርጅቱ እንዲከፋፈል አድርጎታል። በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ተሐኤ (ኢ.ሕ.ልፍ.) እና በቅርቡ ተመሥርቶ የነበረው ሕግሓኤ (ኢ.ፕ.ኤል.ኤፍ.) ከሁለቱም ወገን ቢጻመር ከ፭ሺህ የበለጠ የታጠቀ የሽምት ተዋጊ ጦር ያልነበራቸው ሲሆን፣ ረብ በሌለው የመቀናቀን ጦርነት እርስ በርስ መተላለቁን ተያይዘውት ነበር። በልዩ ልዩ ምክንያት (9) የአረብ አገሮች ለሽምት ተዋጊዎች ድጋፍ በመስጠታቸው በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ላይ ያመጣው ጫና ፖለቲካዊ ነበር። የኢትዮጵያ ወታደሮች ግጭቱ ግለቂያ የሌለው በመሆኑ ቅሬታ ነበራቸው። ለጦር ግንባር አገልግሎታቸውም የደሞዝ ጭማሪ ጠይቀዋል። የኤርትራው እንደራሴ ራስ አሥራተ ካሣ በጦርነቱ መቀጠል ትርፍ ስለሚያገኙበት ጥረታቸውን ባያሰናክልባቸው ኖሮ ሽምት ተዋጊዎቹን ሊያቸንፉ እንደሚችሉም ይገምቱ ነበር።(10)

ሽምት ውጊያዎች ግብታዊነት ያሳቸው የአርሶ አደር በመሆኑ፣ ሠራተኞች የተደራጀ ጡንቻቸውን እያሣዩ መምጣት፣ ምሁራን በምስጢር መምከር፣ በመሣፍንቱና በቢሮ ከበርቴዎች ሊደረግ ነው እየተባለ የደስታ ወሬ መዛመት፣ ለመፈንቅለ መንግሥት የሚደረግ መመላለጠር፣ ሀገሪቱም ወደድኅነት አዘቅት እያደር ማቴልቴል፣ ... ይኸ ሁሉ ውጥንቅጥ ሁኔታ ሊታይ፣ በርግጥ የሆነ ነገር እየተንቀሳቀሰ ነበር። በ1965 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ ይታይ የነበረው አፍአዊ ሰላምና ፀጥታ በውስጡ ጭንቅና እምሳት የተመላበትን ሁኔታ ሸፍኖ ይዞ ነበር። ንጉሡ ነገሥቱ ያንኑ ፍጹም ሥልጣን እንቀው ይዘው የነበር ሲሆን፣ ባለሟሎቻቸው ደግሞ «ከሾንሆይ በኋላ» ሰሚሆነው ለመዘጋጀት ነገር ይጐነጉኑ፣ በመካከላቸው ትስስር ይፈጥሩ ገቡ። አብዮታውያኑ ደግሞ ከገቡአዊነት በዓታቸው መድምደው መሸጉ። ከቶ ምን ሊመጣ እንደሚችል ማንም በርግጥ ሊተነብይ አልቻለም። በእንድ ሊታይ ገሸም ተገሸም እንድ ነገር ሊፈጠር ነው ብለው የሚጠባበቁበት ሁኔታ መጣ።

አብዮቱ በመጣ ጊዜ ለሁሉም ፉብዕላ ሆነበት። ማንም በቂ ዝግጅት ያደረገ አልነበረም። ማንም ቢያንስ በመጀመሪያው ደረጃ ጥልቀቱንና እንድምታውን የገመተ አልነበረም። ለመንግሥት ደግሞ የከፋ ያደረገው ብልጣ ብልጥ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት አርቆ ማስተዋል ተሥኗቸው የቢተ መንግሥት ደኝፍ መቈርቈፍ የጀመረውን አብዮት ዘወትር ይሆን ከነበረው የተለየ አይደለም፤ በቀላሉ ልናልፈው የምንችለው የተለመደው ችግር ነው ብለው በሚያሳዝን ሁኔታ መገመታቸው ነበር።

ስህተታቸው ዙፋናቸውንና ሕይወታቸውን ሊያሳጣቸው፣ ኩትኩተው ያሳደጉትና የገነቡት ሥርዓት መገረሰስ እንዲፋጠንም አድርጎታል። በአብዮቱ ተዋንያን በሆኑት ታጋዮችና በሕዝቡ በኩል የነበረው የዝግጅት ማነስ ደግሞ አብዮታቸውን አሳጥቷቸዋል። ከዚህም የተነሣ ይኸው ኢትዮጵያ በሽምት ውጊያ፣ በእምባንኖች፣ በድኅነት፣ በረሐብ፣ በሞት ተሰንጋ ተይዛ ትገኛለች።

እንድ አብዮት፣ ይህ ያ የሚባል ጦር ሠረር ላይ የተወሰነ ወታደራዊ ማጥቃት ከማድረግ ጋር ተመሳስሎ መቅረብ የለበትም። አንድ ወታደራዊ ንቅጣ የተመታበት ትክክለኛው ቀን ሊታወቅ ይችላል። በትክክል መቼ ጥቃቱ እንደተጀመረ ማን እንደጀመረው ማን እንደጨረሰው፣ መቼ እንደተጨረሰ ሊታወቅ ይችላል። ሕዝባዊ አብዮት ግን የተለዩ ነው። የብዙ ዓመታት ቅሬታ

ነበልባሉን ሊያራግበው ይቅያል፤ እዚህ ብልጭ ይላል፤ እዚያ ድርግም ይላል፤ ሌላ ቦታ ደግሞ እንደገና ብልጭ ይላል፤ የተጸፈነው እሳት፣ የመራራ ትግል የቀቢፀ ተሥፋ፣ የችንፈት፣ የከፈል ድል፣ የነዚህ ሁሉ የዓመታት ከምችተ የተለኩሰ ጊዜ እገር አጥለቅልቅ እሳት ይነሳል።

ስለዚህም የ፲፱፻፷፮ ዓ.ም አብዮት በርግጥ መቼ ተጀመረ? ማን ጀመረው? በእውነቱ ጥያቄዎቹ በደንብ የተስተካከሉ አይደሉም። ለዚያች ለመጨረሻይቱ የተፍጸም ፍንጸታ ምክንያት የሆነው ጉብረተሰቡን ሲከፋፍሉት ከነበሩት መሠረታውያን ምክንያቶችና ተቃርኖዎች ጋር ተንጸጽሮ መቅረብ ያለበት አይደለም። ለንገሩ፣ ታሪክ፣ ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችና አጫፋሪዎቻቸው እንዳሻቸው የሚያደርጉት መስክ ነው። በቦታው ላለው ሥርዓት ግጠየቂያ ለመስጠት ወይም ሥልጣን ላይ ለተቄናጠጡ አዲስ መሪዎች ተቀባይነት ለማስገኘት ታሪክ ይጻፋል። ለእንደዚያ ላሉ በኢትዮጵያ ውስጥም በውጭም ብዛት በነበራቸውም ሳላቸው ሰዎች የየካቲቱ አብዮት የተጀመረው በወታደሩ ነው። ለእንደዚህ ያሉ ሰዎች እንግዲህ አብዮቱ የተጀመረው ጥር 4 ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ.ም በንገሌ የጦር ሠፈር ንጹሕ የመጠጥ ውኃና የተሻለ ምገብ እንዲቀርብላቸው ተቃውሟቸውን ለማሰማት ወታደሮች ዐመፅ ሊሥነስተው አዛዥ መከንኖቻቸውን ያሠሩበት ጊዜ ነበር ማለት ነው። ለንጌሌው ዐመፅ ትልቅ ግምት የሚሰጡት ሰዎች ዓላማ፣ አብዮቱን ያነሣሳው ወታደሩ መሆኑን ለማስረጃ የሚያቀርቡት ስለሆነ ዐመፁ በጣም ባጭር ጊዜ ያቆመ መሆኑንና ሕዝቡም ላይ ሊቀሰቅስ የቻለው ስሜት ሊምንት እንደነበረ የሚያሳየውን ሀቅ ሳይጠቅሱት ያልፋሉ።

መፍቀሬ ደርግና ከላሽ ታሪክን ወደጎን ትተን፣ ያ አገር አጥለቅልቅ ታላቅ የአብዮት እሳት ለዓመታት ሲብላላ ከቆየ በኋላ ግርግውን የገለጠው በሚከተለው ዓይነት ነበር።(11)የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን መንግሥት የደበቀውንና በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ የፈጀውን የወሎና የትግራይ ረሐብ ለሕዝብ አጋለጡ። (12) የባንክ ሠራተኞች የሥራ ግቆም አድማ አድርገው መንግሥት ጥያቄዎቻቸውን የግድ እንዲቀበላቸው አስደረጉ። የአዋሽና የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ካላገኙና የተሻለ የሥራ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው የሥራ ግቆም አድማ እንደሚመቱ ዛቱ። መምህራን በተማሪዎች እየተደገፉ አከራካሪ የነበረው ሥርዓተ ትምህርት ላይ የቀረበው መሻሻል (ሴክተር ሪቪው)

ሥራ ላይ ከሞለ ሥራ እንደሚያቆሙ አስፈራሩ። በደቡባዊው ጠቅላይ ግዛት (አሁን አስተዳደራዊ ክልል) በሲዳሞ ውስጥ በሚገኘው በነጌሌ የተነሣው የወታደር ዐመፅ በዚህ ላይ ተደመረበት።

መንግሥት ደግሞ የእህልና የቤንዚን ዋጋ በመጨመር በእሳቱ ላይ ነዳጅ ጨምሮበት አረፈ። የካቲት 11 ቀን ታክሲ ነጅዎች አዲስ አበባ ውስጥ ሰላማዊ ሠልፍ ሊያደርጉ ዓድማ ላይ የነበሩት መምህራን ተማሪዎችም ተባባሪዎቻቸው ሆኑ። ሰላማዊ ሠልፉን ለመበተን የሴክዩሪቲ ኃይሎች ሞከሩ፤ ረብሻ ተነሣ፤ ብዙም ሰዎች ተገደሉ። አዲስ አበባ ተጨነቀች፤ ተጠበበች፤ ወታደሮችም ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችንና ሕንፃዎችን እንዲጠብቁ ተደረጉ። ከዚህ ቀን ጀምሮ አሥመራ ውስጥ ወታደሮች እስካመፁበት እስከየካቲት ፲፱ ቀን ድረስ በሰላማዊ ሠልፍ አድራጊዎችና በወታደሮች መካከል አዲስ አበባ ውስጥ በየዕለቱ ግጭት እየተፈጠረ ብዙ ሰው ይቈስል ወይም ይሞት ነበር።

የካቲት ፲፮ ቀን ንጉሥ ነገሥቱ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ንግግር አደረጉ፤ ንግግራቸው የተለመደውን የመታበይና የእልበገሬነት ቃና እንደያዘ ሆኖ ሳላ ለቀቅ ግድረግንም አጣምሮ የያዘ አቀራረብ ነበረው። ሴክተር ሪቪው፣ ለጊዜው እንዲገታ ተደረገ፤ የቤንዚን ዋጋ በሊትር አሥር ሳንቲም እንዲቀንስ ሆነ፤ በዋና ዋና ሸቀጦች ላይም ይዋጋ ቁጥጥር እንዲደረግ ታዘዘ። መንግሥት መልሶ ለማጥቃት ይችል ዘንድ አፈገፈገ። «ረብሻ የሚፈጥረውን» ሁሉ እዚያው በታየበት እንዲገድሉ ለወታዳሮች ትእዛዝ ተሰጠ። አንድ የመንግሥት «ሁኔታ መግለጫ» ወጥቶ ፻፲፱ «ጴርቡዎች» በሳምንቱ ውስጥ እንዲታሠሩ፣ ፍሬ አውቶቡሶች፣ ፴፮ የግል መኪናዎች፣ ፭፮ የመንግሥት መኪናዎች፣ ፮ የዲፕሎማቲክ መኪናዎች፣ ፴፰ ቤቶች፣ ሁለት ባቡሮች፣ ... ወዘተ በሰላማዊ ሠልፍ እድራጊዎቹ እንደተነዱ ገለጸ። የሪፖርቱ ትክረት በንብረት ላይ ስለደረሰ ጉዳት ስለንበር ግልጽ በሆነ ምክንያት የሞቱት ቁጥር ፫፣ የቆሰሉት ፭፮ ተብሎ ቀረበ። በማስታወቂያ ሚኒስቴር የወጣው የሳምንቱ የሁኔታ መግለጫ «ለረብሻው» ተጠያቂ ያደረገው «ጥቂት ታክሲ ነጂዎች»ን፣ «ቁጥራቸው እንሰተኛ የሆነ ከትምህርት ገበታ የተገለሉና ፈተና የወደቁ ግለሰቦች»ን፣ «ሥራ ፈቶች»ን፣ «ጴርቡዎችና አሉባልተኞች»ን ነበር። የሆነ ሆኖ እንድ

ጊዜ ዓይነጥላቸው ተገፍፏልና ተግሪዎችም ሆኑ አስተግሪዎቹ ሊረኩ አልቻሉም፤ አድግው ቀጠለ።

የካቲት ፲፱ ቀን ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎች አሥመራ ውስጥ በመው በቀጣዮቹም ቀናት ችግሩን ለማብረድ በመፍጨርጨር ንጉሥ ነገሥቱ ለወታደሮች ደሞዝ ጨመሩ፤ ግን በመው ቀጠለ። የአዲስ አበባ ወታደሮችና የቢሸፍቱ (ደብረዘይት) አየር ኃይል በመውን ተቀላቀሉ። ከዚህም የተነሣ ጠ/ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ከጠቅላላው ካቢኔ ጋር ከሥራ ተሰናበተ። እንዲህ ዓይነት ነገር በሀገሪቱ ውስጥ ሲታይ ከቶውንም ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ከዚህ በኋላ የነበሩት የሁኔታ እድገቶች በብዙ ምንጮች በደንብ የተዘገቡ ናቸው፤ ግን እኛ ለምንፈልገው ጉዳይ እንዳንድ በመፍቀሬ ደርግ ታሪክ ፀሐፊዎች አብዛኛውን ጊዜ ተድበስብሰው የሚያልፉትን እንዳንድ አስፈላጊ ነጥቦች እናነሣለን።

▶በይበልጥ የኢኮኖሚ ጥያቄና እንዳንድ በያካባቢው በተፈጠሩ ቅሬታዎች ላይ ተመሥርቶ የተነሣው ትግል፣ መሬት ለአራሹ፣ ዲሞክራሲያዊ መብት፣ ሕዝባዊ መንግሥት የሚሉ ጥያቄዎች ታክከው ወዲያውኑ ፖለቲካዊ በመሆን የልዩ ልዩ ክፍሎች ጥያቄዎች ሆኑ።

▶አብዮቱ ከሕዝቡ ሰፋ ያለውን ክፍል ያሣተፈ ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ ተባ ያለና ሳቅ ያለ ድርሻ የነበረው የከተማው ኗሪ ነበር፤ ሠራተኞች፣ ተግሪዎች፣ ምሁራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ወታደሮች፣ ባለሌላ ማዕረጎች፣ ቀሳውስት፣ ሴቶች፣ እስላሞች፣ ሥራ አጦች፣ ... ወዘተ ሁሉ ተካፍለውበታል።

▶ከጦር ኃይሎች ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው ክፍሎች (አርሚ አቪየሽን፣ የመሐንዲስ ክፍል አየር ኃይል ... ወዘተ)ና ሲቪሉ ወገን ተግባብቶ ለመሥራት የሚያስችል ትሥስር የፈጠሩ ቢሆኑም ጦር ኃይሉ እርስ በርሱ እንድነትም ሆነ በአብዮቱ ውስጥ ግንባር ቀደምነት አልነበረውም። ይልቁንም የሚያጠርትት ሁኔታ በተፈጠረ ቁጥር መሰናክል ከመሆንና ከማፈግፈግ አልተመለሰም። ወታደሮቹ አሁንም አሁንም ለንጉሥ ነገሥቱ ታማኝነታቸውን በማለጽ አድማ በመቱ ሠራተኞች ላይ እርምጃ ይወስዱ የነበሩት ትንሽ በትንሽ የንጉሥ ነገሥቱን ሥልጣን

ለመሸርሸር ሠፊ መርሐ ዕቅድ ኑሯቸው ሳይሆን (13) ለራሳቸው የሚበቃንን እግኝተናል ብለው ስላመኑና ፈረሸው። መቆም አለበት ስላሉ ነበር። የተግሪው፣ የሳብኤደሩ፣ የመንግሥት ሠራተኛው፣ ሰላማዊ ሠልፍና የካቲት ሠላሳ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ሀ-ተብሎ በኢሠአግ የተጠራው አጠቃላይ የሥራ ማቆም አድማ ተጸምሮ የእንዳልካቸው መኮንን ካቢኔ ለመውረድ እበቃው። ከጦር ሠራዊቱ መሠረታዊ ለውጥ የፈለጉት ክፍሎች፣ በኋላም የደርግ ዐመፃ ሲሳካው ያደረጋቸው የሕዝቡን ጥያቄና ሕገ መንግሥት እናሻሽላለን (14) በሚል ሽንገላ አቅጣጫ ለማሳት የነበረውን ተቃውሞ ደገፈው ቆሙ።

በዚያን ፈጣን እድገት እያገኘ ይሄድ የነበረው ልፈንዳ ልፈንዳ በሚል የተጋጋመ ሁኔታ ውስጥ «አብዮቱን ለማራመድ» በሚፈልገው ተራማጅ ክፍልና (ሲቪልና የተወሰኑ ክፍሎችም ከጦር ኃይሉ) ጠቅላላውን ነገር ሲገታ በሚፈልገው ድምሩ ወታደር መካከል ነቅ መኖሩን ብዙዎች ሊያዩ አልቻሉም ነበር። ከሁሉም በላይ እንዳልካቸው ሥልጣን በያዘበት በዚህን ጊዜም ነበር በተራማጅ ምሁራን የነበረው ንፍቀት (መከፋፈል/chasm) በእደባባይ ረግጦ የወጣው። ውለው አድረው መኢሶን ሆነው ብቅ ያሉት ወታደሩን በመደገፍ «አዲሱን መንግሥት የማሻሻል እርምጃዎች እንዲወሰድ ጊዜ እንስጠው። ሲሉ በኢሕአፓ ዙሪያ የተሰባሰቡት ደግሞ ያረጀ ያፈጀውን ሥርዓት ለመገልበጥና ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንግሥት ለመተካት ትግሉ መቀጠል አለበት አሉ። ባጭሩ አብዮቱን በመምራት ተራማጅ መኩንኖች የሚቀፀሉት ስም የተሳሳተ የመሆኑን ያህል ባለሌላ ማዕረጉችና ወታደሮች ደግሞ ድርሻ አልነበራቸውም ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ደግሞ በዚያው መጠን የተሳሳተ ነው።

▶ትግሉ ጥልቀት እንዲያገኝና ቀጣይነት እንዲኖረው ተራማጅ ምሁራን ሳቅ ያለ ድርሻ የነበራቸው ቢሆንም በሁኔታው ላይ አሻራቸውን ለማተም በሚያስችል የጥንካሬ ደረጃ ግንኙቸውም አልተደራጁም ነበር። ኢሕአፓ በዚህን ጊዜ ከላብ አደር ማኅበራትና ከወጣቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ቢመሠርትም ድርጅታዊ ጥንካሬ አልነበረውም። በወቅቱ እጅግ ተወዳጅና በጎጡዕ ይሠራው የነበረው ልሣኑ ዲሞክራሲያ የራሱ ልሣን መሆኑን ያረጋገጠው ኑሐሊ

፲፱፻፫፫ ዓ.ም ራሱን ይፋ ያወጣ ጊዜ ብቻ ነበር። መኢሶንን በኋላ የመሠረተው ክፍል ገና የተወሰነ ቅርፅ ያልያዘና አገር ውስጥ የነበረው የዴሞክራሲያን አቅኖኞች ሲያስተጋባ፣ የውጭው ክፍል ደግሞ ታናው የተለየ ነበር። («ለአዲሱ መንግሥት ጊዜ እንስጠው ... ወዘተ» ዓይነት)

› ከዕውነት በተቃረነ መንገድ እንደቀረበው፣ ደርግ ከሶር ኃይሎች ንቅንቄ ተራማጅ ክፍል የተመሠረተ አልነበረም። ከተራማጅ የሲቪል ተቃዋሚ ወገኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው አብዛኛዎቹ መኩንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ወደንዑስ ደርግ ደረጃ የተገፉ ወይም በመደበቅ ላይ የሚገኙ ነበሩ። ስለዚህም ደርግ በአጠቃላይ መልኩና በተጨባጭ ድምሩን ወታደርና ከሕዝቡም «እዚህ ላይ ይብቃ» የሚለውን «ለውጥ ያስ ደም መፍሰስ» የሚል ቅኝት የያዙትን ነበር የወከለው።

የግን አብዮት? የሚለው ጥያቄ ፈርጠም ብሎ ሊመለስ የሚችል ነው። አብዮቱ የሕዝቡ የገዛ ራሱ ነበር። የርሱም ፍሬ ነግ ነበር። የየካቲቱ አብዮት የወታደር ንቅናቄ አልነበረም። (የወታደር ዐመፆች በሚታዩአቸው የሥራ ማቆም አድማዎች ግን በሚሠወሯቸው ሰዎች ዓይን ሲታይ ካልሆነ በስተቀር) ወታደሩ ማሳረጊያው ላይ የወሰደው እርምጃ፣ ሕዝቡ በአጠቃላይ ዓመቱን በሙሉ ባዴረገው ትግል ይተካል ካልተባለ በስተቀር የሚንኳተት መፈንቅለ መንግሥትም አልነበረም። በአብዮቱ ውስጥ የፖለቲካ ትምህርት ቀሰመ፣ የኢኮኖሚ ጥያቄዎችን ከመሠረታውያን የፖለቲካ ጥያቄዎች ጋር አዛምዶ አቀረበ። መንግሥት ተለሳልሶ ሲቀርብ፣ የቤንዚን ዋጋ ሲቀንስ፣ ወይም አዲሱ መንግሥት ሕገመንግሥቱን ሊያሻሽል ቃል ሲገባ፣ ትግሉን አላቆመም። በገዛ ራሱ ትግል በነጻ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የሥራ ማቆም ... ወዘተ መብቶችን ተቀዳጅቶ ነበር። እነዚህን መብቶች ለመጠበቅና ለማስፋፋትም ነበር የፈለገው። ኢትዮጵያውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻነት ቢያገኙም እንዴት እንደሚጠቀሙበት አሳውቅም በማለት ትግሉን እንዲያቆም የፈለጉት ተጪጪሁ(15) ግን ሕዝቡ የሚፈልገውን ያውቅ ነበር። በዚህን ጊዜም የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ተርቦ ነበር። ፈውዳሊዝም — እምቢኝ! ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ — በጅ! የሚል ይዘት የነበረው የወቅቱ መፈክር። ሕዝቡ በራሱ ትግል መንግሥቱን

እሽመድምዶ ያገኘው ነጻነት ከልቡ ገብቶ ነበር። እኒህን መብቶች ለመንከባከብ ለተቀዳጀው ነጻነት ዋስትና ለማግኘት ሥልጣን ፈለገ።

ስለደርግና እመክለዋለሁ ስለሚለው እንቅስቃሴ ይህንኑ ማለት አይቻልም በተደጋጋሚ ጊዜ ከአሮጌው መንግሥት ጋር ለመደራደርና ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ለማፈን ሞክሯል። እስከመጨረሻው ጊዜ ድረስ የተነወረውን የንጉሥ ነገሥት አገዛዝ የማቆየት ሐሳብ ሲያሞናሙን ቆይቷል። የሱ መፈክር ኢትዮጵያ ትቅደም — ብሔራዊ ስሜትን በከርትፉ የያዙና የተቀያየሙ ሐሳቦችን ያዘለ የመደብ ልዩነቶችንና የፖለቲካ ሥልጣንን ዐበይት ጉዳዮች እድበስብሶ ለማለፍ የተመቻቸ ነበር። ወታደሩ እያደር ጡንቻ እየተሰማው መጣ። ሥልጣን ለመያዝ የመቻሉ ጮራ በእድማሱ ላይ እየፈነጠቀ ሲመጣ ሲቪሉ ለመሠረታዊ ለውጥና ለሕዝባዊ ሥልጣን የሚያሰማውን ጮኽት ለመግታት የሚያደርገውን ግፊት መጨመር እመጣ። «ኢትዮጵያ ትቅደም» ለሚለው ወታደራዊ መፈክር ሕዝቡ «ሠፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅደም» የሚል ተገቢ መፈክር ተካለት። ከላይ በሚደረገው ጥገናዊ ለውጥ እርካታ ሳገኙትና ያንንም ለመስበክ ለሞከሩት ሁሉ፣ ከፓርቲዎች፣ ከብዙኃን ድርጅቶች፣ ከሲቪሎች፣ ከወታደሮች ... ወዘተ የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት እንዲቋቋምና፣ ይህም፣ ሠፊ መሠረት ያለው ሕዝባዊ መንግሥት በጊዜያዊነት የሚሠራና ሰምርጫ መንገድ የሚጠርግ እንዲሆን የሚል ሐሳብ ደቀነባቸው። የግዮቱን ውስጣዊ ባህርይ ማየት የተሳናቸው፣ ትግሉ በሲቪልና በወታደር መካከል እንደተፈጠረ ግጭት ሆኖ ታያቸው። እርግጠኛው ግጭት ግን በዴሞክራሲያዊውና በአምባገነናዊው መሥመር መካከል ነበር።

በሕዝባዊው ንቅናቄና በወታደሩ መካከል የነበው መለያየት ግልጽ እየሆነ መጥቶ ነበርና ይህም የመራራት ሁኔታ ጎራ ለይቶ መሠለፍን አስከተለ። የተወሰነ ክፍል ከሶር ኃይሎች (ከአየር ኃይል፣ ከአርሚ አቪየሽን ... ወዘተ) ከሲቪሉ ጋር ሲወግን፣ ከተራማጅ ምሁራን የተወሰነ ክፍልም ከደርግ ጋር ወገነ። ልክ ንጉሡ ከመውረዳቸው በፊት በነዚያ ቀናት ግልጽ እየሆነ የመጣው ሕዝባዊ ንቅናቄው ከሁለት የተከፈለ መሆኑ ነበር። ሕዝቡ — እውነትም ይገባዋል — አብዮቱን የገዛ ራሱ አድርጎ በመውሰድየሕዝባዊ ዴሞኮራሲያዊ ሥርዓት ጉልላት ሊያበጅለት ነበር የፈለገው። ደግሞ ራሱን በራሱ ግንባር ቀደም

አድርጎ ሠይሞ የ«አብዮቱ» ታዳጊ መሆን ነበር የፈለገው። በሁሉም ክፍሎች ማለት ይቻላል ይስተጋቡ የነበሩ አጠቃላይ መፈክሮች ረቀቅ እያሉ መምጣት፣ እንድምታቸውም መብዛት ጀመረ። በጎራ መከፋፈሉም እንዲያውም ይበልጥ ገኃድ ሆነ። የዲሞክራሲን አስፈላጊነት የከዳ ማንም አልነበረም፤ ግን ወደዲሞክራሲያዊ መሄጃው መንገድ ወይም እንዲያውም ዲሞክራሲ ምን ማለትም እንደሆን በየጎራው የነበረ አመለካከት ተመሳሳይ አልነበረም።

እንዳንዶች የተናገሩት የደርግ ሥልጣን መያዝ ያለቀለት ጉዳይ ከሆነ በኋላ ቢሆንም መከፋፈሉ የመጣው በኋለኛው ጊዜ ሲሸሉ ደርግን ሊተካ ከፈለገ በኋላ ነበር ብለው ያመካኛሉ። ከዚህ የበለጠ ከእውነት የራቀ ነገር ሊገኝ አይችልም። ከፍፍሉ የተፈጠረው ደርግ ሥልጣን ከመያዙ አስቀድሞ ነበር። ተደግሞነት የነበረው የሕዝባዊው ንቅናቄ ተራማጁ ክፍል ገና ከጥንስሱ ደርግ የተባለው ፍጡር ምን ሊያስከትል እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር። ስለሆነም ከመስከረም ፪ በፊት አስቀድሞ የማስጠንቀቂያው መጥቅዕ አስተጋብቷል። የነሐሴው ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የዲሞክራሲያ እትም በግልጽ እንዳስቀመጠው፤

«ደርግ የሕዝቡን ዲሞክራሲያውያን ጥያቄዎች ሊያሟላ አይችልም፤ ምክንያቱም ሕዝቡ የሚፈልገው ሞግዚት ሳይሆን .....

* ዲሞ አውጎስት 23 1974 በትክክል ቅዳ።

ከዚህ የበለጠ ግልጽ መሆን አይችልም: ንጉሣዊው መንግሥት በአምባገነናዊ ወታደራዊ መንግሥት እንደሚተካ ፅውን እየሆነ መጥቶም ነበር። በቀጥታ «የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል» እንደተባለው ተረት ሆነና መስከረም ፪ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ተገልብጠው ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። የአድኃሪው መንግሥትና የሥርዓቱም ከፍተኛ መገለጫ የሆነው ንጉሥ ብሎ ብሎ በመግልበጡ (ሕዝባዊ ንቅናቄው ከጠየቀው በተቃራኒው ንጉሣዊ መንግሥት በዚያ ጊዜ የተወገደ ባይሆንም) ሕዝቡ ፈነደቀ። ግን መጪው ሁኔታ ስላሳሰበው ፍንደቃው የተቆጠበ ነበር።(17) ለነገሩማ

ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፣ በቀውጢ ሰአት የኢትዮጵያ ሕዝብ በወታደር ላይ እምነቱን ፈጽሞ እንደማይጥል አሳምሮ ያውቃል። ሕዝቡም ያ ክፉኛ የፈራው ነገርም ብዙም ሳይቆይ ደረሰ። ወታደራዊ መሪዎቹ፣ ዲሞክራሲያዊ መብት መጠየቅም ሆነ ተቃውሞ ማሰማት እንደወንጀልና እንደፀረ አብዮት ተግባር የሚቆጠር መሆኑን ለማወጅ ብዙ ጊዜም አልፈጀባቸውም።

ወደሽብሩ ያመራው የግፍጫው መነሻና መንደርደሪያ ይህ ነው። ደርግ ራሱን እደላድሎ ለመቀመጥ በጎይል ከመጠቀም ሌላ ምርጫ አልነበረውም። ከዚህ እንጻርም ስንመለከተው ሽብሩ ከደርግ ጋር የተወለደ መሆኑን እንገነዘባለን።

፫

ኩሹኩ ሽብር
አዲሱ አምባገነንትና ሕዝቡ

«የዲሞክራሲ መብቶች ከመታጣታቸው የተነሣ ... አብዮቱ አደጋ ላይ ወድቋል ... የአብዮቱ ሂደት አቅጣጫውን እንዲቀይር እየተደረገ ነው፤ ... »
የኢሠአግ ልዩ ጉባዔ መስከረም ፰- ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

«ከመንፈቀ ሌሊት እስከንጋት የሚዘልቅ የሰዓት እላፊ ዓዋጅ በዋና ከተሞች ከታወጀ ወዲህ ... የኢትዮጵያው ሌሊት ሰላም የሠፈነበት ሆኗል፤ ዝምታም በዕውኑት «ወርቅ» ነው። በእኛ ሁኔታ የሰዓት እላፊው ዓዋጅ አውሮፓ ውስጥ ካሉ የድምፅ ሚትሮች የተሻለ ውጤት አሳይቷል።»

ኢትዮጵያን ሄራልድ ኖቬምበር 9, 1975

ደርግ በይፋ ያወጀው በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በኢሕአፓ ላይ ግልጽ ባወጀበት ጊዜ ነበር። ግን በ፲፱፻፷፯ እና በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም መካከል ምን ሁኔታ ነበር? አካቶ የሰላም ጊዜ ኑሯልን? አንዳንዶች እንደሚያመካኙት የደርግ ተቃዋሚዎችስ ወደዐመፅ ተግባር በመሠማራታቸው ደርግ አጸፋውን እንዲመልስ አልገፉትም ነበርን? የከተማው ሥውር ጦርነት ተብሎ ለመጠራት ቢያበቃው ጦርነትስ የመጀመሪያዎቱን ጥይት የተኩሳት ማን ነው?

ረገጠሀ ግዛ አሠራሩስ በአስመሳይ ዴሞክራሲያዊ አሠራር በማጀብ ላይ ያለው ወታደራዊ መንግሥት ወደዐመፅ ያመራሁት ለኢሕአፓ «ነጭ ሽብር» ለመመለስ ስል ነበር ብሎ ዓይን አውጥቶ ይከራከራል። አንዳንድ ሌጣ ትንተና የማድረግ ዝንባሌ ያላቸው ወይም ወታደራዊ መሪዎቹ ላይ በጎ አመለካከት ያሳደሩ የውጭ ፀሐፊዎች ይህን የመንግሥቱን ከርከር ከጊዜ ወደጊዜ ሲያስተጋቡ ቆይተዋል። አሁንም ሌሎች ደግሞ የተጠማዘዘ አመክንዮን በማንፀባረቅ፣ ደርግ ወደዐመፅ ተግባር ቢሠማራም ተቃሚዎቹ መፈናፈኛ አሳጥተውት÷ ለመግዛት ተስኖት ነበርና ምርጫ አልነበረውም ብለው ያቀርባሉ። በሌላም አንጋገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ኢሕአፓ በራሱ ላይ መዓት ጠራ መባሉ ነው። «ነብርን የነካካ ...» ወይንም የአገራችን ምሳሌያዊ አባባል ጎልደፍ ባለ አነጋገር እንደሚያስቀምጡ "አሳሪፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትወጣለች" ዓይነት:: (18)

ነገሩን የሚያውቁትማ ኢትዮጵያውያን ስለትንሹ ሽብርና ስለትልቁ ሽብር ያወራሉ። ትንሹ ሽብር ወይም አንዳንዶች «ኩሹክ ሽብር» ብለው የሚጠሩት ገና ከጠዋቱ የደርግ አገዛዝ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ አብሮ የመጣና በኋላ ለተከተለው ቀይ ሽብር» ተብሎ ለታወቀውና መንግሥትም «ቀይ ትርኢት» እያለ ከፍ ከፍ ሲያደርገው ለነበረው የሰው እልቂት፣ የደም መጉረፍ መንገድ የጠረገ ነው። ከመስከረም ፲፱፻፷፯ ዓ.ም እስከ መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ሰላም አልነበረም። አዲስ ጦርነት ተከፍቶ ነበር። በዚህን ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ ጠመንጃ አላነሳም፤ የገደለውም ባለሥልጣን አልነበረም፤ ያለው ዋና መሣሪያ በሰላማዊ ሠልፍ ተቃውሞን ማስተላለፍ፣ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግና የመሳሰሉት ነበሩ። ሕዝቡ በራሱ ትግል ከፈውዳሉ መንግሥት ፈልቅቆ ያወጣውን መብት ለመጠቀም ብቻ ነበር እየሞከረ ያለው። በተጨማሪም ሕዝቡ ወታደራዊው መንግሥት ወደካምፑ ለመመለስ የገባውን ቃል ኪዳን ጠብቆ ሥልጣን ለሕዝቡ እንዲያስረክብ ጠይቆ ነበር። ሕዝቡ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን አቀረበ፤ ደርግ ግን ኃይልን በመጠቀም አጸፋ ሰጠ። እዉነቱ ይህ ነው፤ ይህም ሆኖ ይኖራል።

መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ደርግ ሥልጣን ሲይዝ በዚያን ዕለት ባስተላለፈው ዓዋጅ ካሠፈራቸው እንቀጾች ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፤

እንቀጽ 3 (ሀ) አልጋ ወራሹ፣ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋወሰን የኢትዮጵያ ንጉሥ ይሆናሉ፤

እንቀጽ 8 ይህ ዓዋጅ ሥራ ላይ እስከዋለበት ጊዜ ድረስ የ«የኢትዮጵያ ትቅደም» ፍልስፍና መታወም፣ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣ ያልተፈቀደ ሰላማዊ ሠልፍ ወይም የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ሊያናጋ በሚችል አድራጎት ውስጥ መገኘት የተከለከለ ነው።

እንቀጽ 9 በዚህ ዓዋጅ ውስጥ በእንቀጽ 8 የተዘረዘሩትን ትእዛዝ የሚጥሱትን ለመዳኘት ልዩ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ይቋቋማል ...
በእነዚህ ልዩ ፍርድ ቤቶች የተሳለፉ የፍርድ ውሳኔዎች ይግባኝ አይጠየቅባቸውም።

በሌላም አንጋገር ደርግ ወደሥር ሠፈሩ መመለሱ ቀርቶ ሕዝቡ ምንም ቅሬታ ሳይተነፍስ እሱ ተሸብበ ወደቀድሞው የግዙነት ሁኔታ እንዲመለስ ይንጎራጉት ጀመር። እንደሚጠቀሰው ሁሉ እኒያ በየካቲቱ አብዮት በንጉሳዊ ቀደምትነት የተሠለፉት አጥብቀው ተቃወሙ። ኢሠአግ ከመስከረም ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የቆየ ጉሳዬ በመጥራት ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ውሳኔዎች አስተላለፈ። እኒህም ጥያቄዎች በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በጥቂት የክብር ዘበኛ መኩንኖችና ወታደሮች፣ በአየር ኃይል፣ በአርሚ አቪዬሽንና በመሐንዲስ ክፍል አባሎች እንዲሁም በመንግሥት ሠራተኞች ተስተጋቡ። ገልጽ እንደነበረው ደርግ እንኳን ሥልጣን ለማስረከብ ለማካፈልም ፍላጎት አልነበረውምና ዓዋጁ ሥራ ላይ በማዋል ወደዕመቃው ተረማመደ።

የላብአደሩ ማኅበራትና የተማሪ ማኅበራት መሪዎች ተያዙ፣ ታደኑ።። ደርግ ከአራተኛ ክፍለ-ጦር የጦር ቡድኖች ልክ የመሐንዲስ ክፍልን እንዲያጠቁ አምስት ወታደሮች ሲገደሉ፣ ከበባት በላይ ቁስለኞል በሃያ ውስጥ የሚገመቱ ከአርሚ አቪዬሽንና ከክብር ዘበኛ ታፍሰዋል። የንጉዘብ ሚኒስተርና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች እንዲሁም ከሠላሳ በላይ የሚሆኑ ምሁራን ታሥረዋል:: ጥቅምት ቀን "ለሥራ ለመመዝገብ" ኢሠአግ ዋና ጽቤት ደጃፍ ላይ የተሰባሰቡ ሥራ አጦች÷ ምንም

እንኳ ለመሰብሰብ የፖሊስ ፈቃድ (በፀጥታ ም/ሐላፊ በኩሎኔል በቀለ ተከሉ የተፈረመ) የነበራቸው ቢሆንም በፀጥታ ኃይሎች መደብደባቸው አልቀረላቸውም። ከሥራ አጦቹ አብዛኛዎቹ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የወደቁ ሥራ ፈላጊዎች ነበሩ። በደረሰው ድብደባ ከሥራ አጦቹ አንድ ሰው ሲሞት በርከት ያሉ ቁስለኞል።

እነሆም ከመያዝ ወደመግደል ሂደቱ አመራ። የፖሊስ ድጋፍ ከነበራቸው የመሬት ከበርቴዎች ጋር አርሶ አደሩ ግፍጫ ውስጥ እንደገባ ግድያውም ወደገጠሩ መዛመት ጀመረ። የወመቤን ንረት በመጨመር ደርግ ያለምንም ፍርድ ጎጻር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ግምሻውን ፶፱ ሰዎች ገደለ። ከዚህ በተጨማሪም የራሱ የወታደራዊው አምባገነን ቡድን የመጀመሪያው ሊቀመንበር የነበረው ሌተና ጀኔራል አማን አንዶም ከ፰ ረዳቶች ጋር ተገደለ። ይህ የመጀመሪያው አጋር የመገደል ሁኔታ ደርግ ሕጋዊ መንገዶች መከተልን አሽቀንጥሮ መጣሉን በግ አድርጎ አሳየ። ከዚህም ጋር ብዙ አሥረኞች (በልዩ ልዩ ምክንያት የታሠሩ) ፀረአብዮተኞች እያለ አዳምሮ የመግደል ፈሊጡን በሥራ ላይ ማዋል ጀመረ።

ጎጻር ፲፬ ቀን ከተገደሉት አብዛኛዎቹ ሚኒስትሮችና የወደቀው መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሲሆኑ እንዳቸውም ለፍርድ አልቀረቡም። ባስቸኳይ በተጠራ የደርግ ስብሰባ ስማቸው ተነብቦ የሞት ፍርዳቸው በእጅ ማውጣት የጸደቀ ነው። ለምሳሌ ጀኔራል ኢሳይያስ ወደመገደያው ሥፍራ የተወሰደው ከሆስፒታል ሲሆን ነፍሰን ስቶ በነበረበት ሁኔታ እንደነበር ይነገራል። ተጨባጭነት ባላቸው ወንጀሎች ሊከሰሱ የሚችሉ የንጉሥ ነገሥቱ የቅርብ ታማኝ አገልጋዮች ሳይነኩ፣ «ከእሀያው ይልቅ ጻውላው» ጥፋተኛ ሆኖ በደርግ መኩንኖች የተለየ መወደድን ለማትረፍ ያልታደሉት እንዲገደሉ መወሰኑ ምርጫው ምን ያህል በዘፈቀደ የተደረገ እንደነበር ለመመዘን ያስችላል። ደርግ ይህንን ሕገ ወጥ ግድያ የፖለቲካ ውሳኔ አለው። ከነዚያው ከአሮጌው መንግሥት ጹማምንት ጋር እኒያ በጥቅምት ወር ውስጥ የወታደራዊ አገዛዝ አብቅቶ የዲሞክራሲ መብት ይከበር በማለታቸው ተይዘው የነበሩቱ እነ ኮሎኔል ይገዙ ይመኑ፣ ኻምበል በላይ ጸጋዬ ከአርሚ አቪዬሽን፣ በቀለ ወልደጊዮርጊስ ባለሌላ ማዕረግ ከከብር ዘበኛ ተገደሉ።

ከነዚህ ግድያዎች በኋላ ደርግ ተጨማሪ ወታደሮች

ወደኤርትራ በመስደድ እየጋመ የመጣውን የኤርትራን ሽምቅ ውጊያ በኃይል ለመፍታት መረጠ።[19] ይህም ብቻ አልነበረም፤ እሥራኤል የሠለጠኑ ልዩ ኮማንዶዎችና አፋኝ ቡድኖች በንሲብ የተመረጡ ወጣቶችን በጥያኖ ሽቦ እያነቁ ለመግደል በአሥመራ ከተማ ውስጥ እንዲሠማሩ ተደረገ። ሽብር በከተማዋም ከዚያም ባሻገር ተስፋፋ። በስም ኤርትራዊ የሆነ ይጨፈጨፉል የሚል ፀረኤርትራውያን አስባልታ በአዲስ አበባና በሌሎች ከባቢዎች ተሠራጨ። (እንዳንዶች ይህን ወሬ ያራገበው ራሱ መንግሥት ነበር ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የኤርትራ ግንባሮች ወታደራዊ ኃይላቸውን ለማሳደጊያ እንዲረዳቸው ያደረጉት ነበር ብለው ይከራከራሉ።) በርካታ ኤርትራውያን ወደስደት ወይም ወደሽምቅ ተዋጊዎቹ ሸሹ። ጎጻር ፮ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ደርግ ደግሞ እንደገና የሚስማማውን ሌላ አዋጅ ይዞ መጣ:: ለቀድሞ የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ ማሻሻያ ሆኖ የቀረበ ነበር። ይኸው ዓዋጅ የልዩ ጦር ፍርድ ቤትን መቋቋም ከማስታወቁም በላይ የተዘረዘሩት አንቀጾች ሠፋ ያሉና በደንብ ያልተብራሩ፣ የተለያዩ ጥፋቶችን ለሞት ቅጣት የሚያበቁ ወንጀሎች አድርጎ ያቀርባቸዋል። በዚህም መሠረት አንቀጽ 5 «በመንግሥቱ መከላከያ ኃይል ላይ መሰናከል የፈጠረ ማንኛውም ሰው በሞት እንዲቀጣ» ይደነግጋል። ሆኖም ይኸው ድንጋጌ በጦር ኃይሎች ውስጥ የደርግን አገዛዝ የሚቃወሙ ዴሞክራሲያውያን ኃይሎች ላይ የተነጣጠረ እንደነበረ ማንም አልሳተውም። ከህደትም በሞት ያስቀጣል ይላልI ግን በከህደት ደረጃ የሚለኩ ምን ዓይነት አድራጎቶች ናቸው የሚለው ውሳኔና ትርጓሜ የተተወው፣ ወታደሮችንም ሊቪሎችንም እንዲኖኑ ለተመደቡት ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ነበር። እንደሚጠበቀውም ዓዋጁ ላለፈውም እንዲሠራ ሆኖ ስለወጣ በታሠሩት ላይ፣ በጎጻር አጋማሽ ላይ ለተፈጸመው ርሽና መንገዱን የጠረገ ነበር። በመሠረቱ ልዩ የጦር ፍርድ ቤቶች የተባሉት ማስመሰያ ከመሆን አልዘለሉም። በጭፍን የሚፈጸሙ ርሽናዎች፣ «ልዩ እርምጃዎች» ወይም «የፖለቲካ ውሳኔዎች»ን ፍርድ ለምልክት እንኳ አለ ማለትን እሳፈ መናገር አድርገውት ነበርና ፍርድ ቤቶቹ ትርጉም አልነበራቸውም። ጠበቅ ያለ ፍርድ የሚሰጡት የፍርድ አካሎች ትንሽ «ለዘብታ» (እንደራሮ ነው) በሚያሳዩበት ጊዜ ውሳኔያቸው በደርግ ይሻራል።

እዚህ ላይ ሊነሣ የሚችል መጋሊት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የተረሸኑት የ፰ቱ ሰዎች ዕጣ ነው። ልዩ የጦር ፍርደ ቤቱ

ብርጋዴር ጀኔራል ታደሰ ብሩን፣ ሌተና ኮሎኔል ኃይሉ ረጋሳና ደጃዝማች አሉላ በቀለን፣ መለስ ተክሌን፣ ግደይ ገብረዋህድንና ረዘነ ሀጎስን ዕድሜ ይፍታህ ፈረደባቸው። አሉላ በቀለ የታወቀ የመሬት ከበርቴ ሲሆን ታደሰ ብሩ ደግሞ በ፲፱፻፷ዎቹ ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ በሜጫና ቱሉማ እንቅስቃሴ (ለኦሮሞ ሕዝብ የሚታገል) ወቢይ ሚና የተጫወተ የታወቀ የኦሮሞ መሪ ነበርና መለስ ግደይና ረዘነ ደግሞ ወታደራዊውን መንግሥት የሚታወሙ ምሁራን ነበሩ። ለንገሩ፣ መለስ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋዜጣ የታገል አዘጋጅ ሲሆን፤ የታሠረበት ምክንያት መለከረም ወር ላይ የደርግ ወኪሎች ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ንግግር ለማድረግ በመጡበት ጊዜ በድፍረት ስለተከራከራቸው ነበር። ደርግ የልዩ ጦር ፍርድ ቤቱን የፍርድ ውሳኔ ከመረመረ በኋላ የእድሜ ይፍታህ ፍርዱን በመሻር ሁሉም በሞት እንዲቀጡ ወሰነ። ስለዚህም ለውጡን የሚታወሙው የመሬት ከበርቴና የማይታወሙቱ ሁለት መኰንኖች፣ ወታደሩ ፖለቲካዊ መድረኩ ላይ ብቅ ከማለቱ የትና የት በሬት «መሬት ላራሹ» እያሉ የታገሉ ምሁራን ተዳምረው ተረሸኑ። የደርግ ይፋ (አፈሌል) መግለጫም የተረሸኑቱ «በመሬት ይዞታው መሻሻልና በኢትዮጵያ ጎብረተሰባዊነት ፍልስፍና) ላይ ያመፁ እንደነበሩ ገለጸ። የግልንቢጥ ሆነና የመንግሥቱን ሽርክት ብሔራዊ ስሜት፣ የግልጽነት ማጣት ሕዝባዊ መሠረት አለመኖር፣ በማኬላቸው መረባረቢያ ተደርገው የነበሩ ምሁራን እንደፀረሶሻሊስት (ጎብረተሰባዊነት) ተቆጥረው «የርካሽ ርዕዮተ ዓለም» ተከታዮች ናቸው እያለ ሲያነሣሳባቸው በነበረው በዚያው በደርግ ተረሸኑ። ግን ይህ ምፀት ብዙ ጊዜ ራሱን የሚደጋገም ሆኖ የኢትዮጵያ ዕውነታ ይሆናል።

ለደርግ ጠንከር ያለ በጎ አመለካከት ያለው፣ ለኢትዮጵያውን ተቃዋሚ ከፍሎች ግን ከቶ በዚህ እንደማይጠረጠረው እንደ ፍሬድ ሃሊደይ ያለው ፀሐፊ እንኳን የደርግ ዕመቃ ከኢሕአፓ ማንኛውም ወታደራዊ እርምጃ በፊት መቅደሙን ሙሉ በሙሉ ሊክደው አልቻለም፤

> «ሲቪል ተቃዋሚዎችን መያዝ፣ ለንብረ ሰቆቃው መዳረግና መግደልም ከሜይ ዲይ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ጎጥት ጀመረ፤ ግን ይህ እድራጉት እስከ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ድረስ የጊዜያዊ አስተዳደራዊ ደርግ ፖሊሲ ውስጥ ማዕከላዊ

ቦታ አልነበረውም። (20)

በእውነቱ በመንግሥቱ ፖሊሲ ውስጥ ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም በፊት ማዕከላዊ ቦታ አልነበረውምን? ከሚዩ ዲዩ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በፊትስ ደርግ ወደግሠርና ወደመግደል አልተረግመደም ነበርን? ባለፉት ገጾች ውስጥ ደርግ ዕመቃውን የጀመረውና ከጠቅቱ እንደነበረ ሞክረናል። ዋና ዋናዎቹን ለመውረድ ጥቂትም ልንጨምር እንችላለን።

- መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. (October 7, 1975) ደርግ የመሐንዲስ ከፍል እንዲያጠቁ ወታደሮች ልኮ ሃምሳ አለቃ መንግሥተ አብ ኃይሌ፥ ምክትል አሥር አለቃ ብርሃኑ መሐሪ፥ ጣሰው ኃይሰ ሚካኤልና ወልደሚካኤል ከበደ ተገደሉ። ኃይለሚካኤልና ወልደሚካኤል ከበደ ተገደሉ። ከቁስለኞች፣ ሻላቃ ይታየው ቦሮቂላ፣ አምላ አለቃ በቀለ ቱሉ፣ ምክትል አሥር ቢካና ሙታር፣ ምክትል አሥር አለቃ ወልደጊዮርጊስ ታቱ፣ ምክትል አሥር አለቃ ስንታየሁ፣ እንደገና እንዳልካቸው ባለሌላ ማዕረግ ይገኛሉ። እነዚህና ሌሎች የተያዙ ወታደሮች እስካሁን የት እንደገቡ አልታወቀም።

- ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፯ (Oct.23,) አዲስ አበባ ውስጥ ሰላማዊ ሰብሰባ ያደረጉ ሥራ አጦች ላይ የፀጥታ ኃይሎች ተኩስ ከፍተው አንድ ሰው ሲገድሉ በርካታ ቆስለዋል።

- ኅዳር ፲፱ -፲፩ ቀን (Nov 23-24) ደርግ በመሰደው የፖለቲካ ውሳኔ መሠረት ፰ ሰዎች ተረሸንዋል::

- መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.(March 13) ሌተና ኮሎኔል አማረ ባሸን ጨምሮ አራት ሰዎች በወበራ ወረዳ፥ በሰላሌ አውራጃ በሴክዩሪቲ ኃይሎች ተገድለዋል::

- መጋቢት ፲ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.(March 19) ፮ ሰዎች (ቀደም ብለው የተጠቀሱት ጀኔራል ታደሰ ብሩና ሌሎች) ተገድለዋል::

- በሚያዚያ ወር የሁለተኛና የሦስተኛ ከፍለ ጦሮች የጊዜ ገደብ ሰጥተው ደርግ ሥልጣኑን ለሕዝብ አስረክቦ

እንዲወርድ በመጠየቃቸው፣ በእነዚህ ክፍላተ ጦሮች ላይ የግፍ እርምጃ ተወስዶ ከሦላሳ አምስት ያላነሱ መኰንኖችና ወታደሮች ተገድለዋል። ዶልታችኋል በሚል ሰበብም ደርግ ሌ/ኮሎኔል ንጉሤ ኃይሌንና ደበሱ በየነን ጨምሮ ብዙዎችን አስሯል።

- ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. (April 30, 1975) ሠላሳ አርሶ አደሮችና የአርሶ አደር ማኅበራት መሪዎች በከፋ ክፍለሀገር (የቡ እና ሊሙ ውስጥ) ዘጠኝ ሌሎች ድግሞ ጊምቢ ውስጥ (ወለጋ ክ/ሀገር) ተጨማሪ ሰድስት ደግሞ ኖጓ ውስጥ (ኤሉባቦር ክ/ሀገር) ተገድለዋል።

- በዚሁ ጊዜ አካባቢ ደረጀ ለገሠ የተባለ ምሁርና ሌሎች ስምንት ሰዎች ሊሙ ውስጥ (ከፋ) ተረሽነዋል።

- ብቸና ውስጥ በአንድ የደርግ አባል (አውን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል) በሻለቃ እንዳለ ተሰማ በተመራ ጭፍጨፋ ከ፩ሺህ የበለጡ አርሶ አደሮች ተገድለዋል። አርሶአደሮችን ማንበርከክ መንግሥት በሂሊኮፕተሮችና በሞርታሮች ከመጠቀሙም በላይ ለወታደሮቹ የተሰጠውም እዝ የተገኘውን ሁሉ ገደል የሚል ነበር። ከተገደሉት ውስጥ በጣም ወጣቶቹ ወንድማማቾቹ ምኒልክና ግርማ ገሠሠ፣ አካለ ስንኩላን የነበሩት አቶ ውበት፣ አቶ አደም፣ በጣም የሸመገሉት የዘጠና አመቱ አባ ውመር የሚታሰቡ ናቸው። እንዲት ሴትዮም ከሰባት ልጆችዋ ጋር ጎጆዋ ውስጥ እንዳለች ተቃጥላ ሞታለች። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሻለቃ እንዳለ «የብቸናው አራጅ» ተብሎ ይታወቃል።

- በየካቲት ፲፱፻፸፯ ዓ.ም በኤርትራ የእስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ። መቸም እንደሚከተር ሃሊዲይ ያሉት ጦርነት ጦርነት ነው፤ ወይንም ደርግ የመደብ ትግል በማካሄድ ላይ ስለነበረ ተቃዋሚዎቹን የግድ መገደል ነበረበት ይሉ ይሆናል። ከላይ በአጭሩ የጠቀስነው በልዩ ልዩ ቦታዎችና ሁኔታ ይንጸባረቅ የነበረውን ቅኝት ብቻ የሚያሳይ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ሰዎች እየተያዙ ነበር። እደኑ፣ የኢሕአፓ አባላትን ለመያዝና ዴሞክራሲያን ፀጥ ለማሰኘት ነበር። በየፖሊስ ጣቢያዎችና በልዩ እሥር ቤቶች ውስጥ ግብረ ሰቆቃው እንደሚፈጸምና ርሽናም እንደሚካሄድ ይዘገብ

ነበር። በዚህ እያደገ በሚሄድ የግፍ ተግባር የተነሣም ነበር በወቅቱ ሕዝቡ ተቃውሞውን ያሰማ የነበረው።

- በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ውስጥ ሚይ ዲይ በተከበረበት ፅለት ከፎ፩ የማያንሱ ሠራተኞችና ተማሪዎች በወታደሮች ሲገደሉ ሌሎች በርካቶች ደግሞ ተይዘው ታስረዋል።

- ከግንቦት እስከሰኔ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም የተማሪዎች መነሣሳት እየተስፋፋ ሄዶ፣ ያደረጓቸውም ሰላማዊ ሠልፎች በኃይል እንዲበተኑ የተደረገ ሲሆን፣ ቢያንስ የ፲፩ ተማሪዎች መሞት በወቅቱ ተዘግቧል።

- ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም.(May 30)ኢሠአማ የአራት ቀናት ጉባኤ ያካሄደ ሲሆን ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ያስተላለፈው ውሳኔ ደርግን ስላስቆጣው ኢሠአማን ዘጋ፤ በሃያ የሚቆጠሩ የላብአደር መሪዎችን ይዞ አሠረ፤ ሌሎችም፣ በተለያየ ቦታ በተደረጉ ግጭቶች ተገደሉ።

- ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. (June 7, 1975) ! ዓ.ም መቢያ ይጥኔ ጋሹ፣ (የቀድሞ የወረዳ አስተዳዳሪ) ከፍሌ ሞገስ (የቡና ቤት አስተናጋጅ) ወርቁ ሥዩም፣ (ንጋዴ) ዝርው ኃይሌ፣ እድሪስ ኪየር፣ አብዱልቃድርና ባለሌላ ግፅረግ ወታደር፣ ጌታቸው ፋንታዬ በይፋ ተረሽነዋል። ከሣቸው «የተንኮል ፕሮፖጋንዳ በመንዛትና ሕገወጥ ሥራ ውስጥ በመሠማራት የሀገሪቱን ሰላምና ፀጥታ በማደፍረስ» የሚል ነበር። ከሡ ጨርሶ የተሣሣተ እንደነበር ወደፊት የምናየዉ ይሆናል።

- ከሰኔ ፭-፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. (June 15-16,1975) ወላይታ ውስጥ የፀጥታ ኃይሎች የሚያደርሱባቸውን ሥቃይ የተቃወሙ ሰዎች የግፍ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፤ በርካታ የሆኑ ሲገደሉ ከዚያ በላይ የሚሆኑ ደግሞ ቆስለዋል፤ ታሥረዋል።

- በሰኔ ፭፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. እና በሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. መካከል (June 22 - June 8, 1975) ብቻ መንግሥቱ ራሱ በአቀረበው ዘገባ ከልዩ ልዩ

በታዎች ከሰላ እምስት ያላነሱ ሰዎች በፀጥታ ኃይሎች ተገድለዋል። ሟቾቹ ላይ የቀረበው ክስ የመሬት ይዞታን ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ3 በመቃወም ሕዝቡን ለማወናበድ በመሞከራቸው ነው የሚል ነበር።

ሌላም ሌላ አለ። ቦንጋ ውስጥ ብቻ በዚሁ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ውስጥ ፩፻፭ አርሶ አደሮች የፖሊስ ዓመፃ ሰለባዎች ሆነው መውደቃቸው ተዘግቧል። በገለታ/ ፈለገ ነዋይ ውስጥ (ጋሞ ጎፋ ከ/ሀገር) በአንድ ቀን ውስጥ ፹ ሰዎች ተገድለዋል። በብዙ ገጠር አካባቢዎች አርሶ አደሮችና ምሁራን የተገደሉ ሲሆን፣ መንግሥቱ ግን ይህን ሁሉ ነገር፣ «የመሬት ይዞታውን መሻሻልና ሕዝባዊ አብዮቱን በተቃወሙ ላይ» እንደተወሰደ የድምሰሳ እርምጃ አድርጎ አቅርቦታል። በዚያኑ ጊዜ የተበተኑ የተቃዋሚ ወረቀቶች ስለግደያዎቹ የጻፉ ሲሆን፣ ደርግም ቢሆን በተገደለው ሰው መጠን ላይ ልዩነት ቢኖረውም የተገደሉ መኖራቸውን አልካደም።

ነሐሴ ፭፮ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ኢሕአፓ ፕሮግራሙን (በሦስት ታላላቅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች) በመላ ሀገሪቱ በማሠራጨት ሕልውናውን በይፋ ገለጸ። ሥርጭቱ ሥፋት የነበረው ሲሆን ምንም ዓይነት መሰናልከል ሳይገጥመው የተከናወነ ነበር። ዴሞክራሲያም እንደፓርቲው ልማን በይፋ ታውቀ። መንግሥቱም ይበልጥ ተርበደበደ።

መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በ«አብዮቱ ቀን» ከብረ በዓል ሰላማዊ ሠልፈኞች፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር የሚጠይቁና የመንግሥቱን ግፍ የሚያወግዙ መፈክሮች በኅዳድ እንግበው ተሠለፉ።

አሁንም በመስከረም የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ) ዋና ጉባኤውን ጅማ ውስጥ በማካሄድ በሰኔ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. አስተላልፏቸው የነበሩትን ጥያቄዎች እንደገና የሚያስተጋቡ ውሳኔዎች አስተላለፈ። በዋነኛነትም የሚፈጸመው ግፍ እንዲቆም፥ የፖለቲካ እሥረኞች እንዲፈቱ፥ ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር ፥ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት የሚጠይቁ ነበሩ። ደርግ መምህራኑን "አድኃሪያን" በማለት ከመንቀፉም በላይ የተመረጡትን መሪዎች አሠረ። መስከረም ፲፫ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የሚከተለውን መግለጫ ሰጠ ::

«ጥቂት መምህራን ርካሽና የሕዝብን እምነት

የሚሸራቡር ፕሮፖጋንዳ ለማሠራጨት ሲሞክሩ እጅ ተጥንጅ ተይዘዋል። እስተሪዎቹ ግላዊ ፍላጎታቸውን ከግብ ለማድረስ፣ የሀገር እንድነት ለማናጋትና ሕዝቡን በሃይማኖትና በጎሣ ከግብ ለማድረስ፣ የሀገር እንድነትን ለማናጋትና ሕዝቡን በሃይማኖትና በጎሣ ለመከፋፈል፣ በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮት ለማጨናገፍ እየሞከሩ ነበር» !

ርካሽና የሕዝብን እምነት የሚሸረቡር ፕሮፖጋንዳ የተባለው፣ በጉባኤው ተሣታፊዎች ተፈርሞበት ከወጣው ከጉባኤው ውሳኔ ሌላ ነገር ተገኝቶ አልነበረም። ፲፩፪ ያህል አባላት ከድርን ኢትዮጵያ የነበረው ኢመማ በጎጣና በሃይማኖት እማከይነት የግል ፍላጎትን በማርካት ረገድ በምንም ዓይነት ሊከሰስ የሚችል አልነበረም። ሆኖም ሁኔታዎች ደግመው ደጋግመው እንደሚያሳዩት፣ ደርግ ጭካኔ የተመላበትንና ሕገወጥ የሆኑ አድራጎቶቹን ለማጠየቂያ ማንኛውንም ስም ለመለጠፍ የሚሰቀጥጠው አልነበረም። በጊዜው ወደሰባ አምስት የሚጠጉ መምህራን የታሠሩ ሲሆን ብዙዎቹ በ«ቀይ ሽብር» ዓመታት ይካሄዱ በነበሩት የግታ ግታ ግድያዎች መድረሻቸው ጠፍቶ ቀርቷል። ደግሞ የሠራተኞች ተራ ደረሰ። ኢሠአግ ግንቦት ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ታገደ፤ ሆኖም በሠራተኞች ብርቱ ተጋድሎ እገዳው ሊነሳ በቅቷል። ኢሠአግ ከመስከረም ፳- ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. (Sep. 18-19) ለምስት ቀናት ልዩ ጉባኤ አዲስ አበባ ውስጥ ያደረገ ሲሆን በጠቅላላ ሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ፩ደ፹፫ አባል ማኅበራት የመጡ ወኪሎች ተሳታፊዎች ሆነውበታል። ጉባኤው በአንድ ድምፅ ታሪካዊውን ውሳኔ በማሳለፍ መንግሥት የሠራተኞች መሪዎችና ሌሎች የፖለቲካ እሥረኞችን እንዲፈታ፥ በዴሞክራሲያዊ መብት ላይ የተጫነው ገደብ እንዲነሣ፥ የሕዝቡን ጥያቄ በመቀበል በነፃ እንዲደራጅና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት እንዲችል ... ወዘተ ዋጋ ላይ ቁጥጥር እንዲደረግበት ለሠራተኞች ደሞዝ እንዲጨመር፥ ተራማጅ የሆነ የሠራተኞች ሕግ አንዲወጣ ጠየቀ። ውሳኔው በተሳተፉት የማኅበራት ወኪሎች ሁሉ የተፈረመ ነበር።

መስከረም ፲፮ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.(Sep.26) የኢትዮጲያ አየር መንገድ ሠራተኞች ማኅበር አባላት፣ የጉባዔውን ውሳኔ ለሠራተኞች በሚያድሉበት ጊዜ ወታደሮች በወሰዱባቸው

የማጥቃት እርምጃ ስምንት ሠራተኞች ሲገደሉ፣ በሃያ ውስጥ የሚቆጠሩ ሌሎች ቆስለዋል። መንግሥትም «በኢትዮጵያ አየር መንገድ መሥሪያ ቤት ውስጥ ፀረአብዮት ጽሁፍ ሲበትን የነበረ አንድ ሰው እንዳይያዝ በማካወቻው ወታደሮች ተኩስ ለመክፈት ተገደዱ።» ብሎ በይፋ አሳበበ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች በጥይት ከተደበደቡ በኋላ የተከለውን ጉባኤ ተሣትፈው የነበሩ የሠራተኞች ማኅበራት መሪዎችን ከየቦታው ማሠር መሥፋፋቱ ነበር። ይህም ወደእምሳት፣ ወደሥራ ማቆም አድማና ወደባሰ ግፍም አመራ። በአዲስ አበባ፣ በአቃቂ፣ በድሬዳዋና በሌሎች ቦታዎች ... ከአሥራ ሁለት ያላነሱ ሠራተኞች በጥይት ሲገደሉ፣ ወደመቶ አምሣ የሚጠጉ ሠራተኞችና የሠራተኞች መሪዎች፣ የኢሠአግ ሊቀመንበር ማርቆስ ሐጎስን ጨምሮ ተይዘው ታሠሩ።

ምናልባት እዚህ ላይ ጣልቃ አስገብተን በደርግ እጅ የወደቁቱ አሥረኞችን ይዞታ ብናነሣ ደበጅ ይሆናል፤ ማርቆስና ሌሎችም ወደደርግ ገቢ ተወስደው በወቅቱ የደርግ መረጃ ቡም በነበረው በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው የበላይ ተቆጣጣሪነት ተደበደቡ፥ ፀዋትወ ሥቃይም ተቀበሉ። በአንድ የምርመራ ወቅት ማርቆስ ደሙ ከፉኛ ይፈስ ነበርና ኮሎኔል ዳንኤል ወንበሩ እንዳይበላሽ መሬት ላይ እንዲቀመጥ አዘዘው። አንድ ጊዜም መንግሥቱ ከምርመራው ክፍል መጥቶ የምርመራውን አካሄድ ከተመለከተ በኋላ ማርቆስን «እጥፊና ጠፊ እንሆናለን» ብሎት ወጣ። በምርመራው ውስጥ ተደጋግሞ ይጠየቅ የነበረው «የኢሕአፓ አባል ነህን?» የሚለው ነበር። በኋላም በደም የተለወሰው ማርቆስ በሌሎች በእሥር ላይ ባሉ ሠራተኞች ፊት እንዲያልፍ ተደርጎ «ተመልከቱት ሊቀመንበራችሁን! ይህ ነው ንጉሥ የሚሆነው?» እያለ ኮሎኔል ዳንኤል ዘበተባቸው። በምርመራው ወቅት ከእሥረኞቹ ውስጥ አንድ መሐንዲስ ፀዋትወ ሥቃይ ሲያወርዱበት ቢሞትባቸው ወታደሮቹ ሬሳውን ወግደው፥ ቁጥር መሙያ የሚሆናቸው ከውጭ ሌላ እሥረኛ ተኩ። አዲሱም እሥረኛ በመሐንዲሱ ስም ከሚኙ ዘመዶች መምጣት የተጠለውን ምንባብ ሲመገብ ባጀ። ይኸው እስረኛ ከሰባት ወራት እሥራት በኋላ ሲለቀቅ የሚኙ ዘመዶች ለረጂም ጊዜ መታሰላቸውንና ሰዋቸውንም ዳግመኛ እንደማያዩት እወቁ። እንደሚጠበቀው ኃዘናቸውን በንሳቸው አድርገው አፋቸውን ተምትመው ተቀመጡ። ማርቆስ ሀጎስ በኋላ በሲያል ወደሚመሰለል

ንድንድ ወደማይጨው ጦር ሠፈር እሥር ቤት እንዲዛወር ተደረገ።

መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.(September 30,1975) እየተሰፋፋ በመሄድ ላይ ከነበረው እምሳት አኳያ፣ ደርግ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የአስቸኳይ ጊዜ ዓዋጅ ዓወጀ። የዚሁ የአስቸኳይ ጊዜ ዓዋጅ እንቀጽ ሦስት የሚከተሉትን፣ የተከለከሉና ሕገወጥ የሆኑ አድራጎቶች አድርጎ ይዘረዝራቸዋል።

ሀ. ያለፈቃድ የሚሠበሰቡና ሰላማዊ ሠልፍ የሚያደርጉ ከሕዝብና ከሃይማኖት በዓላት ውጭ ተሰብስበው የተገኙ ሰዎች፣
ለ. ሥራ የሚያቆሙ ወይም ሥራ የሚያቀዘቅዙ ሰዎች፣
ሐ. ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ማቆም አድማ እንደአማራጭ የሚወስዱ ሰዎች፣
መ. ሕገወጥ ቃላትን በሕዝብ መሰብሰቢያም ሆነ ወይም በማንኛውም ሌላ ቦታ የሚናገሩ ሰዎች፣
ሠ. ሕገወጥ የሆኑ ጽሁፎችን፣ የመፈክር ሰሌዳዎችን፣ ወይም ሥዕሎችን የሚያዘጋጁ፣ የሚጽፉ፣ የሚያስቀምጡ፣ ወይም የሚያሠራጩ፣ ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ የሚያደርጉ ሰዎች፣
ረ. ሌሎች ሰዎችን ሥራ እንዲያቆሙ የሚያበረታቱ፣ የሚገፋፉ፣ የሚያስፈራሩ፣ ትእዛዝ የሚያስ ተላልፉ፣ ሐሳባቸውን የሚያካፍሉ፣ ወይንም የሚያስገድዱ ሰዎች
ሰ. የሰእት እላፊውን ትእዛዝ የሚጥሱ ሰዎች፣
ሸ. የፀጥታ ኃይሎችን ትእዛዞች የሚያውኩ ወይም የሚጥሱ፥ ከነሱም ጋር በሥራቸው የሚተባበሩ ሰዎች፣
ቀ. ሌሎችን ሰዎች ሕገወጥ ሥራ እንዲሠሩ የሚያስገድዱ ሰዎች
በ. ከቢታቸው ውጭ ማንኛውንም ዓይነት መሣሪያ፣ የእጅ ቦምብን ወይም ሰንጢን ጭምር ይዘው የሚገኙ ሰዎች፣
ተ. ያለበቂ ምክንያት ከሥራቸው የሚቀሩ ሰዎች፣
ቸ. በአጠቃላይ የሕዙቡን ሰላም የሚነሣ ማንኛውም ሰው፣

እነሆም፣ ይበልጥ ግልፅ በሆነ መልክ በአጠቃላይ ማንኛውም ደርግን የሚቃወምና ለመቃወምም የሚያስብ እንደወንጀለኛ ተቆጠረ። በእንዲህ ዓይነት ሕግ የሚገዛ መንግሥት እንዴት የሕዝብን ፈቃድና ፍላጎት እንደሚያንፀባርቅ፣ እንደሚስተር ሃሊ ደይና ፒተር ሽዋብ የመሳሰሉት ሲያስረዱን መስማት

ነዋ!

የአስቸኳይ ጊዜ ዓዋጁ በአፈሊል (ይፋ) ሲሠራበት የቆየው እስከ ታኅሣስ ፲፱፻፷፮ ዓም ቢሆንም፣ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እስካሁን በተጨባጭ ሥራ ላይ እየዋሉ ናቸው። የአስቸኳይ ጊዜው ሕግ ለፀጥታ ኃይሎች «የሕዝብ ሰላምና ፀጥታ በሚያውክ ማንኛውም ሰው ላይ ተገቢውንና የመጨረሻውንም እርምጃ» እንዲወስዱ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። ተገቢ እርምጃ ማለት ሌላ ላይሆን፣ በኃለኛው ጊዜ እንደታየው እንደ «አብዮታዊ ወይም ነጻ እርምጃ» ዓይነቱ ወዲያውኑ ያለፍርድ መግደል ማለት ነበር። «በታየበት ግደል» የሚል ፖሊሲ ወታደሮች በተግባር ላይ ያውሉ እንደነበር የ1977 (እአቆ) አምነስቲ ኢንተርናሽናል በኢትዮጵያ ላይ የጻፈው ዘገባ ገጽ 4 ያረጋግጣል። በዚህ ጊዜም የንበረው የሞት መጠን የሚናቅ አልነበረም።

የግያፈናፍኑት ሕጎች አሁንም ከወራት በኃላ ሌላ የወንጀለኛ መቅጫ "ማሻሻያ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. (July 5,1975) ተደርጎላቸው" ይበልጥ እንዳያፈናፍኑ ተደረጉ። አዲሶቹ አንቀጾች በግንኛውም «ፀረአብዮት ጽሁፍ» በሚያሠራው ላይ ቅጣቱን ሲጨምሩ «ከፀረሕዝብ ወይም ከፀረአብዮት ድርጅቶች ጋር ባገር ውስጥም ሆነ ውጭ ግንኙነት በሚመሠርት፣ በጎ አመለካከት በሚያሳድር ወይም እርዳታ በሚያደርግ» ማንኛውም ሰው ላይ የሞት ቅጣት ያዝዛሉ። መንግሥት ዝቅተኛ በሆነና በዘፈቀደ ባወጣው የዋጋ ተመኑ መሠረት እህላቸውን ሊያቀኑ ፈቃደኛ ያልሆኑ አርሶ አደሮች «በማከማቸት ፣ ከዋጋ በላይ በመሸጥ፣ ወይም እህልና ሌሎች ሸቀጣ ሸቀጦች ወደሕዝቡ እንዳይደርሱ በማገድ «ወንጀል» የሞት ቅጣት የሚገባቸው ያደርጋቸዋል። ይኸው የሐምሌው ሕግ ማንኛውንም ሀገሩን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለቆ የሚወጣ፣ ወይም የሚሞክር በሞት ወይም በዕድሜ ይፍታህ እንዲቀጣ ያዝዛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደርግን «የዓዋጆች ማንግሥት» የሚለው ለዚሁ ነው። የጠባዩም መግለጫዎች የሚያደርጋቸው እንደነዚህ ያሉትን ሕጎች ነው።

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ መታወጁ ግሩን አባባሰው። አሠአግ ተዘጋ፤ መሪዎቹም «የኢምፐሪያሊስት ወኪሎች» እየተባሉ ተወረፉ። ወታደራዊው መንግሥት በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲተካ ብለው የጠየቁ ሁሉ «የሕዝብ ጠላቶች ወይም

ፀረአብዮተኞች» የሚል ሥያሜ ተለጠፈባቸው።(22)ከኤርትራና ከሌሎች ቦታዎችም በመንደር ኗሪዎች ላይ ግፍ ይፈጸም እንደነበር ይዘገብ ነበር። በየአሥር ቤቱ ፀዋትው ሥቃይ መድረሱ የተለመደና የሚያሰቅቅ ሆነ። ተይዘው የታሠሩም "መጻረሻቸው ይጠፉ" ጀመር። ጎጻር ሰኔ ቀን ደርግ አዲስ የሠራተኛ ሕግ ዓወጀ። ሠራተኞውና መሪዎቹ ግን አዲሱ የባርነት ሕግ የሚል የፌዝ ስም አወጡለት።(23) ግፍጫው ቀጠለ፣ ከትላልቅ ከተሞች ውጭ በገጠሩ አካባቢ አንድ ሺ የሚሆኑ "ፀረ አብዮተኞች" በመንዝ (ሸዋ) በአርሲና ባሌ አንደተገደሉ ደርግ ራሱ ዘግቧል።
ዘግቧል።

የሠራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ ምሁራንን፣ ኢሕአፓንና ሌሎችንም የፈውዳላዊውን መንግሥት የታገሉትንና አሁንም አምባገነናዊውን ወታደራዊ አገዛዝ አንቀበል ያሉትን ሁሉ «የሕዝብ ጠላቶች» ብሎ ስም በመለጠፍ፣ ደርግ የተፈጠረውን መፈራረቅ ወደ ፀመፀ ደረጃ አሸጋገረው። ደርግ «ፀረአብዮተኞች» መደምሰስ አለባቸው በሚለው እየገፋ «ከሕዝብ ጠላቶች» ጋር መወያየት አይችልም። ግፉ ተፋፋመ፤ በአንድ ቀን ብቻ በትንሽቱ የንፈ ከተማ ከአርባ ሰዎች በላይ ተይዘው ታሠሩ። ከሠራተኞች ማኅበራት የተያዙት ከአምስት መቶ በላይ ሲያድግ፣ የምሁራኑና የተማሪዎች ደግሞ ተዚህ እጥፍ ሊሆን ምንም የቀረው አልነበረም። በርካታ ታጋዮች ከአደባባይ ተሠወሩ ወይም ወደገጠር ገቡ።

በዚህ ጊዜ የተገለጸው አዲስ ከሥተት የደርግና የመኢሶን ትሥስር መጠናከር ሲሆን፣ እሱም መንበሩን ያገኘው በሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ነበር። በዚህም ሽፋን መኢሶን የደርግ አማካሪና ቀኝ እጅ ሆኖ ብቅ አለ። ብዙም ሳይቆይ በሠናይ ልኪ ይመራ እንደነበረው የወዝ አደር ሊግ (ወዝ ሊግ)፣ በባር ቱምሳ ይመራ እንደነበረው የኢትዮጵያ ሙቱኖች አብዮታዊ ትግል (ኢሙአት) እና፣ ግርክሳዊ ሌኒናዊ ረቮሉሽናዊ ድርጅት (ማሌሪድ ዓይነት ትናንሽ የግራ ቡድኖች የመኢሶንን እርአያ ተከተሉ። ይኸው የሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽ/ቤት መኢሶን ከፍ ያለ ድርሻ የያዘበት ሆኖ የሌሎች ቡድኖች አባላትን ያጠናቀረ ሆነ። ሚናቸው ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ተግባራት መሥራት ሲሆን ፅውነታቸው ያሳየው ተግባራቸው ግን፣ ሕዝቡ የምሩን እንዳለው ፖለቲካዊ የፖሊስ ተግባራት በሚል ርእስ ሥር

የሚመጣ ነበር። አጠቃላይ መንጋው ይጠራ የነበረው፣ ኢትዮጵያ በሞሰሰኒ ዘማች ጦር በተወረረችበት ጊዜ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወታደሮች ጎን ተሠልፈው ለተዋጉት ከሃዲዎች በተሰጠው "ባንዳ" በሚለው ተገቢ ሥያሜ ነበር።

የመኢሶንን ምክር በመስማት ደርግ ሚያዚያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. (April 20, 1976) የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ተብየውን አወጣ። ይህም ውጥንቅጡ የወጣውን "የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት" (ሶሻሊዝም) የተባለውን ለመከላትና "ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም" ን በቦታው ለመተካት የሚያመች እጋጣሚ ሆነ። የግራ ተቃዋሚው የደርግ "ማርክሳዊ ሌኒናዊነት" የጣመው እንዳልነበር ከመሆኑ አንጻር ሲታይ፣ ቢያንስ በቃል ደረጃም ቢሆን አጋጣሚው እንዳገለገለው አከሉ መናገር ያስፈልጋል። ይበልጥ አስፈላጊ በሆነው ላይ ለማትኮር (በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጫና ልንሰጣቸው ከምንፈልጋቸው ጉዳዮች አንጻር) የደርግ ምሁራን ግብረአበሮቹ ደርጉ ቄራጥና አስቸኳይ እርምጃ ወስዶ ኢሕአፓን ከንፍን የተመታች እሞራ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ተንጫጩ፤ ስዊዲን አገር የተማረው የመኢሶን ሊቀመንበር የነበረው በኋላም ራሱ በደርግ እጅ የሚጠፋው ከበደ መንገሻ የተባለ ምሁር «በቢት ቤት ፍተሻ» ማካሄድና «አዲስ አበባን ከአናርኪስቶች ማጽዳት» እንደሚያስፈልግ ለደርግ ማስታወሻ ጻፈ። «አናርኪስቶች የሚለው ለኢሕአፓ የተሰጠው ትክል ቢሆን፥ ሌሎችም አብረው የሚጎዳኙ እንደ ትሮትስካይቶችና ሌላም ሌላ ተቀጥላዎች ነበሩ። የወዝ ሊጉ ሠናይ ልኬ የከበደ መንገሻን ሐሳብ ደግፎ «የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች» የሚባሉ ሰዎች የስም ዝርዝር በመኢሶንና በወዝ ሊግ ተሰናዳ።

የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. (March 3,1976) ደርግ ሽብር ከፍቶ የኢሕአፓን ታጋዮችና ደጋፊዎችን ለመጨፍጨፍ ማቀዱን በማጋለጥ ኢሕአፓ ይፋ መግለጫ አወጣ። ደርግ እጅግ አረመኔና እጅግም ይፈሩ የነበሩትን ሁለት ሻለቆች ወደደቡብ በመላክ አዲስ የዐመፃ ማዕበል ሁር ተለቀቀ። የመንግሥቱ የቅርብ ጓደኞች የነበሩና አሁንም በአምባገነኑ ገዥ ቡድን የበላይ አመራር አባላት የሆኑት ሻለቃ አሊ ሙሳና ሻለቃ ጌታቸው ተቈጣጥረው ያስፈጽሙ ዘንድ ወደጅማ (ከፋ) ወደሐረር (አሰበ ተፈሪ ...) ወደአዋሽና ወደወልቂጤ ሄዱ። ሕዝቡ እጅግ ሲፈራ የነበረው የደርግን የዐመፃ ባሕርይ እንዚህ ሁለት ሻለቆች እረጋገጡለት። እንድም ለመሐላ ላያስተርፉ የተጠረጠሩትን ሁሉ ረሽኑ።- የተያዘ ልጁን ፍለጋ የጣ እባት እዚያው ተገደለ፣ በመኖሪያ ቤቶች የተጠረጠሩ ሰዎች ድመቶች እንኳን ሳይቀሩ በሻለቃ አሊ ተገደሉ። ታላላቅና ትናንሽ ነጋዴዎች ከሐረር/አሰበ ተፈሪ ውስጥ ተይዘው ንብረታቸውን በሻለቆቹና በጓደኞቻቸው ከተወረሰ በኋላ "አናርኪስቶች" ተብለው ተረሸኑ። የተያዙት ሰዎች ከከተማ ወጠ ብሎ ገደል አፋፍ ላይ እየተረሸኑ ወደታች ይወረወሩ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሚያዚያ ፲፪ ቀን (April 22) አዲስ አበባ ውስጥ የብሔራዊ ቲያትርና ከትያትር ጋርግንኙነት ያላቸው የግዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ተዋንያንና ዘፋኞች ሰላማዊ ሠልፍ አድርገው የደርግና የመኢሶንን የሚያዚያ ፲፪ ቱ (April 20) ዴሞክራሲያዊ መብትን ለሕዝብ የሠጠውን የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተግባር ፈተኑት። ማኅበራት የማቋቋም መብት እንዲኖራቸው፥ የሥራ ሁኔታ እንዲሻሻል የሚሉ ነበሩ ጥያቄዎቻቸው። ግን የታጠቁ ወታደሮችና ቆመጥ የያዙ ፖሊሶች በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያቸውን ያሰሙ በነበሩቱ ሠልፈኞች ላይ የጥቃት እርምጃ በመውሰድ ፭ ሲገድሉ (፫ ወዲያውኑ ሲሞቱ፣ ሌሎች ዘግይተው ሆስፒታል ውስጥ ሞተዋል።) ከፎ በላይ ተይዘው ታሥረዋል። እነሆም ደርግና መኢሶን ስለዴሞክራሲያዊ መብት የገቡት ቃል በሰላማዊ መንገድ ተፈትኖ ባዶ ቃል መሆኑ ተረጋገጠ።

ሚያዚያ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በኤርትራ ላይ የአርሶ አደር ዘመቻ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነበር፤ የሐሳቡ ጠንሳሽ መኢሶን ቢሆንም እንደሚጠበቀው የደርግን ትምከህታዊና ደመነፍሳዊ የወኔ ስሜት ሊኩረኩር ችሏል። ዕቅዱ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ አርሶ አደሮችን በሰላምም ሆነ በኃይል ከጉጃም፣ ከትግራይ፣ ከበጌምድርና (ጎንደር) ወሎ አሰባስቦ፣ ያን የረባ መሣሪያ ያልነበረውን የሕዝብ ማዕበል በኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎች ላይ ለማጉረፍ ነበር። አሁን በስደት ላይ አውሮፓ የሚገኘው የመኢሶን መሪ ነገደ ጎበዜ «ዘመቻውን፣ ተገንጣይ ወንበዴዎች ላይ በግበት ገንፍሎ የወጣ የሕዝብ ስሜት፣ እንደሆነ አድርጋችሁ ማቅረብ አለባችሁ» ብሎ ለተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቲክ ሠራተኞች ለማስረዳት ወደቦን (ምዕራብ ጀርመን) ሄዶ ነበር። ኢሕአፓም ይህን የጥፋትን የዕልቂት ድግሥ አጋለጠ። በሀገሪቱ ዋና ከተማ በአዲስ አበባና

በሴሎች ብዙ ከተሞች ይህን የታሰበውን ዘመቻ በመቃወም ሰላማዊ ሠልፎች ተደረጉ። ብዙ ሰላማዊ ሠልፉን የተካፈሉ ሞቱ፤ ከዚያም የሚበልጡ ቈሰሉ፤ ታሰሩ።[24] ሆኖም «ሬዛ ዘመቻ» የሚል መጠሪያ የተሰጠው ያ የአርሶአደር ዘመቻ ውጤቱ ጨርሶ መና ሆኖ ቀረ። ምክንያቱም፣ እፍኝ የማይሞሉ የረባም ጥቅስ የሌላቸው አረቦችና ከሃዲዎችን ነው የምትገጥመው ተብሎ የተነገረው፣ ይህ ነው የሚባል መሣሪያ ያልያዘ ዘማች በደንብ በታጠቁ በሽምቅ ተዋጊዎች ከፉኛ ምት ደርሶበት ተበትኖ ነበርና።

የ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ሚይ ደይም በአዲስ አበባና በሴሎች ከተሞች ስፋት ያላቸው ተቃውሞዎች የታየበት ቀን ነበር። ሰላማዊ ሠልፍ አድራጊዎቹ ሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ምሁራን ... ወዘተ ያነገቧቸው መፈክሮች ዲሞክራሲያውያን መብቶች እንዲከበሩ፣ አሠሪተኞቹ የመነሻ ደሞዝ እንዲጨመር፣ («ደሞዛችን ፴ ብር፣ የጤፍ ዋጋ ፭ ብር» ይባል ነበር። በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አንድ ኩንታል ጤፍ ፪፤ ብር ደርሶ ነበር።) በኤርትራ ውስጥ የሚካሄደው ግድያ እንዲቆምና፣ ጥያቄውም በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ፣ ኢሠአግ ሕጋዊነቱ እንዲመለስለት፣ ... ወዘተ የሚሉ ነበሩ። በከተሞች ሁሉ ወታደሮችና ፖሊሶች ሰላማዊ ሠልፍ አድራጊዎች ላይ የማጥቃት እርምጃ በመውሰድ ቁጥሩ በውል ያልታወቀ አንድ ፭ የሚሆን ሰው መሞቱ ሲዘገብ በርካታ የሚሆኑ ታሥረዋል። ከነዚህም ብዙዎቹ በኋለኛው ጊዜ ማታ ማታ ይካሄድ በነበረው በይፋ በታወጀው ሽብር መጻረሻው ጠፍቶ ቀርቷል።

ግንቦት ፳፭ ቀን (June 2) ደርግ የኢንዱስትሪ ላብአደር ማኅበራትን ስብሰባ በኃይል በተነ፣ በሃያም የሚቆጠሩ ታሠሩ። በሠኔ ፳፩ (July 5) ደግሞ ቀደም ብሉን የጠቀስነው የወንጀለኛ መቅጫ ማሻሻያዎች ታወጁ፤ በዚያም መሠረት እንደ ኢሕአፓ ባሉት ፓርቲዎች ላይ እንኳን በጎ አመለካከት ማሳደር ቀርቶ በሕይወት የሚያስቀጣ ወንጀል ሆነ። በሐምሌ ውስጥ ሻለቃ አሊ ሙሳና ሻለቃ ጌታቹው ሽበሺ የግድያ ዘመቻቸውን በሚያካሂዱበት ወቅት በሻለቃ ታከለ ወልዴ የሚመራ ቡድን ደግሞ በሲዳሞ ክፍለሀገር በአፈር ውስጥ ከ፰፻ በላይ አርሶአደሮችና ዘማች ተማሪዎች ተጨፈጨፉ። የደርግ ወታደሮች የፈጸሟቸው ወንጀሎች ሕዝቡን ከፉኛ አስቆጥቶት ዐምፆ ተነሣ። ደርግም በአካባቢው ፈንቅሎ የወጣውን ያንን የሕዝብ መነሣሣት

ለማቀዝቀዝ ባደረገው ጥረት ሻለቃ ታከለን ይዞ ሚሠር ተገደደ፤ በዚህም አላበቃም፤ ሻለቃ ታከለ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. (August 28,1976) ሶዮማ ውስጥ በሲሮ ወረዳ በይፋ በስቅላት ተቀጣ።

በደርግ መሥዋዕት ሆነ ማለል ይቻላል። ሻለቆቹ አሊና ጌታቸውና በአዋሽና በአሰበ ተፈሪ ልክ የሌላቸው ላብአደሮች ከማረጻቸው የተነጣ እንዚያ ሰማእታት በአብዮታውያን መዝሙሮችና ግጥሞች ውስጥ ንዑድ ክቡር ሥፍራ ይዘዋል።

ሐምሌ ፮ (July 13) ደርግ አዲስ አበባ ውስጥ ሰዎች መረሽኑን ገለጸ። ከሞቱት ውስጥ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ (የደርግ አባልና የውጭ ግንኙነት ሐላፊ)፣ ብርጋዴር ጀኔራል ጌታቸው ናደው (የኤርትራ ዋና አስተዳዳሪ) መርሥጌ ይሁን፣ ዶክተር አበበ አስናቀ፣ ግዛቸው ዋለልኝ፣ ጄኔየር ቴክኒሻን አበበ አቦዘን፣ በትረማሪያም አስናቀና ሽታው አበበ የሚገኙበት ሲሆን እነዚህ ሁሉ «፬ረአብዮትና ፬ረዲሞክራሲ እንቅስቃሴ በማካሄድ» የተከሰሱ ነበሩ። ዘውዴ ተረፈ «ምሥጢራዊ ሰንድ አተቃዋሚ ወገን በመሸጥ» ክስ የተገደለ ሲሆን፣ ዊሌ መኑር፣ ካሊል ሀሰን፣ ሼክ ጀሚል ኢብራሂም፣ ጎዳ ጋቢ፣ ተስፋ ኪሮስ ወልደሥላሴ፥ ሃጂ አደም ሞሐመድ፥ መሐመድ ሰይድ በረሄና ባዘዘው ኑጋሽ "የኢኮኖሚ ሻጥር" በማድረግ ወንጀል ተገደሉ። ደምሴ ክበደ፣ አሰፋ ካሣ «ንብ በመቀበል ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል።» በዚሁ ጊዜ ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁ የተባለው የደርግ አባል ተይዞ ታሥሮ ነበር። በኋላም እዚያው እሥር ቤት የተገደለ ሲሆን ራሱን ገደለ ተብሎ ተመካኘ።

እዚህ ቦታ ላይ ከሶች የተባሉትን መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ ይሰማናል። አብዛኞቹ ተከሳሾች ዳኛ ፊት አልቀረቡም። ታዲያ ለመሆኑ ክሶቹ ከፅሁነታው ጋር የተዛመዱ ኑረዋልን? ሐቁ እንደሚያሳየው ስለተፈጸሙት የሞት ቅጣቶች መግለጫ በተሰጠበት ጊዜ የተነበቡት ክሶች በሁሉም ላይ ለግለት በሚያስደፍር ደረጃ ፈጠራዎችና የተዛቡ ነበሩ። ለምሳሌ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ አምስት ዓመት እሥራት ተፈርዶበት የነበረው መለስ ተክሌ «ፀረ–አብዮት ጽሑፍ» በመበተን በደርግ ተይዞ የነበር ሲሆን የሞት ፍርድ የተፈረደበት ግን የመሬት ይዞታ መሻሻልና ጎብረተ–ሰብአዊነትን በመቃወም፣ እንዲሁም በሀገሪቱ ዋና ከተማ ውስጥ ቦምብ በማፈንዳት «ወንጀል» ነበር።[25] ረዘነ ኪዳኔ ደሴ፣ ግደይ ገብረ ዋንድ ደግሞ መቀሌ ነበሩ። የተባለው ቦምብ አዲስ አበባ ውስጥ ሲፈነዳ ግን በዚህ «ወንጀል» ከመለስ ጋር አብረው ተረሽኑ። በመጀመሪያ መንግሥቱን በመቃወም ወንጀል መከሰሳቸውን ከምንም የጣፈው የለም።

ኢድሪስ ኪሂር አብዱልቃድር ለረጅም ጊዜ ጣሊያን አገር ኑሮ አዲስ አበባ ሲመለስ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ላይ ተያዘ። ኢድሪስ በኤርትራው እንቅስቃሴ ውስጥ ተሣትፎ ያልነበረውና የአእምሮ መታወክ ታሪክም የነበረው ነበር፤ ሁኖም «የገጠሩን የመሬት ዓዋጅ የሚፃረር የተንኮል ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የኢትዮጵያን ሰላምና ፀጥታ በማናጋትና ሕገ ወጥ ተግባሮችን በተለያዩ ቦታዎች በማካሄድ» «ወንጀል» ከሌሎች ጋር ተጸምሮ ተረሸነ። ከቶውንም ክሱን ይበልጥ ለማከበድ «ኢድሪስ የኤርትራ ነጻ አውጪ ድርጅት የተወሰኑ ሕዝቦች መሪ» ነበር ብሎ መንግሥቱ ወነጀለው።

የተሻለ የሥራ ሁኔታንና ደሞዝ ለማግኘት መብቶችን የጠየቁ ሳብ አደሮች «የኢምፔሪያሊስት ወኪሎች» ተብለው ተጠሩ፤ ለረጅም ጊዜ የግፍ እንዛዝን የታገሱ ምሁራን «ፀረ–አብዮተኞች» የሚል ቅጽል ተሰጠፈባቸው፤ ሻለቃ ሲማይ የደርግና የመኢሶንን ትሥስርና ከሞስኮ ጋር ይደረግ የነበረውን መተሻሸት፣ የመንግሥቱ ኃይለ ማሪያምን አምባገነናዊ እርምጃዎች ይቃወም ነበር፤ ይህም ለሞት አበቃው። ጀኔራል ጌታቸው፣ የኤርትራው ጉዞት ሰላማዊ መፍትሔ ይፈለግለት የሚለውን በኤርትራ ያሉ ወታደሮች የጠየቁትን ጥያቄ ለደርግ ወስዶ በማቅረቡ በደርግ ዓይን ችግር ፈጣሪ ሊሆን እንደሚችል አስደርጎ አስገመተው። የመንግሥትን ምሥጢር በመሸጥ የተከሰሰው ዘውዴ ተረፈ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ በርግጥ ምሥጢራዊ ሰነድ ለሶማሊያ ሽመ በጦር ፍርድ ቤት (ሻለቃ ስለነበር) ተቀጥቶበት ነበር። ደርግ ይዞ ባሠረው ጊዜ ግን ለጥቂት ዓመታት በሥራ ፈትነት ያለ ሲቪል ነበር። «በኢኮኖሚ አሻጥር» የተከሰሱት ስድስቱ የቀረቡት እንደ «ስግብግብ ነጋዴዎች» ተቁጥረው ነበር፤ ሁኖም እንዱ የነጋዴ መጋዘን ዘበኛ፣ ሌላው፣ በኋላ በማከማቸት ክስ ይፈልግ ለነበረ ነጋዴ መጋዘን ያከራየ ሽማግሌ ሰው፣ እንዱ ደግሞ ላይታዝ ያመለጠው ነጋዴ ልጅ ነበር። የኢኮኖሚ አሻጥርና ማከማቸት የተባለውም መጠኑ አነስተኛ ከሆነ በርበሬ ያለፈ ሁኖ አልተገኘም።

«ሀብታም ነጋዴዎች» ከተባሉት ውስጥ አራቱ እስላሞች ምስኪን ድሆች ከመሆናቸው የተነሣ ለቤተሰቦቻቸው መርሻ ይሆን ዘንድ ግዕከላዊው መስጊድ የገንዘብ መዋጮ እንዲደረግላቸው መግለድ ነበረበት። (26)

ንጹሐንና በደል የሌላቸውን ሰዎች መረሸን የርቱዕ ኀሊናን ሚዛናዊ ብያኔ የሚጋፋ ሲሆን፣ አእምሯቸው ለተዛባ መረዎች ግን ተገቢነቱ ትክክለኛ ምክንያት ላይ የተመሠረተ ምንም ሕፀፅ የሌለው መስሎ ይታያቸዋል። የርሸናዎቹ ዓላማ በሕይወት የቀረው ፍርሐት ረዓድ እንዲይዘው ለማድረግ ነበር። ሰኔ ሽቱ ቀን ማክሣቸትን ወንጀል የሚያደርግ ሕግ ወጣ። ከላምንት በኋላ ሕጉን በሥርዓት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በዚህ ወንጀል ጥቂት ሰዎች መሞት ነበረባቸው። ተከሳሾቹ ንጹሐን ሆኑም ወይም ጥፋቱ በጣም ቀላል ሆነ፣ ግድ አልነበረም። የመንግሥቱ ከሃዲነት ይታወቅ ዘንድ ከርኑን መቅመስ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቶ

ነበርና። እኔ ኃይለ ሥላሴ ሕዝብ ማጉረምረም በጀመረ ቍጥር ሞት ከተፈረደባቸው ውስጥ ከእሥር ቤት በማስወጣት እደባባይ ላይ ሥቅላት እንዲፈጸምባቸው ያስደርጉ ነበር። እንዲህ ዓይነቶቹ የመንግሥትን ኃይል የሚያስታውሱ የድንገት እርምጃዎች መንግሥትን ከወሰዱ ለመጠበቅ ፍቱን አብነቶች ሁነው ተገኝተዋል። ያለፈው መንግሥትና ሥርዓት ውጤት የሆኑት የደርግ መኰንኖችም ከዚህ እምነት ሊላቀቁ አልቻሉም። የሐሰት ክሶች ደርግ ተቃዋሚዎቹን የሚገድልበትን ዕውነተኛ ምክንያት ይሸፍኑ ነበር። የታወቁ አድኃርያንን ከታወቁ አብዮታውያን ጋር ደብልቆ ማቅረብም ብዙውን ነገር እምታድል። ስድሣ የአሮጌው መንግሥት ባለ ሥልጣናት ጎጃር ፲፩ ቀን በሞት ተቀጡ፣ ብለው ይጽፋሉ ጋዜጠኞችና ጋዜጠኛች። ግን እብረዋቸው ስለተረሸኑት ዲሞክራቶች ምንም የለም፤ ተረስተዋል። ሻለቃ ሊሣይና ጌታቸው ናደው ተገደሉ፤ ይላሉ የጋዜጠኞች አርእስት፤ ስለሌሎቹ ደንታ የለም። መለስ ተክሌ፣ ታጋዩ፣ በሠራው ከታወቀው አሉላ በቀለ ከተባለው ፈውዳል ጋር ይገደላል፤ የሁሉም ክስ ግን የመሬት ይዞታውን መሻሻል በመቃወም ነው። የታጋዩን ያለፈ ታሪክ የማያውቁ ሁሉንም ነገር «ፈውዳሎች ላይ እንደተወሰደ እርምጃ» አድርገው ይወስዱታል። በዚህ መንገድ ነበር ማወናበዱ የሚካሄደው። ደምሴ ከበደ በእውነት ንብ ይቀበል አይቀበል ማን ተጨንቆ ያጣራል? ቢጨነቅስ ስንቱ? በኢ.ሻ.ኤ. ስኳር ፋብሪካ ማከፋፈያ ኮርፖሬሽን ውስጥ ደምሴ የነበረውን የሽያጭ ሐላፊነት ቦታ ለመውሰድ በሚቀናቀኑ፣ ደርግ ውስጥ ዘመድ በነበረው ወደረኛ ሠራተኛ በቀረበበት ክስ እንደነበር፣ የዚሁ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምሩቅ የሆነው ጓደኛቸው፣ መሠረት በሌለው ክስ መረሸኑ የሥራ ባልደረቦቹን ከፉኛ እንዳስደነገጣቸው ሊታወቅ አይችልም።

የሐሰት ክሶች፣ የበዘፈቀደ እሥራቶችና ግድያዎች የደርግ ባህርይ መግለጫዎች ነበሩ። መኢሶንም ኟኵር የተነሣበትን የምልመላ ዘመቻ ያልተቀበሉትን ምሁራንና ሠራተኞችን ለመቅጣት ይህንኑ ዘዴ ነው ሆይ ሆይ ሲል የነበረው። ስለሆነም እሥር ቤቶች እየሞሉ ደምም እየጐረፈ መጣ። በሐምሌና በነሐሴ (፲፱፻፷፰) ከትግራይና ከወሎ የተያዙ ተማሪዎችና መምህራን በምስጢር ተገደሉ፤ የሁሉም ክስ የኢሕአፓ አባላት ናችሁ የሚል ነበር። በሐምሌ ውስጥ የመኢሶንና የወዝ ሊግ መሪዎች ተጨማሪ የኢሕአፓ መሪዎችና አባሎች ስም ዝርዝርና ኢሕአፓም የሚደመሰስበትን የሥር

ንቀል ዘመቻ ዕቅድ ለደርግ አቀረቡ። ነሐሴ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ላይ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ማለትም በብዙ የሽዋ ክፍሎች (በተለይም በሐይቆችና ቡታጅራ፣ በይፋትና ጥሙጋ፣ በጨሰና ጉራጊና)፣ በከፋ (ጅማና አጋሮ) በሲዳሞ (በወላይታ፣ ከምባታና ደራሳ)፣ በወለጋ (ቄለም አውራጃ ውስጥ በተለይ) በወሎና በትግራይ፣ በሐረርጌ (በተለይም በሐረር፣ ድሬዳዋ፣ በአረማጶ፣ ገለምሶ፣ አሰበ ተፈሪ) ወዘተ... የሚፈጸመው ግፍ እየከፋ መጣ። ያልተነካ ክፍለ ሀገር አልነበረም። ያልተዳሰሱ ከተሞች ጥቂቶች ናቸው፤ ደረጃው ይለያይ እንጂ ያልተለከፈ የሀገሪቱ ማዕዘን አልነበረም።

በሐምሌና በነሐሴ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የነበረው ሁኔታ ጭንቀትና ጥበት የሠፈነበት ነበር። ሐምሌ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ላይ ኢሕአፓ የሚፈጸመውን ግፍ በማውገዝና የደርግንና የመኢሶንን የጦርነት ዕቅድ በማሳወቅ መግለጫ አወጣ። በተጨማሪም በእስራኤል የሠለጠነው ነበልባል የተባለው ከፍለ ጦር በሙሉ የተጠንቀቅ እዝ ላይ እንደነበርና በአዲስ አበባ ላይም ለማሠማራት የታቀደ እንደነበር ግልጽ ተደርጓል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የላዘሪድስ ጥጥ ፋብሪካና የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ላብ አደሮች የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ። የኤርትራ ወታደሮች አሁንም እንደገና የኤርትራው ጦርነት በሰላማዊ ውይይት እንዲፈታ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሥልጣን እንዲረከብ የሚል ጥያቄ ለደርግ አቀረቡ። በሥውር የሚዘጋጁ የአየር ኃይልና («የአየር ኃይል ድምፅ») የጦር ኃይሉ («ሞቱን ወታደር») ጽሑፎች እምባነናዊውን ወታደራዊ አገዛዝ አውግዘው ጻፉ። ከቢሾፍቱ/ደብረዘይት አየር ወለዶች ዐመፁ፤ ዐመፃቸው በኃይል በነበልባል ጦር ቢፈታም ብዙዎች ከነትጥቃቸው አመለጡ። የጅጅጋዎቹ ወታደሮች በሚይ ዴይ 1968 እንዳደረጉት ሁሉ፣ ተቃዋሚ ወገኖች ላቀረቧቸው ዲሞክራሲያዊያን ጥያቄዎች ድጋፋቸውን ገለጡ።

ደርግም ሥራ አልፈታም ነበረ። ሐምሌ ፭ ቀን ብቻ ወደ ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች ታሠሩ። የታጋይ ላብ አደሮችና መሪዎቻቸውን ከቤት ቤት ማደኑ እየጨመረ ሄደ። መኢሶንና ወዝ ሊግ ባወጡት የስም ዝርዝር እየተረዳ የሰው መያዙ ነገር ተስፋፋ። አጋሮ ውስጥ (ከፋ) ተማሪዎች መምህራን እንደተጨፈጨፉ ተዘግቧል። የመንግሥት ሠራተኞች

በተለይም በመረት ይዞታ ውስጥና በስዊድን የነንዘብ እርዳታ ይካሄዱ የነበሩ የእርሻ ፕሮጀክቶች (ዋዱ፣ ካዱ) ውስጥና ኢፒድ ውስጥ ይሠሩ የነበሩት ዋና ኢላማዎች ተደረጉ። ብዙዎች ተሠወሩ። በደርግና በመኢሶን የታዘዙ ወታደሮች በተሠወሩቱ ምትክ ዘመዶቻቸውን እሠሩ።

ባጭሩ ነሐሴ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ዓይነ ርግቡ ተገልጦ ጦርነቱ ቁልጭ ብሎ ወጣ። ደርግ፣ ከግፍ እገዛዝ ጋር እየተመሳሰለ ከመምጣቱ የተነሣ የቀደመ ትርጉሙን አጥቶ ጭካኔና እንዳሻ ማድረግን የሚገልጽ ሆነ። «ደርግ ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ» የሚለው የሕዝብ አባባል ከዚሁ የመጣ ነው። ማንም ማን ይሁን ለደኅንነቱ ዋስትና አልነበረውም። በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. ደርግ፣ በግራም በቀኝም ገደለ፤ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ከሐምሌ እስከ ነሐሴ ድረስ – ባለፉት ገጾች ባልተሟሉ ዘገባዎች ቢሆንም – እጉልቱን ለማሳየት እንደሞከርነው ያልተጻረጠ ግድያ አካሂዷል። መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ላይ የተቀየረው የደርግ ጠባይ አልነበረም። የተቀየረ ነገር ቢኖር፣ የሽብሩ ደረጃና የግፉ ይዘት አዲስ ገጽታ መያዙ ነበር – ይበልጥ መስፋፋትን ይበልጥ መፈራራትን አመጣ። ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ግፍና ሽብር ከኢትዮጵያ አልተለየም። በኋላ ከተከተለው ጋር ሲወዳደር አነስተኛ ነበር ሊባል ይችላል፤ ግን ዙሮ ዙሮ ከሽብርነት አልዘለለም። ይህ ነው እንግዲህ ደርግና ሰሉም የሚያጋፍሩ፣ ተታዋሚውን ወገን ከመስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. በኋላ ራሱን ወደ መከላከል በመሄዱ ለመወንጀል በሚያደርጉት ሙከራ ሊሸፋፍኑት የሚፈልጉት መራራው ሐቅ።

፱

ምን ምርጫ?

ምን ግትርነት?

ያም ያም ምርጫ ነው። ዛሩ ላይ ሁኖ ከበላዩ የተቈጣ ነብር፣ ከበታቹ የተራበ ጅብ ያፋጠጡት ሰው ምርጫዎች አሉት። ዝም ብሎ መበላት፣ ወይም ወደ ላይ ከፍ፣ ወደ ታች ዝቅ ብሎ ጠላቱን መግጠምና ከመበላት ራሱን ማዳን ነው። ንጉሡ ነገሥቱ ከወረዱ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ የገባው ተመሳሳይ ምርጫ ውስጥ ነበር – የደርግን እገዛዝ ጸጥ ብሎ መቀበል ወይም እሱን መታገል።

ማን መበላት ይፈልጋል? ስለሆነም ሕዝቡ መታገልን መረጠ። ይህንንም በማድረጉ ከተጠበቀው የደርግ መቅሠፍት በተደራቢ በግትርነትና «አብዮቱን ላምጠኝ» ብሎ የመጠየቅ ያህል ነው። ብለው ከስ ከሰነዘሩበት እንደ አታሞይና ፒተር ስቻዮብ ከመሳሰሉት የውጭ ኤክስፐርቶች የተወረወረ የመርዝ ብዕርና የማብጠልጠል ውርጅብኝ አረፈበት። መቼም ከላሉቹ ዒላማቸው ገራውን ብቻ ወይንም ኢሕአፓን ብቻ የሚመለከት ነው ሊሉ ይችላሉ፤ ግን እንዚህ በዚያን ጊዜ እንግን ነበሩ? በዚያን ጊዜ ደርግን ይታወም የነበረው ማነው?

በደርግና በሠራተኛ–ተማሪ–ምሁር መካከል የነበረው መቈራረጥ ገና ከጠዋቱ ግልጽ ነበር። እንዲያው ለመሆኑስ በየካቲት አብዮት ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ፣ በኃይለ ሥላሴ ጊዜም እንኳን በሐቅ አብዮታውያን ነበርን ለማለት የሚችሉ፣ ኑረው ብቅ ያሉት መኩንኖች ላይሆኑ እንዚህ ሠራተኛ–ተማሪ–ምሁር አልነበሩምን? ከፖለቲካው ፍጭት

እንጻር ሲታይ ሕዝቡ፣ ሠራተኛው፣ ተማሪው፣ ምሁሩ ወዘተ ነበር ወታደራዊውን አምባገነን መንግሥት የተጋፈጠው።

በኢትዮጵያ፣ ምናልባትም እንደዚሁ ባሉ አገሮች በዋናው ከተማ የሚደረግ የፖለቲካ ተቃውሞ በመላ ሀገሩ ወስጥ ከፍተኛ ተደግሞነት አለው፤ ይህም ተደግሞነት ከከተማ ነዋሪው፣ ከሠራተኛው ወይም ከተራማጅ ምሁሩ ነፍስ ወከፍ ሞጥር እጅግ ልቆ የሚሄድ ነው። ደርግ፣ ከሠራተኞች ከተማሪዎችና ከምሁራን ጋር በከተሞች ውስጥ መቈራረጡ ወደ ገጠሩም ዘልቆ ያስገመገመ ሲሆን፣ የመንግሥት ሠራተኞችና የዴሞክራሲያውያን ወታደሮች፣ ተቃውሞም እስተጋብቶ ነበር። በአብዛኛው ለዴሞክራሲያ (ለኢሕአፓ) ድጋፍ የነበራቸው ዘማች ተማሪዎች ፀረ–ፈውዳል ትግል ለማፋፋምና ይህንንም ትርጉም ካለው ነጻነትና ሥልጣን ጋር ለማቈራኘት ራሳቸውን ከአርሶ–አደሩ ጋር አዛመዱ። በሌላም አንጋገር አንዳንድ የውጭ ተቺዎች «የመጠቁ... ምሁራን ተቃዋሚዎች» በከተሞች አካባቢ ብለው የጠሯቸው ራሳቸውን የነጠሉ የመጠቁ ምሁራን ሳይሆን የአብዛኛው ሕዝብ እንደበት እንጂ ነበሩ። የመሬት ይዞታው መሻሻል ሕዝባዊ ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ስለነበር – ለጊዜው የተወሰነ የአርሶ አደር ክፍልን ሊያረጋጋ ችሎ ነበር፤ ግን ደርግና አርሶ አደሩ አርስ በርሳቸው ከቶ የሚጣጣሙ አልነበሩም። ደርግ ቦናፓርቲስታዊ ለመምሰል እስቦ ከነበር (ነገሩ እከራካሪ ነው) በራሱ ቅጀት ተታሎ ነበር ማለት ነው። የሰሜን አርሶ አደሮች በመሬት ይዞታው መሻሻል ያገኙበት ፋይዳ፣ ከሞላ ጐደል፣ አልነበረም። የደቡቦቹም ቢሆኑም ምንም እንኳ ረውዳላዊው ሥርዓት መወገዱን ቢገነዘቡም ጭቆናው ግን እየገረረ መምጣቱን ለማየት ረጅም ጊዜ አልፈጀባቸውም።

ደርግን ተቃውሞ የቆመው ወገን ሰላማዊ መንገድን ነበር የተከተለው። የኢሕአፓ (፲፱፻፷፯ ዓ.ም.) የፖለቲካ ፕሮግራም እንኳን በመቅድሙ ላይ የሚከተለውን አሥፍሯልI «የሠራተኛው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ከተከበረ፣ ኢሕአፓ የመጨረሻ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይታገላልI እንዚህ መብቶች ከተገፈፉ ግን አብዮትን ለማራመድ አስፈላጊና ተገቢ የሆነውን የትግል ዘዴ በመቀየስ በተግባር ያውላል።» «ኢሕአፓ ወይም ሕዝቡ አይደለም ደርግን ፀረ–ዴሞክራሲ እንዲሆን የተነኩሰው። ደርግ ራሱ ነው ሰላማዊ የፖለቲካ

ተቃውሞ ሊገለድባቸው የሚችሉባቸውን መንገዶች ሁሉ የዘጋው። የግጎበር መብታቸው የተነፈጋቸው፣ በሰላማዊ ሁኔታ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙበት መንገድ ግድያና እሥራት ያስከተለባቸው ሠራተኞች፣ ከመሠናዘር ሌላ ምርጫ የላቸውም። መቼም ሌላው «ምርጫ» ደግሞ ባርነት ነው። ግን ከባርነት ሞት ይሻላል ብሎ የተነሣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ባለመቀበሉ እንደ ጥፋት እይቈጠርበትም። ግትርነት የተባለው ተቀጥላ ደግሞ ተገቢ ቦታው ከአምባገነናዊ ደርግ ሠፈር ነው። ሕዝቡ ተንኳሽ አልነበረም። ወደ ጠብ እንዲያመራ፣ ከሱዓላዊ ግቦቹ ይደርስ ዘንድ ሕገ ወጥ የትግል መንገዶችን እንዲመርጥ ተተንኰሰ እንጂ። ሳንሱር አንድያውን ገድግዶ ይዞ፣ በሥውር የሚሪጨ ወረቀቶች ተትረፈረፉ፤ ፓርቲዎች ታገዱ፤ ፓርቲዎች ወደ ጎቡዕ ጎላዊ ተገፉ፤ ሰላማዊ ተቃውሞዎች ተከለከሉ፤ የሥራ ማቆም አድማ ተሰፉፉ፤ ማሠር፣ መረሸን ከዳር እስከዳር ደካ፤ ራስን መከላከልም የግድ ሆነ፤ ደርግ የጨመተ ተቃውሞን እንኳ አልፈለገም፤ ከቶውንም ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልፈለገም። ሁኔታዎች እንደሳዩት ምሁራን ግብረ አበሮቹን እንኳ አልማራቸውም። የወታደራዊው መንግሥት ተሽከርካሪ የዐመፃ ጎማ በመንገዱ ላይ ያገኘውን ተቃውሞ ሁሉ ለማዳመጥ ነበር የተንቀሳቀሰው ከበስመ አቡ አደጋውን የተመለከቱት እድገቱን መገደብ መረጡ። በራሳቸው የግል ጥቅም ታውረው የተደናቆሩቱ ግን አጠቃላይ የሁኔታውን ሥዕል መማተር ተስኗቸው ራሳቸውን ከደርግ ጋር በማጣበቃቸው ጊዜው ሲደርስ እዚያው ተደቈሱ።

እንድ መንግሥት ርትዕ ያለው ሥልጣኑን የሚቀዳጀው ከሚያስተዳድረው ሕዝብ ፈቃድ መሆን አለበት። ይህ የኢሕአፓ ጥቅስ አይደለም። ይህ ፈቃድ በሌለበት፣ የሽብር እገዛገዝና እምባገነንነት የበላይነቱን በያዙበት ሁኔታ ሕዝቡ ወደ ዐመፅና ወደ ጠብመንጃ ከመሄድ ሌላ ምርጫ አይኖረውም። ደርግ የሰላማዊ ተቃውሞ መንገዶችን በሙሉ ከመዝጋቱም ሌላ ታቃውሞን «ኢትዮጵያዊነትን የሚፃረር» አስመስሎ ለማቅረብ ሞከረI እንዲህ ዓይነቱ ተቃውሞ እንዳልነበረ ንጉሥ ነገሥቱን ያወረደ፣ እገሪ መንገዱንም ሰራሱ ለደርግም ሥልጣን ላይ ለመውጣት መንገድ የጠረገ በነዚያ በየካቲቱ ቀናት ውስጥ ደርግ የንጉሥ ነገሥቱን ስሕተት ሊደግም አልፈለገም ነበር ማለት ይቻላልI ግን ይህም ደግሞ እንዳረጁት ንጉሥ ሁሉ አምባገነን እንደነበረም ያመለክታል።

ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከገደበና በማያፈናፍኑ ዓቀጀች የሚካሄድ አገዛዝ ከመሠረተ በኋላ፣ ደርግ የሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን አቋቋመ፤ ግን በሐቅ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ቡድኖችና ፓርቲዎች ትሥስር አልነበረም። ደርግ የሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን ያሰበው ርዕዮተ ዓለማዊ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ የፖሊሲ ኃይል እንዲሆነው ነበር። ደርግ ስለ ተራማጆች የጎበረት ግንባርም ለእፉ ያሀል ግውራቱ አልቀረም። ይሽው ግንባር ግን ሐቅን ተመርኩዞ እንደዚያ ላለ ለተለያዩ ኃይሎች (29) አገር አቀፍ ዴሞክራሲያዊ መተባበር መንገድ አልጠረገም። ደርግ ለተቃዋሚ ወገኖች ቢሮክራሲያዊ የሥልጣን ቦታዎችን በመለገሥ በጥቅማ ጥቅም ለመግዛት ሞክሮ መኢሶን በመሐሉ ሲታለል ኢሕአፓን አልዳዳውም። ደርግን የታገሉቱ የሚፈልጉትንና (ለዴሞክራሲና ለሕዝባዊ ሥልጣን) የማይፈልጉትን (አምባገንንት በግንኛውም መልኩ) ያውቁ ነበር። ደርግ የገጠማቸው ወደረኞቹ ከታሪካዊና አብዮታዊ ትግል በኋላ ይበልጥ የጎቁና የተጠነቀቁም ኃይሎች መሆናቸው ከፉ ዕድል ሆነበት።

ተቃዋሚው ወገን ወዲያውኑ ወደ ዐመፅ ተሸጋግሮ ቢሆን ኑሮ፣ ሰላማዊውን የትግል ፋና መሞከር ነበረብህ ብሎ በማመልከት ሊወቀስ ይገባ ነበር፤ ግን ተቃዋሚው ወገን የሰላማዊውን የተቃውሞ ፋና ይዞ ለመጓዝ ሞክሮ ያገኘው መልስ እጥፍ ድርብ ግፍ ነበር። ግነው እንግዲህ ቁስቋሹ? የትኛው ነው ግትሩ? ይልቅስ ጭብጡ ሁኔታ ሁሉ የሚያመለክተው ደርግ ጨርሶ እንደተጠላና እሱ ራሱም አሳምሮ ያውቀው እንደነበር ነው። በዚያን ጊዜ አሁንም ቢሆን አንዳንዶች እንደሚሉት ደርግ ተወዳጅ ቢሆን ኖሮ በተቃዋሚው ወገን የፈለገውን ያህል ቅስቀሳ ቢደረግ ሕዝቡን ሊያነሳሰበት ባልቻለ ነበር። የኑሮ ሁኔታ ያረካው አንድ ሕዝብ በቀላሉ ለዐመፅ አይነሣሳም። እንዲያውም በተቃራኒው፣ የለውጥ ተስፋ እንኳን ሕዝብን እንዲታገሥ ያደርገዋል። ሀብተ ነቢብ የተሰማቸውና የመሳስሉት በቀላሉ ሕዝብን ወደ ዐመፅ ሁኔታ እንማስተው ይከቱታል ብለው የሚያስቡ፣ ሕዝቡ ከመንግሥት ጋር ያለው ቅርበት ያን ያህል በሆነበት ሁኔታ እንኳ የፖለቲካ ቅስቀሳ አስቸጋሪነቱን አያውቁትም።

ሕዝቡ በዕድሉ ረክቶ፣ ለወታደራዊው መንግሥት

አጨብጭበ፣ የ«አድኃርያንን» ርሽና ደግር ያን ቋት የሚለውን የግዙነት ኑሮ መኖሩን በቀጠለ ነበር፤ ግን ያን ቢያደርግ ኑሮ ደርግን ተንኩስክ ብለው የወነጀሉቱ እነዚያው ሰዎች በዚህ ሁኔታ ደግሞ ለአምባገነኖች ዝም ብሎ የሚገዛ ሞኝ ደንቆሮ ብለው መዝለፋቸው አይቀርም ነበር። ሆኖም ኢትዮጵያውያን ይታገሉ የነበሩት የውጭ ሰዎችን ለማሳመን ወይም የነሱን በጎ ፈቃድ ለማግኘት ስላልነበር ጥያቄው እሳስጨነቃቸውም። ለውጥ ፈለጉ፤ እሱንም ለማግኘት ተገቢ በመሰላቸው መንገድ ተራመዱ።

የተከፈለው ዋጋ ያለጥርጥር ከፍ ያለ ነበር፤ ግን እኮ ነጻነት ያለዋጋ አይገኝም የሚለው እንጋገር የዋዛ አይደለም። ምናልባት ተቃዋሚው ወገን፣ በተለይ ኢሕአፓ ደርግን ያስገዝፈው ለነበረው ልክፍት በጣም የማይጋለጥበትን ሥልት መቀየስ ነበረበት ማለት ይቻላል፤ ያስኬዳልም። ግን የመዋጋትን፣ የመታገልን ፍጹም አስፈላጊነት አሌ የሚያሰኝ፣ የሚያሳምን ከርከር ሊቀርብ አይችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ (ወይም አፍሪቃ ውስጥ ባጠቃላይ ማለት ይቻላል) ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል «ከሀገሪቱ ልዩ ሁኔታ፣ ባህልና ልምድ ጋር ያልተዛመደ» (ኮስሞፖሊታን) ወይም «ከሁኔታዎች መጥቶ የሚገኝ» (ኤሊቲስት) ነው በሚል ሰበብ በማስታቀር የሚመለከቱት፣ እያውቁትም፣ አሳውቁትም፣ በልባቸው ዘረኞች ናቸው ብለን ልንጠረጥር የገባን ነው።(30) የጀርመን ናዚዎች ከነሱ እንዱ በአርበኞች በተገደለ ቁጥር በግዕገታቸው ከነበሩት ታጋቾች ውስጥ በብዙ መቶ የሚቆጠሩትን እያወጡ ይረሽኑ ነበር፤ ግን የናዚ ወረራን አሻፈረኝ ብለው በተጋፈጡት ላይ ውግዘት ያስፋፋባቸው መጽሐፍ ፈጽሞ እንብበን አናውቅም። ታይም መጽሔት «ኋላ ቀር ኢትዮጵያውያን» የሞሶሎኒዱቱን «የሠለጠኑችዱትን ጣልያንን» ሊዋጉ መሞከራቸው ብሎ ማሾፉ ይነገራል። የሆነ ሁኖ ፀረ-ፋሽስት ወረራን በመቃወም በሚደረጉ ትግሎች ላይ የሚሳለቁ የኋላ ኋላ ሰም ይተርፋቸዋል። ስለ ሰላማዊ ትግል ይቅርና የጠመንጃ ትግል ጉዳይም እንኳ ሲመጣ ሁለት መመዘኛ ሲቀርብ ይታያል። የአርጋን ሙጅሃዲዶች በመዋጋታቸው ሶቪየቶቹን እየተነከሱ ነውን? በርግጥ ሶቪየቶቹ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ነው። ታጋዮቹ ጠመንጃዎችን ጥለው ትግላቸውን ቢያቆሙ ምናልባትም መንደሮች ላይ ቦምብ እያወረዱ ድምጥማጣቸውን ከማጥፋት ይገቱ ይሆናል፤ ነገር ግን በአፍጋኖችና በሌሎች ነጻነት

ወላድ ሕዝቦች ዓይን ሲመለከቱት ምን ዓይነት አፍጋኒስታን ነው የምትሆነው? በሺዎች የሚቆጠሩ ኬንያውያን ለነጻነታቸው ሞቱ፤ ያን በማድረጋቸው ምንም እንኳ የተሟላ ነጻነት ባያገኙም፣ መልካም አደረጉ። ለሩቅ ተመልካች ምርጫ ይታይ ይሆናል፤ ቀረብ ብሎ ከቀየው ገብቶ ለታዘበው ግን አምባገነናዊ አገዛዝ ሲያጋጥም ከአንዲት በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ ገጎድ ይሆናል። እሱም ተገቢ በሆነ መንገድ ሁሉ መታገል ነው።

የተባለ ትንኩላ ዲሞክራሲያዊ መንግሥቱን ወደ ፋሽስታዊ መንግሥት አይለውጠውም። ይህማ ቢሆን ኖሮ የ1970ዎች አውሮፓ በተለይም ጣልያን፣ ስፓኝ ...ወዘተ ፋሽስታዊ አምባገነኖች በሆኑ ነበር። ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ መንግሥትን ሕዝባዊ ያልሆነ እርምጃ እንዲወሰድ አይገፋውም። እንዲያውም የሕዝብን ድምፅ እንዲያዳምጥ ነው ሊያደርገው የሚገባ። ደርግ ሀ ብሎ ሲነሣ አምባገነን ነበር። በሰላማዊ መንገድ የሚቀርብ ቅሬታን ለመስማትም ሆነ ተቃዋሚዎችን እሀ ለማለት ዝግጁ አልነበረም። በአፍ ያሳይ የነበረው አባታዊ ገጽታ በውስጡ ሞኳኔ የተመላበትን አምባገነናዊነት ሸፍኖ የያዘ ነበር። ምናልባትም በአንዳንድ የውጭ ሰዎች ዓይን ደርግ ለኢትዮጵያውያን የተገባቸው ነበር። ተወደደም ተጠላም ኢትዮጵያውያን ግን ከደርግ የተሻለ እንደሚገባቸው ያስቡም ያምኑም ነበር። ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ከነገረ ቀደም ጠመንጃ አላነሡም፤ ደርግ ግን አፍጀ ካልገዛኋችሁ ብሎ ጠመንጃውን አቀናባቸው። ታዲያ ፀጥ ብላችሁ ተደምሰሱ ብሎ የሚወቅሳቸው ማነው? ለዲሞክራሲ ያደረጉት ትግል ኩራትን ከሚያንፀባርቁት የታሪክ ምዕራፎቻቸው እንደ አንዱ ሁኖ ገና ይወጣል፤ ከዚህም የተነሣ ደርግና አደንዳኒዎቹ ስሚታቸው እንደደነዘዘና እንደ ጨካኞች ወይም ቅጥረኞች ሐላፊነትም እንደማይሰማቸው ሁነው ይታያሉ።

ማስታወሻዎች

ክፍል አንድ

1. የዚህን ደፈር ያለ አባባል እውነተኛነት ለማረጋገጥ በአርሞ ነጻ እውጪ ግንባር ስም የተነሡ ልዩ ልዩ ቡድኖች በጽሑፋቸው ያሠፈሩትን መመልከቱ ብቻ ይበቃል::- በአንድ የኦ.ነ.አ.ግ. ቡድን ጽሑፍ (OROMIA SPEAKS, Vol.1 no.1, Jan. 1979, "የኦ.ነ.አ.ግ. የውጭ ግንኙነት ቢሮ ጽሑፍ") ለምሳሌ፥ ቀይ ሽብር ራሱ፥ ደርግ፥ መሊሶንና ኢሕአፓ የአማራ ደባ ነው ብሎ አሥፍሯል::

2. ታሪካዊ ነክ ለሆነው ዝርዝር ከዚህ የሚከተሉትን ይመለከቷል፡
Jean Doresse, Ethiopia የተተረጉመ New York: Putnam's, 1959
J.S. Trimingham, Islam in Ethiopia. London: Oxford University Press,1952
Sven Rubenson, The Survival of Ethiopian Independence. London: Heinmann, 1976
A.H.M. Jones & Elizabeth Monroe , A History Of Ethiopia. Oxford, 1978
የኃይለ ሥላሴን መዋዕለ መንግሥት በሚመለከት የሚከተሉት መጻሕፍት ጠቃሚ የሆነ ሥዕል ያሳያሉ፡
Richard Greenfield, Ethiopia -A New Political History. London: Pall Mall Press, 1965
Christopher Clapham, Haile selassie's Government. London:Longman, 1968
Patrick Gilkes, The Dying Lion: Fuedalism And Modernization In Ethiopia. New York: St. Martin's Press,1975
John Markakis, Ethiopia: Anatomy Of A Traditional Polity. Clarendon: OUP, 1974

Addis Hiywot, Ethiopia: From Autocracy To Revolution. Review of African Political Economy.London: 1975

በተጨማሪም፥ The Historical Dictionary of Ethiopia, by Chris Pronty and Eugene Rosenfeld, The Scarecrow Press, Inc., London,1981 ተመልከት::

3. R.L. Hess Ethiopia- The Modernization of Autocracy. Ithaca, NY: Cornell University Press, 1970

4. በ Greenfield (Ethiopia- A New Political History) Ch. V. መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝር ታሪክ ወይም በሪፖርት መልክ የተሰናዳ (ሪፖርታዥ) ቢባል የሚሻል ቀርቧል፡- በተጨማሪም የChristopher Clapham'ን "The Ethiopian Coup d'Etat of December 1960"ን እንዲሁም Journal of Modern African Studies Vol. 6, no.4, 1968 ገጽ 495-507

5. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ዝርዝር ታሪክ፣ ንቅናቄውና በመሩቱና በተሣተፉት ገና መጻፍ ያለበት ጉዳይ ነው:: ያም ሁኖ ግን በልዩ ልዩ ማኅበራት ጽሑፎች ውስጥ (ለምሳሌ እንደ Challenge, ታኅሳሥ፥ Combat, ታጠቅ፥ ትግላችን፥ Forward, WWFES Bulletin, መዘተ.) በእማርኛና በእንግሊዝኛ በሥፋት የተጻፈ ይገኛል::

ከዚህ በተጨማሪም፥ የለገሠ ለማን "The Ethiopian Student Movement 1960-1974", NorthEast African Studies, Vol. 1. #2, 1974 እንዲሁም የR.R.Balsvicን Haile Selassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952-1977. EastLansing Michigan, USA, 1985 ይመለከቷል::

6. በ፲፱፻፷ ዓ.ም ከዩኒቨርሲቲ ትጽር ግቢ ውስጥ ሊደረግ በነበረው የልብስ አታቂር ትርዒት (ፋሽን ሾው) ሰበብ የተቀሰቀሰ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የጉሼምን አርሶ አደር በመደገፍ ሪጅም የትምህርት ማቆም አድማ አድርገው ነበር::

እዚህ ላይ በተጨማሪ በ፲፱፻፸ዎቹ ዓ.ም ውስጥ በትግራይ በእንግሊዞች እርዳታ የተደመሰሰ ትልቅ ዐመፅ እንደነበር መጥቀስ ያስፈልጋል:: የእንግሊዞች (በዚህ ዓይነት) ጣልቃ መግባት እንዳለ ሁኖ ወያኔ እየተባለ የሚታወቀው ዐመፅ፥ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠልና ከኤርትራ ጋር (ቢያንስ ከደጋው የኤርትራ ክፍል ጋር) አንድ አድርገው በእንግሊዝ የበላይነት ሥር ያለች ነፃ መንግሥት ለመመሥረት ዕቅድ ነበራቸው በሚባሉት በራሳቸው በእንግሊዞች አስቀድሞ የተጠነሰሰ ነበር የሚሉ አሉ:: ያሁኖቹ በህወሓት ሥር የተሰባሰቡት የትግራይ ብሔርተኞች ወያኔን እንደ ሀቀኛ የሕዝብ ዐመፅ ይወስዱታል::

7. የኢትዮጵያ ሠራተኛው መደብ ታሪክ ገና መጻፍ ያለበት ነው፣ ሁኖም ድኅረ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ከመጡት በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌደሬሽን እየታተሙ ከሚወጡት የሠራተኛ ድምፅ እትሞች አጠቃላይ ሥዕሉን ማግኘት ይቻላል::

"በኢትዮጵያ ላብ አደር ትግል ላይ አጠቃላይ ማስታወሻዎች" በሚል ርእስ በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም በኢሕአፓ የተጻፈ ሪቲት ጽሁፍ ተመልክቼ ማመሳከርያ አድርጌያለሁ::

8. ስለ ኢሕአፓ ታሪክ ታትሞ የወጣ አንዳችም ጽሑፍ ስለመኖሩ የማውቀው የለም:: አንዳንድ ምንጮች የኢሕአፓ ሁለተኛው ኮንግሬስ መጋቢት ፲፱፻፹፯ ዓ.ም "የኢሕአፓ ታሪክ ተጨባጭ ግምገማ ፲፱፻፷፬-፲፱፻፹፯" በሚል ርዕስ ዝርዝርነት ያለው ጽሑፍ እንደወጣ ያመለክታሉ፣ ግን እኔ አላየሁትም::

በኢሕአፓ ላይ የሚቀርቡ የውጭ ሪፖርቶች፥ በተለይም በፓርቲው የአመሠራረት ወቅቶች ላይ የሚሰጡ ትችቶች ባጠቃላይ ሲታዩ፥ ግምት ላይ የተንጠለጠሉና መረጃ የጎደላቸው ናቸው:: ለምሳሌ የኢሕአፓ ምንጮች በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም በመመስረታው ጉባኤ ወቅት የፓርቲው ስም ኢሕአፓም ወይም ለውጭ ግንኙነት እንዲያገለግል ብቻ የተሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርነት ድርጅት የሚለው ስምም አልነበረም ብለው ያረጋግጣሉ::

የፓርቲው ስም ወደ ኢሕአፓ የተቀየረው ነሐሴ ፳፮ ከተደረገው የፓርቲ ዕወጃ በፊት በ፲፱፻፷፯ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የፓርቲ ኮንፈረንስ ነበር:: አዲስ አበባ ውስጥ

በምስጢር የተሰበሰበው ኮንፈረንስ የፓርቲውን የፖለቲካ ፕሮግራም አሻሽለ፡ የፓርቲውን ዋና ፀሐፊ ወንበር አጠፊ (የማዕከላዊ ኮሚቴ ፀሐፊ የሚለውን በመተካት) እንዲሁም በማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በሚደረግ የምርጫ ሥነ ሥርዓት (በ Cooptation) አማካይነት የማዕከላዊ ኮሚቴን ቁጥር አሳደገ::

9. ሲሪያና ኢራክ ኤርትራን "የአረብ ቤሐውርት" አክል አድርገው ሲመለከቱ፥ እንደ ሱዳንና ሰውዲ አረብያ ያሉ ወግ አጥባቂ

አገሮች ደግሞ "እስላማዊት ኤርትራ" ከ"ክርስቲያናዊት ኢትዮጵያ" ጋር እየተዋጋች ነው በሚል የተሳሳተ ግምት ሃይማኖታዊው ጥያቄ ላይ የበለጠ ሚና ይሰጣሉ። ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ በአንዳንድ የኤርትራ ግንባሮች በራሳቸው እንደተራዘ መጠቀስ ያለበት ነው። ከዚህ ሁሉ የተነሳ አንዳንድ የአረብ አገሮችና ድርጅቶች ኢትዮጵያ ራሷ ቁጥሩ ከፍ ያለ እጅ የእስልምና ተከታዮች እንዳሏት አልተገነዘቡም ነበር።

10. በኤርትራ ትግልና በልዩ ልዩ ግንባሮች ሚና ላይ ነባራዊ በሆነ መንገድ ግመገማ ያደረገ መጽሐፍ የለም። ስትግሉ ባጠቃላይ፥ ለእንዱ ወይ ለሌላው ድርጅት ወገንተኛ በመሆን የቀረቡ ትንተናዎችን በሚመለከት የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

Bereket H. Selassie, Conflict and Intervention In The Horn of Africa. MR Press, New york,1980.

J.Firebrace & S. Holland, Never Kneel Down. Spkesman Press, UK, 1984.

R. Sherman, Eritrea- The Unfinished Revolution. New York: Praeger Publishers, 1980.

David Pool, Eritrea- Africa's Longest War. London: Anti Slavery Society, 1979.

Lieonel Cliffe and Basil Davidson (eds), The Long Struggle of Eritrea. Nottingham: Spokesman 1988.

James Petras, The Eritrean Revolution and Contemporary World Politics. Trenton: Africa Research and Publication Project, 1984.

የተለያዩት የኤርትራ ግንባሮች ስለየትግላቸው የሚያወጧቸው ጋዜጦችና መጽሔቶች አሏቸው። ከመሪዎቹ አንዱ ኡስማን ሳልህ ሳቤ፥ ከሌሉች ርእሶች በተጨማሪ፤

A History of Eritrea (Beirut 1974) ና The Root of the Eritrean Disagreement (Beirut 1978) ሂስ ላዘለ ግምገማ የሚከተሉትን ይመለከቷል፥

Proletarian Internationalism or Burgeois Nationalism? By the Ethiopian Student Union in North America, 1978.

Revolution or Capitulation By Eritreans for Liberation in North America, 1978.

Haki Yiwza etal; Debate on the Eritrean Revolution in ALTR AFRICA, September 1977, Roma. Emanuel (Desta) Gebre Yesus, Class struggle and the Problem in Eritrea. Addis Abeba, 1979.

Tesfatsion Medhane, Eritrea- Dynamics of a National Question. B. Gruns, Amesterdam.

Haggai Erlich, The Struggle Over Eritrea 1962-1978: War and Revolution in the Horn of Africa. Stanford: Hoover Institution Press, 1983.

በተጨማሪም፤ John Markakis : National and Class Conflict in the Horn of Africa. London: (Cambridge University Press,1987.

11. በዚህ ወቅት ላይ ዝርዝር ለማግኘት የሚከተሉትን ይመለከቷል።

J. Markakis and Nega Ayele, Class and Revolution in Ethiopia. Nottingham: Spokesman, 1978.

Colin Legum, Ethiopia- The Fall of Haile selassie's Empire. London: Rex Collins,1975.

Rene Lefort, Ethiopia- An Heretitial Revolution? London: Zed Press,1983.

David and Marina Ottaway, Ethiopia- Empire in Revolution. New York: African Publishing Co., 1978.

Fred Halliday and Maxine Molyneaux, The Ethiopian Revolution . London: Verso, NLR, 1981.

Dawit W. Giorgis, The Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia. Trenton, N.J: The Red Sea Press, 1989.

እነ አታዊይና ሌፎርት የየካቲቱን አብዮት የመሠራት ሚና ለወታደሩና ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይሰጡታል። የሊዲይና ሞሊኔም ረቀት ባለ የክርክር አካሄድ ያንኑ ይደግፋሉ። ሻለቃ ጳዊትም እንደሚጠበቀው በዚሁ ይስማማል። ፍሬድ ሃሊዴይ "How tight the bearhug?" ("የድቡ አስተቃቀፍ ምን ያህል ጥብቅ ነው?") New African Magazine, London, April 1980, pp. 44-45.ብሎ በጻፈው ድርሰት የሰቪየቶችን፥ በኢትዮጵያና በአፍጋኒስታን ጣልቃ መግባት ተገቢነት ያለው ያደርገዋል።

12. በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የኮሎኔል መንግሥቱ ወታደራዊ መንግሥት ከ፲፱፻፷፭ዓ.ም ጀምሮ ሀገሪቱን የጨመደደው ረሐብ የደረሰበትን

ደረጃ ለመደበቅ ወይም ለማቃለል በመሞከር በተራው ተከሰሰ። ንጉሡ ነገሥቱ ከዙፋን የወረዱበትን አስረኛ አመትና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ፓርቲ የተባለው ጭፍ ፓርቲ መመሥረትን ለማክበር በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ፈሰሰ። በዚያን ጊዜ ግን በብዙ መቶ የሚቀጎጠሩ ሰዎች (በመንግሥቱ የዜና ማሰራጫ ላይገለጽ) በመሱና በትግራይ ይሞቱ ነበር። ለዝርዝሩ የጻፍትን The Red Tears ይመለከቷል።

13. Colin Legum, op.cit. በተጨማሪም፣ Raul Valdes Vivo, Ethiopia- The Unknown Revolution, Havana, 1977.
14. በጦር ኃይሉች ውስጥ የተፈጠረው የመከፋፈል ደረጃ የደረሰበትን፥ በልዩ ልዩ የጦር ኃይሉች ክፍላት ውስጥ ፈልቶ በነበረው የ"ወረቀት ጦርነት" መገመት ይቻላል።
15. Charles Mohr, New York Times, April 10,1974.
16. ዴሞክራሲያ፥ ቅጽ:፭ ቁ.፮፣ ነሐሴ ፲፱፻፷፮
17. አንዳንድ እንደ Colin Legum ያሉ በተሳሳተ መንገድ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘውድ አገዛዝ ያለውን "ፍትር" ለማየት ሞክረዋል።

18. በመንግሥት የተፈጸመውን ወንጀል፥ በደሉ በደረሰባቸው (ሰለባዎች) ላይ ስለሚለጠፈው የተጠማዘዘ አመክንዮ (logic) ማብራሪያ ለማግኘት፥ የሚከተሉትን ይመለከቷል፣

Marina and David Ottaway, Empire in Revolution.

Halliday and Molyneux, The Ethiopian Revolution.

Peter Schwab, Ethiopia: Politics Economics and Society, Colorado (USA), 1985.

ከላይ ከተጠቀሱት ምስቱ፥ Peter Schwab በጥራዝ ነጠትነቱ ላት ያለውን ቦታ የያዘ ሲሆን፥ እንደሚጠበቀውም ለወታደራዊው መንግሥትና ለሽብሩ አድማጭነ የቆመ ነው።

19. አማን እንዶም የኤርትራን ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ነበር ፍላጎቱ የሚባልለት ተስማሚ የሆነ የድኅረ ሞት ታሪክ (በዋናነት በበረከት ሀብተ ሥላሴ) ተጽፏል፣

ተራግቧልም። ሁኖም ተወባው ታሪክ የአማን ጎደኛ እንድናምንለት ከሚፈልገው የተለየ ይመስላል።

አማን እንዶም በርግጥ በሠራዊቱ ውስጥ ተወዳጅ ነበር፣ ግን የተወዳጅነቱ መሠረት ዲሞክራሲያዊ ወይም ሰላማዊ ዝንባሌ ያለው በመሆኑ የተነሣ ሳይሆን፥ የጦረኝነት አትኖም ስለነበረው ነበር። በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም የኦጋዴን ጦርነት ወታደሮቹን ሱማሌዎች ላይ መሪን ከመልተቀም በላይ በፖለቲካው ሪገድ ይበልጥ ጠንቃቃ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ባያስቆሙት ኖር ድንበር ጥሶ በመግባት የሱማልያን ግዛት በያዘ ነበር። አማን የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር እንደመሆኑ መጠን፥ ለኤርትራ ግንባሮች የትልት እደጋ ምልክት ነበር። ኤርትራዊ እንደ መሆኑ መጠን፥ (ትግሪኛ፥ ትግሪና አረብኛም ጭምር ይናገር ነበር) ሌላ ሊቀ መንበር ላይ ሊወረወርበት የሚችል ከብሔር ጋር የተያያዘ ጥላቻ እሱ ላይ እንቅፋት የሚሆንበት አልነበረም። ኤርትራን ተሟዙሮ በጉበኘበት ጊዜ፥ የኤርትራ ሕዝብ የጋለ አቀባበል ነበር ያደረገለት። እንዲያውም አንዳንድ የአረብ አገሮች ሱዳንም ጭምር፥ ግንባሮቹን "ከወንድማችሁ ጋር ጉዳዩን በሰላም ፍቱ!" እያሉ ይመክሯቸው ነበር። በግለሰብ ደረጃ፥ አማን የኤርትራን ነጻነት ይቃወም ነበር፣ ሰግንባሮቹም በጎ ስሜት አልነበረውም። (በሁለቱም ኑግቦች ላይ በወቅቱ ዶክተር በረከትም ተመሳሳይ ነበር አመለካከቱ) ፅቅዱ ግንባሮቹን ከሕዝቡ ለመገንጠል ነበር። ከዚህ አያይዞ አማን ቢቆይና በሥልጣን ላይ ቢኖር ኑር ግንባሮቹ አስቸጋሪ ጊዜ ይጉጣቸው እንደነበር መገለጽ ያለበት ነው። የደርግ አባላት አማንን አሳመኑትም ነበር፣ እሱም ለነሱ ትዕግሥት አልነበረውም። አማን ተወዳጅነትን የማትረፍ ችሎታ ነበረው፣ ነገር ግን በስተፖለቲካው ወደ ቀኙ ጽንፍ ያዘነበለ እንደመሆኑ መጠን፥ በኢትዮጵያ ሁኔታ ለአምባገንነት ብቁ የሚያደርገውን ያሟላ ነበር።

አማን ከኤርትራ ግንባሮች ጋር ያብራል የሚል ፍራቻ የደርግ አባላቱ አልነበራቸውም። በዋናነት የፈሩት ወታደሩን አነሣስቶ ራሱን ደርግን እንዲያስወግድ ነበር። እንዲህ ዓይነቱን የመፈንቅል ሙከራ ለማክሸፍ መንግሥቱና ጓደኞቹ ቴሌፎኑን ከመጥለፋቸውም በላይ ለአማን ቅርብ በነበረው በሺመልስ አዱኛ (አሁንም የመንግሥት ባለ ሥልጣን/ ሚኒስትር) በሚተርብ የውስጠ ምስጢር ሪፖርት ተጠቅምዋል። አማን

የኤርትራን ጥያቄ ለመፍታት አማራጭ የማይኖሰት አብዮት ራሱን እንደማትረቡ መጠን፥ በደርግ መኮንኖችና በሱ መካከል በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ የኤርትራ ጥያቄ በስተጀርባ ይንሳፈፍ ነበር። ከዚህ ውጭ በአማን ወታደራዊ ታሪክም ሆነ በፖለቲካ አመለካከቱ በረከትና ሌሎች የለጠፉበትን "የሰላም ሰው" የሚያሟላበት ጭብጥ የለም።

እንደ አማን ሁሉ የበረከትም ታሪክ ከአናቱ ላይ የተቀረጠፈ ነው። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ በረከት የኤርትራ ግንባሮችና ፕሮግራማቸውን ይቃወም ነበር። ወደ ኢትዮጵያው የግራ ጎይል ቀረብ ለማለት ያደረገው ሙከራም በዞር በል (ወግድ) ያከተመ ነበር። ከታመነ ምንጭ እንዳገኘሁትም መኢሶንን የመሠረቱት ምሁራን የ"ሲ.አይ.ኤ. ቅጠሮች" (CIA agent) አድርገው ይመለከቱት ነበር። ይኸው ከስ በ1970ዎቹ ውስጥ ኤርትራ ለነጻነት በስሜን አሜሪካ(EFLNA) በተባለው ቡድን አሜሪካ ውስጥ ተሰተጋብቷል። ደርግ ሥልጣን በያዘ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ሚኒስትሮች እንዲመረምር የተቋቋመው የመርማሪ ኮሚሽን አባል ተደርጎ ነበር። እንደ ጠቅላይ ዓቃቤ ጎግና እንደ መርማሪ በጣም ጨካኝ ከሚሆኑ የተነሣ ብዙ የደርግ አባላት ትቡነቱን ሲያደንቁ የተከሳሾች ዘመዶች ደግሞ ይፈሩት፥ ይጠሉት ነበር። በረከት ከአማን ጋር በነበረው ቅርበት የተነሣ አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ ሰለወደቀ (አንዳንዶች በውትቱ የአማን አማካሪ ነበረ ይላሉ) ወደ ስደት ሸሸ። በአሁኑ ጊዜ በረከት የኤርትራን ግንባር (ሀግሓኤ)፥ በቅርብ የተቀየረ ዕውንተኛ አማኝ በሚያሳየው የተጋቱለቀለ ስሜት በመደገፍ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያዊ ለሆነ ተቃዋሚ ጎይል ልክፍት ያሰከረው ጥላቻ እንዳለው፥ ይህም በቸድርሰቶቹና ቀደም ብሎ በተጠቀሰው መጽሐፉ ጎልቶ እንደሚታይ ማከል ያስፈልግ ይሆን?

20. The Ethiopian Revolution, Ottaway, p.22; በተጨማሪም የሚከተለውን ይመለከቷል፤ Halliday and Molyneux. "Ethiopia's Revolution From Above", Merip Reports, no. 106 June 1982.

21. የኢትዮጵያ አብዮት፥ መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በታተመ በዚህ መጽሔት

ላይ የሁኔታዎች ዝርዝር ሲደረድር በጎጻር ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.ና በሌሎች ጊዜያት በአፈሲል ስለተገደሉት የኢሕአፓ አባላት ምንም አይጠቅስም።

22. The Ethiopian Herald, February 27, 1976.

23. ስለ ደርግ የሠራተኛ ሕግ ዝርዝር ሐተታ ዲሞክራሲያ ቅጽ.፱ ቁ.፴፣ ፲፱፻፷፱ ይመለከቷል:

24. ለኤርትራ ትግል የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች የሚሰጡት እንዲህ ዓይነት ድጋፍ በራሳቸው በኤርትራ ግንባሮች አብዛኛውን ጊዜ አይጠየቅም። -ኢሕአፓ እንዲያውም ከኢ.ኤ.ኤፍ (ELF) ጋር በማቀናጀት የአርሶ አደሩን ጦር ተዋግቷል። አስመራ ፀረ-ጦርነት ቅስቀሳዎችን፥ በወታደሩ ውስጥ ለማካሄድ የኢሕአፓ ሕዋሳት ከሀግሓኤ (EPLF) ጋር አብረው ሠርተዋል። ደርግ የኢሕአፓ ቅስቀሳ ወታደሩ ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ በአሉታዊ መንገድ ሲጠቀመው፥ ግንባሮቹ ግን ይህ ዓይነቱ ነገር ከቶውንም እንዳይነሳባቸው አጥብቀው ይጠነቀቃሉ።

25. በመሠረቱ ቦምቦቹ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትና ዋቢ ሸበሌ ሆቴል በኢ.ኤ.ፊ.ኤፍ (ELF) የከተማ ኮማንዶዎች (ፈዳዩን) የተተከሉ ነበሩ።

26. ለዝርዝር ሁኔታው፡ ABYOT, Information Bulletin of the EPRP Vol.1 no. 6, August 1976. የታደሰ ብሩና የመለስ ተክሌ ርሸና ሙሉ ዘገባው በዲሞክራሲያ፥ ቅጽ.2 ቁ.3 ነሐሴ ፲፱፻፷፯ ይመለከቷል።

27. Schwab, op.cit; page 41.

28. የኢሕአፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ፲፱፻፷፯፥ ገጽ XI በእንግሊዝኛው እትም።

29. ለደርግ የንብረት ግንባር ጥሪ የኢሕአፓን መልስ በዲሞክራሲያ ልዩ እትም ቅጽ ፫ ፲፱፻፷፰ ይመለከቷል።

ኢሕአፓ በመተከል ደረጃ "የዲሞክራሲያውያንና የተራማጅ ጎይሎችን የንብረት ግንባር" ተቀበለ፣ ነገር ግን እንደዚያ

ዓይነት ግንባር ትርጉም የሚኖረው ለውይይት በር ይከፈት ዘንድ ዲሞክራሲያውያን መብቶች ሲከበሩ፥ የፖለቲካ እሥረኞች ሲለቀቁ፥ የግፍ እርምጃዎች ሲቆሙ...ወዘተ ብቻ ሲሆን፥ በተጨማሪም ልዩ ልዩ ፓርቲዎችና ድርጅቶች፥ ግንባሮች፥ ሕዝባውያን ድርጅቶች...ወዘተ የንብረት ግንባሩ ሂደት አካል እንዲሆኑ ከተፈቀደላቸው ነው፣ በሚል ፈርጠም ብሎ ቆመ። የኢሕአፓ ቅደመ ሁኔታ በደርግ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ኢሕአፓ በተገቢ ምክንያት ላይ ተመሥርቶ የወሰደውን አቅዋም "ግራ አክራሪዎች" በግውንዝ ወዲያውም አክታ-ትለው "የማእ ቤ ጾንግን መርሓ ሕግብ" የሚቀበል "የኢትዮጵያ ኮሚዩኒስት ፓርቲ" መሥርተናል ብለው እንዳወጁ ነው። ኢሕፓ በኢትዮጵያ ውስጥ ይሆን ያህል የሚባል ተከታይም ሆነ ተጽዕኖ አልነበረውም።

ባሞር ጊዜ ውስጥም ተቧቃተነ። ወደ ስደት ከሸሹት ምስት የኢሕፓ አባላት በ፲፱፻፸፭ ዓ.ም "ግለ ሂስ" አትመው በማውጣት የ"ማእን መርሓ ሕግብ" "እድጎራና ኢማርክሲዊ" ብለው አመገቡ።

30. ምሁራዊ መጠትተኝነት፥ (elitist) ስለሚለው ቅጽል፣ Marina Ottaway's "Social Classes and Corporate Interests in the Ethiopian Revolution" Journal of Modern African Studies, vol. 14 no. 3, 1976ን ይመለከቷል።

ክፍል ሁለት

የ፫ፋው ሽብር

አርከን አንድ፤

ዒላማው ታወጀ

«አሁን የሚፈለገው ዲሞክራሲያዊ መብት ሳይሆን የዲሞትፎር ጥይት ነው።»
የመኢሶን መፈክር፣ ነሐሴ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

«ከኢምፔሪያሊስቶች የሰላ አገልግሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ጎጡን አሸባሪ ድርጅቶች በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች የፍርሐትና የጥርጣሬ ሁኔታ ለመፍጠር እየሞከሩ ነው።»
ኒው ታይምስ፣ ሞስኮ፣ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

«በመሠረቱ ኢሕአፓ ፀረ-አብዮተኛ ነበርና ደርግን በኃይል የመጠቀም አቅሞም እንዲወስድ አስገደደው። ያም የኃይል እርምጃ የደርግን ቊርጠኛነት ከማሳየቱም በላይ በአብዮቱ እድገትም ላይ አንድ ሞኑኛ ደረጃን የሚያመላክት ሆነ።»
ፒተርስ ሽዋብ፣ ከዚያው መጽሐፍ፣ ገጽ 42

የ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. የዘመን መለወጫ ለሕዝቡ ያመጣው ብሥራት የለም። ደስታ የሠፈነበት አዲስ ዓመት እንዲሆን መመኘት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከልብ የሚንጨለት ቢሆንም የሚገጣጠም አልሆነም። ምክንያትም ነበረው።

በዚሁ ዓውደ ዓመት ወታደራዊው መንግሥት ኢሕአፓን በስም ጠርቶ እንደ ቁጥር አንድ የሕዝብ ጠላት አድርጎ በማቅረብ በሬዲዮ የይፋ መግለጫ ሰጠ። መግለጫው ኢሕአፓ ላይ ፣በጣም ከሚቀፉ ከሶች እንስቶ መሣለቂያ ሊሆኑ

እስከሚችሉ ዓይነት ድረስ ያሉትን ቁሉለበት። የእርሻ ምርት መቀነስ፣ የእህል መበላሸት፣ የእርሶ እደር በመፅ፣ የሸቀጣ ሸቀጥ ዋጋ መጨመር፣ የመለዋወጫ ዕቃ መታጣት፣ በየፋብሪካዎች ማሺኖች መሰባበር፣ የሠራተኞች የኑሮ ደረጃ ማቄልቄል፣ ሠራተኞች የሥራ ማቆም እድማ ማድረግ፣ የተማሪዎችና የመምህራን ሰላማዊ ሠልፎች ማድረግ፣ የአውሮፓ የወደብ ሠራተኞች ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ የድርቅ እርዳታ መርከብ ላይ ለመጫን እሻፈረኝ አሉ መባል፣ የሽሙጥና መሥፋፋትና ሌሎችም የችግር ዓዞች የኢሕአፓ ሥራዎች ተብለው ተደረደሩ።

ዓዋጁ ሰብዙ ሰው ዱብ ዕዳ አልሆነበትም፣ ምክንያቱም የግፉ መጠን በሐምሌና በነሐሴ ከመጨመሩም በላይ ኢሕአፓም ራሱ ደርግና መኢሶን ለጦርነት ዝግጅት እያደረጉበት እንደነበር ገልጾ ነበርና። በደንብ የተቀነባበረው የፕሮፓጋንዳው ወጀብም ምንም ጥርጥር ውስጥ የሚከት አልነበረም። የብሔራዊ ልማት እድገት ሚኒስቴርን የቀድሞ ሚኒስትር በአሻጥር ወንጀል ለመክሰስ ሞብተ ለማቅረብ ሲባል የተዘጋጀውን ፊልም ማላከኪያ በማድረግ «የኢሕአፓን የኢኮኖሚ ወንጀል ለማረገጫ» ብለው በቴሌቪዥን አሳዩ። ፊልሙን ቀደም ብለው ያዩት የንግድ ምክር ቤት አባላት ብቻ ነበሩ ቅሬቷውን ልብ ሊሉት የሚችሉት:: ያም ግድ አልነበረም::(1) መኢሶንና ሌሎች ከደርግ ጋር የተሻረኩ ቡድኖች ኢሕአፓን እንደ አናርኪስት፣ ትሮትስካይት፣ የሲ.አይ.ኤ. ወኪል፣ ፊውዳል፣ ፋሺስት፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ደጋፊ ወዘተ... እድርገው ለማሳየት ተረባረቡ። የተዉት ስድብ፣ የነደፉት ክስ አልነበረም። ለመንግሥቱ ድክመትና ችግር ማመካኛ አዲስ «ዳውሰላ» የተገኘ መሰለ። «የፈውዳሎችና የመሣፍንት ፓርቲ» ብሎ መኢሶን ተንጨረጨረ፣ የመሣፍንቱ ወንድ፣ ሴት ልጆቻቸው የሞሉት እዚያው መኢሶን ማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ እንዳልነበረና ቢሆንም እንኳ ይህ ከጉዳይ የሚገባ ይመስል። ኢሕአፓ እንደ ፀረ-አብዮት እንዲታይ መደረጉ እየታወጀበት የነበረውን የከረረ የግፍ እርምጃ ማጠየቂያ ነበር። ደርግና መኢሶን ከዚህ ወይም ከዚያ ያልሆነ «መሐል ሠፋሪ» (ገለልተኛ) ሊኖር አይችልም፣ አሉና መሐል ሠፋሪ የስድብ ቃል፣ የወንጀል እድራጎት ሆነ። ፖለቲካ የማይነካካቸው ብዙ ምሁራን በኋላ እንደደረሱበት ከመኢሶን ባለመወገናቸው፣ የደምስሰው የስም ዝርዝር ውስጥ ስማቸው መግባቱ ሲታይ ደርግና መኢሶን ከኛ

ያልወገኑ ሁሉ ከኢሕአፓ የወገኑ ነው የሚሉ መሰሉ::(2)

በይፋ የታወጀው ሽብር እሙም አንድ እነሆ መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ተጀመረ። በዓመቱ ውስጥ የካቲት ላይ መጠኑ እየጨመረና አረመኔያዊ እየሆነ በመምጣት ቀለሙን ለውጦ መደበኛው ቀይ ሽብር ለመሆን በቃ። በመስከረሙ ሽብርና ተከትሎት በመጣው ቀይ ሽብር በሚሉት መካከል በዓይነት ልዩነት አልነበረም፤ ለውጡ በዕውነት የቁጥር ብቻ ነበር። ፀረ-ኢሕአፓ ጦርነት በአፈሴል ደረጃ መታወጁ የቀደመውን የግፍ መጠን በደረጃ ከፍ ከማድረጉም ጋር ቀይ ሽብር የወረሰውንና ያስፋፋውን አዳዲስ ገጽታ እምጥቷል። የመኢሶን ምክር ላልተለየው ደርግ ግን ልዩነቱ ከበድ ያለ ነበር። የራሱን ሽብር፣ «ቀይ» የተቃዋሚዎቹን የራስ መከላከል እርምጃ ደግሞ «ነጭ ሽብር» ብሎ በመሠየም የቦልሼቪክን ተመክሮ በግጥሞስና እዚያም ከነበሩት የአብዮት ኃይላት ጋር በግወዳደር ሆን ብሎ መልእክት እያስተላለፈ ነበር። በዚህም መሠረት ጠላቶች በመገናኛ ብዙኃን እንደ ትሮትስካይቶች፣ ዲኒኪንስ፣ ነጭ ዘበኞችና ኮልሻኮች፣ ወዘተ... ተመስለው ታዩ።

ኢሕአፓ ላይ የጦርነት ዓዋጅ ከታወጀ በኋላ፣ የፔፐሲና የኮካኮላ፣ የሞዝቮልድ፣ የአዲስ ንግ፣ የጨርቃ ጨርቅና የሌሎች ፋብሪካዎች ሠራተኞች፣ የባንኮች፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የቴሌርን መገናኛ ሠራተኞች፣ ወዘተ... ተማሪዎችና ምሁራን ተለቀሙ። በእስራኤል የሠለጠነው የነበልባል ቡድን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደርጎ በማፈሱና በሚፈጸመውም የግፍ እድራጎት እንዲተባበር ሆነ። ምንጠራ የተካሄደባቸው ቀበሌዎች (የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር) የፍርድ ሰው አካሎች እንዲያጽቁሙና እዚያው በዚያው ፍርድ እንዲሰጡ ሥልጣን ተሰጣቸው። ቀበሌዎች የራሳቸውን እሥር ቤቶችና የስይል ማዕከላት ከፈቱ:: የመስከረም ሁለት ክብረ በዓል (ንጉሡ የወረዱበት) ኢሕአፓን ይበልጥ ለማውገዝያ ዋለ። ንብታውያን የሆኑ የተቃውሞ ሠልፎችም በኃይል እንዲበተኑ ተደረገ። ያለምንም ማስታወቂያ በአዲስ አበባ ውስጥ ከቤት ቤት ፍተሻ ተደርጎ ፲፬ ሰዎች መገደላቸው ሲዘገብ፥ ብዙ ወጣቶችና ተጠርጥረው የጠፉባቸውን ሰዎች ቤተ ዘመዶች በከበቡበት ወቅት ወታደሮቹ የመድፈር ወንጀል ፈጸሙ፤ ዘረፉ።

ሃ ከአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎ ሚትሮች ወጣ ብሎ ከሚገኘው ከሰበታ አካባቢ የጅምላ ቀበሬ የተካሄደበት የሬሳ ሰዎች የተቈራረጠ አስከሬን የያዘ መታብር ተገኘ። ጥልቀት ከሌለው ከዚያ መታብር ጅቦች አስከሬኖቹን አውጥተው ነበርና ሚቾቹ (ሁሉት ሴቶች ነበሩባቸው) እጃቸውን ወደ ኋላ ታሥረው ከመረሸናቸው በፊት በሰይል ውስጥ ያለፉ እንደነበሩ ማየት ተችሏል። ቄራም አጠገብ፣ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሁ፣ ፴ አስከሬኖች የያዘ ተመሳሳይ የጅምላ መታብር ተገኝቷል። የነጀህ የጅምላ መታብሮች መገኘት አሥረኞች በምስጢር ማታ ማታ ይገደሉ እየተባለ ይሠራው የነበረውን ልዩ ልዩ ወሬ ጭብጥነት ያለው አድርጎታል። በአዲስ አበባ የሚገኙ ነዋሪዎች የቀፋሮ መኪናዎችን (ካተርፒላሮችን) የተደጋገመ የተኩስ ድምፅን፣ እሪታና ጮኽትን ይሰሙ እንደነበር ተናግረዋል።

ጦርነት ከታወጀ ከአንድ ሳምንት በኋላ አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች በሽብር ተፈጥርቀው ተያዙ። በመቶዎች የሚቈጠሩ በተለይ በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት፣ በድሬዳዋ፣ ወዘተ... ተደገሉ። በሽዎች የሚቈጠሩ ተይዘው ታሠሩ። ሁሉም ግለት ይቻላል፤ በሰይል የተፈጸዩ አሥረኞች በየግታው በመድብል በመድብል (batch) ሁነው ከከተሞች ውጭ እየተወሰዱ ይገደሉና የጅምላ መታብር ውስጥ ይደፉ ነበር። በዚህ በመጀመሪያው ወቅት እንኳን ሽብሩ በዘፈቀደ ነበር የሚካሄደው። ማንኛውም መንግሥቱን የተቃወመ፣ መኢሶንን የተቃወመ፣ መኢሶን ላይ ያለው አመለካከት ከለብታ ያላለፈ ምሁር፣ በተለይም ወጣት ሁኖ ታማኝነቱን ለደርግና ለመኢሶን ማረጋጋጫ ማቅረብ ያልቻለ ሁሉ ዒላማ ሆነ። ኢሕአፓ በአበዛኛው ወጣት፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ወዘተ... የተደገፈ በመሆኑ እኒህን ሁሉ ለመደምሰስ ውሳኔ የተላለፈ መስሎ ታየ። እንዲህ ዓይነቱም ፍራቻ በኋላ የሚያሳዝን ሐቅ ሊሆን መቻሉን ሁኔታዎች የሚያረጋግጡት ሆኑ።

መስከረም ፱ ቀን በሕዝብ አገልግሎት ክፍል የሚሠሩ ሠራተኞች በመፈጸም ላይ ያለውን ግፍና እየተባባሰ የሄደውን የሥራ ሁኔታ በሚመለከት ተቃውሟቸውን በማሰማት የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ። ከመስከረም ፲፩-፲፫ (Sept. 21-23) የአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ቀበሌዎች ሕዝብ የሚፈጽመውን ግፍ አስመልክቶ የተቃውሞ ሠልፍ አደረጉ። ሰላማዊ ሠልፎች በኃይል የተበተኑ ሲሆኑ ከ፴ ያላነሱ

እንደተገደሉ ታውቋል ከመስከረም ፲፩ እስከ መስከረም ፳፩ ድረስ ከ፮ መቶ ያላነሱ ሰዎች በወታደሮች የተገደሉ ሲሆን ብዙ አስከሬኖች ምኒልክ ሆስፒታል ማዕከላዊ (morgue) ውስጥ ተቈልለው ነበር።

እነሆም ለሽብሩ ኃላፊነቱን የሚወስደው ደርግ እንደነበር ግልጽ ነው። ሽብሩ መረን የተሰደደው ኢሕአፓ ለሚያደርሰው ወታደራዊ ጥቃት አጸፋ መልሶ ለመስጠት ሳይሆን፣ ኢሕአፓንና ግንኙውንም ተቃውሞ ለመደምሰስ ነበር። ኢሕአፓም ሆነ ማንም ተቃዋሚ በዚያን ጊዜም ሆነ ደርግ ፀረ-ኢሕአፓ ጦርነት ከማወጁ በፊት እንዲትም ጥይት ከተሞች ውስጥ ይሮህ አልነበረም። መስከረም ፲፫ (Sept. 23) መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ላይ የተደረገው፣ አድራጊኑቱም ለኢሕአፓ የተሰጠው፣ የመግደል ሙከራ ከብዙ ሳምንታት የቀንና የማታ ግድያዎች፣ የይፋው ሽብርም ከተጀመረ ከሃያ ምስት ቀናት በኋላ ነበር የተካሄደው። ደርግ ለግድያዎቹ ግጠየቂያ ይሆነው ዘንድ የራስ መከላከል ክርክርን ሊያቀርብ እንደማይችል ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ግን ፍርዱ ነው። ለነገሩ የኢሕአፓ የፖለቲካ ቢሮ ወደ «ከተማ ታጥቆ ራስን መከላከል» መረማመድ ማስፈለጉን የሚገልጽ የፖሊሲ መግለጫ («ደርግ በኛ ላይ ጦርነት ዓውጇብናል» በሚል ርዕስ) በጥቅምት ወር አውጥቶ ነበር። የዚህም ፖሊሲ የመጀመሪያው ሰለባ የሆነው የመኢሶኑ መሪ ፍቅሬ መርዕድ የተገደለው በደርግና በመኢሶን በየዕለቱ ለእንድ ወር የሚያስቅቁ ግድያዎች ከተካሄዱ በኋላ መስከረም ፳፮ (Oct.2) ነበር።(3)

በሌላ ደረጃ ደግሞ የሁኔታዎች ሂደት በማጠናቀር በኢሕአፓ የተፈጸሙት ግድያዎች ደርግ ካካሄዳቸው የገፍ ግድያዎች ጋር ሲወዳደሩ ኢምንት ነበሩ ብሎ እፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፤ ይህ ግን እንዱን ዐመፅ ለመባረክና ሌላውን ዐመጽ ለማውገዝ አይደለም። ተጨባጩን ትተን ደርግ ራስን መከላከል ወይንም አጸፋ መመለስ የሚለውን ማመካኛ እንደ ትክክል እንውሰደው ብንል እንኳ፣ የሱ ሽብር የትናየት ገደብ አልፎ የሄደ መሆኑ ጎልቶ ይታያል። ሐቁ እንዳሳየው ደርግ ራሱ ሽብሩን በቅድሚያ በመከፈት ኢሕአፓን በማጥበብ፣ ምቹ ባልሆነ የከተማ ሁኔታ ወደ ትጥቃዊ እርምጃ እንዲሸጋገር አስገድዶታል። በግፉ ሂደት ውስጥ ሁሉ የደርግ ጭካኔና ዐመፃ ወደር የማይገኝለትና ኋላ ቀርነትን የሚያሳይ ነበር።

ኦ ከአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎ ሚትሮች ወጣ ብሎ ከሚገኘው ከሰበታ አካባቢ የጅምላ ቀበራ የተካሄደበት የሸኔ ሰዎች የተቈራረጠ አስከሬን የያዘ መታብር ተገኘ። ጥልቀት ከሌለው ከዚያ መታብር ጅቦች አስከሬኖቹን አውጥተው ነበርና ሟቾቹ (ሁሉት ሴቶች ነበሩባቸው) እኛቸውን ወደ ኋላ ታሥረው ከመረሸናቸው በፊት በሰይል ውስጥ ያለፉ እንደነበሩ ማየት ተችሏል። ቄራም አጠገብ፣ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሁ፣ ፴ አስከሬኖች የያዘ ተመሳሳይ የጅምላ መታብር ተገኝቷል። የነኚህ የጅምላ መታብሮች መገኘት አሥረኞች በምስጢር ማታ ማታ ይገደላሉ እየተባለ ይሠራጭ የነበረውን ልዩ ልዩ ወሬ ሙብዥንት ያለው እድርነታል። በአዲስ አበባ የሚገኙ ነዋሪዎች የቍፋሮ መኪናዎችን (ካተርፒላሮችን) የተደጋገመ የተኩስ ድምፅን፣ እሪታና ጮኽትን ይሰሙ እንደነበር ተናግረዋል።

ጦርነት ከታወጀ ከአንድ ሳምንት በኋላ አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች በሽብር ተፈጥርቀው ተያዙ። በመቶዎች የሚቈጠሩ በተለይ በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት፣ በድሬዳዋ፣ ወዘተ... ተደንሉ። በሽዎች የሚቈጠሩ ተይዘው ታሠሩ። ሁሉም ማለት ይቻላል፤ በሰይል የተፈጻፀሙ አሥረኞች በየማታው በመድብል በመድብል (batch) ሁነው ከከተሞች ውጭ እየተወሰዱ ይገደሉና የጅምላ መታብር ውስጥ ይደፉ ነበር። በዚህ በመጀመሪያው ወቅት እንኳን ሽብሩ በዘፈቀደ ነበር የሚካሄደው። ማንኛውም መንግሥቱን የተቃወመ፣ መኢሶንን የተቃወመ፣ መኢሶን ላይ ያለው አመለካከት ከለበታ ያላለፈ ምሁር፣ በተለይም ወጣት ሁኖ ታማኝነቱን ለደርግና ለመኢሶን ማረጋጋጫ ማቅረብ ያልቻለ ሁሉ ዒላማ ሆነ። ኢሕአፓ በአበዛኛው ወጣት፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ወዘተ... የተደገፈ በመሆኑ እኒህን ሁሉ ለመደምሰስ ውሳኔ የተላለፈ መስሎ ታየ። እንዲህ ዓይነቱም ፍራቻ በኋላ የሚያሳዝን ሐቅ ሊሆን መቻሉን ሁኔታዎች የሚያረጋግጡት ሆኑ።

መስከረም ፱ ቀን በሕዝብ አገልግሎት ክፍል የሚሠሩ ሠራተኞች በመፈጸም ላይ ያለውን ግፍና እየተባባሰ የሄደውን የሥራ ሁኔታ በሚመለከት ተቃውሟቸውን በማሰማት የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ። ከመስከረም ፲፩-፲፫ (Sept. 21-23) የአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ቀበሌዎች ሕዝብ የሚፈጽመውን ግፍ አስመልክቶ የተቃውሞ ሠልፍ አደረጉ። ሰላማዊ ሠልፎች በኃይል የተበተኑ ሲሆኑ ከ፹ ያላነሱ

እንደተገደሉ ታውቋል ከመስከረም ፲፭ እስከ መስከረም ፳፩ ድረስ ከ፮ መቶ ያላነሱ ሰዎች በወታደሮች የተገደሉ ሲሆን ብዙ አስከሬኖች ምኒልክ ሆስፒታል ማዕከላዊ (morgue) ውስጥ ተቈልለው ነበር።

እነሆም ለሽብሩ ኃላፊነቱን የሚወስደው ደርግ እንደነበር ግልጽ ነው። ሽብሩ መረን የተሰደደው ኢሕአፓ ለሚያደርሰው ወታደራዊ ጥቃት አጸፋ መልሶ ለመስጠት ሳይሆን፣ ኢሕአፓንና ማንኛውንም ተቃውሞ ለመደምሰስ ነበር። ኢሕአፓም ሆነ ማንም ተቃዋሚ በዚያን ጊዜም ሆነ ደርግ ፀረ-ኢሕአፓ ጦርነት ከማወጁ በፊት እንዲትም ጥይት ከተሞች ውስጥ ይሮህ አልነበረም። መስከረም ፲፫ (Sept. 23) መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ላይ የተደረገው፣ አድራጊነቱም ለኢሕአፓ የተሰጠው፣ የመገደል ሙከራ ከብዙ ሳምንታት የቀንና የማታ ግድያዎች፣ የይፋው ሽብርም ከተጀመረ ከሃያ ምስት ቀናት በኋላ ነበር የተካሄደው። ደርግ ለግድያዎቹ ማጠየቂያ ይሆነው ዘንድ የራስ መከላከል ክርክርን ሊያቀርብ እንደማይችል ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ግን ፍርሱ ነው። ለነገሩ የኢሕአፓ የፖለቲካ ቢሮ ወደ «ከተማ ታጥቆ ራስን መከላከል» መሪማመድ ማስፈለጉን የሚገልጽ የፖሊሲ መግለጫ («ደርግ በኛ ላይ ጦርነት ዓውጇብናል» በሚል ርዕስ) በጥቅምት ወር አውጥቶ ነበር። የዚህም ፖሊሲ የመጀመሪያው ሰለባ የሆነው የመኢሶኑ መሪ ፍቅሬ መርዕድ የተገደለው በደርግና በመኢሶን በየዕለቱ ለአንድ ወር የሚያሰቅቁ ግድያዎች ከተካሄዱ በኋላ መስከረም ፳፮ (Oct.2) ነበር።(3)

በሌላ ደረጃ ደግሞ የሁኔታዎች ሂደት በማጠናቀር በኢሕአፓ የተፈጸሙት ግድያዎች ደርግ ካካሄዳቸው የገፍ ግድያዎች ጋር ሲወዳደሩ ኢምንት ነበሩ ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፤ ይህ ግን እንዱን በመፅ ለመባረክና ሌላውን በመጽ ለማውገዝ አይደለም። ተዉባጩን ትተን ደርግ ራስን መከላከል ወይንም አጸፋ መመለስ የሚለውን ማመካኛ እንደ ትክክል እንውሰደው ብንል እንኳ፣ የሱ ሽብር የትናየት ገደብ አልር የሄደ መሆኑ ጎልቶ ይታያል። ሐቁ እንዳሳየው ደርግ ራሱ ሽብሩን በቅድሚያ በመከፈት ኢሕአፓን በማጠበብ፣ ምቹ ባልሆነ የከተማ ሁኔታ ወደ ትጥቂ እርምጃ እንዲሸጋገር አስገድዶታል። በግፉ ሂደት ውስጥ ሁሉ የደርግ ጭካኔና ዐመፃ ወደር የማይገኝለትና ኋላ ቀርነትን የሚያሳይ ነበር።

ደርግ ኢሕአፓን የሕዝብ ጠላት ብሎ በማወጅ የድምሰሳ እርምጃውን ቀጠለ። ለሰላማዊ ተቃውሞ በግድያና ጭካኔ በተመላበት ሰይል መልስ ሰጠ። ደርግ "ወደ ዐመፅ እንዲራመድ በመተነኮስ!!" (እንዲህ እድርጎም መተንኮስ የለ!!) ኢሕአፓን ለመወንጀል በሚያደርጉት ጥረት የደርግ አጋፋሪዎች ይህንን ሐቅ፥ የሽብር ዘመቻ ኢሕአፓ ላይ የጀመረው ደርግ የመሆኑን ሐቅ - ነው ለማለባበስ የሚሞክሩት።

ክፍል

ለምን ፲፱፻፸፱?

«ጠላቶቻችን ምን ሊያደርጉን ሲፈልጉ እኛ ጮርሰ አደረግናቸው።»
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ፲፱፻፸

መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ኢሕአፓ ላይ የተላለፈው ግልጽ ዓዋጅ የራሱ ምክንያት ነበረው። ታዲያ ከላይ የተጠቀሰው የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቃል ባጠቃለለው ነበር። ግን ዐመፁን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሸጋገር ደርግን እንዲጅጅጥ ያደረጉትን ዋና ዋና ነጥቦች ጠለቅ ብሎ ገብቶ መመርመርና ቁልጭ ብለው እንዲወጡ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ባጠቃላይ፣ ደርግ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት ያወጀው በፖለቲካው ትግል ኢሕአፓ በማያጠራጥር ደረጃ እያቸነፈው በመሆኑ ነበር። ደርግ ተራማጅ ሕጎች ቢደነግግና የሳይንሳዊ ሶሻያሊዝም ተከታይ መሆኑን ቢለፍፍም፣ ተራማጁ የተቃዋሚ ክፍል በዚህ ሊታለልም ሆነ ጥርጣሬውን ሊፍት፣ ለመንግሥት ለውጥም ያለውን ጥያቄ እርግፍ አድርጎ ሊተው አልተገፋፋም። መንግሥቱ ቃላት በማሾጕድጕድ ግራውን ወገን ሊበለጥበት (አጥፎት ለማለፍ) በሞከረ መጠን ግራው የበለጠ እጅጉን ጯሮ ይዞ የጦርነት ዓዋጁን የጊዜ አመራረጥ በሚከተሉት ምክንያቶች ማስረዳት ይቻላል፤

1) ወታደራዊው እገዛዝ ላይ እያደገ የመጣው ተቃውሞ በልዩ ልዩ ምክንያት ኢሕአፓን እያደር ተወዳጅ እያደረገው መጥቶ ነበር። ለደርግና ለመኢሶን ሥጋት በሚፈጥር ደረጃ ቊጥሩ እየጨመረ የሄደ ሕዝብ ወደ

ፓርቲው እየተሰባሰበ የአባላቱና የደጋፊዎቹ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ግልጽ እየሆነ ነበር። (5) የኢሕአፓን ተጽዕኖ በፖለቲካ መንገድ ለመቋቋም በመኢሶን በኩል የተደረጉ ሙከራዎች በምንም ዓይነት መንገድ አልተሳኩም። በጋዜጦችና በየቢሮዎች ይካሄድ የነበረው የውይይት መድረክ ኢሕአፓ ሠፊ ቅስቀሳ እንዲያካሂድና አመለካከቱንም ለማሠራጨት እንዲችል በቂ ዕድል ሰጠው። የወዝ ሊጉ ሠናይ ልኬ፣ መድረኩን ኢሕአፓ እየተጠቀመበት ስለሆነ እንዲታጠፍ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለማሳመን ቻለ። ሕዝቡ መንግሥቱን እምነት ነሣው፤ ታዲያም መንግሥትም አፍ አውጥቶ ጋዜጦችን የሚያንብለት፣ ሬዲዮውን የሚሰማለት እንደሌለ በይፋ አማረረ። (6)

መንግሥቱ ኃ/ማርያምና የቅርብ ጓደኞቹ፣ ኢሕአፓና በሱም የሚመሩት ተቃዋሚ ወገኖች እደጋ እንዳንጠለጠሉባቸው ታያቸው፤ ስለዚህም መኢሶንና ወዝ ሊግ «ፈጣንና ቁራጥ እርምጃ» ኢሕአፓ ላይ እንዲወሰድ ምክር ማካፈል ሲጀምሩ እህ ብለው ጆሯቸውን ሰጧቸው።

2) ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም እንጻር ይበልጥ የሚያሸብር ሁኖ የተገኘው እምሳቱ በጦር ኃይሎች ውስጥ እየተስፋፋ መሆኑ ነበር። እየር ኃይል ውስጥ ተፈጥሮ ከነበረው እምሳትና ከእየር ወለዶች ዐመፅ በኋላ፣ ሻለቃ መንግሥቱ ራሱ የወታደር ካምፖችን በመጉብኘት ከመኰንኖችና ከወታደሮች ጋር ተነጋገረ። ለደርግ እገሣዝ ተቃውሞው ያደገበትን ደረጃና በኢሕአፓ ጋዜጣ በዲሞክራሲያ ላይ ለተገለጹት አቅዋሞች የነበረውን ድጋፍ በተገነዘበ ጊዜ ደነገጠ። ይህንን ሁኔታ ለመለወጥም ተወዳጅነት ሊያተርፉለት የሚችሉ ዘዴዎችን ሞከረ። (ጦር ሠፈር ውስጥ በመተኛት፣ በሚማርክ ንግግር በመሸንገል «እኛ እንድ ነን፤ ፍላጎታችሁ ከሆነ ከሥልጣን እንሰናበታለን» ወዘተ... እያለ ከ«ልቡ» መሆኑን ለመግለጽ እንባውን እስከማፍሰስ ደረሰ» እንዲሁም ሙልሞ ያለ ውሸት ዋሸ። (ሶማሊያና ኤርትራ ሀገሪቱን ለመከፋፈል ባሳቸው ዕቅድ ላይ ኢሕአፓ መስማማቱን የሚያረጋግጥ የሬርማ ማስረጃ አለን፤» «ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ጦር ኃይል በመከፋፈልና አሻጥር በመሥራት ሶማሊያን ሊረዳ ቃል

ገብቷል» ወዘተ...)

ወታደሩ ውስጥ የነበረውን እምሳት ለመግታት በኢሕአፓ የሚመራው የሲቪል ተቃዋሚ ወገን ወታደሩ ውስጥ ካፈነገጠው ወገን ጋር ትሥስር ፈጥሮ የሠመረ ቅንብር እንዳያደርግ፣ ኢሕአፓን መንጥሮ የማጥፋት አስቸኳይነት ተሰማው።

3) ሐምሌ 1969 ዓ. ም. ላይ ደርግ በውስጣዊ ሁከት እየተብላላ ሂዶ አብዛኛው ወገን መንግሥቱና ጓደኞቹ ላይ ተነሣባቸው፤ ሁኖም እንመንግሥቱ ሰደድ በተባለው ምስጢራዊ ቡድን የተደራጁና ይበልጥም ወሳኝነትን የያዙ መሆናቸው ልቀው እንዲነጡ አድርጓቸዋል።

እጦር ኃይሎች ውስጥ በተፈጠረው እምሳት በመደፋፈር የደርግ አባሎች ስብሰባ አድርገው ደርግን ራሱን እንደገና የሚያዋቅር ኮሚሽን ለመቋቋም ወሰኑ። ዋናው «የማዋቀሩ» ዓላማ እምባገነናዊ ሥልጣንን ለመገደብ እንደነበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም ራሱም ሆነ መኢሶን አልጠፋቸውም። የተደረገውም ልክ ይኸው ነበር። የተቋቋመው ፲፮ ሰው የያዘ ኮሚቴ «የደርግን ዴሞክራሲያዊና የጋራ አሠራር» የሚያጠናክሩ እርምጃ እንዲወስዱ የሚጠይቅ ሐሳብ አቀረበ። ሊቀ መንበሩ ተፈሪ በንቲ፣ ሻለቃ ሞገሥና ሌሎችም በመንግሥቱ ኃ/ማርያም የቅርብ ዙሪያ ያልነበሩ ከፍተኛ ሥልጣን የተሰጣቸው ኮሚቴዎችን እንዲመሩ ተደረጉ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ወደ ጀርባ «ሳበ»። ከዚያም ተያይዞ ደርግ የመኢሶንና የሕዝብ አደራጅ ጽ/ቤት ተብሎውን «አሳፈ ተግባራት» የሚመረምር እንድ ኮሚቴ አቋቋመ።

ለመንግሥቱ ኃ/ማርያምና ለመኢሶን ቀኑ እያጠረባቸው ነበር። ሥልጣን ከእጃቸው ላፈትልክ አለ። ይህን ሁሉም ኢሕአፓ ላይ ላክኩ። መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ጓደኞቹ (እንደ ለገሠ አሥፋው፣ ተስፋዩ ወልደ ሥላሴ፣ ተካ ቱሉ፣ ጌታቸው ሺበሺ፣ አሊ ሙሳ፣ ሥዩም መኰንን፣ ጄንኤል አሥፋው) አበከረው በምስጢር መሰብሰብ ጀመሩ። የመንግሥቱ ኃ/ማሪያም የቅርተ ታማኞችና መኢሶን (እንዲሁም ወዝ ሊግ» የደርግ አባላት ከኢሕአፓ ጋር ሰላም ይፈጥራሉ ብለው ድንጋጤ ገባቸው። ይህንንም ሁኔታ ለመቅደም ኢሕአፓን ለመምታት መላ መቱ። ዕቅዳቸውን ለደርግ አባላት ያቀረቡ ሲሆን የመኢሶን መሪዎችና መንግሥቱ ኃ/ማርያም

የታሰበው «ለአዲስ አበባ ሰላም» ለማምጣት እንድ ለ«ፈጣን የቀዶ ጥገና እርምጃ» ሆኖ የተወሰደ መሆኑን እንዳስረዱ ይታወቃል። አብዛኞቹ የደርግ አባላት ይህንን እምነው ሊሆን ይችላል፤ በሌላ ወገንም ደግሞ የኢሕአፓን ተሰሚነት መቀነስ የኋላ ኋላ ይጠቅመናል ብለው አስበውም ሊሆን ይችላል። በኋላም በየካቲት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ከኢሀአፓ ጋር ግንባር ለመፍጠር ጥሪ እደረጋችሁ በመባል በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ቤተ መንግሥት ውስጥ በተደረገው መፈንቅለ መንግሥት መገደል ያልቀረባቸው ተፈሪ በንቲ፣ ዓለማየሁ ኃይሌና ሌሎችም መኩንኖች መንግሥቱና መኢሶን እንዳላከሉባቸው የኢሕአፓ ደጋፊዎችም አባላትም አልነበሩም። እነሆም መንግሥቱ ኃ/ማርያምና መኢሶን ኢሕአፓ ላይ ጦርነት የማወጅን አስፈላጊነት በገለጹላቸው ጊዜ ተስማሙ። ፈጣን እርምጃ የተባለው በገፍ መግደል መሆኑንና ኢሕአፓን ማጥፋትም የመንግሥቱ ኃ/ማርያምና የመኢሶንን የበላይነት እንደገና እንዲመለስ ማድረግ መሆኑን በተገነዘቡ ጊዜ ያለቀለት ነገር ሆነባቸው። ማመንታታቸው ሕይወታቸውን ለማጣት ሲያበቃቸው፣ ከተገደሉ በኋላ ደግሞ የኢሕአፓ አባላት ነበሩ ተብለው መከሰሳቸው ምፀት ሁኖ አረፈ።

ስለዚህም ከደርግና ከመኢሶን እንጻር መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ኢሕአፓን «ለመግታት» የማይታሰፍ ወቅት ነበር። በተለይም ደርግ ሥልጣኑን ትንሽም ቁንጥር ለማከፈልም ሆነ የተቃዋሚዎቹን ጥያቄ ለማዳመጥ ምንም ዓይነት ፈታደኝነኝተ ባልነበረው ሁኔታ - ይበልጥ ቅስቀሳው በቀጠለ መጠን ይበልጥ ጦር ኃይሎቹ ውስጥና እንዲያውም ደርግ ራሱ ውስጥ ይሠራጭ ጀመር። ኢሕአፓ ላይ፣ ባጠቃላይም ተቃዋሚ ወገኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ግፍ ያው ያለ፣ የቁየ ነበርና የቀረው ነገር ቢኖር በይፋ ዓውጆ ደረጃውን ከፍ ማድረግ ነበር። መስከረም 1969 ዓ.ም. ያደረገችው ልክ ይህንኑ ነው።

የሽብሩ መጋበርት

"በጅብ መበላት ይሻልሃል ወይስ
በኑብር" ቢለው
"ልዩነት የለውም፣ ጥርሳቸው ሥል ነው::"
ብሎ መለሰ የአበሻ ምሳሌ

የደርግ ግፍ መፈጸሚያ መጋበርት በርግጥም ሥሊታም ጥርሶች ነበሯቸው። ግን ወገን ሲታይ ምን ዓይነት አውሬ ነው ያሩጠጠሀ የሚለውም ከግምት የሚገባ ነው። ለምሳሌ ተራው ፖሊስ ከፀጥታው ፖሊስ ጋር ሲወዳደር ለዘብ ያለ ነበር፤ የፀጥታው ፖሊስ ደግሞ በመኢሶን ቁጥጥር ሥር ከነበሩ ቀበሌዎች ጋር ሲወዳደር «የተሻለ ነበር። ለእስቲ የሽብር ዘመቻውን መጋበርት ዘርዝር ባለ መልክ እንቃኛቸው፤

ጦር ሠራዊት፤ መጀመሪያ ላይ ፲፱፻፷፱-፲፱፻፸፮ ነበልባል የተባለው በሚካኤው የታወቀው ቡድን አዲስ አበባ እንዲመጣ በተደረገበት ጊዜ ከጥቅም ላይ ውሎ ነበር። ሁኖም በአንዳንድ ከሕዝባዊ ሠልፎች ጋር በተገናኘ ሁኔታ እንዲሠማራ ከመደረጉ በስተቀር «ቀይ ትርሺት» እየተባለ በብዙኃን መገናኛ ይጠራ በነበረው የሽብር ትዕይንት ውስጥ ሚናው ዝቅተኛ ነበር።

ፖሊሶች፤ በጣም ዝቅተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው። የግይታመኑና በኢሕአፓም የተበከሉ ናቸው ተብለው የተገመቱ ነበሩ። ተግባራቸውም በደርግና በመኢሶን በተቋቋመ አዳዲስ የግፍ መፈጸሚያ አውታራት ተወሰዶ ነበር።

ፀጥታ፤ («የሕዝብ ደኅንነት») ተካ ቱሉ በሚባለው የደርግ አባል እየተመራ፣ በጠቅላላው የሽብር ዘመቻ ውስጥ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ሚና ተጫውቷል። አዲስ አበባ ውስጥ ከሦስተኛው ፖሊስ ጣቢያ የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤቱ የመጨረሻው አረመኔያዊ ግፍ የሚደርስበት ቦታ ነበር። በዕኩይነቱ የታወቀው ላሺን ተሾመና ሌሎችም ጨካኝ አግዓዚዎችና ነፍሰ ገዳዮች ይህን የዕከይ ተግባራቸውን የሚፈጽሙት እዚሁ ቅጽር ግቢ ውስጥ ሲሆን የፀጥታው ኃይል መንግሥቱ ኃ/ማርያምና መኢሶን የከፈቱትን ሽብር የሚያገለግል የግድያ መሣሪያ (Machine) ነበር።

ወታደራዊ የምስጢር ፖሊስ፤ መጀመሪያ በዕኩይነቱ በታወቀው ኮሎኔል ዳንኤል እሥፋው፣ በኋላም በሻለቃ ጌታቸው ቪበቪ ይመራ የነበረውና የወታደራዊ መረጃ ሰላዮችንና ልዩ የደርግ «መረጃ» (መረጃና አጥፊሽን) የተባሉትን የሚያካትት ነበር። እንደ ፀጥታ ፖሊስ ሁሉ የራሳቸው እሥር ቤትና ሰይል የሚፈጽሙ ነበሯቸው፤ ግድያም ያካሂዱ ነበር። ገዳይ ስኳዶቹ የሥራ ግንኙነት/ሪፖርት የሚያደርጉት በቀጥታ ለራሱ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ነበር።

የቀበሌ ስኳዶች፤ ተቃዋሚው የተራማጅ ወገን ያካባቢ የራስ አስተዳደር ጥያቄን ተቀባይነት ያገኘ መፈክሩ አድርጎት ነበርና ቀበሌዎች ወይም የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር የተቋቋሙት ይህንኑ ለማጨናገል ነበር። ስለሆነም እነሀ ማኅበራት ወደ ግፍ መፈጸሚያ አውታራት ለመለወጥ ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም። የቀበሌ መሪዎች ምርጫ የነጻ ምርጫ መምሰል (አምሳያዎች) ነበሩ። ቀበሌዎችን ከ«ኢሕአፓ» የጸዱ እንዲሆንም በየጊዜው «ምንጠራ» ይካሄድ ነበር። ፀረ-ኢሕአፓ ጦርነት በታወጀበት ጊዜ የአዲስ አበባ ፱፱፲፱ ቀበሌዎች በአብዛኛው በመንግሥቱ ኃ/ማርያምና በመኢሶን ቁጥጥር ሥር ወድቀው ነበር። ፱፱፻፱ ኡ ቀበሌዎች÷ ከፍተኛዎች በተባሉ ሽፍ ማኅበራት ተደራጅተው ነበር። ከፍተኛው አካል የሆነው የማኅበራቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከራሱ ውስጥ ከንቲባውን «ይመርጣል»። በዚህም መንገድ ነው። በ«ቀይ ሽብሩ» ውስጥ በደም የተጨማለቀ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት ውስጥ አንዱ የሆነውና በወቅቱም የመኢሶን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው ዶክተር ዓለሙ አበበ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ለመሆን የበቃው (8)

ቀበሌዎቹ የራሳቸው አብዮት ጥበቃ ጓድ ወይም አብዮታዊ መከላከያ ስኳዶች ነበሯቸው። እነዚሁ በመጀመሪያ የታጠቁት ጓንዴ ጠመንጃዎች (ሊ ኤንፊልድ 303) ሲሆኑ በኋላ ግን ክላሽንኮቭ (Ak 47) ተሰጡ። በአብዛኛው ለየቀበሌ መሪዎች የቀድሞ የጦር ሠራዊት አባላት፣ በጡረታ የተገለሉ ወታደሮች፣ ሥራ አጦችንና ዱርዬዎቸን ያጠናቀረ ነበር፤ ግን ደንሞ ኮርኔል (ኑ ዮርክ) እንደተግረው፣ ዕድሚያቸው ከ፲ ዓመት በታች የሆኑ የልጅ እሥረኞችን በሰይል ማሥቃየት ያስደስተው እንደነበረው እንደአሳዘነው በይሳና፣ ፴ ሰዎችን፣ የስምንት ወራት ነፍሰ ጡር የነበረችውን ዳር ነጋሽ የተባለችውን ሠራተኛ ጨምር የገደለው የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ ግርማ ከበደም ይገኙበታል። የሚያጉተመትሙ ፀሐፊዎች ጡረታ የወጡ ወታደሮች፣ የለየላቸው ዱርዬዎችና እእምሯቸውን ጭካኔ ያንበረው ምሁራን ጥርቃሞዎች ላይ ነው። ማርክሲስት ሌኒኒስት ነኝ ባዩ መኢሶን እመራሩን ያደረው። ለቀበሌ መሪዎች ዘበኞች «የፖለቲካ ትምህርት» በመኢሶን ተሰጥቷቸው በ፲፱፻፷፱ና በ፲፱፻፸ ዓ.ም. አብዛኞቹ ከመኢሶን የሚበልጥባቸው ሌላ ነገር አልነበረም። ቀበሌዎቹ በየአካባቢያቸው ያለውን ሰው በሕይወቱ ላይ ከትትልም ቁጥጥርም ያደርጉበታል። የትም የት ይገኛሉ፤ ሥልጣናቸውም የተለጠጠ ነበር። የራሳቸው እሥር ቤቶች ነበራቸው፤ በነዚህ እሥር ቤቶች ውስጥም ከሁሉም የከፋው ሰይልና ጭካኔ የተመላባቸው ግድያዎች ይካሄዱ የነበሩት – የቀበሌ ዘበኞች ሥራዬ ብለው የያዙት ሴቶችና ወጣት ኩሪዳዎችን ማሠር ነበር። ለእካለ መጠን ያልደረሱ ሴት ልጆችን መድፈር የተለመደ ነበር።(9) እኒሁ የቀበሌ ዘበኞች በጠቅላላው በሽብሩ ዘመቻ ውስጥ ወሲይ ሚና የተጫወቱ ሲሆን እንደ ግንባር ቀደም ኃይል መሆናቸው የኢሕአፓ የአጸፋ እርምጃ ዒላማዎች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በቀበሌዎች መካከል ውድድርም ነበር (ምናልባት ለሶቪያሊስታዊ ውድድር መኢሶን ያበረከተው አስተዋጽኦ መሆኑ ይሆናሳ!) በማሠር በመግደል ዝቅ ያለ አስተዋጽኦ ያደረገ ቀበሌ መሣለቂያ ይሆን፣ ይወቀስ ወይም እንዲያውም በጥርጣሬ ዓይን ይታይ ነበር፤ ይህም የፉክክር ሁኔታ እንዱ ቀበሌ በሌላ ተወዳዳሪ ላይ የበላይነት ለማግኘት ከሌላው ይበልጥ «አናርኪስቶችን» ማሠርን ይበልጥም መግደልን አስከተለ፤ እንሆም ምንም ዓይነት ሐሳፊነት የማይሰማቸው ፍጡሮች ጠመንጃ ሰጥተው እንዳሻቸው (ያለምንም ጥያቄ) እንዲገድሉ ሲበረታቱ በነበረበት

ትዕይንት ምን ሊደረግ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ዋናው የቊጥር ማብዛት ነበር፤ በሺዬትናም ጦርነት ጊዜ እንደነበረው የአስከሬን እንድ በእንድ ቈጠራ ዓይነት፣ ይበልጥ መግደል ሆነ ተፈላጊው። በዚህ ውድድር ውስጥ ከተራ ጸርዬዎች እንሥቶ ቀደም ብለን እስከጠቀስነው ዓይነት ምሁርና እንደ አብዴል ዩሱፍ (ጀርመን አገር የተማረ የመኢሶን መሪ በሐረር፣ ድሬዳዋ ብዙ ሠራተኞችን በሰይል ያሠቃየና ያረደ) እንዲሁም የቀድሞ ተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበረ፣ ሬሱም ኤርትራዊ ሆኖ ትሆረት ያደረገው ኤርትራውያን የኢሕአፓ አባላትን መግደል ላይ እንደነበረው ዓይነት ግለሰብ ነፍሰ ገዳይ «ከዋክብት» ብቅ ብቅ አሉ። እንደሸዋ ልውል ዓይነት ቊጥር የሌላቸው ሰዎች የገደሉ ሴት ነፍሰ ገዳዮችም ነበሩ። ባጭሩ፣ ቀበሌ ባጠቃላይ አሬጀች የሚዳብሩበት፣ ነፍሰ ገዳዮች የሚቀፈቀፉበት መሣሪያ (Machine) ሆነ። ግድያዎቹን ማርክሳዊ የቃላት ቅብ ቀባብቶ ተገቢ መስለው እንዲታዩ ለማድረግ መኢሶን አቢት ጊታዬ ብሎ ቀረበ። ውጭ የተማሩ የመኢሶን መሪዎችና አባላት ሴቶችን ከደፈሩ በሰይል የቊም ስቅል ካሳዩና ከገደሉ ያገር ቤቶችን ያልተማሩ ደናቊርትን ማን ሊወቅሳቸው ይችላል?

ባሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ቀበሌ ማለት የሚዘገንን ነገር ነው፤ ቀበሌተኛ መባልም ትልቅ ስድብ ነው።

ኅቡዕ ስኳዶች፤ የሰደድ ስኳዶችና የመኢሶን ስኳዶችም ነበሩ። የሰደድ ስኳዶች በአጠቃላይ መልካቸው ሲታዩ ወታደሮች የነበሩና በመጀመሪያ በኮሎኔል ዳንኤል በኋላም ራሱን የቻለ ነፍሰ ገዳይ በነበረው የደርግ አባል ለገሠ አሥፋው ይመሩ ነበር። መኢሶን፣ ቀበሌዎች ብቁነት የላቸውም ተብሎ የማይሣተፉባቸው ለልዩ ተግባራት የሚውሉ ስኳዶች ነበረው። መንግሥቱ ኃ/ማርያም በየካቲት ፲፱፻፸ ዓ.ም. ባደረገው በቢተ መንግሥት ውስጥ የተካሄደ መፈንቅል ባለ ሙሉ ሥልጣን ከመሆኑ በፊት እኒህ ስኳዶች የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን ዕቅዶች በሥራ ላይ እንዳይውሉ አደገኛ እንቅፋቶች ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ ባለ ሥልጣኖችን ይረሽኑ ነበር። ግድያዎቹ በኢሕአፓ ላይ የተመካኙባቸው አንዳንድ ጊዜያትም አልጠፉም።(11)

የሰደድ የመኢሶን የኅቡዕ ገዳይ ስኳዶች በሽብሩ ዘመቻ ውስጥ ሳት ያለ ሚና ተጫውተዋል።

በአውሬጃና በክፍለ ሀገር ከተሞች ውስጥ የተደገመው ይኸው ትዕይንት ሲሆን ለየት ያለ ነገር ቢኖር፣ ለግድያ የተቡ በደርግ ወይ በመኢሶን ቊጥጥር ሥር የነበሩ አርሶ አደር ማኅበራት (ልክ እንደ ቀበሌዎቹ ተመንጥረውና «እድተው») መታከላቸው ነበር።

የሽብሩ ዘመቻ እንደተራመደ ከልዩ ልዩ አውታራትና ከወሮበላ ቡድኖች በአረመኔነታቸውና በጭካኔያቸው (በአዲስ አበባ ላይ ስድ እንደተለቀቀው የግዲዮ ቡድን ዓይነት) ተመርጠው የወጡ ምርጦች በልዩ ልዩ የገዳይ ስኳዶች ተቧድነው ርኅራኄ የተለየው ዐመፅና ግድያ እንዲያካሂዱ አላፊ ሥልጣን ተሰጠቷቸው ነበር:: (12)

የሁኔታው አጠቃላይ ሥዕል፣ ደርግ ለሕግ የበላይነት ባዕድ እንደነበር ግልጽ አድርጎ ያሳያል። ተቃዋሚዎቹን ለመታገል በሕጋዊ አውታራት (ፍርድ ቤቶች ወዘተ...) ከመጠቀም ፈንታ ዋና ዓላማቸው ግድያ ብቻ የሆነ ሕገ ወጥ አውታራትን አቋቋመ። ቀበሌዎችና እስኳዶች እንዳሻቸው ይይዛሉ፤ ይገድሉማል፤ ፍርድ የለ፤ ጥያቄ የለ፤ ለግል በቀልም በሩ ክፍት ሆነ፤ የቀበሌ ዘበኞች በገንዘብ እየተዋዋሉ የመግደል ተደራቢ ሥራ ከማኅበታቸውም ጋር የራሳቸውንም የግል ጠላትና ወደረኛ ይገድሉ ነበር። ቀበሌዎች በስሕተት ቢገድሉ፣ ለደረሰው በደል መካካሻ ምንም የሚደረግ ነገር የለም፤ አጥፊዎቹ አይቀጡም። የንፁሐን መገደል እንደ ድንገተኛ አጋጣሚ የሚመጣ ሳይሆን እንደ አጠቃላዩ የሽብሩ ዕቅድ አካል ምን ጊዜም የሚጠበቅ የአዘቦት ነገር ነበር። ከቶውንም፣ የመኢሶን ካድሬዎች በወቅቱ ደጋግመው ይሉት እንደነበረው የሽብሩ ዓላማ ለማሸበር እንደመሆኑ መጠን መምረጥ ግለት ግቡን መሳት ነው፤ (ወይም መስሏቸው እንደሁ እንጃ) ዘግየት ብሎም ደርግ የነጻ እርምጃ ፕሮግራም የሚለውን አመጣ። ይህም እንደ ፈቀዱ እዚያው በዚያው ከስ ሳይመሠረት ወይም ታል ሳይጠየቅ የመግደል መብትን የሚሰጥ ነበር። በደርግ ቋንቋ እርምጃ ማለት ድምሰሳ፣ ግድያ ከማለት ሌላ ትርጉም አልነበረውም። አብዮታዊ እርምጃ፣ ቁራጥ ውሳኔ፣ የመጨረሻ እርምጃ፣ ነጻ እርምጃ ... ሁሉም ሞት፣ ርሸና፣ አካላዊ ድምሰሳ ማለት ነበሩ።

መንግሥት ራሱ ሽብርን የክብር ቦታ ሰጠው። የለየለት

የግድያ ተግባር እሠይ፣ በጀ ተብሎ ተሞገሠ። ከበታች ያሉት ወንጀል ፈጻሚዎቹ በዚያ ከንቱ ውዳሴ ምርቃና በደስታና በድል መንፈስ በሺዎች የሚቆጠሩትን በመግደልና በግረድ የሀገሪቱን ምርጥ (ጎሩያን) ዕውቅ ድንቅ ልጆች ያካተተ አንድ ትውልድ እንዳልነበረ አደረጉ። ሽብሩ ይህ ዲካህ ይህ መሰንህ የማይባል ለስት የሌለው ዓመፃ አድርሷል። ዋና አቢጋዞቹ ደርግና መኢሶን ሲሆኑ ሰለባ ሁኖ የቀረበው ሕዝቡ ነበርI በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ሲታይ ደግሞ ሀገሩቱ ባጠቃላይ።

ከእርከን አንድ

እስከ ቀይ ሽብር

«መንግሥቱን እውነተኛ አብዮታዊ አድርጌ እመሰደሞለሁI አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው አብዮትም እውነተኛ አብዮት ነው።»
ፊደል ካስትሮ (ከአፍሪካዚ መጽሔቶች ውስጥ ፓሪስ] ሚይ ፲፯] ፲፱፻፸፭ የተጠቀሰ)

የካስትሮው በእውነተኛ አብዮታዊ የተመራ እውነተኛ አብዮት የተራመደው በብዙ ሺህ የሚቁጠር አስከሬን አንጥሮ ነበር። ከንዚህም ውስጥ የባቲስታውን አምባገነን መንግሥት ለመገልበጥ ለተደረገው የኪዩባ አብዮት ጠንካራ ድጋፍ የሰጡ ይገኙበታል።

ከሽብሩ እመም አንድ (መስከረም ፲፱፻፷፱) እስከ መደበኛው ቀይ ሽብር (የካቲት ፲፱፻፷፱ የተከፈተው) ድረስ አምስት ወራት አልፈዋል። ከጫፍ ጫፍ ሽብሩ የተዳረሰባቸው አምስት ደም-ዘንብ ወራት ነበሩ።

ከጥቅምቱ የምስጢር ርሸናዎች በኋላ ወደ ውሩ መጨረሻ (in November) ላይ በይፋ የተነገረ ፱ የኢሕአፓ አባላት ርሸና ተከተለ። ጥቅምት ፳፫ ቀን (Nov. 2) 23 የሚሆኑ የኢሕአፓ አባላት አብዛኞቹ በመስከረም ታሥረው የነበሩ ምሁራን ተረሸኑI እንዲያም ሆኖ የተከሰሱት በክተማ የትጥቃዊ እርምጃ ውስጥ በመሣተፍ ነበር። በኢሕአፓ በኩል ግን ያን የመሰለ እርምጃ የተጀመረው በጥቅምት ነበር። ፳፫ቱም በሙሉ በቁጥጥር ሥር በነበሩበት ጊዜ ጭካኔ የተመላበት ሰይል የደረሰባቸው

ሲሆን፣ ሁሉም ማለት ይቻላል በውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የተጫ የትግል ታሪክ የነበራቸው ናቸው። ኅዳር ፱ (Nov.18) የተረሸኑት ፳፯ ቱም የተከሰሱት ከጥቅምት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ጀምሮ ትጥቃዊ እርምጃ ውስጥ በመሣተፍ ነበር። እሁንም እንደገና እዚህ የሐሰት ክሶች የመንግሥቱን ከጎደትና ጭካኔ የሚመሰክሩበት ሆኑ። ከሃያ ሰባቱ ጥቂቶቹ በሐምሌ-ነሐሴ ውስጥ፣ እንዳንዶቹ በጳጉሜን፣ አብዛኞቹ ኢሕአፓ ላይ መስከረም አንድ ቀን ጦርነቱ ልክ እንደታወጀ ነበር የተያዙት (13)።

ምንም እንኳ የደርግ ሬዲዮ የተረሸኑቱ ለፍርድ የቀረቡና የተፈረደባቸው፣ ፍርዳቸውም በደርጉ ሊቀ መንበር (በተፈሪ በንቲ) የፀደቀ እንደነበር የተነገረ ቢሆንም፣ እውነትነት አልነበረውም። ጉዳዩ ለተሰበሰቡት የደርግ አባላት በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ከኅዳር ፫ ቀን (Nov. 12፣ ጀምሮ ሌተና ኮሎኔል) በፍቅረ ሥላሴ ወግ ደረስ፣ በለገሠ አሥፋውና በተካ ቱሉ ቀረበ፤ ከሕግ እንጻር ሲታይ፣ የተመሠረተ ክስ አልነበረም፤ ጠበቆች አልነበሩም፤ የመከላከያ ክርክር አልተሰማም፤ መቼም ተከሳሾቹማ አልቀረቡም። መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሃያ ሰባቱ ላይ የክስ ዝርዝር አንበበና የሞት ቅጣት እንደፈረድባቸው ጠየቀ። ድምፅ ተወሰደ፤ 45 ለሞት ቅጣት ድምፃቸውን ሲሰጡ፣ 40 ተቃወሙ። ከተከሣሾቹ እንዳንዶቹ ከደረሰባቸው ሰይል የተነሣ ሕይወት ነበራቸው ለማለት የማያስደፍሩ ያው ተረሸኑ። እንድ እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ነጥብ፣ መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና ጓደኞቹ ፭፮ቱ ተከሣሾች በሙሉ ከ፭፭ ዓመት ዕድሜ በላይ እንደነበሩ አድርገው ለደርግ አባላቱ ማቅረባቸው ነው። (በመሠረቱ የደርግ አባላቱ ድምፅ ከመስጠታቸው በፊት የተከሳኞች ቁጥር ፭፮ እንደነበር እንጂ ማንነታቸውን አያውቁም ነበር) የሆነ ሁኖ ከ፭፮ቱ ፫ ብቻ ከ፭፭ ዓመት በላይ ሲሆኑ አብዛኞቹ ከ፲፰-፲፱ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነበሩ። ከሁሉም ትንሹ ባቢሌ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜው ፲፬ ዓመት ብቻ ነበር።

ከዚህ ተመክሮ በመነሣት መንግሥቱ ኃ/ማርያምና መኢሶን ምልአት በሌለው የፍርድ አሰጣጥና የደርግ አባላትን ድምፅ በሚጠይቅ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ከግለፍ ይልቅ አናርኪስቶችን ይበልጥ ለመገደል እርግጠኛው መንገድ በደረቅ ሌሊት፣ በምስጢር ወይም እዚያው በዚያው

እንደተያዘ መገደል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰው እንደነበር ጠቅሶ ግለፍ ያስፈልጋል።

ከጥቅምት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. እስከ የካቲት ፲፱፻፸ ዓ.ም. ግድያዎቹ ቀጠሉ። በጥቅምት መባቻ (Oct 9) ለቀበሌዎች ተጨማሪ ሥልጣን ተሰጥቶ ነበርና ርሽናው ጨመረ። ፀመው እድገት እያገኘ በሄደ መጠን ትላልቅና ትናንሽ ከተሞች ወደ ጦር ዓውድማነት ተለወጡ ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ በጥቅምት ውስጥ የኢሕአፓ የራስ መከላከል ስኳዶች ከ፲፱ እስከ ፲፱ የሚሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን፣ የፀጥታ ሰዎችንና ሌሎችም «ከሽብሩ ጋር አግባብ አላቸው» ተብሎ የተወሰንባቸውን ገድለዋል። በዚያኑ ጊዜ ደርግ በሺዎች የሚቁጠሩ ገድሏል።14 የደርግን የግፍ እገዛ በመቃወም በተደረገ በአንድ ሰላማዊ በሆነ ሠልፍ ብቻ ኅንደር ከተማ ውስጥ ከ54 ያላነሱ ሰዎች በጥይት ተገድለዋል። በአንድ የፀጥታ ባለ ሥልጣን ግምት (ደራሲውን ያነጋገረ) በጥቅምት ወር ውስጥ በተደረጉ የግታ ግድያዎች በትንሹ በየግታው ፵ ሰዎች ይገደሉ ነበር።

ወጣቱ በአብዛኛው የኢሕአፓ ደጋፊ ነው ተብሎ ይገመት ስለነበር ግፉ የተነጣጠረው እሱ ላይ ነበር። ሽብሩ በተጨማሪም የሠራተኛ መሪዎችን፣ በሲቪሉ አስተዳደር ውስጥ፣ በሕዝባዊ ማኅበራት ውስጥ፣ በቀበሌዎች ውስጥ በፖለቲካ ተባ ብለው የሚሣተፉትን ነጥሎ መታቸው። በወታደሩ በኩል የሕዝባዊ ንቅናቄውን ጭንቅላት በመቅላት መሪ ለማሳጣት፣ ድምፅን በትክክልና በሚገባ የሚያቀርቡለትን አንደበቶቹንና አደራጂዎችን ፀጥ ለማሰኘት ሆን ተብሎ የወጣ ፖሊሲ ነበር። በዚህ መንገድም ማንኛውም ወጣት ወይም ምሁር ታማኝነቱን ለመንግሥቱ የሚያረጋግጥበት አንዳች የሚያሳየው ነገር ከሌለው፣ ወይም የመኢሶን ወይ ደግሞ የሌሎች መፍቀሬ ደርግ ቡድኖች አባል ካልሆነ ዕጣው ርሽና ነበር። የመኢሶን ስኳዶች አባሎቻቸው ለመሆን ፈቃደኛ ያልሆኑትን ምሁራን የኢሕአፓ አባላት ባይሆኑም (መኢሶንም ልቡ እያወቀ) ለመገደል ይሆን ዕድል ተጠቅመውበታል።

ሽብር እዲስ አበባንና ሌሎች ከተሞችን ፈጥርቶ ያዛቸው፣ ቤተ ሰቦች ልጆቻቸው በንሲብ በሚሪጭ ጥይት ሲወድቁ በመመልከት ሁከት ውስጥ ወደቁ። በትክክል

ለመፍረድ ግን ደርግና የመኢሶን አባላትም በፍርሐት ተጨብጠው ቢሯቸው ሲሄዱ እንኳን ጠመንጃ ያነግቡ፣ መኖሪያቸውን ይቀያይሩ ወዘተ...ነበር። ኢሕአፓ ይገድለናል ነበር ፍርሐታቸው። ይልቅ በገፍ የገደለ የሚፈራው ፍርሐት ነበር ፍርሐታቸው። በመስፋፋት ላይ የነበረው የአጋዴን ጦርነትና ሽምቅ ተዋጊዎች ጉልህ በሆነ መንገድ መግፋታቸው፣ ኤርትራ ውስጥ የፀጥታው ሁኔታ መደፍረስ አጠቃላይ ሁኔታውን ይበልጥ የተወሳሰበ እደረገው። በሐምሌ ወር እነዚያ ከደርግ ወስጥ እንደገና ውስጣዊ እደሪጀት ለማድረግና የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን ሥልጣን ለመገደብ ያነሳሱት መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና መኢሶን እንዳፈተታቸው የሚወስዱት እርምጃ የት እንደሚወስዳቸው እንደገና ማሰብ እንዲጀምሩ እደረጋቸው። አብዛኞቹ እንደባቢሌ ኃ/ሥላሴ ያለውን የ፲፱ ዓመት ልጅ እንዲረሽን ድምፅ እንዲሰጡ በመንግሥቱ ኃ/ማ ተታለው የነበሩ መሆናቸው አብግኗቸዋል። በተጨማሪም የመኢሶን ሥልጣን እያደገ መሄዱንና ያለምንም ቁጥጥር የሚደረገውን የተቃዋሚዎችን ግድያ አግርረዋል።

ይህን ሁኔታ ለማስተካከል መንቀሳቀስ ቢጀምሩም እንደ ተለመደው አቅማሙ። መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና ሰደድ ውስጥ የነበሩት የቅርብ ጓደኞቹ ግን እንደዚያ አልነበሩም። በዚህን ጊዜ «የኢሕአፓ አባላት ወይም ደጋፊዎች» ብለው የለዩአቸውን ደርግ ውስጥ የነበሩ «ወላዋዮችን» ለመከወን ጊዜው እንደደረሰ አመኑበት። የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ምስጢራዊ ቡድን የእርምጃ ዕቅዱን ለመትለም ምስጢራዊ ስብሰባዎች እደረገ። በመኢሶንና በወዝ ሊጉ ሠናይ ልኬ ወሳኝ እርምጃ እንዲወሰድ ተገፋ። «በሮቱን ወታደሮች ድርጅት። ውስጥ በገዙዕ ይሠሩ የነበሩ መሪጉናኖች ስለ ምስጢራዊ ስብሰባዎች ወሬ ተናፍሰላቸው ዕቅዱን በይፋ በጋዜጣቸው አወጡት።15 ሆኖም እነተፈሪ በንቲ የወሰዱት የመከላከያ እርምጃ አልነበረም፤ እንዲያውም እንደሚባለው ሁለቱም ተፈሪ በንቲና ሻለቃ ሞገሥ በተናጠል ከመንግሥቱ ጋር ፈት ለፈት ተገጣጥመው «እኛን ለመከፋፈል የተደረገ የአናርኪስት ውሸት ነው፤ የዘለዓለም ጓደኞችሁ ነኝ፤ ከናንተ በፊት እኔን ያስቀድሙኝ» ብሎ ተፈጥሞላቸዋል። ሁለቱም በኮሎኔሉ ታል የተረጋጉ ይመስላሉ።

የተፈሪ በንቲው ቡድን፣ የምስጢር ርሸናዎች እንዲጀረጡ፣ የመኢሶን የግድያ እርምጃዎችና ሥልጣን

እንዲገደብ፣ ኢሕአፓን የሚያስገባ የሕብረት ግንባር ፖሊሲ እንዲወጣ ገፉ። በነተፈሪ በንቲ አመለካከት የጊዜው ዋነና ጠላቶች፣ በሱዳን የሚደገፈውና ጎንደር ውስጥ እየተስፋፋ የነበረው የቀኝ ክንፍ የሆነው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃብረትና በዚህን ጊዜ መደበኛ ጦሩ ከአጋዴን ሽምቅ ተዋጊዎች ጎን ይታይ የነበረው ሶማሊያ ነበሩ። ይህ ለመንግሥቱ ኃ/ማሪያምና ለመኢሶን የአባሪ ተባባሪ ንግግር ነበር። አንድ የመኢሶን መሪ በጓላ በጥር ወር (Jan 29) አብዮት አደባባይ ላይ በተደረገ ሕዝባዊ ስብሰባ እንደተናገረው፣ «የሩቅ ጠላትን ለመውጋት መጀመሪያ የቅርቡን ጠላት ማስወገድ ያስፈልጋል» በሌላው አንጋገር ኢሕአፓን ማጥፋት የሶማሌን ወረራ ለማቸነፍ «ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት» እንዳለውና መሟላት እንዳለበት አስፈላጊ ሁኔታ ተደርጓ ቀረበ።16

የነተፈሪ ሞገስ ቡድን በዚያን ጊዜ መንግሥቱ ኃ/ማ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ሥልጣኑ ቢኖራቸውም አቅማሙ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የመንግሥቱ ኃ/ማ ሰደድ ስኳዶች፣ እንደገና በተዋቀረው የደርግ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ አባል የነበረውንና መንግሥቱ ኃ/ማሪያምንም ይታወም የነበረውን ሻለቃ ሚካኤል አስገዶምን ገደሉ። አንድ የተወሰነ ጊዜ ላይ ሻለቃ ሞገስና ሻምበል ዓለማዩሁ በሰደድ ስኳዶች ከታቀደ ግድያ አስቀድመው ወሬ በማግኘታቸው ሊያመልጡ ችለዋል። ባጭሩ ለነተፈሪና ሞገሥ ቡድን መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና መኢሶን ሊያጠፏቸው እንደተነሡ ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባ ነበር፤ በደንብም ግልጽ ነበር። ግን ለሕጋዊ አሠራር ምንም አክብሮት የሌላቸውን መንግሥቱ ኃ/ማርያምና መኢሶንን ለመታገል፣ ዘገምተኛ በሆኑ ሕጋዊ መንገዶች መንቀሳቀሱን ግራ በሚገባ ሁኔታ ሙጭጭ ብለው ያዙ። ለነገሩ ተፈሪ በንቲ ከባለቤቱ ጋር በዚያን ጊዜ መቀረቡ የነተፈሪን ቡድን ግር የሚል አመለካከት ለመግምገም ይረዳ ይሆናል። ተፈር በንቲ እንደሚሞት አውቆ ግን ለመከላከል ምንም እርምጃ አልወሰደም ማለት ይቻላል።(17)

ጥር ፳፩ ቀን (Jan. 29) ተፈሪ በንቲ ብዙ ሕዝብ በተገኘበት ስብሰባ ላይ በአዲስ አበባ አብዮት አደባባይ ንግግር አደረገ። መንግሥቱ ኃ/ማ ለማንም ግጎድ በሆነበት መንገድ ያልተገኘበት የሕዝብ ስብሰባ ነበር። ተፈሪ በንቲ «ተራማጆችን ሁሉ የሚያቅፍ የኅብረት ግንባር» እንዲፈጠር

ጥሪ እደረገ። «አናርኪስቶች» ላይ ይሠነዘር የነበረውን ዘለፋ በሙሉ ከንግግሩ ውስጥ ሆን ብሎ ያስወገደው በመሆኑ ለኢሕአፓ ጥሪ እንደማድረግ ተደርጎ ተተረጐመ። የመኢሶን መሪዎች በይፋ በመጨስ፣ «ኢሕአፓ ሊያስከትል ስለሚችለው ጥፋት የመናቅ እደጋ» በተንጨረጨረ ድምፅ አስጠነቀቁ። በታላት ዱላም ብቻ አልተወሰኑም። ጥር ፳፭ ቀን (Feb. 2) በማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፥ በነገደ ጎበዜ (አሁን በስደት ምዕራብ አውሮፓ የሚኖር) የሚመራ ልዩ የመኢሶን ስኳድ ስድስት ኪሎ በሚገኘው (ዋናው ካምፓስ) የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በርገዶ በመግባት በርካታ ተማሪዎችን ገደለ፤ ሌሎች ብዙዎችንም አቁሰለ። የመንግሥቱ ኃ/ማሪያም ሰደድ ስኳዶች ዋናው ከተማ ውስጥ ግድያ በማካሄድ ተጠምደው የነበር ሲሆን አብዛኞቹ በመንግሥቱ ሬዲዮ በኢሕአፓ እንደተፈጸሙ ተደርገው ይወሩ ነበር።

ጥር ፳፱ ቀን (Feb 3) ተፈሪ ባንቲና ሌሎች፥ በዋና ከተማይቱ ውስጥ እየተበላሸ ስለሄደው የፀጥታ ሁኔታ ለመወያየት ተሰበሰቡ። በሞኝነትም እነሆ መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና ዓደኞቹ ባጠመዷቸው ወጥመድ ውስጥ ወደቁ። ተፈሪ በንቲ ከቢሮው ደጃፍ ላይ የነበሩት ዘበኞች መቀየራቸውን እንኳ ተገቢ ክብደት አልሰጠውም። ታዲያ መንግሥቱ ኃ/ማ ከውጭ ሆኖ ሲጠብቅ (ብረት ለበስ መኪና ውስጥ ሁኖ) የሱ ሰደድ ስኳዶች ተፈሪ በንቲን፣ ምገሥ ወ/ሚካኤልን፣ አሥራት ደስታን፣ ጎሩይ ኃይለ ሥላሴን፣ ዓለማየሁ ኃይሌን፣ ተፈሪ ደንቱንና ኃይሉ በላቡን ያዙ። በመንግሥቱ ኃ/ማ ቡድን ላይ ወሳኝ እርምጃ እንዲወስድ እነተፈሪ በንቲን ይጐተጉት የነበረው ኝምበል ዮሐንስ፣ ተፈሪ በንቲ ቢሮ ደጃፍ ላይ አዳዲስ ዘበኞች በተመለከተ ጊዜ አንድ ነገር እየተካሄደ መሆኑን ጠረጠረ። ቶምሶን ጠመንጃውን ይዞ መንግሥቱን መፈለግ ጀመረ። ግን በሱ ፈንታ ያገኛቸው ሠናይ ልኬንና ዳንኤል አስፋውን ነበር። ሁለቱንም ገድሎ ከባድ የተዘጋ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ አንድ አሥራ ሁለት የሚሆኑ የመንግሥቱ ኃ/ማሪያምን ታማኞች ከገደለ በኋላ ሞተ።

መንግሥቱ ወዲያውኑ ተፈሪ በንቲ፣ ምገሥ ወዘተ ... እንዲረሽኑ አዘዘ፤ ተደረገም። መፈንቅለ መንግሥቱ ተሳካ። መንግሥቱ ኃ/ማ እሥልጣን ቁንጮ ላይ ቁጠ አለ። ሶቪየት ኅብረት ወዲያውኑ መንግሥቱን እውቅ አድራጉቱን እንደ

«ፀረ አብዮተኞች ላይ የተወሰደ አብዮታዊ እርምጃ» አድርጎ አወደሰ። መንግሥቱ ራሱም የተረፀኑትን የደርግ አባሎች ከኢሕአፓና ከሌሎች አድኃርያን ጋር ተመሳጥረው አብዮቱ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ሲያቅዱ ነበር ብሎ ከሰሳቸው።

ጥር ፳፯ ቀን (Feb. 4) ተበሌዎች ሕዝቡን አሁንም ገና ለሰላማዊ ሠልፍ እንዲወጣ አዘዙት። ያሁኑ ሙውጣት ግን በመንግሥቱ ኃ/ማሪያምና በባለ ድሎቹ ሕዝብ አደራጅ ጽ/ቤት ውስጥ በነበሩት የመኢሶን መሪዎች እንዲደሰኩርለት ነበር።

«አብዮቱ ከመከላከል ወደ ማጥቃት ተሸጋግሯል» ብሎ መንግሥቱ ኃ/ማ እምቢረቀ። «ሽብሩን ወደ አናርኪስቶቹ ሠፈር እንወስደዋለን» ብሎ ማለ። «አይ ሽብር» ብለው ሁሉም ጮሁ። ዐመፃና ግፍን ወደ አዲስ አረመኔያዊ ደረጃ ለማምጠቅ የተደረገ ግልጽ ጥሪ ነበር፤ እናም «ቀዩ ሽብር» ተወለደ፤ ወይም ዳግሚት ልደቱን አገኘ። ሽብሩ ከደርግ ጋር አብሮ ተወለደ። በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ባለቀ። በ፲፱፻፸ ዓ.ም. ሙሉ እድገቱን አወጀ። ኢሕአፓ አሻፈረኝ ብሎ ባይጋተረው ኖሮ ወይም ወደከተማ ትጥቃዊ እርምጃ ባይረግመድ ኖሮ፣ ደርግ በመፁን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ባላሸጋገረው ነበር የሚል የደርግ ኢጋፋሪዎችን የተመጻደቀ ሚሜታ እንሰማለን። ለደርግና ለሱም ባደሩ ኢጋፋሪዎች ዘንድ ሁሉም ነገር፣ የኢሕአፓን «ነጭ ሽብር» ለመከላከል «አብዮቱ» የወሰደው ሕጋዊ መከላከል ነው ተብሎ ይቀርባል። ለሌሎች ደግሞ፣ ደርግን ሙሌነት ባለው መንገድ ለሚከላከሉለት፣ «የኢሕአፓ የሽብር ፖሊሲ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥትን አዲሱን የግፍ እመም እንዲያውጅ የገፋፋው መሆኑ ልናመልጠው የማንችል መደምደሚያ ነው" በሚል ይቀርባሉ።[18] እንደገና «ተተንኩሰ» ይሉናል፤ ሰለባ ሆነው የወደቁቱ ጮኽት ተውጦ በመተንኩሰና በራሳቸው ላይ ግፍ በመጫን እንሆ እየተከሰሱ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ምን ይሏል? የተጠማዘዘ አመክንዮ (ሎጂክ) መግለጫ እንጂ።

ባለፉት ገጾች ጎላ አድርገን ለማሳየት እንደሞከርነው ደርግ ወደግፍ ተግባር የተሰማራው ገና ከቡቃያው ነበር። በማንኛለውም ዓይነት መንገድ ኃይልን የተመረኰዘም ሆነ በትጥቃዊ መንገድ ግፍጫ ከመጀመሩ በፊት ኢሕአፓ ላይ፣

ሠራተኛ ማኅበራት ላይ፣ ተማሪዎች ላይ፣ ምሁራን ላይ፣ እንዲሁም ሰላማዊ ተቃውሞ ባሰሙት ላይ ግልጽ የሆነ ጦርነት ዓውጆ ነበር። በመስከረም ብቻ አዲስ አበባ ውስጥ ኢሕአፓ እንዲት ተይት ከግሎኼ በፊት በደርግና የመኢሶን ሽብር በመቶዎች የሚቁጠሩ ታጋዮች ተጨፍጭፈዋል፤ አስከሬናቸውም በገፍ መታበር ውስጥ ተደፍቷል (ቀደም ብለን እንደገለጽነው አንዳንዱን አስከሬን ጅቦች አውጥተውት ተመግበውት ነበር)። ለተቃዋሚ ወገኖች፣ ያለምንም ሕግና ርኀራኄ በጅምላ እንደሚረሽኑ ግልጽ ነበር እንደገና ምርጫው «በሰላም» መሞት (ፀጥ ብሎ ያለምንም መከላከል) ወይም መታገል ሆነ።

ከዚህም በላይ «ከቀይ ሽብሩ» ወቅት ቀደም ብሎ በሺዎች የሚቆጠሩ በመንግሥቱ ተገድለዋል፤ ከዚህ ቁጥር የበለጠው ደግሞ እሥር ቤት ውስጥ በሰይል ቁም ስቅላቸውን እያዩ በርግጥ የማይቀርላቸውን ሞት ይጠባበቁ ነበር። የኢሕአፓ የትጥቅ እርምጃዎች ምንም እንኳ ወደከተማ ትጥቃዊ እርምጃ መሸጋገሩ ስሕተት ነበር ብሎ ምንጊዜም መከራከር ቢቻልም፣ በምንም ዓይነት ከደርግ ግድያ ጋር የሚወዳደር አልነበረም። ያም ሆነ ይህ እኒህ ከስንት አግርጠ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ ደርግ ፀጥታውን ወደአረመኔያዊ ደረጃ ከፍ እንዲያደርገው ገፋፉት ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር መሣለቂያ መሆን ነው። ደርግ «የፀጥታ ዝንባሌ» ያለው ብቻ ሳይሆን አውሬነቱን በግያወላውል ሁኔታ አረጋግጧል። ሽብሩን ለመግታት የፈለጉትን የደርግ አባላት ድምጥማጣቸውን ለማጥፋት መንግሥቱ ኃ/ማሪያምና ኅብር አበሮቹን የገፋፋው የኢሕአፓ ፀጥታ አልነበረም፤ በገፍ በመግደል ማንኛውንም ነገር ልክ ለማስገባት የነበራቸው ጠንካራ ፍላጎትና ቁርጥ ሐሣብ እንጂ። እንተፈሪ በንቲ መንግሥቱ ኃ/ማ ወደ ፍጹም ሥልጣን በሚጓዝበት መንገድ ላይ፣ ኢሕአፓንም «ለማጥፋት» በነበረው ቁርጠኝነት ላይ እንቅፋት ነበሩ። ስለዚህም በሚያውታትና በተራቀቀባትም እንዲቱ መንገድ – በርሸና – አስወገዳቸው። እነሱን ካስወገደ በኋላ ለርሱና ለመኢሶን በቀደዱት ደም ባጥለቀለቀው መንገድ ለመቀጠል ጥርጊያው ከፍት ሆነላቸው። ይኸውም መንገድ ከመስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. በፊት የተቀየሰና በዚሁ ዓመት ግን ቡራኬውን የተቀበለ ነበር። ለመሆኑ ኢሕአፓ ከመታገል ተቆጥቦ ቢሆን ኖሮ በደርግ በኩል ፀጥ ይቀር ኦሯልን? ይህማ ሆኖ ቢሆን መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ኢሕአፓ ላይ ጦርነት

ማወጅ ባላስፈለገም ነበር። ይህ የማይታበል ነው፤ «ሽብርተኛ» እንደሚለው ዓይነት ስሜት ላይ የሚደውሉ ቅጥያዎች መለጠፍ የደርግን ወንጀሎች ለመቀነስም ሆነ ተጠያቂነቱን ለማሳነስ እይችልም። በመጨረሻም የደርግን እርምጃዎች በበጎ ዓይን የሚመለከቱትንና ኢሕአፓን የሚነቅፉትን ትምህርት የጠለቃቸው የውጭ ሰዎችን ጥያቄዎች መጠየቅ ይፈታተናል። መንግሥታዊ ሽብርን እንዲት መታገል ይቻላል? ማታ በር ሲቈፈጭ መከረት በርግጥ መሞትን የሚያስከትል በሆነበት ሁኔታ እንድ ሰው ማድረግ የሚችለው ምንድር ነው? መያዝ ማለት፣ ጥፋት፣ ሰይል ብሎም ርሽና በሆነበት ሁኔታ እንዲት እድርጎ መያዝ ይመረጣል? ሚዛናዊ አስተሳሰብና ሰብአዊነታቸውን ካጡ ገዳዮች ጋር ማን በቀኖ ነገር መከራከር ይችላል?

ሥልጣኑን ለማደላደል ደርግ የነበሩት መሣሪያዎቹ ፀመፅና ሽብር ነበሩ። «ቀዩ ሽብር» እንደሚመጣ ታውጧል። ባንድ በኩል ሲታይ ሽብሩን ማስቀረት ይቻል የነበረው ኢሕአፓና ሕዝቡ መንግሥቱን መታወግቸውን አቀመው ቢያጉነብሱለት ነበር። ይህ ደግሞ በሚመለከታቸው ዘንድ የተወገዘ የባሪያ ምርጫ ሆነ።

፭

አሻቶቹ

«መንግሥቱ እንደ ሌሊን ሁሉ ሶቪያሊዝምን እገራው እንዲተበለው ለማስገደድ ወደኋላ ካለማለቱም በላይ በካድሬ አመራር ሰውነት በማመን በተራዘመ ሕዝባዊ ትግል ውስጥ የሚወለደውን ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ለመጠበቅ ፈጽሞ ፈቃደኛ አልነበረም። ስለዚህም (መንግሥቱ) የራሱን ሥልጣን ወደ ማጠናከርና በደርግ ውስጥ ያሉትን ጠላቶቹን ወደ ማስወገድ ተራመደ ...»

ፒተር ሽዋብ (1981) ማርክሲስት
ገሸርንመንትስ ኢ ወርልድ
ሰርቪይ ቅጽ 2 ለንደን ገጽ 303-304

«የሚገርመው ነገር ለምን (ማንም ማን) ለኢሕአፓ ቀን መስጠት እንደነበረበት ነው። አብዛኞቹ ውጭ አገር የተማሩ ከመካከለኛው መደብ የመጡ ግራ-ክንፈኞች ነበሩ። ከ(ደርግ) ጋር ስምምነትን አበክረው እምቢ አሉ ... በጦር ኃይሎች አማካይነት የተገለጸው በጉብረተሰባቸው ውስጥ የመጣው እድገት ምን ያህል ትርጉም እንደነበረው መገንዘብ አልቻሉም።»

ሬችድ ጎት በጋርዲየን ዊክሊ
ፌብርዋሪ 14፣ 1982

«መኢሶን ቀኝ መንገደኛ፣ ሽንፍተኛ ሥልጣን ያለከረው ድርጅት ነው።
ደርግ፣ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.

ደርግ፣ በአንድ በኩል «ቀይ ሽብር»፣ በአንጻሩ ደግሞ «ነጭ ሽብር» የሚል ዘይቤ ይዞ ሲመጣ በትግሉ መድረክ «የአባትነቱን» ቦታ ይዘው በነበሩት መካከል በትክክል ልዩነታቸው ምን ነበር? የሚለው ብዙዎችን ያደናገረ እንደመሆኑ መጠን ትንሽ ወጣ ብሎ በአብዮቱ አዲስ «ልውጥ እነጋገር» የተሸፋፈነውን፣ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኋሀን «አቫቶቹ» ልዩነት ለመግለጽ ጳሰስ አድርጎ ማለፍን የሚጠይቅ ሆኗል።

ኮሚኒዝምን ከመቃብሩ ሄደው ለመቀስቀስ» (ሐውልትም ሊያሰሩለት ብለን እሁን ማከል እንችላለን) ተገደዱ። በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. አንድ የደርግ አባል ለዘግች ተግሪዎች «ጠላያችሁን ካሳመራችሁ ኮሚኒዝምን እናውጅላችኋለን» ብሎ መናገሩ ይታወሳል። ሚካኤል ገብረ ንጉሥ የተባለ የቀድሞ የደርግ አባል ከ፲፱፻፷፮ – ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ይደረጉ የነበሩ የደርግ ስብሰባዎች እጀጉን እንዳልነበራቸውና ሥራዬ ብለው ይዘውት የነበረው በሳምንቱ ውስጥ በዲሞክራሲያ ላይ ተጽፎ የወጣውን ማውጣት ማውረድን እንደነበር መግለጡ ይነገራል።

ቅጥራቸው የማይናቅ ጸሐፊዎች (በረከት፣ አዲስ ሕይወት ወዘተ...) ኢሕአፓና መኢሶን፣ ሥልጣን የያዙትን ወታደራዊ መሪዎች በመጉተትና በመግፋት (በማዋከብ) እደናግረዋቸዋል ሲሉ ስሞታ አቅርበዋል። ለኢትዮጵያ ዕውነታ መስከራቸው ያፈጀና የደበዘዘ ትዝታቸው የነበረ፣ አንድ ነባር ኢትዮጵያዊ ስደተኛ መኢሶንና ኢሕአፓን በኢትዮጵያ አብዮት ፊት እንደተደነቀረ «ሁለት ራስ ያለው አንጻች አርዌ (ሃይድራ)» አድርገው አስከመሰል ደርሰዋል። (ደርግ ቅዱስ ጊዮርጊስ መሆኑ ነው?)[1] ባለፉት ገጾች ባጠቃላይ መንገድ የአንዲህ ዓይነቱን መደምደሚያ ፉርሽነት ለማሳዬት ሞክረናል። ደርግ ላይ ደጎና ተጽዕኖ የነበረው መኢሶን እንኳ በባህርዩ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ደርግን ገፈኛ በማድረግ ረገድ ሊወቀስ አይችልም። የመኢሶን ስሕተቱ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት ከደርግ ጋር የግበር የተሳሰተ ፖሊሲ መቀየሱ ላይ ነበር። ደርግና መኢሶንን በዶክተር ፍራንከንሰቴይንና በሞራቱ እንጻጽሮ ማየት አይቻልም፤ ደርግ በባሕርዩ የነግው ሞራቅነት በመኢሶን አድርባይነት ጉልምሶ አረመኔና ምሕረት የለሽ የሆነ ፍጡር ተቀምሮ የወጣ ሲሆን፣ በመጨረሻ በጉልበት የሳቀው ሞራቅ፣ ደርግ፣ ደካማውን መኢሶንን ውጦት አረፈ።

የሆነ ሁኖ ባጠቃላይ ግራው ወታደራዊ መኩንኖቹ ላይ ተጽዕኖ እንደነበረው ጥርጥር የለውም። ደርግ እስኪያቅለሸልሽ ድረስ እየተጠቀመባቸው የመጣው የአብዮቱ ቃላትና ዘይቤዎች ግራው ያበረከታቸው፣ ወይም በትክክል ለማስቀመጥ ከግራው የተወሰዱ ነበሩ። ደርግ ወሮታውን የግሉ ሊያደርገው የሞከረበት ተራማጁ የመሬት ማገር ሕግ እንኳን የረቀቀው ከእንዱ ወይም ከሌላው የግራ ድርጅት ጋር (መኢሶንና ኢሕአፓንም ጨምሮ) በተያያዙ ምሁራን

ነበር። ባጠቃላይ ደርግ በግራው ተጽዕኖ ውስጥ ነበር፤ እንደገና በትክክል ለማስቀመጥ በላ ትኩረቱን ግራው ይዘበት ነበር። ደርግ ቀደም ሲል ማርክሲዝም ላይ ያወረደበትን («ርካሽ የውሎ ርዕዮተ ዓለም» ዓይነቱን) ለከፋ መልሶ መዋጥ የግድ ሆንበት። ያ ሁሉ ቅጥፕት ቀረና ከግራው መጥቆ ለመገፕትና እያደገ የመጣባቸውን ተቃውሞ ለመበረዝ «ሊኒንን ከመቃብሩ ሄደው ለመቀስቀስ»

ጊዜ ምን እንደሚሉ የሚገቡት አልነበሩም። አናርኪስት የሚለው ቃል እንኳ ፅውቀት ሊታደሉት ለጥቂቶች በስተቀር ለሠፊው ሕዝብ ምንም የሚሰጠው ስሜት አልነበረም።

ኢሕአፓና መኢሶን ለምን እንድነት አልፈጠሩም ብሎ እዩዩ ማለቱም ዋጋ የለውም። ከፍፍሉ (ንፍቀቱ) ከየካቲት አብዮት ቀደም ብሎ የተፈጠረ፤ ልዩነታቸውም መሠረታዊ ነበርና። ስለዚህም ነው ለመቀራረብ የተደረገው ሙከራ (ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. በፊትም በኋላም በአዲስ አበባ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.) የከሸፈው። ስለ ደርግ ስለ መኢሶንና ስለ ኢሕአፓ ብዙዎች ያቀረቧቸውን የተሳሳቱና የተዛቡ ድሑፎች በመልክ በመልካቸው ለማድረግ በትግሉ ውስጥ ወበይት ሚና የነበራቸውን እኒህን «አቫቶቹ» ቀረብ ብሎ ማየቱ አስፈላጊነት አለው።[1]

ደርግ[1]

ተረት እንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ይፈጠራል፤ ተረት የሚፈጥሩ ደግሞ አጥጠው አያውቁም። «እሱ ብቻ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ አካል» (ይለዋል ሽዋብ) «አብዮትን ከላይ ለማካሄድ የፖለቲካ ብቃት ያለው» (ይሉታል ሃሊዴይና ሞሊኒ) «ፈውዳሊዝምን እንኩታኩቱ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ የሚችል እሱ ብቻ የሆነ ኃይል» (ይለዋል ኮርሊኮቭ) በነዚህ ላይ ደግሞ የለርነትን፣ የነአታዊይን፣ የቪ.ቮ ኤ.ጂ. ስቴይነርና ከምዕራብ ምሥራት አውሮፓ መንጋ የኮሚዩኒስት ፓርቲ መሪዎችን በነሲብ የተቸሩ የዚሁ ዓይነት መግለጫዎችን ማከል ነው። ያን ጊዜም፣ በታሪክም ሆነ በወቅቱ ለዲሞክራሲያዊነቱና ለአብዮታዊነቱ ፀዓዳ አበባ የመሰለ ጉድፍ ያልነካው ታሪክ፣ የሚመሰክርለት የደርግ ምስል ብቅ ይላል። በሂደት ውስጥ ደርግን በስም ብቻ የሚኖር፣ ልብ ወለድ ያደረገውን፣ ወደሪኖ የሌለው ሁኖ ብቅ ያለውን በእካል ንዑስ የሆነ አምባገነን ኮሎኔሉንም እንደሚጠበቀው ይኸው ተረት ይጠቅሰዋል። እውነታው የማይታወቅ ቢሆን ኑሮ ተረት ፈጣሪዎቹ ምንኖ በፈንጠዙ ነበር።

፩ደ፰ አባላት የነበሩትና ደርግ ተብሎ ዓለም አቀፋዊ ታዋቂነትን ያገኘው አካል በመሠረቱ በጦር ኃይሎች ውስጥ የተቋቋመ የመጀመሪያው አስተባባሪ ኮሚቴ አልነበረም። መጋቢት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዳልካቸው መኩንን በትርብ ጓደኛው በአየር ወለዱ ኩሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰግ ሊቀ መንበርነት የሚመራ አስተባባሪ ኮሚቴ ይመሠረት ዘንድ ሁኔታውን ያመቻቸው እሱው ነው። ሌላ በኮሚቴው ውስጥ ዋነኝነት የነበረው መኩንን፣ ጥበበ መንክር ሲሆን የዓለም ዘውድ ምክትል ደግሞ ጄኔራር ኤር ክራፍትስ ማን ገርግ ፍሥሐ ነበር፤ የኮሚቴው አባላትም ከሸ ያነሱ ነበሩ። የዓለም ዘውድ ኮሚቴ የተቋቋመው የእንዳልካቸውን ከንድ በጦሩ ላይ ለግጠናከር ሲሆን ለረጅም ጊዜ ግን የሚሠራ አልሆነም። በመሠረቱ ሚያዝያ ላይ ብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽን በመከላከያ ሚኒስትሩ በዐቢይ አበበ (መሥፍንም ጀኔራልም በነበረው) ሥር ተቋቁሞ ነበር። የብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽኑ ፴ የሚሆኑ አባላት የነበሩት ሲሆን፣ ከጦር መኩንኖች (በኋላ የደርግ አባል የሆነው ሻለቃ ሚሳይ ሀብቴና ፋንታ በላይም የዚህ ኮሚሽን አባላት ነበሩ) ከፀጥታው ክፍልና ከትምህርት ሚኒስትር ጥቂት ሲቪሎች ነበሩበት። የብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽኑ ዋናው ተግባር በጦሩ ላይ ክትትል ማድረግና ራሙድ ብለው የሚሄዱ ተቃውሞዎችን ማክሸፍ ሲሆን ከዚሁም ጋር የተማሪዎች ሰላማዊ ሠልፎችንና በሕዝቡ የሚደረጉትን የሥራ ማቆም አድማዎችን መፍታትም ሌላ ተግባራቸው ነበር።

ደርግ እንዲመሠረት ያደረገውን ሁኔታ በውል ለመጨበጥ ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን በተቋቋመበት በዚያን ወቅት ወታደሮች ከሞላ ጉደል ተረጋግተው እንደነበር (የደሞዝ ጭማሪ ካገኙ በኋላ) መረዳቱ አስፈላጊ ነው። በዚያን ጊዜ ግን በየአውራ ጉዳናው የሚደረጉ የተማሪዎች ሰላማዊ ሠልፎች እየተጋጋሙ፣ የሳብ አደሮችና የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ እየቀጠሉ እንደነበሩም መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። የሥራ ማቆም አድማዎቹና ሰላማዊ ሠልፎቹ ወታደሮቹን በ«ከህደት» ወነጀሏቸው፤ እንዳልካቸውም በዚያኑ ጊዜ በየጦር ሠፈሩ እየዞረ ጦር ሠራዊቱን ለመቆጣጠር ያደርግ በነበረው ጥረት ለተመረጡ መኩንኖች ገንዘብ ይሸጉጥ ገባ። በእንዳልካቸው አድራጎትና የብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽኑም እያካበተ በሄደው ሥልጣን ተራማጅ መኩንኖች ተደናገጡ። በመሠረቱ ብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽኑ አድማዎችን ለመበተን መፍትሔ አድርጎ የወሰደው በኃይል መጠቀምን ሲሆን ሁኔታውን «ይበልጥ ፈርጠም ብሎ» ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ እንዳልካቸውን የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እንዲያውጅ ጠየቀ። የእንዳልካቸውን አካሄድ

የተጠራጠሩ መኰንኖችም በምስጢር እየተሰባሰቡ ነበር። ለምሳሌ ሻለቃ ተፈሪ ተክለ ሃይማኖት (በኋላ ከኢጂን ገብቶ ውጊያ ላይ የሞተ) ሌሎችም የሐረር አካዳሚ ምሩቆች ከአዲስ አበባ ወጣ እያሉ ሚካ ውስጥ ምስጢራዊ ስብሰባ ያደርጉ ነበር።

ሁኔታው ይቀጣጠል ዘንድ ከብሪቱም ያቀበሉት ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው ነበሩ። በአንዲት ታሪክኛ በሆነች ወርብ ዕለት ወደ ሰኔው መጨረሻ ላይ ሚጂር ጀኔራል አሰፋ ደምሌ ከቢተ መንግሥት ወደ መከላከያ ሚኒስትሩ ደወለ፤ ስልኩን የተቀበለው ኮሎኔል እምቢበል አየለ (አሁን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል) ሲሆን በጊዜው መከላከያ ሚኒስትሩ ወጥቶ ስለነበር ለመከላከያ ሚኒስትሩ ከንጉሡ የተላለፈውን መልእክት ተቀበለ። ንጉሠ ነገሥቱ «የኮንጎ ዘማቾችን» ለመቀበልና ለመነጋገር ፈልገው ኑሯል። የኮንጎ ዘማቾች እንደሚታወቀው የተባበሩት መንግሥታት ጦር አካል ሁነው ኮንጎ የዘመቱና የተባበሩት መንግሥታት እንዲከፈላቸው የሰጠውን አበል እየጠየቁ የነበሩ ወታደሮችና መኰንኖች ነበሩ። ወደታረሱ እንመለስና፣ መልእክቱ ተላለፈ። ዘማቾችም በሳጂን ሚጂር ባሻ እየተመሩ ተንጋግተው ወደቤተመንግሥቱ ሄዱ። ንጉሠንም ተገናኙ። እንደከፋቸው በግልጽ የሚነበብባቸው ንጉሥም «ጉዳያችሁ በኮሚቴ እየተጠና ነው፤ ስለዚህም ታገሡ፤» በማለት ወዲያውኑ አሰናበቷቸው። ዘማቾችም የተለመደውን «ግርማዊ ቀ.ኃ.ሥ. ለዘለዓለም ይኑሩ» የሚለውን ጮሁ፤ ግን ቀዝቀዝ ያለ ነበር። ከቢተመንግሥቱ እንደወጡም አንዳንዶቹ ንጉሡ «ምንም ባያዳርጉላቸው» ያን በጎ ምኞች የሚገልጽ ጮኽት እንዲጮሁ በማዘዙ ሳጂን ሚጂር ባሻ ላይ ተናደዱበት። ከዚያም ወደጠቅላይ ሚኒስትሩ ሂደው ለመገናኘት ፈለጉ፤ ግን ላጂን ሚጂሩ አሻፈረኝ አለና በምክትሉ መሪነት ወደእንዳልካቸው ሄዱ። እሱም ሞቅ ያለ አቀባበል አድርጎላቸው፣ ወዲያውም እርምጃ እንደሚወሰድ ተስፋ ሰጣቸው፤ እያመሰገኑም ወደ፱ኛው ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ አመሩ።

የኮንጎ ዘማቾች አስተባባሪ ኮሚቴ ለማቋቋም ሐሣብ ነበራቸው፤ ይህንንም እንዳልካቸው አያውቅም ነበር ማለት ያዳግታል። ጠ/ሚኒስትሩ ቀደም ሲል የዓለም ዘውድ ኮሚቴን በማቋቋም የሥልጣን ክንዱን ለማጠናከር ሞክሮ ነበር። በዚያ ኮሚቴ አማካይነት አንድ ፲፱ የሚሆኑ (ለምሳሌ

እንደራስ መሥፍን ያሉ) ንጉሡ ነገሥቱ ላይ ጠንከር ያለ ተጽዕኖ የነበራቸው ባለሥልጣኖችን ይዞ ለማሰርና ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ ፈልጎ ነበር። እኒሁ የቀድሞ ወታደሮችም እንዲሁ ንጉሠ ነገሥቱ ጉዳያቸውን ችላ ማለታቸው ከነዚሁ ባለ ሥልጣኖች እጉል ምክር የመነጨ ነው ብለው ያምኑ ነበር። ስለዚህም ጠ/ሚኒስትሩ የአዲሱ ኮሚቴ መቋቋም ለራሱ ዕቅድ የሚበጅ ሆኖ እንደሚታየው የሚገመት ነው። ያም ሆነ ይህ ዘማቾች ወደ አራተኛው ክፍለ ጦር ሂደው ወታደሮቹን ከነሱ ጋር ሁነው አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲያቋቁም ጠየቋቸው። በዚያን ጊዜ በክፍለ ጦሩ ሜጻ ቴኒስ ይጫወት የነበረው ሻለቃ እጥናፉ ክፍለ ጦሩን እንዲወክል ተመረጠ። የኮንጎ ዘማቾች የራሳቸውን ወኪሎች መረጡ። እዚህ ላይ አንድ መጠቀስ ያለበት በአራተኛው ክፍለ ጦር የነበሩ ብዙ መኰንኖች በጦር ኃይሎች ውስጥ እያደገ በመጣው መከፋፈል ተደናግጠው በልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች መካከል ሊመጣ የሚችለው ግጭት ትኩረታቸውን ስቦት እንደነበር ነው። በርግጥም ይህ ፍራቻ በስተጀርባ መኖሩ ነበር ደርግን እንዲፈጠር ያደረገው። «ወታደሮች እርስ በርሳቸው እንዳይዋጉ» የአስተባባሪ ኮሚቴ አስፈላጊነት የግድ ሁኖ ታየ።

የራሱ የሆነው «የኮሚዩኒስት ሕዋስ» እንደነበረው በገለጸ ሻለቃ ተፈራ በተባለ የእጥናፉ የግል ጓደኛ አማካይነት ሁኔታው ግፊቱን ወደፊት እየጨመረ መጣ። ይኸው ሻለቃ እጥናፉና ሌሎቹን ራሳቸውን እንዲያስታዋቁና ሬዲዮ ጣቢያውን ተቈጣጥረው እያንዳንዱ የጦር ክፍል ምስት ምስት ወኪሎች (አንድ ተራ ወታደር፣ አንድ ባለ ሌላ ማዕረግ፣ አንድ ከሻለቃ በላይ ያልሆነ መኰንን) ይልኩ ዘንድ ጥሪ እንዲያደርጉ ምክሩን ለገሣቸው። በዚህም መሠረት በቅልጥፍና ሬዲዮ ጣቢያው ተያዘና በዚያኑ ምሽት የኮሚቴ አባሎቹ ከአንዱ የጦር ክፍል ወደሌላው እየተዘዋወሩ ወኪሎቻቸውን እንዲልኩ ጠየቁ። ሚክሲኮ አደባባይ የሚገኘው የፖሊስ ማዕከላዊ ጠቅላይ መምሪያ እንደተባለው ሲፈጽም ሌሎቹ (ክብር ዘበኛ፣ የጦር ሠራዊት፣ መሐንዲስ ክፍል፣ ፈጥኖ ደራሽ) እምቢ አሉ። እነ እጥናፉ የሚያደርጉት ጨነቃቸው፤ የተገለሉም ሆኑ። እንዳልካቸው ግን ምንም ዓይነት እርምጃ አልወሰደም። በዚያን ጊዜ ሁኔታውን በቅርብ ይከታተሉ የነበሩ፣ እስከ እሑድ ድረስ እንዳልካቸው እንእጥናፉ ላይ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችለው ሁኔታ ላይ ይገኝ እንደነበር ይጠቁማሉ።

እሑድ ላይ ግን አዲስ አበባ ውስጥና በዙሪያዋ ያሉ የጦር ክፍሎች ሁሉ በአጥናፉ ለሚመራው ኮሚቴ ምስት ምስት ወኪሎች ላኩ። በዚሁ ዕለት ከሰአት በኋላ ወታደሮች ከፍተኛ መኰንኖችና የክፍለ ጦር አዛዦችን ማሠር ጀመሩ።

ደርግ ተወለደ፤ ሁኖም ግን ገና ከሌሎች ራቅ ራቅ ካሉ የጦር አካሎችና ክፍለ ጦሮች በተለይም ከሁለተኛና ከሦስተኛ ክፍለ ጦሮች በኤርትራና በአጋዴን ወኪሎች አልተላኩም ነበር። በተጨባጭ ሲታይ ደርግ በአዲስ አበባና በአካባቢው የጦር አካሎች የተመሠረተ ነበር። የአራተኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መመሪያ ውስጥ የሚገኘው የስብሰባ አዳራሽ (ሕገ አዳራሽ) ጠባብ ነው። በሚል ሰበብ መገኘት የሚችሉና ያለባቸውም ከየጦር አካሉ የተላኩት ምስት ምስት ወኪሎች ብቻ ናቸው። በሚል የኮንጎ ዘማቾች እንኳ ከተሳትፎ ተሸቀነጠሩ። አጥናፉና ሌሎቹን ከአራተኛ ክፍለ ጦር የመረጧቸው እነዚያ የኮንጎ ዘማቾች የቀድሞ ወታደሮች እንጂ ከጦር ክፍላቸው ተመርጠ የመጡ ስላልነበሩ እንደገና እንዲመረጡ ተደረጉ የሚል የመረጃ ምንጭ አለ። የሆነ ሆኖ የኮንጎ ዘማቾች በምክንያት እንዲወጡ ሲደረግ አጥናፉና ጓደኞቹ ግን እዚያው ቀሩ።

እንዳልካቸው ከነአጥናፉ ጋር መደራደር ጀመረ። ንግግሩ ይካሄድበት በነበረው የአራተኛ ክፍለ ጦር ቢሮ ውስጥ «ለንጉሥ ነገሥታችንና ለሀገራችን ታማኝ ነን» እያለ በሚለፍፍ ጥቅስ ሥር ነበር አጥናፉ የተቀመጠው። መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ሌሎቹ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ መጡ? ጓደኛው የሆነው ጠቅላይ ሚኒስትር የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ያደረገው ግርማ ፈለቀ መኰንኖቹን ለስብሰባ ጠርቶ በአዲስ አበባ የነበረውን የሁኔታዎች እድገት ገለጸላቸው። ስብሰባው ሐረርጌ ውስጥ ተካሂደና «ሁኔታውን አይተው ተመልሰው ሪፖርት የሚያቀርቡ» ወኪሎች ለመስደድ ተወሰነ። ልዑካኑን የመምረጥ ጉዳይ ሲመጣ መኰንኖቹ ሻለቃ መንግሥቱንና ቀደም ብለው የሦስተኛ ክፍለ ጦር የቀድሞ አዛዥ የነበረውን ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝን ገንዘብ በማጉደል የከሰሱትን ጥቂት ሌሎችን ለመስደድ ወሰኑ። የገንዘብ ማጉደሉ ጉዳይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይም ወጥቶ ነበር። ዋና ከሳሹ ከጀኔራሉ ጋር የቆየ ጠብ የነበረው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ነበር። ግርማ ፈለቀ መኰንኖቹን በመስደድ በክፍለ ጦሩ ወታደሮች አጠቃላይ ምርጫ ተካሂዶ በሱ ግምት «ተራማጅና ፀረ-እንዳልካቸው» የሆኑ ወኪሎች

ሊመረጡ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማስቀረት አስቦ ነበር።

መንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ ለገሠ አስፋው፣ ብርሃኑ ባይህ (በሐረር አካባቢ የተላኩ) አዲስ አበባ ሲደርሱ እነ አጥናፉ ፈነደቁ። ወዲያውኑም ምስተኛው ክፍለ ጦር ለኮሚቴው ወኪሎች መላካቸውን አስታወቁ፤ ብሮኘጎታቸውም ያበቃለት መሰሉ ተሰማቸው። በዚያ የፈንጠዝያ ስሜትም ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ወኪሎች እንዴ የደርግ ሊቀ መንበር እንዲሆንም ሐሣብ አቀረቡ። በኮሚቴው ውስጥ የሆለታ ምሩቆች የበላይነቱን ይዘው ስለነበር፣ እንደበቁ የረታው መንግሥቱ ኃ/ማ ሊቀ መንበር ሲሆን፣ አጥናፉ የም/ሊቀ መንበርነቱን ቦታ ያዘ። ሁለተኛ ክፍለ ጦርም ወኪሎቹን ላከ። በዚያን ጊዜ ሐረር ውስጥ መኰንኖች፣ ባለ ሌላ ማዕረጎችና ወታደሮች ተናደዱ። ሻለቃ ተፈራ ወልደ አብም እዚያ ሂዶ እነ መንግሥቱ በአብዛኛው የክፍለ ጦር አባላት ያልተመረጡ ስለሆነ ደርግ ውስጥ መኖር የለባቸውም፤ እያለ ወታደሮቹን ይቀሰቅስ ገባ። መኰንኖቹም እነመንግሥቱን የላኩት ተመልሰው ሪፖርት እንዲያቀርቡ እንጂ «የደርግ አባላት እንዲሆኑ» ስላልነበረ ተታወሙ። ስለዚህም ምስተኛው ክፍለ ጦር እነመንግሥቱ እንዲመለሱ ጠሩ። እነሱ ግን እሻፈረን በማለት እንዲያውም ሻለቃ ተፈራ እንዲያዝ አዘዙ። ሐረር ውስጥ ማንም ሊይዘው አልደፈረም፤ ግን ሻለቃው ከልክ በላይ ስለተማመነ ድሬ ዳዋ ሂደና ከዚያ ተይዞ ወደ አዲስ አበባ ተላከ። ሻለቃ ተፈራ ከእሥር ቤት የተለቀቀው በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ነበር።

ይህ ነበር እንግዲህ የደርግ አደገኛዎች ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ብለው የሚፍነከነኩበት። እነዚያ ምርጫ ውስጥ የተሳተፉት እንኳ ምርጫቸውን የሰጡት አገር ለሚያስተዳድር ገዥ አካል ሳይሆን «በልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች መካከል ግጭትን ለማስቀረት ለሚያስችል» አስተባባሪ አካል ነበር። «ምርጫው» በተካሄደበት ጊዜ ከጦር ሠራሩ የነበሩ መኰንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ነበሩ የተመረጡት። እንዳንዶቹ ወደ አዲስ አበባ የተላኩት ከፍሎቻቸው ከዚያ እንዲወገዱላቸው የተሻለ መንገድ ሁኖ ስላገኙት ሲሆን፣ ሌሎች ከፍሎች ደግሞ የታወቁ አዋኪዎችን ነበር የላኩት። ግንም ግን እነዚሁ ለሰዎች ገዥዎች ይሆናሉ ብሎ ያሰበም ያወቀም አልነበረም። ይህን መገንዘብ ሲጀምሩ ግን ብዙዎቹ ክፍሎች ወኪሎቻቸው እንዲመለሱ ጥሪ አድርገው ነበር። ግን በጀ ያለ አልነበረም። ከዚያም በላይ እንዚሁ ወኪል

ተብቡዎች ንዑስ ደርግ የተባለውን አጥፈው፣ ራሳቸውን ሕጋዊ አድርገው ሥልጣናቸውን አረጋገጡ። እንደ ጎዳጎ ማስታወሻ ለማከል፣ የኮንጎ ዘማቾችን የተባበሩት መንግሥታት አበል ይገባኛልን ጉዳይ ወዲያ ብለው ሳይሰሟቸው ቀርተዋል።

እንደ አካል ደርግ እደብ ያልነበረው፣ ይህ ነው የሚባል ቅርፅ ያልያዘ ነበር። በኋላ የተጐነጐነውን እፈ ታሪክ ትተን፣ ከየካቲት በፊት ማንም ከደርግ ውስጥ የታወቀ የታጋይነት የፖለቲካ ታሪክ የነበረው አልነበረም። በዘውድ አገዛዝ የሚያምኑም የማያምኑም ነበሩባቸው:: ማንኛቸውም ግን ምን እንደሚፈልጉ በጎሊናቸው የቀረፁት ግልጽ ሆኖ የሚታያቸው ነገር አልነበረም:: በድምሩ ሲታዩ ያሳንጻቸ ዝግጅት ንግገር የማድረግ ተሰጥዎ ነበራቸው:: "የኢትዮጵያ ትቅደምን" መመሪያ ለማስረዳት መንግሥቱ ኃ/ማ ለሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ንግግር ደህና አድርጎ የሚገልጠው ነገር አለው::

> «ኢትዮጵያ ትቅደምና፣ እውን ለማድረግ ራስ ወዳድነትን ማስወገድ፣ ሴትና ቁን መሥራት፣ መጥፎ ዝንባሌንና ሥንፍናን በታታሪነት፣ በትብብርና በፍቅር መተካት ይኖርብናል። በተለይ በመሩ ውስጥ ሌሎችን መናቅን፣ መሠረት የሌለው ነቀፌታን ማስወገድና እርስ በርስ በመከባበርና ከሃይማኖት ይበልጥ መመለክ ባለበት ሥነሥርዓት መተካት ይኖርብናል። ለሀገራችን ማሳየት ያለብን ጀግንነትና ፍቅር እንደገና መታደስና መጠናከር አለበት።»

ለጦሩ ስለ አክብሮትና ስለ ሥነሥርዓት የተደረገው ጥሪ፣ በክፍለ ጦሩ ውስጥ የደርግን ሚና በሚመለከት በወታደሮችና በመኩንኖች ዘንድ የነበረው ተቃውሞ ምን ያህል እንዳሳሰባው ያሳይ ነበር። ባጠቃላይም ሲታይ ንግግሩ፣ «ከ፲፱፻፶ምቹ ዓ.ም. ጀምሮ በማርክሲዝም የፀና እምነትና ግልጽነት ያለው አብዮታዊ» እየተባለ በኋለኛው ጊዜ ሲካብ ከነበረ ሰው የሚጠበቅ ዓይነት አልነበረም።

እንዲያውም እዚህ ላይ ስለ ራሱ ስለ መንግሥቱ ኃ/ማ ማንሣቱ ተገቢ ነው። ስለ ደርግ የሚነገሩት ሐሰቶች ስለ መንግሥቱ ሕይወት ታሪክ ከሚባሉት ፈጠራዎች ጋር

አብረው የተጐነጐኑ እንደመሆናቸው መጠን መጋለጥ ያለባቸው ናቸው። መንግሥቱ ምንም እንኳ የሆለታ የጦር ት/ቤት ምሩቆች ከሐሪር አካዳሚ ምሩቆች ጋር «በእኩል ዓይን» ባለመታየታቸው፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሽንጡን ገትሮ የቆመ እንደነበር ቢታወቅም፣ ከየካቲት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በፊት የፖለቲካ ታሪክ አልነበረውም። ጥቂት ጊዜ እሚሪካን አገር መቆየቱ የፖለቲካ ንቃት ሰጥቶት ከሆነም ለራሱ እምቆ ያላወጣው ጉዳይ ነው። መንግሥቱ ምስተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ በረብሸኛነቱና በቀምቃሚነቱ (እዘውትሮ የሚጠጣበትም ቡና ቤት የታወቀ ነበር) እንዲሁም በተደባዳቢነቱ የታወቀ መኩንን ነበር። በክፍለ ጦሩ የግቹ ክፍል ውስጥ እንደመሥራቱ መጠን ከመንግሥት ካዝና አዘውትሮ እጁን መዶሉ አልቀረም። ሁኖም እዲተሮቹ የሆለታ የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ባይሆኑ ኑሮ ተይዞ በታሠረ ነበር። (እንዲታሠር ከማድረግ ይልቅ በምስጢር እሰባስብ የጐደለውን እንዲከፍሉ ያደርጉ ነበር)። መንግሥቱ ኃ/ማ ምንም እንኳ ጉብኚዎችን «ትጐትና አደብ የገዛ» ሰው መስሎ በመታየት አሁን ሊያደናግር ቢችልም ሞኪዬውና ግልፍተኛነቱ የሚረሳ አይደለም።

መንግሥቱ ኃ/ማ ጐልጻሩነቱ ጎላ ብሎ በሚታየው አፍሪቃዊ መልኩ የተንማም በእበሻ ዘረኝነት እንደተሠቃየ ጥርጥር የለውም። ግን መንግሥቱም ቢሆን ተቀናቃኞቹንና ጠላቶቹን ለማጣበቢያ ይህንኑ እንደተጠቀመበት የሚያሳዩ ምሳሌዎች አሉ። የመንግሥቱ ሥረ-መሠረቱ፣ ታሪኩም እንደየጸሐፊዎቹ አምሮት ይለዋወጣል። ሥረ-መሠረቱ ዝቅ ካለው ወገን መሆኑን ለማስረገጥና «ሞቴን» መሆኑን ለማሳየት የሚፈልጉቱ እንደእርሞ ወይም እንደወላይታ አድርገው ሲያቀርቡት፣ ከተለየ ዓላማ የሚነሡት ደግሞ «እማራኑቱ» ላይ ጫና ይሰጣሉ። እንዲያውም ፪ ጸሐፊዎች መንግሥቱ የወጌ ምኒልክ የዲታላ ልጃቸው የልጅ ልጅ ነው ተብሎ ስለሚገመት ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥቱ በፍርሐትና በአክብሮት ነው የሚታየው ብለው እስከመጻፍ ደርሰዋል::(22) ብዙ ኢትዮጵያውያን ልጅ እያሱን ከሥልጣን በመገልበጥ ወዬ ኃይለ ሥላሴን የረዱና በኋላም የጣሊያን ወረራ ባበታበት ጊዜ ኃ/ ሥላሴ ከሱዳን ስደት ተመልሰው ካገር እንዳይገቡ ለማድረግ ይደራጁ የነበሩትን አርበኞች አሜጥር የሰሩባቸው የታወቁት ፈውዳል የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ልጅ መየም የቀርብ ዘመድ ነው ብለው በእርግጠኝነት ይናገራሉ:: ከበደ ተሰማ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ኃይለ ሥላሴን ለመገልበጥ የተደረገውን

መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፍ ረገድም ቁልፍነት ያለው ሚናም ነበራቸው። በደኅዝግቹና በመንግሥቱ መካከል ያለው የመልክ መመሳሰል የሚያሳጣ ነው። ከልጆቻቸው ጋርም በደንብ ይመሳሰላል። (አንዱ ልጃቸው ካሣ ከበደ ለጀኔቭ አምባሳደር ሲሆን አያሌው ወይም ያሬድ ከበደ ደግሞ ተደም ሲል ኢሕአፓ ውስጥ ሰርጎ ገብቶ፣ ኢሕአፓን ለማጥፋት ታልሞ የነበረውን የብተና ዘመቻ መርቷል) ያም ተባለ ይህ፣ ደኅዝግች ከበደ ለመንግሥቱ ኃ/ማርያምና ደርግ ውስጥ ላሉ ጓደኞቹ የቤተ መንግሥቱን ውስጠ ምስጢርና ንጉሥ ነገሥቱ ምን ያስቡ እንደነበር በመዘከዘክ ረድተዋል። ለዚህ ውለታም ይሁን፣ ልጅ ሳባቱ ማድረግ ከሚጠበቅበት ኃላፊነት የተንሣ፣ ፊውዳላዊው ከበደ ለጓደኞቻቸው ላይ የደረሰው የንብረት መታገርና መወረስ እንዳይነካቸው አስደርጓል። ከበደ ተሰማ በ፲፱፻፩ዎቹ ውስጥ እስኪሞቱ ድረስ በመቀማጠል የኖሩ ሲሆን ሲሞቱም ሙሉ የቀብር ሥነሥርዓት ተፈጽሞላቸዋል። የመንግሥት ሬዲዮም ውዳሴ አንብቦላቸዋል።

ቀሪብ ብለን የደርግ መኩንኖችን ይዘት ስንመለከት፣ የበታች መኩንኖችና ሃምሳ አለቆች እየተባለ የሕዝብ ስሜትን ለመሳቢያ ይቀርብ የነበረውን ወግ የሚያፋልሰው ሁኖ እናገኘዋለን። ከሰባት እስከ አሥር ከነበሩት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ውስጥ አብዛኞቹ ሻለቆች ወይም ሻምበሎች ነበሩ፤ ለገሰ ብቻ ነበር ያ አለቃ የነበረው። መንግሥቱ፣ ሞገሥ፣ ብርሃኑ ባይህ፣ ፍቅረሥላሴ፣ ደበላ ዲንሳ፣ ኪርስ፣ ሚሳይና አሥራቱ ደስታ፣ ወዘተ ሁሉ ሻለቆች ነበሩ። በፖለቲካው በኩል ደግሞ መላቅጡ ጠፍቷቸው ስለነበር አንዱን ወይም ሌላውን የሲቪል ቡድን መጠጋታቸው አልቀረም። ደምሴ ዴሬሳ በኋላ እሞአትን ከመሠረተው ከባሮ ቱምሳ ምክር ሲለገሥ፣ ፍቅረሥላሴ ከሠናይ ልኬ ጋር ሞገሥ ከኢሕአፓ ጋር ወዘተ ይቀራረቡ ነበር። እያደርም ጦር ኃይሎች ውስጥ የተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው ተባረሩ፤ ንዑስ ደርጉም ፈረሰ። ደርግ አንድ ጊዜ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ራሱን ለማደላደል ይችል ዘንድ ሕዝባዊ ተቃውሞን መግታት እንዳለበት በደመነፍሳዊ ስሜት ከመንገዘቡ በስተቀር እንዴት መቀጠል እንዳለበት አያውቅም ነበር። መንግሥቱና ጠቂት መኩንኖች መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. (Sep.16, 1974) የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ለማነጋገር የሄዱ ሲሆን ያን ጊዜም ነበር ማርክሲዝም ላይ የታወቀውን ዘለፋቸውን ይወርዱበትና «የኢትዮጵያ ትቅደም ፍልስፍና»

እንዳላቸው ገልጸው፣ «ሊኒንን ከመታብሩ መቀስቀስ» አስፈላጊ እለመሆኑን ተፈጥመው የተናገሩት። ልክ ከዚያ በኋላም ነበር የግራውን የሶሻሊዝም ጥሪ ለማደብዘዝ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም የተባለው የመጣው። ነገር ግን ውጥንቅጡ የወጣ ንድፈ ሐሳብ ስለነበር የተሻለ ግንዛቤ በነበራቸው ምሁራን ተነቀፈ። ደርግ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት ባለመፍቀድ ደግሞም የራሱ የሆነ ግልጽ አቅጣጫ ለመትለም ባለመቻል እንዲያው በጨለማ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ይታብዙ ነበር ማለት ይቻላል።

የአብዮታዊ ሰደድ እበቃቀልም ብዙ ነገር ያብራራል። ይህንን የምስጢር ቡድን መጀመሪያ የመሠረቱት መንግሥቱ፣ ፍቅረሥላሴ፣ ለገሰ አሥፋው፣ ተካ ቱሉ፣ ተሥፋዬ ወልደኪዳን፣ ዳንኤል አሥፋው፣ ጌታቸው ቪበሺ፣ አሊ ሙሳና ሌሎች ጥቂቶች በወታደራዊ ኃይል እምነታቸው ጠንካራ ጠንካራ የተባሉትን ይጨምራል። አከታትሎም መንግሥቱ ኃ/ማ ሻለቃ ሞገሥንና ደምሴን ለዚሁ ጉዳይ ቀርበ ያነጋገራቸው ሲሆን፣ ሞገሥ ሐሣቡን ከተቀበለ በኋላ ሻምበል ዓለማየሁና ጀኔራል ተፈሪ በንቲም እንዲገቡበት አጥብቆ ጠየቀ። እንደጥያቄውም ተደረገና መላው ሰደድ የኩድኔል አጥናፉን ቡድን ተፃርሮ እንደቆመ ቡድን ተደርጎ ታየ። በተጨባጭ መንግሥቱ ኃ/ማ ያስተነትን የነበረው የራሱን የፖለቲካና ታማኝም የሆነ ቡድን ፈጥሮ በፖለቲካ የማደራጀቱንና ቡድን የመፍጠሩን መስክ ለመኢሶንና ለሌሎች አለመተውን ነበር።

የመጀመሪያው የሰደድ ፕሮግራም ኢሕአፓን እንደ ጠላት አድርጎ ያቀረበ ሲሆን «ጠላትን ለመታት የሐሰትና የማታለል ዘዴን መጠቀም ትክክለኛ የትግል ሥልት ነው። የሚል ነጥብም አሥፍሯል። እኒህ ሁለት ነጥቦች የተወሰነ ከርከር ያስነሡ ሲሆን እንደገና ረቅቆ የቀረበውም በይዘት ደረጃ ብዙ አልተለወጠም። ሌላው የከርከር ነጥብ በጦሩ ውስጥ ማደራጀት የሚችለው ሰደድ ብቻ ነው ብሎ የሚያረጋግጠው ሲሆን ጥቂት የመኩንኖች አባላት ከነበሩት ከወዝ ቡድን ጋር ግንኙነት እንደነበረው እንደ ፍቅረ ሥላሴ ባሉ በወዝ ደጋፊዎች ዘንድ ንትርክ እምጥቶ ነበር። በተቻለ መጠን መንግሥቱ ኃ/ማ ሠራውን ሰደድ እያማከረ ሲሠራ፣ እነ ሞገሥ መታወም ሲጀምሩ ግን እንሱን ገሸሽ እያደረገ ከጠንካራው የሰደድ ቡጥ ጋር ምክሩን ያደርግ ገባ። በጥር ፭፮ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.(Feb.3, 1977) መፈንቅለ መንግሥት የተዶለተው በምስጢራዊ ግንኙነት በሰደዱ ጠንካራ

ቡጥ ነበር።

ኮሎኔል አጥናፉ መቼም ተራማጅ አልነበረም፤ በርግጥም የወግ አጥባቂ አመለካከት የሚያንፀባርቅባቸው ብዙ ነገሮች ነበሩት። ሁኖም በዚህ አመለካከቱ አሁንም ጊዜያዊ አስተዳደራዊ ደርግ ውስጥ ካሉት ከእነደበላ ዲንሳና ሌሎች የተለየ አልነበረም። የአጥናፉ ችግር የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አምባገነናዊ ሥልጣን መቃወሙ ነበር። ለነገሩ መንግሥቱ ኃ/ማ የተለያዩ መኰንኖችን ሲያስወግድ አጥናፉ የሚቀጥለው ተራ የሱ መሆን እንዳለበት ተሰምቶት ነበርና የመንግሥቱን ለደድና መኢሶንን ለመቋቋም አብዮታዊ ሠይፍ የሚባል የራሱን የወታደር ቡድን ማደራጀት ጀምሮ ነበር። ሁኖም አጥናፉ ወሳኝ ለሆነውና ሥልጣን ለተራበው መንግሥቱ ኃ/ማ በማጥቃት ዝግ ያለ ነበር። ታዲያም ተያዘና ተረሸነ፤ ከሞተ በኋላም የኢሕአፓም፣ የኢድህም፣ የኢ ኤል ኤፍም አባል ነበር በሚል ተወነጀለ።

በዚያ ሁሉ የደርግ ትርምስ ውስጥ ግልጽ የሆነ ፖለቲካዊ ግቡት የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። አጥናፉ ሶቪዬቶችን በጥንቃቄ የሚመለከት ሲሆን ሌሎችም ከመንግሥቱ ኃ/ማ ጋር አሁንም ያሉ ከሱ የተለዩ አልነበሩም። አጥናፉ ማርክሳዊ አልነበረም፤ በለ ሁሉም የደርግ አባላት መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ ይህንኑ ግለት ይጋሳል። መንግሥቱና ቡድኑ ያደረጉት የርዕዮተ ዓለም ምርጫ መነሻ ምንጩ ፖለቲካዊ አድርባይነት ነበር። ከሞስኮ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ያስገደዳቸው የሶማሌ ወረራ አፍጥጦ በመጣበት ሁኔታ፣ አሜሪካ መሣሪያ ለመሸጥ አሻፈረኝ ማለቷ ነበር። እንዲህ ዐይነቱን አድርባይነት አጥናፉም ለሌሎቹም ባልቈረቈራቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ የነ ኃይሌ ፊዳ ቡድን ለረጅም ጊዜ መፍቀሬ ቻይናነቱ ለማንም ግልጽ እንደነበር ሊታይ፣ የመኢሶን ወደ መፍቀሬ ሞስኮነት መዞር በፖለቲካዊ አድርባይነት የተቃኘ አርምጃ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።(23)

ለዚህም ነው አሁንም እንኳ መፍቀሬ ሶቪዬት፣ ፀረ-ሶቪዬት ወይም በወታደራዊ ጉዳዮ አካል ያሉ ብሔረተኛ ወገኖች እያለ የሚቀርብ ጋዜጣዊ አገላለጽ የተሳሰተ የሚሆነው። እንዳንዶቹ በሶቪዬቱ ሥርዓተ መንግሥት መንፈሳቸው መማረኩ እንዳለ ሁኖ (መንግሥቱ ኃ/ማ ተከለ ሰውነት እንደሌለው አድርገው ሳይታክቱ የሚያነበንቡለት

እደግዳጊዎቹን በማሳፈር ባሁኑ ጊዜ በኪም ኢል ሱንግ ሥርዓተ መንግሥት እንደነሆለለው ሁሉ) ሥልጣን ላይ ያሉት መኰንኖች እዚያው ሥልጣን ቁንጮ ላይ መቆየት የሚችሉት የሶቪዬትን ድጋፍ እስከያዙ ድረስ መሆኑን አውቀዋል። በርግጥም የመንግሥቱ ኃ/ማ መንግሥት ፊቱን ወደ ውጭ ድጋፍ ፍለጋ ማዞሩ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የራሱ የሆነ የፖለቲካ ችሎታ እንዳልነበረው ያመለክታል።

ምናልባትም እዚህ ሥፍራ ላይ በደርግ ውስጥ የነበሩ ልዩ ልዩ መኰንኖች ድምፃቸውን አጥፍተው – ግለት ይቻላል – እንዲት ወደ ሞት እንደተነዱ ማንሳቱ ተገቢ ሊሆን ይችል ይሆናል። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የሻለቃ ሚሳይ መገደል በደርግ ስብሰባና ውሳኔ የፀደቀ አልነበረም። ተፈሪ በንቲና ሌሎች ጥር ፲፱፻፷፱ ላይ ሲገደሉ ሁኔታው ይኸው ነበር። በዚህን ጊዜ ምክትል ሊቀ መንበሩ እዲስ አበባ እንኳን አልነበረም። አጥናፉም በተመሳሳይ መንገድ ነበር የተገደለው። ይህን እንግዳ የሆነ ሁኔታ ለመረዳት የመንግሥቱን ጠላይ (ወሳኝ፣ ምሕረት የለሽ፣ የግል ጥቅም ያገበረው፣ ሕጋዊና ሞራላዊ ጥያቄ የማይገታው) እንዲሁም የንጉሥ ነግሥታዊው መንግሥት መኰንኖች ላይ ሰፍኖ ይታይ የነበረውን አስተሳሰብ (ለሥልጣን ማደግደግ፣ ወላዋይነት ... ወዘተ) አስተንትኖ ማየት ይጠይቃል። በዚህ ረገድ መንግሥቱ ኃ/ማ ከሌሎቹ «የተለየ» ነበር፤ ሥልጣን ይፈልግ ነበር። ይሁኝ እንጂ እንዴት የሚለው የሚጨንቀው አልነበረም። ይልቁንም የመኰንን ጓደኞቹን የአእምሮ አወቃቀር፣ የሚተረትለት ወላዋይነታቸው፣ በቃላት ሽንገላና ተስፋ በሚሰጥ (በመንግሥቱ ኃ/ማ ቤት ዘይንተረፍ የሆነውን) የማመን ዝንባሌያቸውን ... ወዘተ ያውቅ ነበር። የቅርብ ጓደኞቹ ለገሠ፣ ጌታቸው፣ አሊ ሙሳና ዳንኤል እሥፋው በብዙ መንገድ እንደሱው ነበሩ። ሲቪሎችንና ማንኛቸውንም ዐይነት ምሁራን የሚያስታቅሩ፣ ኃይልን የሚያመልኩ፣ ቈራጦች፣ የመዋሸትና የማደል ነገር ሲመጣ ምንም ዓይነት የሞራል ልጓም የማይገታቸው («ከንብ እስካደረሰ ድረስ ማንኛውም ዓይነት ሥልት ትክክል ነው» የሚለውን መርሐቸው ያደረጉ) ከፍ ባለ ደረጃም ለመንግሥቱ ኃ/ማ ታማኞች የነበሩ ነበሩ። ታዲያም መንግሥቱ ኃ/ማ በተቀናቃኞች ላይ የበላይነት ነበረው።(24)

የ"ቀይ ሽብርን" ያወጀው ደርግ የሠኔ ፳፭ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. (June 28,1975) ደርግ አልነበረም፤ በጣም

የተቀናነሰ እክል ሆኖ ነበር። በተጨባጭ ሲታይ መንግሥቱንና ሰደድ ውስጥ የነበሩትን የቅርብ ጓደኞቹን የያዘ ነበር። ሊሎች አባላት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ይህ ነው የሚባል ድርሻ የነበራቸው አልነበሩም። ከሆነ በኋላ ይነገራቸዋል፤ ይቀበሉማል። የአምባገነኑ ሥልጣን ይበልጥ ፍጹም እየሆነ ሲመጣ የፖለቲካ ክብደትንና ተደማጭነትን በሚመለከት ደርግ በጎብር ሲታይ ሀልው መሆኑ ቀረ። መኢሶን፣ ወዝ ሊግ፣ ኢሮአትና፣ ኢማሌዲን ሲወገዱ፣ ጥቂቶቹ የደርግ መሥንኖች መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ከአናት ላይ እድርገው የሥልጣን ባለቤቶች ሁነው ቀሩ። ኢሠፓአኮ ሆኑ፤ ቀጥሎም ወደ ኢሠፓ ተቸጋገሩ፤ ነገር ግን የሲቪል አጋሮቻቸውን ብቻ ሳይሆን ደርግ ራሱንም ባስወገዱት በመንግሥቱ ኃ/ማርያምና በጥቂት የወታደር ጓደኞቹ እጅ ሥልጣን የመግባቷ ሐቅ ግን እንዳለ ነው።

መኢሶንና ኢሕአፓ

የሁለቱ ድርጅቶች ሥሮቻቸው በአንድ ላይ የተገመደ ስለነበር እያንዳንዱን ነጣጥሎ ማየት አስቸጋሪ ነው። በትግሉ ውስጥ የአባትነቱን ቦታ ይዘው ስለነበሩት ስለነዚህ ፀበይት ድርጅቶች አመሠራረትና እቅሞምቻቸው በስመ ከፉው «ቀይ ሽብር» ወቅት ጥቂት የማይሉ ስሕተት ላይ የተመሠረቱ ታሪኮች ተጽፈዋል። ስለዚህም መኢሶንንም ኢሕአፓንም ትክክለኛና ተጨባጭ ነው ብለን በምናምንበት መነጽር ማየት ይቻል ዘንድ ሐተታችንን እናቀርባለን።

ሁለቱም መኢሶንም ኢሕአፓም በአጠቃላይ መልክ ሲታዩ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ምሁራን እንቅስቃሴ ውጤቶች ነበሩ። ሀገሩ ውስጥ የነበረው የተማሪ እንቅስቃሴ ይበልጥ ሥር ነቀል የሆነ መሥመር ይዞ መድረኩን ፀረ-ፈውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ሲያደርግ፣ በውጭ ሀገር የነበሩ የተማሪ ማኅበራትም ይህንኑ መሥመር በመከተል ደገፉት። በዚህ ወቅት ኃይሌ ፊዳና ጓደኞቹ በውጭ ማኅበራት ተራማጅ አመለካከት እንዲሠርፅባቸው በማድረግ ረገድ ጉልኅ ሚና ተጫውተዋል። ሁኖም ፲፱፻፷ ዓ.ም. ላይ አዲስ አበባ ያሉ ተማሪዎች በነሱ አመለካከት ውጭ አገር ያሉ ጓደኞቻቸው «መጽሐፍት በማውጣት»። የረኩና ድርጅትም ለመፍጠር ምንም ዓይነት እርምጃ እየወሰዱ አይደለም በሚል ትእግሥት

እያጡባቸው ነበር????። በ፷ዎቹ ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ወደአውሮፓና ወደአሜሪካ የሄዱት ተማሪዎችም መደላድላቸው ውጭ አገር የሆነው የተማሪ መሪዎች «አብዮቱ ገና ጥቂት ትውልዶችን ማሳለፍ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፤» ማለታቸውን በደረሱበት ወቅት ቅር ተሰኙ። እኒሁ ተማሪዎች፣ እነኃይሌ ፊዳ ውጭ አገር ብዙ በመቴየታቸው ከሀገሪቱ እውነታ ጋር ተለያይተዋል የሚል ስሜት ተሰማቸው። የአውሮፓውን የተማሪዎች ማኅበር የተቆጣጠሩት እነኃይሌ ፊዳ በ፲፱፻፷፱ዓ.ም. ላይ አዲስ አበባ የወጣውን ዝነኛውን ጽሑፍ («እንኳን ለሮቷኛው የደም ልደት አደረሰዎ» በሚል ርዕስ ንጉሠ ነገሥቱ ላይ የወረደባቸውንና የንጉሣውያን ቤተሰብንና የሚኒስትሮችን ገበና ያጋለጠውን) እንዲሁ ዓይነቱ ንጉሠ ነገሥቱ ላይ የተደረገ ውርጅብኝን ሕዝቡ አይወደውም በሚል ማኅፀናቸው ሲታይ ተማሪዎቹ በዚህ ረገድ የተሰማቸው ስሜት በተወሰነ ደረጃ ማጠየቂያ ነበረው። ልዩነቱ ጊዜ ወስዶ ነው የሠፋው። የኃይሌ ፊዳው ቡድን እንደታሰበው እጁን አጣጥፎ የተቀመጠ እንዳልነበር ሳይጠቅሱት የሚያልፉት አይደለም። ሀገር ቤት ውስጥ ግንኙነት ነበራቸው፤ በውጭ ሀገርም ጋዜጦች እያወጡ (በተማሪ ማኅበሩ ስም) ሀገሪቱ ውስጥ በድብቅ ለማስገባት እየሞከሩ ነበር፤ ከውጭ የገሩ ድርጅቶችም ጋር ግንኙነት ነበራቸው። ኃይሌ ፊዳና ጓደኞቹ እንድ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት ለመፍጠር ቀስ ብሎ ለመጓዝ የሚፈልጉ ይመስሉ ነበር። ግን ስለ ፓርቲ አመሠራረትም ሆነ መካሄድ ስለነበረበት ትግል የነበራቸው ትልም ብዥ ያለበት ነበር። ይህ እንዳለ ሁኖ ኃይሌ ፊዳና የቅርብ ጓደኞቹ የቻይኖቹ መሥመር አማልኧቸው ስለነበር «የሶቪዬት ክላሽንትን» ያኪሱ ነበር።

በመጀመሪያ ነቁ የታየው በቬሐር ጥያቄ ላይ ነበር፤ በአሜሪካ የነበረውን የተማሪዎች ማኅበር (ESUNA) ይመሩ የነበሩት ዓለም ሀብቱ፣ ሀጎስ ንብረ ኢየሱስ፣ መለስ አያሌው፣ ደሳለኝ ራህመቶና ሌሎች ኢትዮጵያ ውስጥ መናገር የሚቻለው ስለ ክፍለ ሀገራዊነት ነው፤ ስለ ብሔራትና ስለ መገንጠል መብታቸው መናገር ግን የተሳሳተ ነው፤ ብሎ የሚሟገት የጉባዔ ውሳኔና አንብር (thesis) ይዘው ብቅ አሉ። በዚህና በኤርትራ ግንባር አመራር ላይ ባደረጉት ሂሳዊ ግምገማ ላይ ተመሥርተው እዚያ የሚካሄደውንም ትግል አወገዙ።[26] ይህ እንግዲህ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. በአገር ቤቱ ማኅበር (የአዲስ አበባ

ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር) ባወጣው ጽሑፍ ከተገለጸው አቅዋም ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነበር።(27) የ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሚን አሜሪካ ውሳኔ ጥላሁን ታከለ በሚል የብዕር ስም አልጂሪያ ውስጥ በዚያን ጊዜ በስደት በነበሩ ምሁራን በተጻፈ ጽሑፍ ተተቸ። የጥላሁን ታከለ ጽሑፍ ቢጋራዊና አጠቃላይ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበርን አቅዋም እንደገና አስረግጦ በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራትና ብሔረ ሰቦች ህልው እንደሆኑና የብሔር ጭቁናም አብዛኛቹ ጭቁን ብሔሮች/ብሔረሰቦች ሜንታ ላይ ያረፈ ዕውነታ እንደነበር መከራከሪያውን አቅርቧል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የብሔራት የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚለውን ያወቀ ሲሆን ኢርትሬውያንም ፣የማኅበር መሪዎቹ ጠላይ ምንም ይሁን ምን፣ ይኸው መብት እንዳላቸው ደራሲያኑ አረጋግጠዋል። በዚህ ነጥብ ላይ ከርከሩ ተቧቧፈ።

የ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. የተማሪ ጉባዔዎች በልዩ ልዩ አቋሞች መካከል የነበረውን ልዩነት ገጎድ አድርገው አሳይተዋል። በመሥፍን ሀብቱ (፲፱፻፷፱ ዓ.ም. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ዋና ፀሐፊ) ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሚን አሜሪካ (ESUNA) ሌሎችም፣ የ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. የክፍለ ሀገራዊነትን አቅዋም ተፃርረው ቆሙ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሚን አሜሪካ የቀድሞ መሪዎች ግን በአቋማቸው ጸኑ። በመጨረሻም የብዙኃን ድምፅ «በብሔር ጥያቄ ላይ ትክክለኛውን ውሳኔ» አሳልፎ የክፍለ ሀገራዊነትን አንብሮ ሻረው። እዚህ ላይ ሦናይ ልኪ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሚን አሜሪካ ተገንጥሎ እንጂ ለመፍጠር ሌላ የተማሪ ቡድን መምራት ጀመረ። በአውሮፓ – በርሊን ላይ በተደረገው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ፣ ጉባዔ ላይ ከርከሮቹ ግለት የነበራቸው ሲሆኑ ሁለት መልእክተኞች ከአልጂሪያ ሁለት ደግሞ ከአሜሪካ (እንድርያስ እሸቴ የክፍለ ሀገራዊነትን አንብሮ ደግፎ፣ መሥፍን ሀብቱ ደግሞ የዚያ ተቀራኒ ሁኖ) ተካፍለውበታል። አሁንም እንደገና የብዙኃኑ ዝንባሌ የብሔር አንብሮን የመቀበልና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን የግወቅ ሆነ። እነኃይሌ ፊዳም ዘግየት ብለው የብዙኃኑን አቅዋም ደገፉ። በውይይቱ ወቅት ነገደ ጉበዜና ሌሎች ከብዙኃኑ ሐሣብ የተቃረነ አስተያየት ሲገልጹ ቄይተው ውሳኔውን መደገፋቸው እንደ

እድርባይነትና ለታክቲክም እንደተደረገ ሁኖ ታየ። ይሄም ለጥርጣሬ በሩን ከፈተ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በአንጻራዊ ደረጃ ሲታይ የተደራጀ፣ ድምፅን በደንብ የሚያስተጋባ ተሰሚነትም የነበረው እንደመሆኑ መጠን፣ ኅቡዕ የፖለቲካ ቡድኖች በርሱ ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸው ዘንድ እትኩሪውበት ነበር። ስለዚህም በብዙ ሁኔታዎች ኅቡዕ ቡድኖችን ይለያዩዋቸው የነበሩ ነጥቦች ተማሪ ማኅበራት ውስጥ እየተሣሙቱ በእንቅስቃሴው ውስጥ ንድፈ ሐሳባዊ ጦርነትን ያስነሡ ነበር። ይህም በተረው ንቅናቄው መሠረተ ሠፊ የሆነ፣ ብዙኃንን ያቀፈ ንቅናቄ ከመሆን ይልቅ ወደፖለቲካ ፓርቲ ቀረብ ያለ ጠባይ እንዲኖሣ አድርጎታል። በዚያን ጊዜ በኃይሌ ፊዳ ቡድንና ኢሕአፓን በመሠረቱት ቡድኖች መካከል ምስጢራዊ ግንኙነት ነበር። ንግግሮቹን ለማካሄድም ኃይሌ ፊዳ ሁለት ጊዜ ወደ አልጂሪያ ተጉዟል። በንግግሮቹ ወቅት የጊዜው ጥያቄዎች ተነሥተዋል፤ – የብሔር ጥያቄ፣ የድርጅት ጥያቄ፣ የትጥቅ ትግል ጉዳይ። በብሔር ጥያቄ ላይ፣ የአሜሪካ፣ የሱዳንና ያገር ቤቶቹን ታጋሮች አቅዋም ይወክሉ የነበሩት አልጂሪያ የነበሩት ምሁራን፣ የኢትዮጵያም አብዮታውያን የመገንጠል እርምጃን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም እያንዳንዱን ሁኔታ በመጣበት ገጹ ለመመርመር ያሳቸው መብት የተጠበቀ ሁኖ፣ የብሔሮችን እስከ መገንጠል ድረስ የሚሄድ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ያለምንም ውልውል ግረጋገጥ አለባቸው ብለው ተከራክሩ። ኃይሌ ፊዳ ባቀረበው ሐሣብ ተስማምቶ ግን በሱ ቡድን ውስጥ «ሁሉም» ይህንን አቅዋም ስለማይደግፉት፣ በዚያን ጊዜ በግልጽ ደግሞ መውጣት እንደማይችሉ አክሎ ተናገረ።

በድርጅት ጥያቄ ላይ የአልጂሪያዎች ምሁራን ምስጢራዊ ግንባር ቀደም ፓርቲ መመሥረት፣ ሥርዓት ባለውና ኅቡዕ በሆነ መንገድ መሥራት፣ የፓርቲውን መዋቅር ባገር ቤት መዘርጋትና ለትጥቅ ትግል ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገለጹ። በድርጅት አስፈላጊነት ላይ የኃይሌ ፊዳ ስምምነትም ነበር። ግን አሁንም እንደዚያ ዓይነቱን ፓርቲ ለመመሥረት ጊዜው ገና እንደነበርና እንደዚያ ዓይነቱን ፓርቲ ከመመሥረት በፊት እመንግሥት ቢሮክራሲ ውስጥ መመልመል ወይም ሰርጎ መግባት መቅደም አለበት ብለው እንደሚያምኑ ገለጸ። (ጠመንግሥቱ እርምጃ ለመውሰድ

ቢያስብ አስቀድሞ ለማወቅ» የሚል ምክንያት ነበር ያቀረበው) የጠመንጃ ትግልን በሚመለከት፣ ኃይሌ ፊዳ፣ የሱ ቡድን በመሠረተ ሐሣቡ ተታውሞ ባይኖረውም ስለ ትጥቅ ትግል መጀመር ማሰብ ጊዜው ደርሷል ብለው እንደማያምኑ አስረዳ። ኃይሌ ፊዳ በዓለም አቀፍ ጥያቄ ላይ ከጠበቁት በላይ «ቻይናዊ» ሁኖ ነው ብቅ ያለባቸው። በቻይና ላይ የሶቪዬት መረራ የማይቀር ነው የሚለውን ፍራቻውን (ይህ የሆነው በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. የዩዙሪ ወንዝ ላይ የሁለቱ ኮሚዩኒስት ኃይሎች ግጭት ከተፈጠረ በኋላ ነበር)። የአልጀሪያዎቹ ምሁራን መሠረት ካሳጡበት በኋላ በበቂ ደረጃ ሁኔታዎችን መከታተል ይችሉ ዘንድ «አስፈላጊ ጋዜጦችን» እንደሚልክላቸው ቃል ገባ።

ከእነዚህ ንትርኮች ውስጥ ጠለቅ ብለን የምንገባው በነዚህ ሁለት ቡድኖች መካከል ለነበሩት ግጭቶች መነሻ መሠረት ስለሆኑና እነዚህን ሳያውቁ የኢሕአፓንና የመኢሶንን ግጭት መረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው። ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና፣ የምስጢር ግንኙነቶች ቀጠሉ፣ ግን ፍሬ ቢስ ነበሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ታጋዮች ውሎ አገር የነበሩ ጓደኞቻቸውን (አልጂሪያ፣ አሜሪካ... ወዘተ) «ከፍ ባለ የትግል ስልት ዝግጁ ያልሆኑ» ከሚመስሉ «ከቀደምት የኢምባሲ ወራሪዎች» ጋር ጊዜ በማጥፋታቸው ቁጣቸውን ያወርዱባቸው ነበር። በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ውስጥ ኃይሌ ፊዳ ወደ አልጂሪያ ጽር አቋማቸው እንዳልተቀየረ፣ ያ እንዳለ ሆኖ ከተስማሙ የሱ ቡድን ለውጊደት ዝግጁ እንደሆነ አስታወቃቸው። እነሱም በመሠረታውያን ጉዳዮች ላይ ልዩነታቸው ያልተፈታ ስለሆነ ውጊደት ከጥያቄ ውጭ እንደሆነ በመግለጽ እምቢታቸውን አስታወቁ። የኃይሌ ፊዳ ቡድን ኢሕአፓ ከመመሥረቱ በፊት በቅርቡ እንደዚያ ዓይነት ፓርቲ መመሥረት «የሚቻልበት» ሁኔታ እንደነበር በደብዳቤ በወግ እንዲያውቁ ተደርጓል።

በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ኢሕአፓ ተመሠረተ። መሥራች ጉባዔው የፖለቲካ ፕሮግራም ነደፈ። (በኋላ የኢሕአድ ፕሮግራም ተብሎ የወጣ) የፓርቲውን አመራር መረጠ። (ከነዚህም ውስጥ ብርሃንመስቀል ረዳ፣ ተስፋዬ ደበሳይ፣ ብንያም አጻናና ክፍሉ ከበደ በሞት ተለይተዋል) የሽምቅ ተዋጊ ቡድን ለማደራጀትና ትጥቅ ትግል መጀመር መሰነ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እርነት ድርጅት (ኢሕአድ) የሚል ውሎ ግንኙነት የሚያገለግል የሽፋን ስም አወጣ። በሶብየት ጎብረት ጥያቄ ላይ ምንም እንኳ ተወከለው ከመጡት ጥቂቶች «ሶሻል ኢምፐሪያሊዝም» የሚል እንብር ይዘው ቢቅርቡም የብዙኃኑን ድምፅ ሳያገኝ በመቅረቱ ውድት ሆነ። ያም ሆኖ ጉባኤው «ከላቧ የሶቭየት ጎብረት የኢትዮጵያ አብዮት ወዳጅ አይደለችም» በሚል ዓይነት መታየት ይኖርበታል ብሎ አሠፈረ። ከሞስኮ ጋር ግልጽ የሆነ ጠብ ውስጥ መግባትም በጊዜው የነበረው የአካባቢ ሁኔታ ሲታይ፣ የኢሕአድን ሥራ (በተለይም የሽምቅ ተዋጊ ቡድን ለማሠልጠንና ሀገር አስገብቶ ለማስጀመር የነበረውን ዕቅድ) በጣም ከባድ ያደርገዋል በሚል ምክንያት የተከለከለ ሆነ።

እንደኢሕአድ ሆኖ ኢሕአፓ ከኤርትራ ግንባሮችና መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አደረገ። የፍልስጥኤሙ አልፋተህ የመጀመሪያውን የሽምቅ ተዋጊ ቡድን— በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት የተባለውን— ለማሠልጠን ተስማማ። በዚያን ጊዜ ኢሕአድ ከኢፒኤልኤፍ ጋር ይበልጥ ተቀራርቦ ነበርና ይህ ሁኔታ ደግሞ በበኩሉ ኢሌልኤፍ የኃይሌ ፊዳን ቡድን ይበልጥ እንዲቀረብ ገፋው። የእነ ኃይሌ ፊዳ ቡድን በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ተስፋዬ ታደሰ በሚባል ቤይሩት ውስጥ ተቀማጭ በነበረ፣ «የመንግሥት ሰላይ» ነው ተብሎ በተማረው ንቅናቄ በተወገዘ ግለሰብ ነበር የተወከለው። ኢሌልኤፍ የኢሕአድ ሠልጣኝ ቡድን (ለሥልጠና) ወደመካከለኛው ምሥራቅ ሊመጣ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ለኃይሌ ፊዳ ቡድን ወሬ አዘለቀና እነሱ ደግሞ ይህንን ዜና እንጠልጥለው ወደተግሪው ጋዜጣ በመሮጥ «ጠመንጃ ለማንሳት የቸኮሉ» የሚል ምንም ያህል ያልተሸፋፈነ ጠበኛነታቸውን ገለጹ። እነዚያኞቹም (የኢሕአድ ወገኖች) በጣም ተናደዱ፤ እንደለየለት ከህደትና በተዘዋዋሪ መንገድም ለንጉሣዊው መንግሥት አገልግሎት እንደማበርከት አድርገው በመቁጠር እነኃይሌ ፊዳ ላይ ያላቸውን አቅምም

አከረሩ።

በውጭ አገሩ የተማሪ ንቅናቄ ውስጥ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን መመሥረትም (የፊተኛውን ዓለም አቀፍ ማኅበር በመተካት) ግጭት አስከተለ። እነ ኃይሌ ፊዳ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች (ፌዴሬሽን) የኢሕአፓን ፍላጎት ለማስተጋቢያ ይሆናል ብለው በማሰብ ብዙ ምክንያት እየደረደሩ ተቃወሙት። በግራና በቀኝ አሉቅኞች መብረር ጀመሩ። በዚያን ጊዜ ይጧጧፍ የነበረው ክርክር በወቅቱ በወጡ የተማሪዎች አሉቅኞች ላይ ይገኛሉ። ልዩነቱ እየሰፋ መጣ።

የየካቲት አብዮት ሲፈነዳ፤ መሠረታዊው የሆነው ልዩነት ይበልጥ ግልጽ ሆነ። የኢሕአፓን መሥመር የደገፉ ማኅበራት «አብዮቱን» ይበል ይበል ሲሉና «ለሠራተኞች» የግንባር ቀደም ሚና ሲሰጡ፤ የኃይሌ ፊዳ ቡድን ግን አብዮቱን መጀመሪያ «ረብሻ» ነው ሲሉ፤ ቆዩት ብለው ደግሞ በንዑስ ከበርቴው የተመራ ሕዝባዊ ንቅናቄ ነው አሉ። የአመራር ሚናን በሚመለከት ሁለቱም አገላለጾች ሊላው ቢቀር የሚያከራክሩ ሲሆኑ በእነ ኃይሌ ፊዳ በኩል "በንዑስ ከበርቴው የተመራ ንቅናቄ" የሚለው አገላለጽ የዚህ መደብ አሉታዊ ጠባዮች ላይ ያሳቸውን ንቀፌታ የሚገለጽ ነበር። በመሠረቱም ፍርሐታቸው እውነት ነበረው። የነኃይሌ ፊዳ ቡድን "የእንዳልካቸውን መንግሥት የማሻሻያ አርምጃዎችን ሥራ ላይ እንዲያውል ጊዜ ይሰጠውና በዚያም ተጠቅመን ዴሞክራሲያዊውን ትግል መቀጠል እንችላለን» በማለት በይፋ ተከራክሩ። በመቀጠል ላይ የነበረውን የሠራተኞች ሥራ ማቆም አድማና የከተማውን ሕዝብ መነሣሳት መደገፍ ለነኃይሌ «ጽንፋዊነት» ሲሆን፣ ሰሌሎቹ ደግሞ «አብዮቱን እንዲቀጥል ለማድረግ» ትክክለኛ ፖሊሲ ነበር። ደርግ ሥልጣን ሲይዝ የኢሕአፓ ደጋፊዎች «የሥልጣን ቅሚያውን በማውገዝ የኢሕአፓን፥ የኢሠማን፥ ...መዘተ ጥያቄዎች ሲያስተጋቡ እነኃይሌ ፊዳ ግን ድጋፋቸውን በመግለጽ የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት ለደርግ አስተላለፉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍፍሉ ጥልቀት ያለው አልነበረም። እንዲያውም ኢሕአፓዎችና ድልዳላቸውን ውጭ ካደረጉት ከእነ ኃይሌ ቡድን ጋር የተተሳሰሩቱ የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። በእነ ኃይሌ ፊዳ ደጋፊዎች ይበተኑ የነበሩትም ወረቀቶች የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን ጥያቄ ያስተጋቡ ነበር። ሆኖም ይህ ዝምድና እነ ኃይሌ ፊዳና ሌሎች ከሰዳት ሲመለሱ

ማብቂያው ሆነ። "ያፈነገጡት" ተባረሩ ወይም ከሐሳፊነት ወረዱና ከደርግ ጋር ለመቀራረብ ተጨባጭ እርምጃዎች ተወሰዱ። ግንቦት ፲፱፻፷፱ ላይ በእንግሊዘኛ የወጣ አንድ የመኢሶን ጽሁፍ በጊዜው የነበረውን ሁኔታ በንዚህ ቃላት ያስረዳል፤

> «.. ከየካቲቱ አብዮታዊ ንቅናቄ ጀምሮ እስከአንድ ዓመት ድረስ የመኢሶን የፖለቲካ መሥመር ከኢሕአፓው ጋር አንድ ዓይነት ነበር። የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ላይ መሥመራችንን እንደገና በጥንቃቄ ከመረመርን በኋላ ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ መምጣት ነበረበት። በተጨማሪም በድርጅታችን አመራር ውስጥ ለውጥ መደረግ ነበረበት።» (ገጽ 14)

ኃይሌ ፊዳና ሌሎቹ ከመጡ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ በኢሕአፓና በእነሱ ቡድን መካከል ንግግር ለማድረግ ሙከራ ተደርጎ ነበር፤ ተሞክሮም አልቀረ፤ የምሥጢር ውይይቶች ተካሄዱ። (ተሥፋዬ ደበሳይ ኢሕአፓን ሲወክል፣ ኃይሌ ፊዳ ደግሞ በኋላ መኢሶን የተባለውን ድርጅት ግን ያን ጊዜ የሠራው ሕዝብ ድምፅ በሚለው የጋዜጣ ልጣን የሚታወቀውን ወገን ወክሎ ቀረበ) ግን ኢሕአፓ ሆነ ኃይሌ ፊዳ ቡድን ደርግን በመደገፍ አትሞሙ ስለአናና "ኢሕአፓም" ከደርግ ጋር ለማበር እየወሰነ ነው። የሚል ፈጠራም ጨምር ስለውይይቱ ወሬ ስላወጣ ንግግሩን አቋረጥኩ ይላል። ኢሕአፓ ተቃዋሚ፣ መኢሶና ደግሞ የደርግ አባሪ ሲሆን መለያየቱ ፍጹም ወደመሆኑ አመራ።

መኢሶን

ምንም እንኳ የሠራው ሕዝብ ድምፅ የተባለው ልሳኑ ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. ጀምሮ ይወጣ የነበረ ቢሆንም እንደፖለቲካ ድርጅት ብቅ ያለው በመጋቢት ፲፱፻፷፰ ዓም ነበር። ድርጅቱ ሊቀመንበር ያደረገው ረጅም የስደት ጊዜ በስዊዲን አገር ያሳለፈውን በአውሮፓው የተማሪዎች ማኅበር

ቅርንጫፍም የተባ ተሣትፎ የነበረውን ከበደ መንገሻን ነበር። ከመኢሶን መሪዎች ይበልጥ የታወቀው ኃይሌ ፊዳ፣ ከፍቅረ መርዕድ፣ ከነገደ ነበዚና ከሌሎች ጋር ረጅም ጊዜ ፈረንሳይ አገር በስደት የኖረ ነበር። እንዳርጋቸው አሠግድና ሌሎች ዝቅተኛ ካድሬዎች ከምዕራብ ጀርመን የመጡ ሲሆን፣ ከሞስኮ ደግሞ ንግሥት አዳነና ባሏ ደስታ ታደሰ ነበሩ። የደስታ ወንድም ዳንኤል ታደሰም የመኢሶን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር።

መኢሶን ምንም እንኳ ራሱን ፓርቲ ብሎ ቁልጭ ባለ መልክ ባያስቀምጠውም እንደግርከሳዊ ሌኒናዊ ድርጅት አድርጎ ራሱን የሚቆጥር ሲሆን፤ ቀደም ሲል እጀግመራ ላይ ከቻይና ጋር የተቀራረበ ነበር። ቻይና አዲስ አበባ ውስጥ ለነበረው ለኃይሌ ፊዳ "ተራማጅ ቤተ መጻሕፍት" በብዙ ሺ የሚቆጠር መጻሕፍት (በነጻ) ልካለች። (ቤተ መጻሕፍቱ አባላት ለመመልመያ ያገለግል ነበር) እንደሚባለው ኃይሌ ፊዳ ነበር በመመሥረት ላይ የነበረውን ሚሊሺያ ለማስታጠቅ ቻይኖችን ለመጠየቅ በምሥጢራዊ የቢጅንግ ጉብኝት ከመንግሥቱ ጋር የሄደው። ቻይና ፩፻ሺህ ጠመንጃዎች ለማቅረብ ስትስማማ ፲ ሺ ውን አሰረከባለች።(29) የመኢሶን አቋም ለደርግ "ሂሳዊ ድጋፍ" መስጠት ነበር። ሁኖም የዚህ ቀመር ሂማዊ ገጹ የታየበት ጊዜ ለመኖሩ ግልጽ የሆነ ጭብጥ አልነበረም። መኢሶን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ማለት ስህተት ነበር፤ ከዚያ ይልቅ በቅድሚያ «ሕዝቡን ማንቃት፣ ማደራጀትና ማስታጠቅ» ያስፈልጋል፤ ብሎ ከርከሩን አቀረበ። ከዚያም ተነሥቶ ኢሕአፓን፣ ኢሠማንና ሌሎች የደርግን አገዛዝ የተቃወሙትን እንደ "ጽንፈኞች" ቆጠራቸው። በኤርትራ ጥያቄም ላይ መኢሶን እቋሙን በመቀየር የኤርትራ አርነት ግንባርን «የአረብ አድኅሮትና የኢምሪያሊዝም መሣሪያዎች» ብሎ አወገዛቸው። ከዚህም በላይ ከፍለሀገራዊ የራስ ገዝ አሠራርን እንደመፍትሔ አድርጎ በማጣጣ፥ በመተክሳዊ ደረጃ አንኳን የመነጠል መብትን የሚከለክለውን የብሔራዊ አብዮት ፕሮግራምን አረቀቀ። መኢሶን በ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ኤርትራ ላይ የተዘመተውን የራሳ ወይም የአርሶ አደር ዘመቻ ጠንሳሽ እንደነበረ ማከሉ በቂ ይሆናል።

መኢሶን ኢሕአፓን እንደቀንደኛ ደመኛው አድርጎ በመመልከት ለማጥፋት ይችል ዘንድ ማንኛውንም ዘዴና

መንገድ በመጠቀሙ ከተጠያቂነት አያመልጥም። ኃይሌ ፊዳ ራሱ፥ ቃሉ በሚያሰማው በጠባቡ መንፈስ የአርሞ ብሔረተኛ (ሁኖ) ባያውቅም፥ኢሕአፓ እንደ መኢሶን ሁሉ ብዙ ብሔራትን ያቀፈ ሁኖ ሳለ መኢሶን "የአማራና የትግራይ ኢሕአፓን" ለመታገል በሚል የአርሞ ብሔረተኝነትን ወደማንሣሳት ተሠማርቶ ነበር። በሌላ ደረጃ ደግሞ የፖለቲካ ውዝንቦችን ለመፍታት በኃይል የመጠቀም አካሄድ ሲቀር በሚችልበት መንገድ ደርግ ላይ በተለይም መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ረገድ መኢሶን ያደረገው አልነበረም። እንዲያውም በተቃራኒው መኢሶን ነበር ተቃዋሚዎች እንዲመቱ ጥሪ ያደረገውም በግንባር ቀደምም የመራው። ከዚህም የከፋው "አናርኪስቶች" የሚል ሁሉን የሚያጸዳር አመች ቅጽል በመስጠት ቁጥር የሌላቸው ዴሞክራቶችና ታጋዮች ባንድ ላይ ተቀይጠው ሲገደሉና ለሲያል ሲጸረጉ የመኢሶን መሪዎችና አባላት ተሣታፊ ሆነዋል። የግራ የንግግር ዘይቤዎች የቦልሸቪክ ተመክሮዎችን ለጭፍጨፋ ማጠየቂያ ማድረግ፥ አድምን ማከረርና ግፉም እንዲቀጠል ማድረግ ሁሉ ዱካቸው ወደመኢሶን ደጃፍ የሚያመራ ነው።

የሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ውስጥ ራሱን በማደላደልና የተሰጠውንም ሥራ ሥልጣን በመጠቀም መኢሶን በአጭር ጊዜ አባላቱን ሊያበራክት ቻለ። እስከተመታበት ጊዜ ድረስም ደርግ ካወጣቸው ፖሊሲዎች ጋር ሙሉ በሙሉ ራሱን አዛምዶ አቅርቧል። ለነገሩ፣ የደርግ ፖሊሲዎች በአብዛኛው በመኢሶን የተረቀቁ ነበሩ። መኢሶን ከሞስኮ ጋር ያደረገው የትብብር ስምምነት ዘላቂ ይሆናል በሚል እምነት ከደርግ መኰንኖች ጋር ግጭት ቢፈጠር ከሬምሊን ከጀርባዬ ይቆማል የሚል ሐሳብ ነበረው። ከደርግ ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ ስለራሱ ዓቅም የተሳሳተ ግምገማ እንደነበረው ሁሉ በዚህ ነጥብ ላይ የነበረውም ሥሌት የተሳሳተ ነበር። በሕዝብ አደራጅ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ውስጥም በአቅሙ ይታበይና ሌሎች ቡድኖች በጥላቻ እንዲርቁት ያደርግ ነበር። ይህም ሁኔታ (መኢሶን) ከደርግ ጋር ግጭት ውስጥ በገባበት ጊዜ የወዝ ሊግና የኢሜሌዲን አባሎች የመኢሶንን አባሎች የሰደድ ስኳዶች እድነው እንዲይዟቸው እስከመርዳት አድርሷቸዋል።

መኢሶን የፈለገውን ያህል አሌ ብሎ ይከራከር፣ ለወታደሪዊ አገዛዝ መቀጠል የቆመ እንደነበር የማይታበል ነው። አቅሞሙ አድርባይነት ላይ ከተመሠረተ የሁኔታ

ግምገማ ላይ ተንሥቶ ቢያንስ ከደርግ እንዱ ክፍል ጋር (በዋናነት ከመንግሥቱ ኃ/ማ ቡድን) በማበር ወደሥልጣን ለማሻቀብ እችላለሁ ከሚል መደምደሚያ ላይ ያደረሰው ይመስላል። መኢሶን ኢሕአፓ ላይ የሚፈጸመው ግፍ እንዲፋፋም በመሪህ በዋና ዋና ከተሞች ገንና የነበረውን ተቃውሞ ለማስወገድና የራሱን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ነጻ መስክ እንዲያገኝና በተማሪዎች በምሁራንና በሠራተኞች ..ወዘተ ላይ የበላይነቱን ለመጫን እንዲያስችለው ነበር ምኞቱ። ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ላይ እኒህ ክፍሎች (ተማሪዎች፣ ምሁራና፣ ሠራተኞች ..ወዘተ) ከመኢሶን ይልቅ ይበልጥ የሚደግፉት ኢሕአፓን እንደነበር ግልጽ ነበርና። ኢሕአፓ በበጎ ዓይን ይመለከታል ተብሎ የማይጠረጠረው የአፍሪካ ኮንፌደንሻል እንዳስቀመጠው፤

> "የደርግ ድክመቶች በራሱና በመኢሶን ላይ ጥላቻ እንዲታከል ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ደርግ ተወግዶ ወዲያውኑ ጊዜው ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ለሚጠይቀው ኢሐአፓ ድጋፍ እንዲጨምርለት አስደርገዋል። ለብዙዎቹ ይህ (የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ሐሳብ) ጥሩ ሐሳብ ሲመስላቸው፥ እጅግ ተወዳጅም የሆነውን አብዮት ለመንከባከብ አማራጭ የሌለው መንገድ ሆኖ ሊታያቸው ጀምሯል፥፥ በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል ያለው ትግል ያለምንም ጥርጥር ይብልጥ ድጋፍ ላለው ለኢሐአፓ በተመቸ መንገድ ካልተፈታና ቢያንስ ኢርቱዕ በሆነ መንገድ ሥልጣን ላይ ካልወጣ አብዮቱ ራሱ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ብዙዎቹ ይሰማቸዋል"። (31)

መኢሶን ÷ ኢሕአፓ የበለጠ ድጋፍ እንደነበረው በማወቅ ይህንን ለመለወጥ ዓይነተኛው መንገድ ኢሕአፓን ማስወገድ ነው ብሎ ወሰነ። እንደዚያ ዓይነቱ ሂደት የራሱ መጥፋት የሚከተልበትን መንገድ እንደከፈተ አላስትዋለውም ነበር። በመኢሶን፣ በደርጉ ለደድና በሌሎች ትናንሽ ቡድኖች የተመሠረተው የኅብረት ግንባር ለዕኩልነት ዋስትና የሚሠጥ አልነበረም። መኢሶን ከደርግና ከፖሊሲዎቹ ጋር ራሱን ሙሉ በሙለ ማዛመዱ ከዐረደርግ ኃይሎች ጥላቻን እንዲያተርፍ ነው ያደረገው። ሽብሩ ሲጀመርና ለዚህም መኢሶን ግንባር ቀደም ሆኖ ሲመጣ እንዲያውም ቁጥሩ የጨመረ ሕዝብን ጥላቻ አከበተ። ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የቀይ ሽብር ሰለባ

ሆነው የወደቁባቸው ቤተሰቦች፣ እሥር ቤቶች ውስጥ የሚንገላቱት እሥረኞች ዘመዶችና ይህን መንግሥት የሚጠሉ ሁሉ መኢሶንን እንደ"ባንዳ" ወይም እንደከሃዲ ይመለከቱታል።

መኢሶንና ሰደድ በተጋጩ ጊዜ የመኢሶኑ ሊቀመንበር ከበደ መንገሻ እንመንግሥቱ ቡዱን ላይ ፋወላኝ እርምጃ። እንወሰድ ሲፈልግ ኃይሌ ፊዳ ግን የተሳሳተ ፖሊሲ ነው በሚል ብዙኃኑን አሳመነ። ታዲያ መኢሶን ነገ ዛሬ ሰደድ አፈፍ ብሎ የመኢሶን አባሎችንና መሪዎችን መምታት ጀመረ ። ሰይል በመፈጸም ስመ ጥሩ የሆነው የመኢሶን መሪ አብዱላሂ ዮሱፍ በጥይት ሲወድቅ በመንግሥት ሬዲዮ ኢሕአፓ እንደገደለው ተደርጎ ቀረበ። ለመኢሶን አድራጊዎቹ ሰደዶች መሆናቸው አልጠፋውም። ሁኔታውን ለመገምገም አስቸኳይ ስብሰባዎች ተደረጉ። በእንዲህ ዓይነቱም የአዲስ አበባው ፍል ውኃ ሆቴል ውስጥ በተደረገ እንድ የአመራር ስብሰባ ላይ እንድ የአመራር አባል እንዳስጠነቀቀው «ምንም እንኳ ኢሕአፓም ጎበዙ ዓለም ውስጥ በመኖሩ እደጋ የሚያመጣ ቢሆንም። በጎበዝ ለመንቀሳቀስ ተወሰነ። መኢሶን የጎበዝ አውታራት ስላልነበሩት በደርግ በቀላሉ ሊፈታ ሲችል፣ ከበላይ አመራሮች ሁለት ብቻ (ነገደ በወቅቱ ውጭ አገር የነበረና፣ እንዳርጋቸው ማሞለጥ የቻለ) ነበሩ የተረፉት። የመኢሶን ጥንካሬ የማይጨበጥ ራዕይ እንደነበር አባላቱና (የተረፉት) መሪዎቹ ደርግና ሰደድን ለመቀላቀል ያደረጉት ሩጫ ያረጋግጣል።

መኢሶን ኢሕአፓን ደመኛው አድርጎ እንደሚመለከተው ሁሉ በኢሕአፓም በኩል ያው ነበር። ኢሕአፓ በተጨማሪ በበኩሉ ያሰማው የነበረው ያለመኢሶን ድጋፍና ምክር ደርግ ለጥቃት ግብዝ ሊሆን ይችልእንደነበር ነው።

ኢሕአፓ

በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን እሱ ራሱ እንደሚያምነው ፓርቲው ደካማና የመሪነት ሚና ለመጫወት ያልተቻለው ነበረ።(31) ሆኖም በየካቲትና ወዲያውንም ከዚያ ቀጥሎ ፓርቲው ጠንካራ ሆኖ ለመውጣት ችሏል። ልሣኑ የሆነው ዲሞክራሲያ እጅግ ተወዳጅ የነበረ ሲሆን ÷ ደርግን

ተቃውሞ የቆመው ኑቃ ያለው የሕዝብ ክፍል ኢሕአፓን የቀድሞውን ንጉሥ ነገሥት ያመሳቸውን ያ የተማሪው ታጋይነት ቅጣይ እንደሆነ አድርጎ ተመለከተው። በድንገ የካቲቱ ሁኔታ በ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ኢሕአፓ የኢንተርዞን፡ የዞንና የንዑስ ዞን መዋቅሮችን በትላልቅና በትናንሽ ከተሞች እንዲሁም በገጠሩ ዘርግቶ የነበር ሲሆን የሽምቅ ተዋጊ ቡድን አሲምላ ላይ ትግራይ ውስጥ ለመትከል ችሏል። (ምንም እንኳ የቡድኑ መኖር ባይታወጅም ወይም ስም ባይሰጠውም) በዚያን ጊዜ የኢሕአፓ ተወዳጅነት ያደገው ነፍሰገዳይ የሆነውን መንግሥት ስለተቃወመ ብቻ ሳይሆን፣ በዋናነት የሕዝቡን መሠረታውያን ጥያቄዎች በትክክልና በግልጽ ለማቅረብ ስለቻለ ነበር። ኢሕአፓ ለዴሞክራሲያውያን መብቶች፡ ለመደራጀት ነፃነት፡ ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት፣ ለድኃ አርሶአደሮች መታጠቅ፣ ለአርሶ አደሮችና ለከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ማቋቋም መብት፣ ለሙቁን ብሔሮች መብት መረጋገጥ ... ወዘተ ያቀረበው የጥሪ አቅዋም ለሠራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ለምሁራንና በተወሰነ ደረጃም ለአርሶአደሮች ደርጎ ካቀረበው ይልቅ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ታያቸው። የሥር ነቀል ለውጥ ከተነሣ ደግሞ ምርጫቸውን ያን ያደረጉ፣ ከደርግ "አዲስ አማኞች" ይልቅ ኢሕአፓን ማመኑ የቀለለ ሆኖ አገኘተውታል።

ከዚህም በተጨማሪ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ግራ ላይ በአጠቃላይ ተጽዕኖ ከነበረው "ለአብዮታውያን ፓርቲዎች) ለብቻቸው የተለየ የግንባር ቀደምንት ሚና ከሚሰጣቸው አፈሌላዊ ቀኖና ጋር የሚገረር ሊሆን ቢችልም የኢሕአፓ ፕሮግራም ብዙ ፓርቲዎች የሚማተፉበትን ሥርዓት ነበር እንዲመሠረት የተለመው። በዚያን ጊዜ የኢሕአፓ አመራር በከተማው የፖለቲካ ትግል ላይ ትኩረቱን አድርጎ የገጠሩን የሽምቅ ተዋጊ ኃይል ለማጠናከር ወይም ለማጀጅ በቂ እርምጃ አልወሰደም:: "ሰላማዊው መንገድ አስከሚያስኪድ ድረስ መሞከር አለበት። የሚል ነበር የአመራሩ መሥመር። ይህም «ይበልጥ ግራ» በሆኑት አባላት ዘንድ አዎኖታዊ በሆነ መንገድ አልታየም። በመሠረቱ ኢሕአፓከልክ በላይ እያደገ ሲመጣ ችግሮችም በዚያው መጠን እደጉ። በርካታ የሆኑ ወጣቶች ወደወጣቱ ሊግ (ኢሕአወሊ) እና ወደፓርቲው መጉረፋቸው ይዞት የመጣው የተወሰነ ደረጃ ጽንፋዊነት ነበረው። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ሠፊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር መቋቋሙ ከኅቡዕ መዋቅሮቹና ሥራ ጋር

ይጋጭ ጀመር። ይኸው ዕድገት በተጨማሪም በፓርቲው በራሱ ውስጥ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት አመጣ። ጥቂት አባሉቹ ባገር ቤትና በአሚሪካም ሙምር) የኢትዮጵያን ሁኔታ ሰክን ብለው ለመተንተን ምንም ዝንባሌ ያልነበራቸው «ሐሳብ ግትር ማኦዋውያን» ነበሩ። ሌሎች ደግሞ የከተግው የፖለቲካ ትግል ራሱን ችሎ የደርግን ድቀት ሊያመጣ ይችላል ብለው የሚያስቡ ነበሩ። በተወሳሰበና በፍጥነትም እያደገ በሚሄድ ሁኔታ የፓርቲው አመራር በተሟላና ፖለቲካዊ በሆነ መንገድ የፓርቲውን አጽሞች ለማስረዳት አልቻለም። በጊዜ መሳብ የነበረባቸው መፈክሮች አልተሰቡም ÷ አዳዲስ አጽሞችም እስከ ሙሉ ዝርዝራቸውና አንደምታቸው መግለጫ አልተሰጠባቸውም::(32)

ኢሕአፓ በደፈናው ሲታይ ተማሪዎችና ምሁራን ጉልተው የሚታዩበት ነበርፒ ግን እንዚያ፣ ኢሕአፓ የተማሪዎች ፓርቲ ነበር የሚሉቱ አጠቃላይ መልኩን አላዩትም። ኢሕአፓም ሆነ መኢሶን የተማሪ ፓርቲዎች አልነበሩም። ሕዝባውያን ድርጅቶች አልነበሩም ብሎ አፍን ሞልቶ መናገርም ከእውነታው የራቀ ነው። በመሠረቱ፣ ኢሕአፓ ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም እስከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም መኢሶን ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.÷ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ከልዩ ልዩ ከፍል የመጡ መጠናቸው በርካታ የሆነ አባላትን ያቀፉ እስከሆኑ ድረስ ሕዝባውያን ፓርቲዎች ነበሩ። ነገሩን እንላብጠ በመመልከት፣ በዚህም ምክንያት ነው ድርጅታዊ ግገራቸው ላልቶ በአንፃራዊ ደረጃ ቀላል ዒላማዎችና የማፍ ጭጻዎች ሊሆኑ የቻሉት ማለት ይቻላል::(33) ኢሕአፓ በአዲስ አበባና በዋና ዋና ከተሞች ጠንካራ ነበር። (በአሥመራ ከተማ እንኳ የመንግሥት ሠራተኞችን፣ መምህራንን፣ ሳብአደሮችንና ወታደሮችን ... ወዘተ ያቀፈ የፓርቲ መዋቅር ነበር) በገጠሩ አካባቢ ጠንካራ ድርጅታዊ ሥራ የነበረው ÷ በሸዋ÷ በክፉ÷ በሲዳሞ÷ በጎንደር በአንዳንድ የጉጀም ክፍሎች፣ በወሎና በሐረርጌ ነበር። የኢሕአፓ አመራር ከልዩ ልዩ ብሔራት የተውጣጣ ነበር። (ነውም) ከዚሁም ዘንድ ኢሕአፓ በትራጌዎች (ከፓርቲው ጋር ግንኙነት የነበረው ብጉሂን (የጉራጌ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) በውስጣቸው የተባ እንቅስቃሴ ያደርግባቸው የነበሩ በከምባታዎች÷ በሃዲያዎች÷ በትግሬዎች ዘንድ በአንጻራዊ ደረጃ ጠንካራ ተቀባይነት ነበረው። በክፉና በሐረርጌ አሌ ሊባል የማይችል ተወዳጅነቱ ከአሮሞ ታጋዮች ሠፊ ድጋፍ እንዳተረፈለትም አቶን ሞልቶ መናገር

የሚያስችለው ነበር። ሙክሹላ ይባል የነበረውን ጎቡዕ ጋዜጣ ያወጣ የነበረው የኦሮሞ ሕዝብ እርነት ድርጅት፣ ሲኢሕአፓ ሙሉ ድጋፍ ይሰጥ እንደነበረው እንደአዲስ አበባ የእስላም ወጣቶች ማህበር ሁሉ ከፓርቲው ጋር ተቀራርቦ ይሠራ ነበረ። (34)

ኢሕአፓ ጎልውናውን ገንድ ያደረገው ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ነበር። (ከዚያ በፊት ዲሞክራሲያ በተባለው ጋዜው ነበር የሚታወቅ።) ቀደም ሲል ግን በሐምሌ ወር አዲስ አበባ ውስጥ ከወትሮው ሠፋ ያለ ልዩ የፓርቲ ኮንፈረንስ በመጥራት የፓርቲው ስም ኢሕአፓ እንዲሆን፥ ማዕከላዊ ኮሚቴ እንዲሠፋ፥ በ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. የፖለቲካ ፕሮግራም ወግ ባለው መልክ እንዲሻሻል ተደርጓል። ከኮንፍረንሱ በፊት አብዮት የሚባል ጋዜጣ (በአማርኛ) ያወጣ የነበረው ቡድን ፓርቲውን ተቀላቅሎ ነበርና ከቡድኑ ሁለት አባሎች የማዕከላዊው ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ ተደርጓል። ከፓርቲው አወጀ ጋር የተሠራጨው የፓርቲ ፕሮግራምና የዲሞክራሲያ ልዩ እትም ሥርጭቱ ሥፋት የነበረው ከመሆኑም በላይ ያለምንም እክል ሊካሄድ ደርግንና መኢሶንን ድንጋጤ ውስጥ ከትቷቸው ነበር።

ከተከታዩ ትግል አንጻር ኢሕአፓ በተጨባጭ መልክ የወሰዳቸው እጅግ ከፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራም ጋር በተሠራጨው ከፍ ብሎን በጠቀስነው የዲሞክራሲያ እትም (ቅጽ ፪ ቁ ፫) ላይ ይገኛል። እትሙ «በጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴን የአቋም መግለጫ» ይዟል። የወታደራዊውን መንግሥት ድከመት ከጠቀሰ በኋላ እንዚያን ጥያቄዎች ለመፍታት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራል። እነሱም፤

1. በፀረ ፊውዳልና ፀረኢምፐሪያሊስት ፖለቲካዊ ድርጅቶች፣ ቡድኖች ሕዝባውያን ድርጅቶች፣ ኢሠማ ፣ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከጦር ኃይሎች በተመረጡ ወኪሎች፣ በመምህራን ማህበር፣ በአርሶአደር ማኅበራት ... ወዘተ በሚመሠረት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ወታደራዊውን መንግሥት መተካት፣
አብዮቱን ያካሄዱትን፣ መቀጠሉንም ሊያረጋግጡ የሚችሉትን ማኅበራዊ መደቦችና ኃይሎችን የሚወክልና ሊወክልም የሚችል ሕዝባዊ ሸንጎ ማቋቋም፤

2. መሠረታውያን ዲሞክራሲያውያን መብቶችን ማወቅ_
እነዚህም ነጻ ሆኖ የመናገርና ሐሳብን በጋዜጣ የመግለጽ፣ የእምነት፣ የመሰብሰብና የመደራጀት ... ወዘተ ናቸው።ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚታገሙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የፖለቲካ ቡድኖች የመደራጀትና ይህንኑ በሥራ ላይ የማዋል መብት ይገባቸዋል።

3. ታጋይ የፖለቲካ እሥረኞቹ ሁሉ መፈታት ይገባቸዋል።

4. የኤርትራ ጥያቄ በዲሞክራሲያዊና በሰላማዊ መንገድ መፈታት ይኖርበታል፤ ይህንንም ዕውን ለማድረግ፣
– ጦርነቱ እሁኑኑ መቆም ይኖርበታል
– የኤርትራ ብሔርተኛ የፖለቲካ እሥረኞች መፈታት ይኖርባቸዋል፤
– ኤርትራውያን የራሳቸውን ዕድል ለመወሰን ያሳቸው ገደብ የሌለው መብት መታወጅ ይኖርበታል፤
– የኤርትራን ትግል ከሚመሩት የኤርትራ ግንባሮች ጋር ቀጥተኛ ንግግር መጀመር ይኖርበታል፤

5. ከአድኃሪያን ራሳቸውን ለመከላከልና አብዮቱን ከጎብ ለማድረስ ይችሉ ዘንድ የሠራው ሕዝብ አካሎች (እርሶ አደሮች፣ ሠራተኞች፣ ዘማች ተማሪዎች ... ወዘተ) መታጠቅ ይኖርባቸዋል።፤

6. የሕዝቡ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች መሟላት ይኖርባቸዋል።
ሀ. የሠራተኞች ዝቅተኛ ደሞዝ በሕግ ወደ፬ ብር በቀን ከፍ ማለት ይኖርበታል፤
ለ. የሠራተኞች የደሞዝ ስኬል መሻሻል ይኖርበታል፤

7. ሀገሪቱ ከየትኛውም ዓይነት ኢምፐሪያሊዝም ግንኙነት ነጻ መሆን ይኖርባታል፤ ለዚህም፤
ሀ. ዕኩልነት ላይ ያልተመሠረቱ ውሎችና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች መሠረዝ ይኖርባቸዋል፤
ለ የውጭ ወታደራዊ ቢዞች መዘጋት፣ ሠራተኞቻቸውም መባረር ይኖርባቸዋል፤

እነዚህ ነበሩ፥ በአጠቃላይ መልክ ኢሕአፓ ይታገልባቸው የነበሩ ነጥቦች። ሕዝቡ ኢሕአፓን ሲደግፍም እኒሁ ነጥቦች

ከፍሳኑቱ ጋር ስለተዛመዱ ነበር። ምንም እንኳ ደርግ መኢሶንና ኢሕአፓ አፍአዊ መመሳሰል ቢታይባቸውም፥ በፖለቲካ ረገድ በፕሮግራም እኳያ መሠረታዊ የሆነ ልዩነት ነበራቸው። በዲሞክራሲ ጥያቄ እንኳን ዲሞክራሲያ (ቅድ ፪ ቁ ፪ ሚያዚያ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም) እንዳስረዳው ልዩነታቸው ከባድና መሠረታዊ ነበር። አብዛኛውን ነገር ቀረጣጥፈውና እስከተቻለ ድረስ አሳንሰው በሊጣው ለማየት ለሚፈልጉ፣ ከኢሕአፓ አቋሞች ለደርግ ያልተዋጠለት፣ ወታደራዊ መንግሥት በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይተካ ማለቱ ሙሉ ዲሞክራሲያውያን መብቶች ይከበሩ ማለቱና (በተለይም የመደራጀትና የማኅበር ማቋቋም) ኢሕአፓ ለብሔር ትግሉች ያለው ድጋፍ፥ ናቸው ማለት ይቻላል።

ኢሕአፓ ላይ ጦርነት በታወጀ በዋዜማው በመላ ሀገሪቱ ፓርቲው ትልቅ ተደማጭነት እንደነበረው ግልጽ ነበር። ከነቃው የኅብረተሰብ ክፍል ያገኘ የነበረው ሠፊ ድጋፍ ለእቋሞቹ ጥንካሬ ሰጥቷቸው ነበር። ኢሕአፓ ለዲሞክራሲያውያን መብቶችና ከላይ ለተጠቀሱት ነጥቦች ይበልጥ በታገለ መጠን በዚያው ልክ ደርግ እሻፈረኝ በማለት በግፍ ላይ ግፍ እየጨመረ ራሱን ይበልጥ ለሕዝባዊ ተቃውሞ አጋለጠ። በወቅቱ የነበረው ሁኔታ ይህ ሲሆን ደርግ ደካማም ነበር። መስሎም ይታይ ነበርና ሥልጣኑን ለመከላከል ይችል ዘንድ መልሶ ለማጥቃት አንድ መንግሥት ለመፈናጠር ያለው ችሎታ ላይ ተቃዋሚው ወገን የተሳሳተ ግምገማ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።

ኢሕአፓ በዚህ ረገድ ደርግ ሊኖረው የሚችለውን ኃይል እንኳስሶ የማየት ስህተት ፈጸመ። ከዚህ የከፋውም አመራሩ፣ በተለይ ፖሊት ቢሮው በከተሞች ውስጥ የሚካሄድ ቁርጠኛ የሆነ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ትግል ቢያንስ መንግሥቱን ያዳክመዋል የሚል ሕልም ውስጥም ገባ። እነሆም እንደራስ መከላከያ እርምጃ የተጀመረው የከተማ የትጥቅ እርምጃ ቢያንስ በአፈሌል ደረጃ መሠረታዊ ተደርጎ የተወሰደውን የገጠሩን የትጥቅ ትግል እስከሚጎዳበት ድረስ ተስጠጠ! ተስፋፋም። ሶቪየት ኅብረትና ባልደረቦቿ ደርግን መደገፍ ሲጀምሩ የሥልጣን ሚዛን በግልጽ ወደደርግ እያጋደለ ነበር! ግን ኢሕአፓ ከባድ መሥዋዕትንት በሚጠይቀው የከተማ ትጥቅ ትግል ገፋበት። በእፍአ ከገጠሙት ችግሮች ባሻገር ውስጣዊ እምሳትን እየተጋፈጠ ነበርና በወቅቱ የከተማውን እርምጃ መሳቡ ተገቢ በሆነ

ነበር:: (35) ፓርቲው ያንን አሳደረገም፥ ዋጋው- ሁኔታዎች እንዳሳቡት – በርግጥ ከፍ ያለ ነበር። የግፉ አስቃቂነት ኢሕአፓን ካጥለቀለቁት አባላት ውስጥ አይቀሬ ለነበረው ትግል ፈጽሞ ዝግጁነት ያልነበራቸው እንደነበሩበትም አሳየ። የከተማ መዋቅሮችም ክፉኛ ተበጣጠሱ። «የበታኞች ዘመቻ» እኳል ሆኖ የመጣ ብሎ ፓርቲው የሚጠራው ችግር እንደገና በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም በገጠሩ የትጥቅ ትግል ውስጥ ገጥሞት ፓርቲው ላይ ከባድ ጉዳት ደረሰበት።

በሽብሩ ዘመቻ ውስጥ ያባቶቹ አስላለፍ ደርግና መኢሶን በአንድ ወገን፣ ኢሕአፓ፣ ኢሠአማና ሌሎች ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት የነበራቸው ቡድኖችና ብዙኃን ድርጅቶች ደግሞ በሌላው ወገን ነበሩ። በደርግና በመኢሶን ወገን ሥስት ትናንሽ ድርጅቶችም ነበሩ።

ወዝ ሊግ

የተመሠረተውና ይመራ የነበረው በሠናይ ልኪ፣ ሽዋንዳኝ በለጠና በሌሎች ሲሆን ፍጹም ሥልጣን በለበሰ የሠናይ ልኪ ሰብእና ሥር የወደቀ ቡድን ነበር:: ጥቂት አባሎች በእየር ኃይልና በአንዳንድ የጦር ክፍሎች ውስጥ ነበሩት። ቡድኑ በአደራጅ ጽ/ቤት ውስጥ ጥንካሬ ባይኖረውም ሠናይ ልኪ በመንግሥቱ ኃይለማርያም በቅርብ ጓደኞቹ ዘንድ ተሰሚነት ነበረው::

ኢሜአት

በባሮ ቱምሳና በዘገየ አስፋው ነበር የሚመራው። ባሮ የፋርማሲ ምሩቅ የሆነ የወለጋ ተወላጅ ሲሆን ተግራራ የፖለቲካ ዓላማዎች ካኋቸው ከልዩ ልዩ ቡድኖች ጋር ራሱን የሚያቧድን ፖለቲካዊ አስስት ነበር። የኢሜአት አባላት በአብዛኛው አሮሞዎች ሲሆኑ ደጋፊዎቹ አንስተኞች ነበሩ፤ ታዲያም ተሰሚነቱን ከፍ ለማድረግ አክራሪ የሆኑ ብሔርተኛ አቋሞችን ወደመያዙ አምርተው ነበር። ሆኖም ያንኑ ታና ያሰሙ በነበሩት በነመኢሶንና ሰደድ ድምፃቸው ተውጦ ተሰሚነት ሊያገኙ አልቻሉም። ዘገየ አስፋው ባሁኑ ጊዜ

እሥር ቤት ውስጥ ሲሆን፤ ባሮ ቱምሳ ከደርግ ከሸሸ በኋላ ሐረር ውስጥ አብሮት ይሠራ በነበረ አንድ አክራሪ የእስላም አሮሞ ብሔርተኛ ቡድን ተገድሏል።

ማሊሬድ

ከኢሕአፓ (፲፱፻፷፯ ዓ.ም) ከድተው ደርግን በተቀላቀሉ የተመሠረተ ትንሽ ቡድን ነበር። ለሱ ቢመስለውም «መልእክቱን» ግስተላለፍ ያልቻለ ቡድን ነበር። ብዙም ሰው ፕሮግራሙን ልብ አላለውም። ከቡድኑ መሪዎች ጥቂቶቹ ዳሚት እሠፋ፣ አበበ ኃይሌ፣ ኃይለኢየሱስ ወልደሰንበት፣ ተስፋዬ መኩንን የሚባሉ ነበሩ። መኢሶንና ኢሮአት ከተወገዱ በኋላ ወዝሊግና ማሊሬድ ጎላ እያሉ መምጣት ጀምረው ነበርI ነገር ግን ሪጅም ጊዜ አልቆየም እነሱንም ደርግ ሲያጠፋቸው።

እነሆ የጦርነቱ ወረዳ ተለየ። የደርግና የመኢሶን ካምፕ የደም ያለህ ብሎ ጮኸ። ኢሕአፓ በሚችለው መንገድ ሁሉ እንደሚከላከል ግልጽ አደረገ። አየሩን የእመቤ ትንፋሳት ወውደው በእርግጥም ደም ተንቆረቆረ፥ በየትኛውም ጎራ የነበሩት በእንድ ወይም በሌላ ዓይነት የተዛባ ኃልዮ (misconception) ውስጥ የመግባት ስሕተት ፈጸሙ።

፮

የሶቭየት ዝምድና፣

«በኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ስም፣ የዓለም የመጀመሪያይቱ የሶሻሊስት አገርና ለሠራተኛው መደብ ስተራግጅና ለብሔር አርነት ንቅናቄዎች የድጋፍ አምባ ለሆነው ለሶቭየት ኅብረት ፓርቲና መንግሥት፣ ስለተደረገልን ከፍታኛ የማቴሪያልና የሞራልድጋፍ ላመሰግን እፈልጋለሁ። ...»
መንግሥቱ ኃይለማሪያም መስከረም ፪ ፲፱፻፸ ዓ.ም

የአንድ የምሥራቅ አፍሪቃ ሀገር አምባሳደር በአዲስ አበባ የሶቭየቱን አምባሳደር በኢትዮጵያ አናቶሊ ራታኖቭን አበባ ውስጥ በተደረገ የኮክቴል ግብዣ ላይ «ቀይ ሽብር» በተጧጧፈበት ጊዜ አግኝቶት የሽብሩን ጉዳይ አንስቶ ከአብዮትና ከሶሻሊዝም ጋር እንዲት እንደሚሄድ ቢጠይቀው፣ ራታኖቭ ከፈሉ ቀልድን በያዘ አንጋገር «የአፍሪቃ ሶሺያሊዝም የራሱ የሆኑ ጠባዮች አሉት፤ የኢትዮጵያ አብዮትም ገጽታ ይኸው ነው።(37) ብሎ እንደመለሰለት ይታወቃል። ራታኖቭ ነገሩን ለምን እደባብሶ እንዳለፈ የምንረዳው ነው። በየካቲቱ የመንግስቱ ኃ/ማ የቢተ መንግሥት ውስጥ መፈንቅለ መንግሥትም ሆነ ኢሕአፓ ላይ በተከፈተው ሽብር ወቢይ ሚና የተጫወተ ነበርና።

የሶቭየት መሪዎች በታወከ ባሕር ውስጥ ዓሣ ማስገር ደስ ይላቸዋል፤ እንዲያውም የሞገድ ምልክቱ በማይታይበት ሞገድ

በመፍጠር የተካኑ ሞገደኞች ናቸው። በየካቲት ፲፱፻፷፮ በኢትዮጵያ ይካሄድ በነበረው ሁኔታ «በማም ተመስጠው» እንደነበር የሚካድ አይደለም። በአፍሪታ ቀንድ ላይ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ያላት ÷ መፍቀሬ እሚሪካ የሆነች ሕዝባዊ ቁጣ ገንፍሎ ሊያጠፋት እየቃጣ ያለበት÷ ለሥር ነቀል ለውጥ የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች በሙሉ እንሆኝ ያሉባት ሀገር ፍንትው ብላ ታየቻቸው። ግን ሶቭየቶቹ እንድ የገጠማቸው ችግር ነበር። ሁኔታውን እንዳሻቸው ለመጠምዘዝ የሚያስችላቸው ከነርሱ ጋር የተሳሰረ ኮምዩኒስት ፓርቲ አልነበረም። በሞስኮ ዓይን ምሁራኑ በአብዛኛው የማኦ ተከታዮች ሆነው ነበር የሚታዩት። በጦር ሀይሎች ውስጥ ሶቭየቶቹ ተሰሚነት አልነበራቸውም። የኢትዮጵያን «የወትር ጠላት» ሶማሊያን መርዳታቸውና መደገፋቸው፣ በኢትዮጵያውያን መኮንኖች ዘንድ ፍቅረኛ የሚያደርጋቸው አድራጎት አልነበረም። የሆነ ሁኖ አብዛኞቹ መኮንኖች መፍቀሬ እሚሪካ፣ ወይም መፍቀሬ እስራኤል፣ ቢበዛ ደግሞ ብሔራዊ ስሜት የነበራቸው ሲሆኑ፣ ለሶቭየት ኅብረት በጉ አመለካከት የሚኖራቸው አልነበሩም።

ጥሩ አጻኝ እድብቶ ይጠብቅና እውሬውን በጥንቃቄ ይቀርበዋል። ሶቭየት ኅብረትም ስለአብዮቱ ለብ ያለ፣ ለወጉ ያህል የሚደረግ መግለጫ እያወጣ አደባ። ደቡብ የመን ሁኔታውን እንዲገመግምለት በማድረግ በጥንቃቄ ወደፊት ተራመደ። ሲአድ ባሬ ካወጓጋቢው አካባቢ ጦሩን ይዞ ጓደኞቹ የመከሩትን አልሰማ ብሎ በኦጋዴን ውስጥ ችግር እንደተፈጠረ ለሶቪየት ኅብረት በሩ ተከፈተ።(38) ጂሚ ካርተርም ለኢትዮጵያ ጦር መሣሪያ ለመሸጥም ሆነ ቀደም ብሎ የተከለለበትን እንኳ ለማቅረብ እሻፈረኝ በማለት ሁኔታውን በውል ሳያስብልት ለክሬምሊን የሚበጀውን እስማምቶለት አረፈ። ደርግ ቻይናን ሞከረ፤ ግን እንደሚታወቀው ደርግ በፈለገው በጣም ብዛት ባለው መጠን ሊያቀርብ አልቻለም። (በዚያን ጊዜ ቻይና ደርግ ላይ ቅር የሚለው እንዳች ነገር አልነበረም።)

ለሶቪየቶቹ ሁኔታው የሠመረ ሆነ። ከመኢሶንና ከካስትሮ ጋር የደራ ግንኙነት እየመሠረተ በነበረው በደቡብ የመን በመጠቀም፣ ሞስኮ ባሬንና መንግሥቱ ኃ/ማርያምን (ደቡብ የመንን ሞምር) በኮንፋዴሬሽን ውስጥ ለማስገባት ሞከረ። ግን ዕቅዱ ከሸፈ። ባሬ ካርተር ይደግፈኛል ወይም ሶቭየቶች ጠብ እርግፍ አድርገው አይተውኝም በሚል ሕልም

ወታደሮችን እንጋግተ አጋዴን ውስጥ አስገባ። በአንድ እርምጃ ባሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ ፀረደርግ ተቃዋሚ ኃይሎች ላይ (ደርግ ብሔራዊ ስሜትን ለመቀስቀስና ኢሕአፓንና ተቃዋሚ ወገኖችን ባጠቃላይ ፀረሀገር ብሎ እንዲከትባቸው ዕድል በመስጠት) ከባድ ሞት አደረሰ። ኢትዮጵያም በሶቭየት የበላይነት ሥር እንድትወድቅ በሩን ከፈተ። ከሬምሊንም እንዳንድ ቀልጠፍ ያሉና ከበድ ያሉ ሥሌቶችን ካደረገ በኋላ፣ በርበራ ቀረ አልቀረ ኢትዮጵያ ከሕዝቧ ብዛት፣ ባካባቢው ካላት የፖለቲካ ክብደት አንፃር ከሶማሊያ የላቀች ሽልማት እንደሆነች እመነበት። ከዚህም ዘንድ ድጋፉን ወደኢትዮጵያ በግዞር፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምን አስታጠቀ፤ በሺዎች የሚቈጠሩ የኩባ ወታደሮች እንዲገቡ አስደረገ፤ ራሱንም የኢትዮጵያ አብዮትና የግዛት እንድነቷ ጋሻ መከታ አድርጎ አቀረበ።

ሶብየቶች ለረጂም ጊዜ ኢትዮጵያን ይመኙ ነበር። «ፈውዳላዊውን ንጉሠ ነገሥት» እንኳ ለማገባባት ሞክረዋል። ስለሆነም ለደርግ የነበራቸው ድጋፍ ለኢትዮጵያ አብዮት ባሳቸው እባቢነት ነበር የሚለው እንጋገር ከተለመዱት መፍቀሬ ሶቭየት ኅብረአበሮች በስተቀር ማንንም አሳሳመነም። በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም እንኳ የሶቭየት ዜና ማሠራጪያ ኢሕአፓና ተቃዋሚው ወገን ላይ ስድብ መቈለሉን ተያይዞት ነበር። እንዲያውም መኢሶን ወደኪዩባና ደቡብ የመን ይበልጥ ሲቀራረብ ፀረደርግ ኃይሎች ላይ ከሞስኮ ይወረወር የነበረው ለከፋ ጨመረ። የኢሕአፓ ታጋዮች በምሥጢርና በይፋ ሲረሽኑ ዋይ ጻፕሊን በኋው ታይምስ ላይ እንደኤ.አ.ቁ. ኖቬምበር 1976 እንዲህ ብሎ ጻፈ፤ «በፀረአብዮተኞችና በኢኮኖሚ አሻጥረኞች ላይ በመንግሥት ተወሰደው እርምጃ ሕዝቡ ውስጥ ሠፊ ድጋፍ አለው።» እምባሳደር ራታኖቭ ለመንግሥቱ ኃ/ማርያምና ለመኢሶን የቅርብ ሰው ነበር። የሞተው የምሥራቅ ጀርመን ፓርቲ መሪ ላምበርት አብዮቱን «አብዮቴ» ብሎ ከመጥራቱም ጋር እዲስ አበባን በማዘውተር ከመኢሶን መሪዎችና ከመንግሥቱ ኃ/ማ ጋር ይወያይ ነበር። ታዲያ ሽምቀቆው እየጠበቀ መጣ፤ ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም የመንግሥቱ ኃ/ማ መፈንቅለ መንግሥት ቀደም ብሎ እንኳ ሶቭየት ኅብረት በአንዳንድ የደርግ መኩንኖችና በመኢሶን አማካይነት ግንኙነት በመፍጠር ወታደራዊውን መንግሥት ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት እርምጃ እየወሰደ ነበር።

የየካቲቱ የመንግሥቱ ኃ/ማ የቤተ መንግሥት መፈንቅለ መንግሥት ወዲያውኑ በሶቪየት ኅብረት ይበል ! ይበል ! የተባለለት ሲሆን የተላለፈውም በእነ ተፈሪ በንቲ (ርሽና) ማንሥት መንግሥቱ ኃ/ማሪያምን እንኳን ደስ ያለህ እያለ ፎቶግራፍ በተነሳው በራታኖቭ አማካኝነት ነበር። ፈተና ማወቁና መደገፉ ራሱ ምን እየተዘጋጀ እንደነበር ሶቪየቶቹ አስቀድመው ያውቁ እንደነበር ጠቁሟል። በእርግጥም ሶቪየቶቹ ያውቁ ነበር፣ በፍንቀላው ዕቅድ ውስጥም ነበሩበት። በቫለኒቲን ኮሮቪኮቭ በራሱ ቃላት መለኪያ እንጥራ ካልን፣ "በደርግ ውስጥ በሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም በሚመራው ወታደራዊ መንግሥት ውስጥ ባለው አብዮታዊ ማዕከል ላይ የታቃጣ ከዳተኛ ከፋፋይ እንቅስቃሴ " ይለዋል።(39)

የሶ/ቪየት ኅብረት በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ ሞስኮ "ለኢትዮጵያ አብዮት" አለው በሚባለው ተቆርቋሪነት "ከሶማሌ ወረራ ኢትዮጵያን ለመከላከል ባለ ፍላጐት" ይሸፋፈናል፣ ወይም ማጠየቂያ ይበጅለታል። የመጀመሪያው ምክንያት፣ የሶቪየት ኅብረት የውጭ ፖሊሲ ለዓመታት የተመራው በአብዮታዊ የመደጋገፍ መንፈስ ሳይሆን ውበት ባለው "የመደጋገፍ፥ የዓለም አቀፋዊነትና የፀረ ኢምፔሪያሊዝም" ተራማጅ ንግግር በተሸፋፈነ፥ አግባ በወጣ ብሔራዊ ጥቅም ብቻ መሆኑን ለሚያውቀው ለማንኛውም ሰው አእምሮ በቀላሉ ግልጽ የሚሆን አይደለም። "የሶማሌ ወረራ" የሚለውን ሁለተኛ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ለመቀበል፥ የሰይድ ባሬን "ሶሻሊስት ሶማሊያ" ከእንዲት ድኃ አገር ፍላጎትና ለመከላከያ ከሚያስፈልጋት በላይ የትና የት በሆነ መጠን ለዓመታት ሲያስታጠቃት የነበረው ሌላ ሳይሆን ሶቪየት ኅብረት እንደነበር መርሳትን የሚጠይቅ ቢሆንም ይህኛው የተመቸ ሽፋን ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ይህን ሁሉ እንዳለ ትተን፥ የሶቪየት ኅብረት ኢሕአፓና በአጠቃላይ ተቃዋሚዎች ላይ በተደረገው የደርግ ሽብር እጁ እንደነበረበት የሚካድ አይደለም። መንግሥቱን ይህ ቀረህ የማይባል ትጥቅ ሲያስታጥቅና ሲደግፍ የሶማሌን ጦር ለመዋጋት ብቻ ሳይሆን በኢሕአፓ የሚመራውን ተቃውሞም ለመምታት ነበር። ለሞስኮ ሁለቱንም መምታት፥ እንደገና በክሪሮቪኮቭ ቃላት ለማስቀመጥ "የውጭ አደጋና አገር ውስጥ ያለው ፀረ አብዮት ተቃራኒዎች አልነበሩም፣ የአብዮታዊ ሂደት ዲያሌክቲክስ የአንድ አደጋ ሁለት ክፍሎች ሆነው እንዲታዩ የሚያደርጋቸው እንጂ" (40)

ሞስኮና አጫፋሪዎቿ «ኢሕአፓ የተባለ የሲአይኤ መሣሪያ» በሚሉት ላይ የቃላት ዱላ በመሠንዘር ብቻ ራሳቸውን አልወሰኑም፤ ደርግ እንዲመስለው ለመምከርና ለመርዳት አልወሰኑም፥ ደርግ እንዲደመስሰው ለመምከርና ለመርዳት ተጨባጭ እርምጃዎችን እየወሰዱ ነበር። እነሆ መንግሥቱን ለማስወጣት እንደረዱት በነሱ በራሳቸው የታመነበት ነገር ነው፥ የሽብር ዲያሌክቲክስ ብሎ ሌላ አዲስ ስም መሠየም የሚቻል ነው።

ከዚህ በታች ለማሳየት እንደምንሞክረው በሽብሩ ውስጥ የሶቭየት ጣልቃ ገብነት ከላይ ከተጠቀሰው ይበልጥ ቀጥተኛ የሆነ ነበር፤

1 በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ አንድ የኬጂቢ የቴሌ ፎን ጠለፋ ጠበብት ቡድን አዲስ አበባ ገብቶ የኢሕአፓ ደጋፊዎች ናቸው በሚባሉ ሰዎች ቴሌፎኖች ላይ የጠለፋ ሥራ አካሄደ፣ ቡድኑ ፭፮ ጠበብትን የያዘ ሲሆን የቡድኑ መኖርና እንቅስቃሴው የኢሕአፓ ደጋፊዎች በነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን ክፍል ሠራተኞች ሊታወቅ ተችሏል።በተባባሩም ከዚያ በኋላ በኢሕአፓንት ተጠርጥረው የተያዙ፥ በተጠለፉ የቴሌፎን ንግግሮችና በቴሌስኮፐ ሊንሶች በተነሱ ፎቶግራፎች ፥ እንዲሁም ላቅ ያለ ሞያን በሚጠይቁ የክትትልና የምርመራ ጥበብ ውጤት በሆኑ መረጃዎች ይፋጠጡ ጀመር። ከዚህ በተጨማሪም የፀጥታ ሠራተኞችና መርማሪዎች፥ ከ"ሶቪየትና ከም ሥራቅ ጀርመን ዓዶች» ስለሚያገኙት እርዳታ ጉራቸው አይጣል ነበር።

2. በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ከረምቱ ላይ ከፍተኛ ምስጢራዊ ስትራቴጂያዊ ኮሚሽን አዲስ አበባ ውስጥ ተመሠረተ። ኮሚሽኑ ስምንት የሶቪየት ከፍተኛ መኰንኖችን (ከነሱ ፭ኛው በሌተና ጄኔራል ማዕረግ ነበር) ፮ ኢትዮጵያውያንና ፫ ኪዩባውያን ከፍተኛ መኰንኖች የያዘ ነበር። በጦር ኃይሎች ሮፍ እፍ ስታፍ ሊቀመንበርነት የተመራው ይህ ኮሚሽን ከፍተኛ ምስጢራዊነት የነበረውና «ሶማሊያና የውስጥ ፀረአብዮተኞች» ላይ ለሚደረገው ጦርነት «ስትራቴጂያዊ ዕቅድ» እንዲነድፍ ተግባር የተሰጠው ነበር። «ፀረአብዮተኞችን» ለመዋጋት የተተለመው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ «ቀይ ሽብሩን

ማፋፋም» እንዲሁም «ከሃዲዎችንና ሰርጎገቦችን ውጤታማ በሆነና ሥርዓት ባለው መንገድ መጠቀምን» ያካተተ ነበር። በፕሮፖጋንዳው ደረጃ «ፀረአብዮቱ» ዓለማአቃፋዊ ተደማጭነት እንዳያገኝ «አሸባሪ» ተብሎ እንዲቀርብ ነበር የሚገፋው።(41)

በዚሁ መሠረት ሽብሩ ተፋፋመ፤ ሕዝባዊ ማጋለጥ የተባለውም እሠራር ተሥፋፋ። በግብረ ሰይል ቅስማቸው የተሰበረ የኢሕአፓ አባላት ሌሎችን እንዲያጋልጡ ተደረገ። የኢሕአፓ አደረጃጀት በንድፍ መልክ ወጣ። ተመሳሳይ የሆኑ ተጨማሪ አርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲረዱ ከልዩ ልዩ የግብረ ሰይልና የምርመራ ጣቢያዎች መረጃዎች በማዕከል እንዲሰበሰቡ ተደረገ።

ሶቭየቶች፣ ምሥራቅ ጀርመኖች፣ ኪዩባዎች፣... ወዘተ ሁሉም ሽብሩን ደገፉ። ግን በቀጥታ ግድያና የግብረ ሰይል ሥራ ውስጥ ገብተው ኑሯልን? እስካሁን መረጃ የለም። ሁኖም ይህ ጉዳይ ከቁም ነገር ላይጣፍ የሚችል ነው፤ ምክንያቱም ኪጂቢ፣ የኩዩባው ዲጂአይ እና የምሥራቅ ጀርመን የሽብር ጠበብት፣ የፀጥታ ኃይሎችንና በፀጥታ ውስጥ የነበረው ፀረኢሕአፓ ልዩ ኮሚቲ ያማክሩ ነበርና። የፀጥታው ልዩ ኮሚቲ ውስጥ ተካ ቱሉ፣ ኮሎኔል ልዑልሠገድ፣ ኮሎኔል ሙሉጌታና ሌሎች ነበሩበት። ከምሥራቅ ጀርመን ፀጥታ ክፍል ፩ ጀኔራል የኢትዮጵያ ፀጥታ እገልግሎት እንደኤክስፐርት ሆኖ እንዲሠራ ተመድቦ ነበረ:: (42) የሶቪየት ሰበካ ሀገሮችና ከክሬምሊን ጋር የተሣሰሩ የምዕራብ ፓርቲዎች ኢሕአፓ «ሽብርተኛ ጽንፈኛ»ና «ፀረአብዮተኛ» ሆኖ እንዲታይ የፕሮፖጋንዳ ውርጅብኞቻውን ከፍ አደረጉ። የደርግ ሽብር እንደ «የማያወላውል፣ ወሳኝ፣ አብዮታዊ አርምጃ» ይበል! ተባለለት።(43)

ኩባውያን የመኢሶን መሪ ነገደ ጎበዜን በድብቅ አዲስ አበባ ውስጥ አስገብተው ከመንግሥቱ ኃ/ማ ጋር ያልተሳካ የዕርቅ ሙከራ ካደረጉ በኋላ ደርግ አሻፈረኝ በማለቱ ነገደ እንዲመለስ በተደረገ ጊዜ ዓይን ያወጣው የሶቭየት ኅብረትና የጭፍሮቹ ጣልቃ ገብነት ገኃድ በሆነ ጭብጥ የታየ ነበር። ሁኔታው በሀሻናና በአዲስ አበባ መካከል ትንሽ መታታር መፍጠሩ አልቀረም። ደርግን በነሱ ቅጽር ውስጥ ለማስገባት በትጋትና በተሳለጠ

ያገለገለገላቸውን ድርጅት ለመታደግ የሶቭየት ሰበካ ሀገሮች ያደረጉት የመጨረሻው ተስፋው ያለቀለት መከራ፣ በነሱና በመኢሶን መካከል ነበርየተባለውን፣ ቅርብ ትሥክር እንደገና ያረጋግጣል።

የደርግ ሽብር በምሥራቃዊው አውሮፓ ከተፈጸመው ግፍ ጋር አስደንጋጭ የሆነ ተመሳሳይነት ነበረው።ተመሳሳይነቱ በአጋጣሚ አልመጣም፤ የምሥራቅ አውሮፓ የሽብር ጠበብት ምክር አልተለየውም ነበር። «በቀይ ሽብሩ» የግጋለጥ ስብሰባዎች ላይ ወላጆቹን ከዶ ለምሥጢራዊ ፖሊስ ስላጋላጣቸው ልጅና ሶቭየት ዩኒየን ውስጥም አንድ የሆነ ቦታ ሐውልት እንዲት እንደቆመለት አዘውትሮ ይጠቀስ ነበር። ኢትዮጵያውያንም ይህንን ምሳሌ እንዲከተሉ ይጉተጉቱ ነበር።

እነዚያ «ለቀይ ሽብሩ» ወንጀሎች ተጠያቂ የሆኑቱ በመጨረሻ ለፍርድ በሚቀርቡበት ጊዜ የሶቭየት ኅብረትና የጭፍሮጀ ሐላፊነት ሞንኖውንና የወንጀለኝነቱን ሥፍራ ከመያዝ የሚያመልጡ አይሆንም። «በዳያሌክቲካዊ የአብዮት ሂደት» ሽፋን ሶቭየት ኅብረት በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ የጨፈጨፈውን መንግሥት የረዳና ያበረታታ ሲሆን በዚያ ሂደት ውስጥ አብዮቱን አጨናንሶ። ፊዲል ካስትሮ የኢትዮጵያ አብዮት ግቡን ለመምታት አንድ ትውልድ መጨረስ ካለበት «ይሁንበት እንጂ!» አለ ተብሎ ይነገርለታል፤ ግን ደግሞ የካስትሮ ጥፋት አፈቅድ መሆን ብቻም አይደል።

ማስታወሻዎች

ክፍል ሁለት

1. ኑሐሴ 1968 ዓ.ም አዳዲስ የተሾሙ የልዩ ልዩ ኮርፖሬሽኖች አለቆች አዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤት አዳራሽ ውስጥ እንዲሰበሰቡ ተደርጎ (ንግግር ባደረገላቸው) በመንግሥቱ ኃ/ማርያም አባባል መንግሥቴ በተባለ በቀድሞው የብሔራዊ ሀብት ልማት ሚኒስትር የተደረገውን "የኤኮኖሚ ሳበታጅ የሚያረጋግጥ" ፊልም እንዲያዩ ተደረገ። መንግሥቴ በአንድ ይፋ ስብሰባ ላይ እስከተጋተረበትና ወዲያውም እንዲታገ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ የቅርብ ጓደኛው ነበር።

2. እንደ ማርክሲያዊ ሁሉ መኢሶን ስለ ኢሕአፓ አቅሞማትና ተግባራት ሲጨነቅ ሲገባው፥ ኢሕአፓን በሕዝብ ዘንድ በተለይም በደቡቡ የንጠር ክፍልና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳጣት ዓልሞ በቆመበት ዕቅዱ፥ እደግጻጊዎች የሆኑ የዓለም መፍቀሬ ሶሺያት ዜና ማሠራጫዎች ኢሕአፓ ላይ ታጥቀው በመነሣት "የነጋሥያንና" "ከመካከለኛው መደብ የመጡ ግራዎች" ፓርቲ ነው ብለው በመቅባት ያስተጋቡትን ክስ እንጠልጥሉ ተነሣ። በመሠረቱ ኃይሌ ፊዳ ከዝቅተኛ ቤተ ሰብ የመጣ ሲሆን ብዙዎቹ የመኢሶን መሪዎቹ ግን ከከፍተኛው መደብ የመጡ ነበሩ። ስለ ኢሕአፓና ስለቀሩት መፍቀሬ ደርግ ቡድኖችም እንኳ ይህንኑ ማለት አይቻልም።

3. መስከረም ላይ የኢሕአፓ ሰኻድ ፖሊስ ጎይል ውስጥ በነበሩት አባላት ትብብር የሰንጻፋውን ፖሊስ ጣቢያ በመውረር መሣሪያ አገኘ፣ ተኩስ አልነበረም፣ የቆሰለም የሞተም አልነበረም።

4. Amnesty International Report on Ethiopia, London, 1977. በተጨማሪም፥ J.C. Gnilleband's "Derg's Red Terror", Guardian Weekly, Feb. 28,1978 ይመለከቷል።

5. በጊዜው ይህ ነው ተብሎ የተነገረ የኢሕአፓ አባላትን መጠን የሚያሳይ ግምት የለም። እንዳንድ የኢሕአፓ የቀድሞ አባላት ምንጮች የወጣቱ ሊግ ብቻ በዚያን ጊዜ ፲፩ ሺህ አባላት ነበሩት ይላሉ። ይህንን ግምት ከኢሕአፓ ማረጋገጥ አልቻልኩም።

6. ሕዝቡ የደርግን ጋዜጦች የማያነብበው ሬዲዮውን የማይሰማው ኢሕአፓ ስለቀሰቀሰው ነው በሚል (ደርግ) አሳበዘ።

7. ከተረሸኑት ውስጥ ሻለቃ ሞገሥ ብቻ ነበር ከኢሕአፓ ጋር ድርጅታዊ ግንኙነት የነበረው፣ - ከኢሕአፓ ምንጮች እንደተገኘው።
Micheal Warr, Horn of Africa, vol. 4 no.3, (New Jersy, USA, 1981) ላይ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ የኢሕአፓ አባል እንደነበረ ሲጽፍ፥ ልጁ የኢሕአፓ አባል ነበር በሚል ጀነራል ተፈሪ በንቲ ላይም ይህንኑ ስም ለጥፏል። ኢሕአፓ ሻምበሉም ጀኔራሉም ምንጊዜም አባላቴ አልነበሩም ብሎ ይክዳል። ሁለቱንም ሰዎች ቀረብ ብለው የሚያውቋቸው የWarrን ልጠፉ፥ የደርግን አትዋም በወገንተኛነት እንደማስተጋባት በመቁጠር አይቀበሉትም።

8. ሶቪየት ዩኒየን የተማረው ዶክተር ዓለሙ አበበ ኢትዮጵያ ውስጥ "የኬጂቢ ሰው" በመባል ተዘውትሮ ይጠቀሳል። ከመኢሶን ከድቶ ወደ ሰደድ የገባና አሁን ደግሞ በጎሾነት ላይ ያለው የኢሠፓ ፖሊት ቢሮ አባል ነው።

9. በስዊዲሹ ዶክተር Arni Meyer-Lie (የኢትዮጵያ የህክምና እገልግሎቶች ዲሬክተር ሁኖ ሰብዙ ዓመታት ያገለገለ) ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል አቂንስ ውስጥ የቀረበ፡ March 10-11,1978.

10. "የደርግ ቀይ ሽብር" ("Derg's Red Terror") በሚለው ድርሰቱ Guilleband እንዲህ ብሎ ጽፏል፣

"ባለ ሥልጣኖቹ በመሩ መወረቻ በቂ ሰው
ያላሰሩ ቀበሌዎችን በተርግሬ ዓይን
ይመለከቷቸዋል። አንድ ሰው፣ ገና ቀበሌ ውስጥ
ለቋጥር የሚገቡ ሰዎችን ሰላሳሩ ገንዘብ
የሚሰበሰብበትን መንገድ ሲያደራጁና ብዙ ገንዘብና
ደም በመር ግንባር ላሉ ወታደሮች ለመላክ
ተጠምደው ነበር ብሎ አመጋ።"

ሽብሩን በተግባር ላይ ሰግዋል ተብቶ አለመገኘት በሌላ "ታማኝነትንና አርበኝነትን" በሚያንፀባርቁ ሌሎች እርምጃዎች መሸፈን ነበረበት።

11. ይህ ልምድ በኋላ የሲ.አይ.ኤ ቅጥረኞች ተብለው የተጠረጠሩትን ለማጥፋት የሰደድ ስኳዶች በለገሠ አስፋው ሥር ሁነው የኬ.ጂ.ቢን ትእዛዝ ሥራ ላይ ሲያውሉ፥ እየጨመረ መጣ።

12. የማደቦ ስኳዶች ስማቸውን የወረሱት በኢሕአፓ ከተገደለው ተመስገን ማዴቦ ከተባለው ከደርግ የመኢሠግ መሪ ነበር።

13. ሙሉጌታ ሱልጣን ሰምሳሌ በሠናይ ልቂ በራሱ በእሠቃቂ ሁኔታ ግበረ ሰይል ተፈጽሞበታል። ሁለቱም አሜሪካ ውስጥ በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜ መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ ልዩነት ነበራቸው። የሁለት ተቃራኒ ግንባራት አባላት ነበሩ። ታዲያ ሠናይ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቋጠረው ቂም ነበረው።

14. Amnesty International Report, op. cit.,1977, p.19.

15. ABYOT ውስጥ ተተርጉሞ የቀረበ vol. 2,special issue, February 1977.

16. Valentin Korovikov, op. cit;page 93.

17. እንድ ወጻጅ ለተፈሪ በንቲ፥ መንግሥቱና መኢሰን እሱንና ጓደኞቹን ሊገድሏቸው ዕቅድ እንዳላቸው ሲያስጠነቅቀው፥ ሰጠ

በተባለው መልስ ምን ያህል የሞሀ እንደነበር ግልጽ ያደርጋል። ተፈሪ እንዲህ አለ ይባላል፡ "ከገደሉን ማን ይተበላቸዋል?"

18. Halliday and Molyneux,op. cit., page 122.

19. የሀነስ ድርሰት ኒስ፡ፈረንሳይ (Dec. 19-22, 1977) ለኢትዮጵያ ጥናት 5ኛ የዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ የቀረበ ሲሆን "The bankruptcy of the Ethiopian Left , Meisone - EPRP, a Two Headed Hydra - A Commentary on the Ideology and Politics of National Nihlism" የሚል ልብ አውልቅ ርእስ ነበር።

20. መኢሶንና ኢሕአፓ የየራሳቸውን ታሪክ ገና ጽፈው በይፋ ሰነላወጡ በብዙ የውጭ ፀሐፊዎች (እነ አታዊይ፡ ቪቮ፡ ሌርሪት፡ ሰችዋብ፡ ሃሊዴይ...ወዘተ) የቀረቡ የሐሰት ዘገባዎች ብዙ ሰዎች ማሳሳታቸውን ይቀጥላሉ። ደርግ በበኩሉ ደግሞ የፖለቲካ ግቡን ለመምታትና የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን ተክለ ሰውነት የመገንባት ተግባሩን ለማከናወን የራሱን አዲስ ታሪክ አሰንምሮና ተወላጩን ሀቅ ለውጦ በመጻፍ ላይ ተጠምዶ ይገኛል። በ፲፱፻፸፩ በግ.ከ 4ኛ ፕሌነም፡ በተለይም በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. በተደረገው ሁለተኛው የፓርቲ ጉባዔ ዘርዝር ያለ የኢሕአፓ ተመክሮ ግመገማ ተደርጓል።

21. በLegum የተጠቀሰ op.cit., pp. 58-59.

22. Halliday and Molyneux, op. cit., p.154 የግርጌ ማስታወሻ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ለደርግ ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት አደረገ። ከአንድ ምንጭ እንደተገኘው፡ ማንም ጥያቄ የጠየቀ፡ ጥርጣሬን ያሰየ፡ ተቃውሞ ያሰማ አልነበረም።

23. ቻይኖቹ የመሬት ማሻሩን ዓላጅ ከማዳነቃቸውም ጋር ደርግን "ፀረ ኢምፔሪያሊስት" ነው አሉ፡ ባጠቃላይ ለሀገሪቱ መንግሥትና -- ከመሪው ከጎይሌ ፊዳ ጋር ግንኙነት ለነበራቸው - ለመኢሶን በጎ አመለካከት አሳዩ። በወቅቱ ኢሕአፓና ቻይኖቹ ግንኙነት አልነበራቸውም።

24. መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በንግግር የመግረክ ተሰጥዎ ያለው ከመሆኑም ሌላ ሮሌነት በተመላበት መንገድ ማታለል የሚችል፡ ከውጭ ጎብኚዎች ጋር ሲገናኝ ግንፍል ቁጡነቱን ሸፍኖ የዓይን አፋርና የትሁት ሰው ገጽታ አስግምቶ ይዞ የመቅረብ ችሎታ እንዳለው ይነገራል። ለመጀመሪያ ጊዜ ለሦስት ቀናት ያገኘው ፊደል ካስተሮ ከዚህ በሚከተለው ዓይነት አሞግሦታል፤

"መንግሥቱን በደንብ ላውቀው ችያለሁብዙ መናገር አችላለሁ። ረጋ ያለ ነው፡ ብልኅ ነው፡ ደፋርና ጀግና ነው። እነደ እንድ አብዮታዊ መሪ ልዩ ችሎታዎችን የታደለ መሆኑ ይስማኛል። መንግሥቱን እንደ አንድ ሀቀኛአብዮተኛ አመለከተዋለሁ።" (በጊዜያዊ መታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከታተመ የኢትዮጵያ አብዮት ስሚለው መጽሔት መስከረም 1969፡ ገጽ 39 የተመለደ)

ካስትሮ ምናልባት ሆን ብሎ የታወቀውን የሻለቃውን የራስ መካብ ፍላጎት ለማርካት ፊልጎ ይሆናል፡ ነገር ግን ኢትዮጵያውያን፡ የደርጉ አለቃ በሦስት ቀናት አጭር ጊዜ ውስተ እንኳ ሌላ አነብናቢ ዲስኩራኛ ለማሞገት ችሎታ አያንሰውም ብለው ወደ ማመኑ ይደርሳሉ።

25. Challenge በESUNA የታተመ፡ New York, vol. XI no. 2, July 1971.

26. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር (USUAA) ጋዜጣ (ታግል) በዚያን ጊዜ በውጣው እትም ላይ፡ የብሔሮችና የብሔር ጭቆና መኖር፡ እንዲሁም የራስን እድል በራስ የመወሰን አቅዋም በ1964 ዓ.ም ባለተሳክ የአውሮፕላን ጠለፋ ላይ በተገደለው ዋለልኝ መኮንን በተጻፈ ጽሑፍ ተገልጾ ነበር።

27. ጎይሌ ለአንድ ዓመት ያህል Guardian ና LeMonde Weekly (በእንግሊዝኛ) ይልክላቸው ነበር የሚል አለ።

28. በዚሁ ጊዜ ውስተ ከዚሁ AK-47 ጠመንጃዎች ጥቂቱ ግይ ለሀም (ፀለምት-ጎንደር) ደፈጣ ላይ በኢሕአሠ ተወስደዋል።

29. Africa Confidential, London, October 8, 1976. ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (CELU) ላይ የነበረውን ተጽዕኖ ደርግ በስሱ ሸፋፍኖ ስለማመኑ፡ The

Ethiopian Herald, April, 1977. በተጨማሪም Micheal Chege, "The Revolution Betrayed: Ethiopia 1974 -9", The Journal of Modern African Studies, 17, 3, 1979, pp. 359 -38 ይመለከቷል።

30. የሊዲይና ሞሊኔ ኢሕአፓ የየካቲቱን አብዮት በማንቦር ቀደምኑት መርቷል ብለው እንደሚያመላክቱት በኔ በኩል እንዲያ ብሎ ቁልጭ አድርጎ ያስቀመጣቸው የኢሕአፓ ጽሑፎች አላገኘሁም። እንዲያውም በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰመደው የኢሕአፓ አቀራረብ፥ ምንም እንኳ ታጋሾቹና ደሞክራሲያ ጉልህ ሚና ቢጫወቱም፥ የአመራሩን ሚና ሰመሚወት "ፓርቲው በቂ ጥንካሬ አልነበረውም።" የሚል ነው።

መኢሶን የየካቲቱ አብዮት አንሣሽ ነበርኩ ብሎ ስለ ባለቤትነቱ የሚለውን በሚመለከት La Monde, Paris, September 3, 1977 ይመለከቷል።

31. ለምሳሌ የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን መፈክር ይዘትና ዓላማ በሚመለከት ለረጅም ጊዜ የቆየ ብዥታ ነበር። ፋሺስት የሚለው መንግሥት ላይ የተቀጠለው አጠራርም በአንዳንዶች ዘንድ "የፋሺስት ሥርዓተ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ" እንዳለ ተደርጎ ተወስዶ ነበር። ወደ ትጥቃዊ "ራስ መከላከል" መዞር ስለማስፈለጉ የወጣው የአመራር የፖሊሲ መግለጫ እንኳ አቀራረቡ ለከተማ ዐመፅ እንደቆመ ተደርጎ እንዲተረጎም ያመቸ ነበር። በመሠረቱ ይህን መመሪያ ያወጣው ፖሊት ቢሮ አድሙ ወደ ከተማ ዐመፅ ያዘነበለ ነበር ብለው አንዳንድ የኢሕአፓ አባላት ይናገራሉ። እንዲያውም የማኮ ቁኖ ፕሊነም ግመግማ ራሱ የተሳሳተው ቅኝት በፓርቲው አመራርና ከአባላቱም በተወሰነ ክፍሉ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ አምኗል።

32. ይህ ከመኢሶን ይልቅ ኢሕአፓ ላይ እውነትነት አለው። መኢሶን፥ አባሉቹ በመንግሥቱ ተሹመውለት፥ ታጥቀውለት፥ ...ወዘተ በራሱ ምርጫ ከሞላ ጎደል በይፋ ነበር የሚሠራው። ኢሕአፓ ተቃዋሚ ወገን ሁኖ የቆመና በጎቡዕም የሚሠራ ነበር። አባላቱ እየተበራከቱ ሲመጡ የተከተለው መላላትና ብዙለት የጎደለው አሠራር ያመጣበት እምሳት ከፉ ጉዳት ላይ ጥሎታል።

33. "የቀዩ ሽብር" ዋነኛ ዒላማ ኢሕአፓና ከሱም ጋር የተያያዙ ቡድኖችና ብዙኃን ድርጅቶች ሲሆኑ፥ ሁኔታው ካለፈ በኋላ የሽብሩ ዋና ዒላማዎች የብሔር ድርጅቶች እንደነበሩ ተደርጎ ለማቅረብ ተሞክሯል። ወግንተኛ ለሆነ ፖለቲካ እንዲስማማ ተብሎ ሀቅን አዛብቶ ለማቅረብ የተደረገ ተልካሻ ሙከራ መሠረተ ቢስና ፍሬ የሌለው ሁኖ ጎልቶ ከመታየት የሚዘል አይሆንም። የብሔር ድርጅቶችን በሚመለከት አዲስ አበባ ውስጥ ጎቡዕ መዋቅር የነበረው ተሐኤ (ELF) ብቻ ሲሆን፥ ሽብሩም በደል አድርሶበታል። ትግራይ ውስጥ እስከ ፩፱፻፸፱ ዓ.ም ድረስ ሽብሩ የተነጣጠረው ኢሕአፓ ላይ ነበር። አሥመራ ውስጥም እንኳ ሽብሩ ያተኮረው በኢሕአፓንት በተጠረጠሩ አስተማሪዎች፥ በመኩነኖችና በወታደሮች መካከል እንዲሁም በአስተዳደር ውስጥ ባሉ ላይ ነበር። አሮሞዎች በሚኖሩበት በከፋ፥ በአርሲ፥ በሐረርጌና በሌሎች አካባቢዎች ሽብሩ በዋናነት ያተኮረው በኢሕአፓ አባላት፥ ለኢሕአፓ በጎ አመለካከት ባላቸው ሰዎችና በደጋፊዎች ላይ ነበር።

ከኢሕአፓ ጋር ይሠራ የነበረውና በደርግ የተመታውን የኦሮሞ ሕዝባዊ አርነት ድርጅትን ባለ ፲ ነጥብ ፕሮግራም ትርጓሜ ABYOT VOL. 2. no.5,1977 ይመለከቷል።

34. እጅግ ከባድ የነበረው የኢሕአፓ ውስጣዊ ችግር የተቃጣው ደርግ ኢሕአፓ ላይ ጦርነት ካወጀ በኋላም እንኳ ደርግ ላይ ትጥቃዊ ተቃውሞ መደረግ የለበትም ባሉት (ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል ረዳ) ሁለት የአመራሩ አባላት ነበር። ኢዲኃንና የሶማሌን ወረራን ለመከላከል ፓርቲው ከደርግ ጋር የጎብረት ግንባር ለመፍጠር መሞከር አለበት ብለው ተከራክሩ። ከሁለቱ በደንብ የታወቀው ብርሃነ መስቀል ረዳ ነበር፡ ይህም ያለ ምክንያት አልነበረም፡ ትቡ የሆነ የተማሪ መሪ ነበር፡ ኢሕአፓንም በመመሥረት ረገድ ጉልኅ ሚና ነበረው። በሌላ በኩል ጌታቸው እስከ ፲፱፻፷፭ ዓ.ም ድረስ ከፖለቲካ የራቀ ሃይማኖተኛ ተማሪ ነበር። በኋላግን የማእን የፖለቲካ መሥመር አቀንቃኝ ሁኖ ከሌሎች ጋር አብዮት የተባለውን ቡድን መሠረተ። ከኢሕአፓ ጋር የተዋኀደው ቡድን ነው።

ኢሕአፓ እንደሚለው፥ ሁለቱ "ድርጅታዊ ደንቦችን ስለጣሱና የመሞጻሞድ አመለካከታቸው ከዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ውጭ ስለገፉ" ኮማዕከላዊ ኮሚቴው ታግደው ነበር።ሁለቱ

መሪዎች የብዙኃኑን ውሳኔ እያከበሩ ሐሳባቸውን በፓርቲው ውስጣዊ ጋዜጣ እንዲገልጹ ዕድሉ ተሰጥቷቸው ነበር። ሁኖም ሁለቱ፥ ተቃውሟቸው በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ መገንጠልና የራሳቸውን እንጂ መፍጠር እንዳለባቸው የተሰማቸው ይመስላል። በኢሕአፓ ጽሑፎች ውስጥ አንጀኞች ተብለው ይጠቀሳሉ። እንደተባለውም በኋላም እንደተረጋገጠው የሁለቱ ተከታዮች፥ ከደርግ ጋር በማበር ጓዶቻቸውን በማደን በሽብሩ ዘመቻ ላይ ደርግን ረዱ።

ብርሃነ መስቀል ከደርግ ጋር ለመደራደር ሞክሮ ነበር፣ ነገር ግን መኢሶኖች ወደ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቅርበት ሊያተኝና ተጽዕኗንን ሊቀንሰው ይችላል በሚል ሥጋት ዘንበት። በኋላም ተይ፡ በደርግ ተረሸኑ። አንጃ የፈጠረው ችግር በጣም ከባድና ኢሕአፓ በከተማ ውስጥ ለሚያካሂደው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ትግል እንቅፋት ነበር።

35. በኢሕአፓ ውስጥ በጉንደር፥ በትጥቅ ትግሉ ቅጽር "የብተና ዘመቻ" ተካሄደ። ከፓርቲው አመራር ግለ ሂስ (፬ኛ ፕሊነም) በኋላ የተወሰኑ ሰዎች፥ በደርግና በእርሶ አደሩ መካከል ያለው ቅራኔ ደብዝዟል፣ በዚህ ምክንያትና ደርግ የሶቪየትን ድጋፍ ከማግኘቱ የተነሣ (ፓርቲው ደግሞ ይህ ነው የሚባል የውጭ ደጋፊ በሌለው ሁኔታ) የትጥቅ ትግሉን መቀጠል የሚቻል አይሆንም፣ ብለው በመከራከር ትግሉ እንዲቆም ጥሪ አደረጉ። ለነገሩ እነዚህ ሰዎች ቡታ በተባለ በኢሕአፓ ፀለምት ውስጥ በሚታተም ጋዜጣ ሐሳባቸውን ለማንሸራሸር ቻሉ። የዚህ ቅስቀሳ ቁልጭ ያለ ውጤትም ቁጥራቸው በርካታ የሆነ የኢሕአፓ አባላትና የነጠር የኢሕአፓ ካድሬዎች ወደ ደርግ መክዳት ወደ ሱዳን መሰደድ ሆነ ጥቂቶችም ወደ ህወሓት ከዱ።

ሁኔታዎች በኋላ እንዳሳዩት የብተና ዘመቻው በተንደኝነት የተመራው እንደ ደርግና ህወሓተ ካሉ "ጠላትነት ካላቸው ኃይሎች" ጋር የቅርብ ትሥሥር በነበራቸው ሰዎች ነበር። ኢሕአፓንና ኢሕአወን "ለማፍረስ" ዘመቻውን የመራው ያሬድ ከበደ፥ ህወሓትን ተቀላቀለ፣ ህወሓትም እሱንና ሌሎችን ቀደም ሲል ግንኙነት የነበራቸውን ሌሎችን፥ ራሱ ህወሓት የሚቆጣጠረው ፀረ ኢሕአፓ ድርጅት ለማቋቋም ወዲያውኑ ተጠቀመባቸው። ያሬድ ኢንዴን ተብሎ የተሰየመው

የዚህ ቡድን መሪ ሁኖ ብቅ አለ። ሁኖም ያሬድን ወደ ዕውነተኛ አለቆቹ ለመክዳት ረጅም ጊዜ አልፈጀበትም። ደርግን በመቀላቀል የኢሠፓአኮ፣ በኋላም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሁኖ ተሾመ።

ከህወሓት ጋር ቀርተው ኢሕዴንን ለማስቀጠል የፈለጉቱ፥ ኢሕአፓ ውስጥ ሁነው እንደተደራጁና ከህወሓትም ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው ይናገራሉ። ይሀንን ግን የኢሕአፓ አባላትና ቀድሞ የኢሕአፓ አባላት የነበሩ ሰራስ እንዲበጅ ተብሎ የተቀናበረ ፈጠራ ታሪክ ያደርጉታል። ከዚያም በመቀጠል ከሃዲዎቹ ኢሕዴን ተብለው የተደራጁት በራሱ በህወሓት ነው ይላሉ። ይህ ከሆነ ህወሓት በኢሕአፓ ውስጣዊ ችግር ለመጠቀም ሲሞክር የመጀመሪያው ጊዜ አይሆንም። በአንጃ ሁከት ጊዜ ህወሓት የንብርሃነ መስቀልን ፀረ ኢሕአፓ ጽሑፎች አባዝቶ በትኖ ነበር።

36. በሌላ የምሥራቅ አፍሪካ ዲፕሎማት ለደራሲው የተነገረ።

37. በሃሊዴይና ሞሊኔ አባባል (op.cit., p.203 የግርጌ ማስታወሻ) ተሓኤ ና(ELF) የሱዳኑ ፖለቲከኛ ሳዲቅ አል መሃዲ ባሬን አጋዴንን እንዳይወር አስጠንቅቀውት ነበር።

የኢሕአፓ ባለ ሥልጣኖች በሶማሌ ጣልቃ ገብነት ላይ ያላቸውን ጠንካራ ተቃውሞ ካርቱም ለሚገኘው "ነገር አድበስባሽና ሶቪያቶች ለኢትዮጵያ አድልተው ሶማልያን አይተዋትም ብሎ እርግጠኛ ለነበረው" የሱዳን አምባሳደር አሰምተው "ለሰይድ ባሬ ሊያስተላልፍላቸው ቃል ገብቶ እንደነበር" ለደራሲው ነግረውታል።

በአጋዴን ጦርነት ላይ የኢሕአፓን አቅዋም በሚመለከ ዲሞክራሲያ ቅጽ 4 ቁ.9 ይመለከቷል።

38. Korovikov, op. cit., p.93.

39. ibid.

40. የጋዜጣ ኮንፈረንስ ላይ (የካቲት ፲፱፻፸፰) መንግሥቱ ኃ/ማርያም እንደዚያ ዓይነት ምስጢራዊ ወታደራዊ ኮሚሽን መኖሩን ካደ::

41. Times, London, March 22, 1978.

ክፍል ሦስት

ቀይ ሽብር ሲተረጐም

፩

የሽብሩ "አርበኞች"

"በኢሕአፓ ፋሽስቶች ላይ ቀይ ሽብር ልንለድባቸው
ተዘጋጅተናል። ደማቸው የፀረ አብዮትን እሳት
የምናጠፋበት ውኃ ሁኖ ያገለግለናል።"
የሠራው ሕዝብ ድምፅ፥ የመኢሶን
ልሣን ፲፱፻፷

"ሰው መገደል የለብንም ባሉ፥ አብዮቱን እንተወው
ግለታቸው አይደለምን?ግድያዎቹ ይቁሙ የሚለው
ውሸት የክርሩቱ ውሸት ነው።"
የኢሊያሮ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መልስ
ለአምንስቲ ኢንተርናሽናል ተቃውሞ
ኖቬምበር 12/1977

ደንበኛው "ቀይ ሽብር" በይፋ የተከፈተው ጥር ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ነበር። ሽብሩን ወደ አናርኪስቶች ሠፈር ውሰዱት፣ በያንዳንዱ የኛ ታጋይ አንድ ሺህ ከሱ የሚለውን ጥሪ ራሱ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አደረገ። የንጉሱን ክብደት ለማሳየት ሂማብን ያጣቀስ የንግግር ፊሊፕ ሳይሆን የምሩን ነበር። መኢሶኖች "ከመምሀሩ ደቀ መዝሙሩ" የሚባለውን ተረት ለማስመስከር አፈፍ በማለት በግድያ ሙያ ከሠለጠኑት ይልቅ የተቡ ሁነው "ሽብሩ ወደ ቀይነት እየተለወጠ ነው፣" ሲሉ ሁሉም ሙሁ። ይህም ይፈጸም ዘንድ ደም መፍሰስ ነበረበት። ያለ ምሕረት አናርኪስቶቹን ምቱና አብዮቱን እድኑ፣ የፓሪስ ኮሚዩንንና የአየንዴን ሲሕተት እንዳይደገም፣ ግደሉ! ብሎ መንግሥቱ አዘዘ፣ መኢሶንም ግደሉ ብሎ አዘዘ። የሽብሩ መጋብርት አራራቸውን

አንዲወጡና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጨረሻውን አረመኔያዊ ወቅት ይዘግቡ ዘንድ መረን ተለቀቁ::

ቀዩ ሽብር ግልጽ የሆነና የለየለት የጭፍጨፋ ጥሪ ከመሆኑም በላይ ጻር እስከ ጻርም ያጻረሰ ነበር:: "ወደ ሀገሪቱ ማዕዘናት ሁሉ" ይል የነበረው፥ የመኢሶን የማሳበቢያ ጥሪ የሚጠቀስ ነው:: ወላጆች በልጆቻቸው "ጥፋት" ተረሸኑ፣ ልጆች ታላላቆቻቸው በፈጸሙት "ወንጀል" ተገደሉ፣ ለሥነ ልቡናዊ ዓላማና የአንጻንድ ንክ ባለኑፍጠኝን ፍላጎት ለማርካት ንጹሕ ሰዎች ታረዱ:: ለክት ያልነበረው በዓመፃ መጠናበዝ ታየ:: ቀዩ ሽብር ማንኛውንም አካባቢ አልማረም፣ ምሕረት እርሙ ነበር፣ ከተልዕኮውና ከተግባር መመሪያው ሊሠርፅ የሚችለው አውሬነትና በዘፈቀደኞነት ነበርና የሽብር ዓላማው ማስደንገጥ ነው:: ታዲያ ጫፍና እግሩ ከማይጨበጥ፥ የአመክንዮን ሕግ ከማይከተል፥ ማስረዳት ከማይቻል በጅምላ ከሚካሄድ ዕመጻ በላይ ምን ሊያስደነግጥ ይችላል? መኢሶን ለዚህኛው የሽብር ገጽታ ጫና በመስጠቱና በተግባር እንዲውል በማድረጉ ወሮታው የሱ ነው:: በዚህን ወቅት ያወጣቸው የነበሩ ወረቀቶች ከፖለቲካ ድርሰት ይልቅ የሽብር መመሪያዎች ይመስሉ ነበር:: መሆን የሚችለውም ያንን ነበር:: ሽብሩ ነጥሉ የሚመታ ሳይሆን አጠቃላይ መሆን አለበት፣ ምክንያትን፥ መቆጠብን የሚጋብዝ መሆን የለበትም፣ ጭፍንና ከአእምሮ ሚዛን የራቀ እንጂ:: (ለመሆኑ በአእምሯዊ ሚዛን የሚለካ ሽብር ከቶ ኑሮ ያውቅ ይሆን?) ሽብሩ ሆን ተብሎ ጭካኔ የተሞላ መሆን አለበት:: ይህ ነበር የመኢሶን መልእክት:: ይህንንም ነበር አባላቱና ደጋፊዎቹ የለከለኩት:: (1)

የመኢሶን ካድሬና የቀበሌ ሹም የነበረው የግርማ ከበደ ታሪክ እንደ ጥሩ ማብራሪያ ያገለግላል:: ግርማ፥ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ ከፓርቲ ፖለቲካ ይልቅ ወደ ፓርቲ ጭፈራ ያደላ ምሁር ሲሆን ከውጭ ሀገር መምህራን ጋር በማዘውተርና በየሳምንቱ መጨረሻ፡ ጃን ሚዳ ፈረስ ከሚጋልቡ የከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ልጆች ጋር ጓደኛ በመሆን የሚታወቅ ነበር:: በ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በመኢሶን

አባልነት ተመልምሎ ከፍ ባለ ደረጃ ባሉ ምሁራዊ ጉዳዮች ላይ ዲስኩራቸውን እያንቆረቆሩ፣ ማታ ማታ ሌሎች ሰብአዊ ፍጡሮችን በማብረ-ሰይል የማሠቃየት ተግባር ውስጥ ይሳተፉ በነበሩ፥ አውሮፓ አገር በተማሩ ምሁራን ይመራ የነበረው ድርጅት ካፈራቸው፣ የጭካኔ ሱስ እጅግ ከነበራቸው ገዳዮች አንዱ ሁኖ ብቅ አለ::

አዲስ አበባ፥ ከቤት እቤት ፍተሻ በሚደረግበት ወቅት ግርማ ራሱ ፬ የሚሆኑ ሰዎችን፥ የስምንት ወር ነፍሰ ጡርና የብዙ ልጆች እናት የነበረችውን የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ ጻር ነጋሽን ገደለ:: ጻር በማብረ-ሰይል ቁም ሥቅሏን ካዩች በኋላ በሳንጃ ተዘክዝካ የመሞቷ አሠቃቂነት የብርሃንና ሰላም ሠራተኞችንና የአራት ኪሎ ሕዝብን ቁጣ ፈንቅሉት በሰላማዊ ሠልፍ ተቃውሞውን እንዲገልጽ አስገደደው:: ግርማ፥ የራሱን የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን የቅርብ ዘመድ የሆነን ሰው በመያዝና ሊገድለውም በመታጣት ከመሥመር ወጣ ብሎ ነበር:: ተቃውሞውን ለማቀዝቀዝ ግርማ ተያዘ:: በዚህም መኢሶን ጤሰ፣ "ፀረ- ኢሕአፓ ትግል ውስጥ የተጋፈጡ ታጋዮችን የጋለ አብዮታዊ ስሜት የሚጉዱ እርምጃዎች" የሚል ተቃውሞውን በማሰማት በንዴት በገነ:: መኢሶንን ለመግጠት ምንጊዜም ነቅቶ ቀዳዳ ይፈልግ የነበረው የሠናይ ልኪው ወዝ ሊግ ግርማ፥ ምሳሌም የፕሮፓጋንዳ ማሳበቢያም እንዲሆን መገደል እንዳለበት የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን ስሜት መሳብ ቻለ:: መንግሥቱና የሰደድ ጓደኞቹም መኢሶንን በዚህ መንገድ መጠቀምን የሚጠሉት አልነበሩም:: ግርማ ሞት ተፈርዶበት በሕዝብ ፊት ተረሸነ:: የሞት ቅጣት ከሚፈፀምበት ሥፍራ ላይ የወዝ ካድሬ ከማለ ዜ ዶንግ ጥቅሶች እነበበ፣ ግርማ ሊናገር ቢሞክርም አቋረጡት:: የሶቪየት ፀሐፊው ከሮቪከቭ ከመኢሶን በተቃረነ መንገድ እንዲያውም ግርማ "የመንግሥቱን ስም ለማጉደፍ በቅዶ የተነሣ የኢሕአፓ ሰርጎ ገብ ነው" ሲል ለጠፈ:: (2)

ብዙ ግርማዎች ነበሩ፣ ከንቲባ ዓለሙ አበበ ከዚያ ይበልጥ ሰው በትእዛዙ አስገድሏል:: አሜሪካ አገር የተማረው

አሳዝኑው ባይሳ ከግርማ ይበልጥ ረሽኗል። ሀምቡርግ ውስጥ የነበሩ የጀርመን ግራዎች ጓደኛ የነበረ አብዱላሂ ዩሱፍ ድራጓዋ ውስጥ የተያዙ ሠራተኞችንና ተማሪዎችን አፍንጫ በፒንሳ ይቦጭት ነበር። ሞሐመድ (አሁን በአሜሪካ ኒዮርክ ውስጥ ፕሮፌሰር የሆነ) ወደ ፻፲ ሰው ያህል ገድሉ ሬሳቸውን ከሐረር ውጭ ጥሏል። በዚሁ አትጣጪያ ብዙ መደርደር ይቻላል። ሁሉም የቀይ ሽብሩ ድንቅ ወታደሮች ነበሩ፣ ...ዝርዝራቸው ብዙ ነው።

በግልጽና በምስጢር ይካሄዱ የነበሩት ርሸናዎች ቁጥራቸው እየጨመረ ግበረ ሰይሉም ይበልጥ እየከፉ መጣ። ግበረ ሰይሉን የሚጠቀሙበት ከአሥረኛው ምስጢር ለማውጣት ሳይሆን እሱን ራሱንና ሌሎችንም ለማሸበር፣ እንዲሁም ለበቀል መውጫ ነበር። አሥረኞች በሌሎች ፊት በግብረ ሰይል-ይሰቃያሉ፣ አሥረኞች ሌሎች አሥረኞች ጓደኞቻቸውን በግብረ-ሰይል እንዲያሰቃዩ እንዲያውም እንዲገድሉ ይደረጋሉ፣ የተቦተራረፈ የሰው አካል ሽፋን አይደረግለትም፣ ሬሳ ካውራ ጉዳና ላይ ይጣላል። ... የሽብር ዓላማ ቀልብን መግፈፍ ነው፣ አይደለምን? ቀዩ ሽብርም የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም ወደ ኋላ አላለም።

ለመሆኑ ቀዩ ሽብር በግብር ሲተረጉም ምን ምን ገጽች ነበሩት?። የጅምላ ርሸና፣ በምስጢርና በግላጭ ሰው አውቆት የሚፈጸመው የበርካታ ሰው ርሸና የቀዩሽብር ዋነኛ ገጽታ ሆኑ። ይህ ዕለት በዕለት ይደረጉ የነበሩትን ቱጥራቸው በምንም ዓይነት ሥሌት ቀላል ያልነበረውን እንጻንዲም በራዲዮም የሚነገሩትን የሚጨምር ሳይሆን፥ በአንድ ጊዜ በጥቅሉ አያሌ አሥረኞች የመረሸኑ ድርጊት ላይ የተወሰነ ነው። በጽሑፍ የተያዘውን ሁሉ (ከ፲፱ በላይ የተገደሉበትን) መደርደሩ ረጅም ስለሚሆን ጉልህ ከሆኑት ጥቂቶቹን ብቻ ነው እዚህ ልናቀርብ የምንችለው።

የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም አርባ አራት አሥረኞች ከአዲስ አበባው ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ከተማዪቱ ጸርቻ ተወስደው ከተረሸኑ በኋላ በጅምላ መቃብር ውስጥ ተቀበሩ።

ከ፵፱ ውስጥ አንስተኛው የ፲፯ ዓመት ወጣት ሲሆን አብዛኞቹ በ፲፯ና በ፰፯ መካከል ነበሩ። አንድ ኢንጂኒየር (መሐንዲስ) ኡስማን አህመድ የተባለ አርባ ዓመት አካባቢ ነበር። ምስጢራዊው ግድያ ሊጋለጥ የቻለው ከፖሊሱ መኪና ዘልለው ለመውረድ ከተሳካላቸው አሥረኞች በአንደኛው አማካይነት ነበር። ታሪኩ እንደሚከተለው ነው፣

"(ምስተኛ) ፖሊስ ጣቢያ ከሰአት በኋላ ፲ ሰአት ላይ ዘጠኞቹ ክፍላችን ውስጥ ከቁለፉን፥ ያች ቁራሽ እራታችንም ቀደም ብላ ከተሰጠችን በዚያን ሌሊት ርሸና እንደሚኖር እናውቅ ነበር። የካቲት ፲፱ እንደዚያ ዓይነቱ ሌሊት ነበረች። ከምሽቱ ፪ ሰአት ላይ የታወቀው ሃምሳ አለቃ ተሾመ ወደ ክፍላችን መጣና የግሬ ሰዎች ስም አነበበ። የኔ ስም እንዱ ነበር። ሁላችንም እንደምንገደል አውቀናል። ስማቸው ከተጠራው አንጻንዶቹ ደርግን የሚነቅፉ፥ ኢሕአፓን የሚያወድሱ አብዮታውያን መዝሙሮችን መዘመር ጀመሩ፣ እንጻንዶቹ ለቀሪዎቹ አሥረኞች ንግግር አደረጉ። እንዲያው ዝም ያሉም ነበሩ። ከክፍላችን እንደወጣን ወታደሮቹ በሰደፍ ደበደቡን፡- እጃችንንም ወደ ኋላ አሥረው እንደ ጆንያ መኪናው ላይ ወረወሩን። መዝሙሩን ወይም ወታደሮቹን መሳደቡን የቀጠሉቱ መኪናው ላይ ከመወርወራቸው በፊት እእምሯቸውን እስኪስቱ ድረስ ተደበደቡ። ኢንጂኒየር ኡስማን ቢደበድቡትም ዝም አልል አለ፣ ስለዚህም አንድ ወታደር እዚያው ፊታችን እንቆ ገደለውና ሬሳውን መኪናው ላይ ወረወረው።

ሃምሳ አለቃ ተሾመ የያንጻንዱን ስም ሲጠራ፥ ኻለቃ ዮሴፍ በሻምበል እሸቱና በሁለት ወታደሮች ታጅቦ እጁ ላይ በያዘው ወረቀት ላይ ምልክት ያደርግ ነበር።

በመጨረሻም መኪናው ሲንቀሳቀስ በየመንገዱ ጸር ባሉ ቤቶች ውስጥ ያሉ ሰዎች ለመረሸን በመሄድ ላይ መሆናችንን እንዲያውቁት መጮህና መዘመር ጀመርን። ጓደኞቼ የታሠርክብትን ገመድ በጥርሱ ፈታልኝ፣ እኔም የሱን

ፈታሁለት። ሌሎቹን ልነፈታ ስንል "ጊዜ የለም ዝለሉ' አሉን። ለመናፈሺያ የሚያገለግለውን የመኪናውን መስኮት በመክፈት ዘለልን። ጓደኛዬ ምን እንደደረሰበት አላውቅም። ሲወድቅ አይቼዋለሁ። ከኋላዬ እየሮጠ ነበር። ጩኸቶችና ተኩሶች ሰማሁ፣ ዳሩ ግን ወደኋላዬ መለስ ሳልል ሩጫዬን ቀጠልኩ። እንዲህ ነበር ያመለጥኩት።"

ሌሎቹ እላመለጡም፣ ተረሽነው በእንድ መቃብር ታጉሩ። በዚህም ዓይነት ግርማ ሠይፉ፥ ተሥፋ ሊመጣ፥ ተሥፋዬ ዘውዴ፥ መስለ ደባልቄ፥ ሰሎሞን ጊዳድት፥ አያልነህ አሰማማው፥ ተሰማ ዲሬሳ (የሙያ ማነበር መሪ) ካሡ ቀማ፥ ፍቅሩ የሴፍ፥ አየሁ ብርሃን ደመቀ፥ ኃይሉ ገ/ክርስቶስ፥ ጥበቡ አበበ፥ ፀጋዬ ኃይለ ሚካኤል፥ ተሾመ አሥራት፥ በቀለ መርኔ፥ አሸናፊ ዘለቀ፥ ጌትነት የማ፥ ኃይለ ማርያም ካሡ፥ ሲማይ ወልደ ማርያም፥ ጌታሁን መኩንን፥ ፍቃዱ ገመዳ፥ ወረቁ ኃይለ ወልድ፥ በላይነህ ገ/ማርያም፥ ዳንኤል ሀብቴ፥ ጌጡ ተገኘ፥ ብሥራት ጂባ፥ ሞሐመድ መሉድ፥ ማሞ በላዬ፥ ደምሰው ብዙ ወርቅ፥ ብርሃኔ የሺጥላ፥ የኋላ እሸት ሽዋ ታጠቅ፥እንዳለ ጎደሌ፣ ዓባይነህ ሁንኛው፥ ዐቢይ መርጌ፥ ካሣ ዓለም ኑጋሽ፥ ዓለማየሁ እንዴ ዓለምና ሌሎች ስማቸውን ማስታወስ ያልተቻለ ሞቱ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም በርካታ ተማሪዎችና ሠራተኞች የ"ሚይ ዴይ" ሠልፍ ለማድረግ ዝግጅት አደረጉ። ደርግና መኢሶን ወሬ ደረሳቸውና ነፍስ ገላቸዉ ስኳዶች ዝግጁ ሆኑ። እንድ ተመልካች እንደገለጸው፥

"ዐርብ ጠዋት ሚያዝያ ፳፱ ቀን በዚህች አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ባላት ከተማ በተለያዩ አካባቢዎጅ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው የከብድ መሣሪያ ድምፅ ሰምቷል። ቀላሉና አልፎ አልፎ የሚተኩሰው የእኩለ ሌሊቱ የሰአት እላፊ ያለ ጊዜው ቀደም ብሎ ሊታወጅ እንደተለመደው ዓይነት የጠመንጃ ተኩስ ሳይሆን፥ በዚያች ዕለት በ፲፱ ሰአት ከፀ ከሰአት በላይ የሰማው ከበድ ያል የማሽን ገን ድምፅ ነበር። በጠመንጃ

ተኩስ የተበተኑ፥ ጥቂት ሰውም የሞተበት የተማሪዎች ሰላማዊ ሠልፍ እንደነበረ አብዛኛው ሰው ሰምቶ ነበር። ቀስ በቀስም ነበር ሰላማዊ ሠልፉ በጣም የተስፋፋ እንደነበር ሰው እየተረዳው የመጣው። (ምናልባትም አንድ አሥር አሥራ ሁለት በሚሆኑ አካባቢዎች ተዳርጀል።) ጦር ሠራዊቱ--- በመሠረቱ ጦር ሠራዊቱ ሳይሆን ማንኛውንም ትእዛዝ ለመቀበል ወደ ኋላ የማይለው በከተማዋ ውስጥ ከነበሩት ድንኑተ ካጠቃቸው ሥራ አጦች፥ መሐይሞችና በዘኑ መሬዎች የተመለመለና በተለየ መልክ የሠለጠነ "ንበልባል" የተባለ ልዩ ቅርንጫፍ በጂፕ መኪናዎች ሁኖ ወዲያው ከተፍ አለ። ከጂፖቹ በስተኋላ የተጠመዱ ቢ.አር. መትረየሶች ነበሩ፤ ከማሽንገኖቹ በስተኋላ ደግሞ ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ከተረው ያገረው ሰው የሚለያቸውን ለዓይናቸው መከላከያ የሚሆን ብጫ ልዩ መነጽር (ጎግልስ) ያደረጉ ወታደሮች ተተምጠው ነበር። በሰላማዊ ሠልፎቹ ላይ ሁሉ እንህ ባለ ግለሰቦቹ መትረየስ ተኳሾች ጥይታቸውን አርከፈከፉበት። በርካታ ኮባብሎች፥ ሠልፈኞች፥ ባለ ሱቆችም ላይቀሩ፥ ወደ ግቃ ትምህርት ቤት የሚሄዱ፥ ከሥራ ወደ ቤታቸው የሚመለሱ፥ ወይም በሆነ ምክንያት መንገድ ላይ የተገኙ ረገፉ። ጥቂት ቦታዎች ላይ ሠልፈኞቹ የተኩሰ እጸፉ ሲመልሱ፥ በአብዛኛው ቦታ ግን የታጠቁ አልነበሩም።

ትዳሜ እሑዱን ሰው በየአብያተ ክርስቲያናቱ በፍትሐት ላይ የሬሳ ሳይጥን ቄጠራ በየሀኪም ቤቱም በአዲስ የተተበሉትን ቄጠራ ገባ። ሠኞ ዕለት ከተማዪቱ የሆነውን ለማመን ባለመቻሏ በደነች። በአሥር ደቂቃ ውስጥ ምናልባት ሦስት መቶ ወጣቶች፥ አብዛኞቹ መሣሪያ ያልነበራቸው፥ ተገድለዋል፤ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ደግሞ ቆስለዋል። በሚቀጥለው ቀን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ (ደርሰት መቶ የሚልም አለ) ተይዘው የነበሩ ከእሥር ቤት ውጭ ተወስደው ያለምንም ፍርድ ወዲያውኑ ተረሽነዋል። በአንድ ላይ ሲጻመር ቢያንስ ዘጠኝ መቶ ሰው ተገድሏል። እንዳንዶች እስከ ሁለት ሺህ አራት መቶ ያደርሱታል። ወላጆች የልጆቻቸውን አስከሬን ለመቀበል ዋጋ መክፈል

እንደነበረባቸው ይታወቃል። በርከት ያለ ገንዘብ በያንዳንዱ ጥይት።" (3)

በመሠረቱ ግድያዎቹ የተፈጸሙት በሰደድና በመኢሶን ስኳዶች ነበር። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ቤት ሰብረው እየገቡ ቀደም ብሎ ተጠቁሞባቸው የነበሩ ሰዎችን ጉትተው በማውጣት ገድለዋል። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የተገደሉቱ ሠልፍ ሲያደርጉ ወይም እንዲሁ መንገድ ላይ የተያዙት ብቻ ሳይሆኑ፥ መኢሶንና ሰደድ በርካታ አሥረኞችንም ከቀበሌ አሥር ቤቶች በማውጣት ረሽነዋል። ሬሳዎቹ በከተማዪቱ መስቀልኛ መንገዶች ላይ ተወርውረው ነበር። (ስለዚሁ ጉዳይ) የስዊዲሽ ሴቭ ዘ ችልድረን ፈንድ ዋና ፀሐፊ የሚከተለውን ብሏል፤ "አዲስ አበባ ውስጥ ፩ ሺህ ልጆች ተወፍጭፈዋል፤ ሬሶቻቸውም አውራ ጐዳና ላይ ተዘርረው ጅቦች ዘነጥለዋቸዋል። ከአዲስ አበባ ወጣ እንዳሉ፥ በአብዛኛው ከ፲፭-፲፫ ዕድሜ ያላቸው የተገደሉ ልጆች አስከሬኖች በመንገዱ ዳር ተቈልለው ይታያሉ።"(4) ሞፍዉፋው በለንደኑ <u>ዴይሊ ኤክስፕሬስ</u> በፒተር ማስን ወዲያውኑ ለዓለም የተጋለጠ ሲሆን ይህንኑ ሰው ደርግ ለሁለት ቀናት እግቶ ካቆየው በኋላ እባርሮታል።ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ደርግ "የጠራ የኑግ የኢምፔርያሊስት ፈጠራ" ነው ሲል ነገሩን ክዷል። በኋለኛው ጊዜም ደርግና መኢሶን "ሲፋቱ" አንድ የደርግ ባለሥልጣን (አሁን እሱ ራሱም በእሥር ላይ ያለና ሙቷል ተብሎም የሚገመት) ሞፍዉፋው በመሠረቱ "የመኢሶን ሥራ" እንደነበር ገልጧል። (5)

፵፱ ሰዎች በእንዲት ነጠላ ሌሊት፥ ከ፱፯ ወጣቶች በላይ በአንድ ሌሊት አዳር ብቻ መፍጀት፥ በካስትሮና በሌሎች ከልክ በላይ የተሞገሡው መንግሥት ገና የወንጀሉ ሃሲታዎች ነበሩ። በየሌሊቱ ፪፻ ያህል የሚገመቱ እሥረኞች እየተረሸኑ ከጅምላ መቃብር ውስጥ ይደቆ ነበር። ቀደም ብለን የጠቀስነው ስዊድናዊ ባለ ሥልጣን አዲስ አበባ የነበሩ ስዊድናዊ ምንጮችን በመጥቀስ ከ፪-፪፯ ሰዎች አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ በየሌሊቱ ይገደሉ እንደነበር ተናግሯል።(6) ነገር ግን ይህ ቍጥር በቀን ይገደል ከነበረው የሰው ቍጥር ጋር

በጣም የተቀራረበ ነበር። ይህ ሁኔታ በናዝሬት፥ በጐንደር፥ በደሴ፥ በደብረ ማርቆስና በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ሌሎች ከተሞች ሁሉ የተፈጸመ ነበር። እንድ የመኢሶን ካድሬ አለ ተብሎ እንደሚነገርለት በርግጥም ረገብ ያሉና ፉታ የማይሰጡ ቀናት፥ ሞት ያሉና ቀዝቀዝ ያሉ ቀናት ነበሩ። ሁኖም ግን በቀንና በሌሊት የሚደረጉት ርሸናዎች ድምር፥ በተንቀሳቀሰ ስሜት ይንደነዱ የነበሩትን ኑፍስ ገዳዮች እስከሚያስደነግጥበት ደረጃ ድረስ ፊጽሞ ወርዶ አያውቅም ነበር።

ደብረ ማርቆስ ውስጥ፥ ጥቅምት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም፥ የካቲት ፲፱፻፷፱ ውስጥ፥ ሠኔና ነሐሴ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ውስጥ የጅምላ ርሸናዎች መካሄዳቸው ተዘግቧል።

ከደሴና ከኮምቦልቻ ገረንገብ (ብዙ ጊዜ በ፲፱፻፷፱ ውስጥ፥ እንደገናም ነሐሴ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ውስጥ)አሥረኞች በቋርጥ በቋርጥ እየተወሰዱ ተረሽነዋል።

ከሚያዝያ ፳፫ እስከ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ብቻ ደርግ ራሱ ፳ሺህ ፯፻፲፫ ሰዎች በጐንደር፥ ሲዳሞ፥ ሐረርጌ፥ ባሌ ....ወዘተ ፀረ አብዮተኞችና አድኅርያን በሚል እንደረሸነ ገልጿል።

ታኅሣስ ፮ ፲፱፻፷፰ ሌሊት ብቻ ፫፻ የሚሆኑ ሰዎች አዲስ አበባ ውስጥ ተረሽነው የተቦተራረፉ አስከሬኖቻቸው አውራ መንገዶች ላይ ተጥለዋል። ያን ጊዜ አዲስ አበባን ይጐበኙ የነበሩ ሁለት የአሜሪካን ምክር ቤት አባላት ቢያንስ ፮ አሬሳዎች አውራ መንገድ ላይ ተወርውረው እንዳዩ ተናግረዋል። ከታኅሣስ ፮ ቀደም ብሎ ከአዲስ አበባ ፫፻፹፭ አሥረኞች፥ ከትግራይ ፱፥ ከወሎ ፹፬፥ ከጪቦና ጉራጌ ፴፪፥ ከጐንደር ፶፭ ተገድለዋል።

አዲስ አበባ ውስጥ በየቀኑ፥ በተለይ ሁለተኛው የተፋፋመ የግድያ ማዕበል ከጀመረ ከጥቅምት ፲፱፻፷፱ በኋላ

በዕከዩ የታወቀው የማንዲቦ ስኳድ ቡድኖች በላንድሮቨር ሁነው የፈለጉትን እንዳሻቸው እየገደሉ ከተማዋን ይዞሩ ነበር:: የስኳድ መኪናዎች ለመንገድ ትርዒት ያለተፈለጉ ሬሳዎችን ለማስለቀም እምቡላንሶችን አዘውትረው ያስከትላሉ፡ የማንዲቦ ነፍስ ገዳይ ስኳዶች ቢያንስ ከሰሯ-ፀ ሰው በማንኛውም "ተራ" ቀን ይገድሉ ነበር::

ወጣቶችና ልጆች ልዩ ዒላማዎች ነበሩ:: ጎዳር ፲፪ ቀን ተክለሃይማኖት አካባቢ (አዲሱ ዝቢያ) መኪና በማጠብ የሚተዳደሩሁለት ልጆች ተገድለው አስከሬናቸው አውራ ጉዳና ላይ ተዘረረ:: ታጎሣስ ፲ አዋሬ አካባቢ ፲፱ አስከሬናች አውራ ጉዳና ላይ የተጣሉ ሲሆን፥ ከዚህ ውስጥ የትናንሽ ልጆች አስከሬናች ጥቂት አልነበረም:: (በተጨማሪም ከነዚሁ ሬሳዎች ውስጥ የአንድ በጣም የሸመገሉ ሰው ሬሳና በመካከለኛ የዕድሜ ክልል የነበሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰሄዱ የተገደሉ ሴት ሬሳ ይገኝ ነበር::)

ታጎሣስ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹ ዓም የማንዲቦ ነፍስ ገዳይ ስኳድ አዲስ አበባ ባለው ማዕከላዊ መሥጊድ ውስጥ ዘው በማለት ፀሎት በማድረስ ላይ የነበሩ ብዙ ሰዎችን በመትረየስ አጨዱ:: በወቅቱ በኢሕአፓ ተገልጸ የነበረው ይህ ሁኔታ አዲስ አበባ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የኖር በነበረ የውጭ ሰው ዘገባ ተረጋግጧል:: በ ዘታይምስ (ለንደን 22/3/78 እንደ አውሮፓ አቆ.) የወጣው የሰውየው ሪፖርት እንደሚከተለው ነበር:: "የትልቁ መሥጊድ ይማም (በሽብር ስኳድ አባል) ተመትተው የሞቱ መስለው ወደቁና በኋላ ቀልባቸው ተመለሰ:: ወታደራዊው መንግሥት ይህን በሰማ ጊዜ የተሰማውን ሐዘን ለመግለጽ ጠርቷቸው "እናርኪስቶች መሥጊድ ላይ ጥቃት ፈጽመው ይህን ያህል ንጹሐን ሰዎች መገደላቸው በጣም አሳዛኝ እይደለምን?" ተባሉ:: እነውንቱ ይማም እንዲህ ሲሉ መለሱ፡ "በቀበሌያችን እናርኪስቶች የሉም፡ ያደረጋችሁት እናንተው ናችሁ፡ ግን ለምን? መሥጊዱ ውስጥ ቁርዓናቸውን በእጃቸው ይዘው የቆሙ ድኖችና ተራ ሰዎች ብቻ ነበሩ:: ዝናመ ምሕረትና እክለ በረከት እንዲሰጠን ነበር የምንፀልየው ፱ ሰዎች

ገደላችሁብን:: ለምን?" መልስ ሳያገኙ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው፡ ግን በማግስቱ ተመለዱና ከዚያ በኋላ ስለሳቸው የተሰማ ነገር የለም::

የማዕከላዊው ዓለም በቃኝ እሥር ቤት እሥረኞች የረሐብ እድማ እደረጉና ዘመዶቻቸውም ድጋፍ ሰጪቸው፡ ታዲያ ምላሹ ምን ሆነ? --- ርሽና::

በታሳልቅና በትናንሽ ከተሞች ከሴት እቤት ፍተሻ ተካሄደ፡ ውጤቱ?---- የጅምላ ርሽና::

እሥር ቤቶች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ሞሉ፡ መፍትሔው? -- ሴሊት ሴሊት በርካታ እሥረኞች እያወጡ መፍጀት::

መንናኛ ብዙኃኑም በተፈጸመው ግድያ እየፈነደቀ፥ ሰላባ ሁኖ ለወደቀው ልጅም ሆነ ፈጻሚት ፲፩ ፲፱፻፸፱ ቀበሌ ፲፫ አዲስ አበባ ውስጥ እንደተገደለው ታደለ ወልደ ጋብር የተባለ) የ፹ ዓመት ሽማግሌ "እጄን አልሰጥም ብሎ የፀጥታ ኃይሎች ላይ ተኩስ ለመክፈት የሞከረ እደገኛና መሣሪያ የታጠቀ እናርኪስት" ብለው ያቀርቡታል:: በመሊሶን ቃላት ደግሞ ግድያዎቹ በሚከተለው መንገድ ተገልጸዋል፡

ርሽና እሥራትና ብረበራ በአፈሊል መካሄዳቸው
የታወቀ ነው:: ግን እነዚህ እርምጃዎች የተወሰዱት
በለየላቸው የኢሕአፓ፥ የኢዲንና የሲ.ኢ.ሊ ቅጥር
ነፍስ ገዳዮች ላይ ነበር:: ...እርምጃዎቹ የተወሰዱት
በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮት በመቃወማቸው
ብቻ ላይሆን ለመቀልበስም በመሞከራቸው ነበር::...
አብዛኞቹ የተገደሉት በሰላም እጅ ባለመስጠታቸው ነበር:: ...
ሕዝቡንና አብዮቱን ለመከላከል እንደዚያ ዓይነቱን
እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነበር::

ለአምንስቲ ኢንተርናሽናል መልስ በእንግሊዝኛ፥ ሚይ 23/1977፥ ገጽ 16

መኢሶን እንዲያውም ከደርግ ጋር ከተቋራረጠ በኋላም እንኳ ያንኑ ቅኝቱን ይዞ ቀጥሏል። መስከረም ፮ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ለመታረቅ ገና ተስፋ ያልቈረጠው ነገደ ጉበዜ ለሷሞንድ (ጋዜጣ) ጥያቄ አቅራቢ በሰጠው ምላሽ፥ ስለ ቀይ ሽብሩ የቀረቡት ዘገባዎች "የዓለም አቀፍ ጎብረተሰብን አመለካከት ለመመረዝ" ሲባል የተጋነኑ ነበሩ ብሏል። አስፈላጊ እርምጃዎች፥ የተጋነኑ ዘገባዎች፥ በኢምፔርያሊስቶች የቀረቡ የተሳሳቱ ዘገባዎች፥ ቀይ ሽብሩ ይፋፋም ....እያሉ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ነገሮችን መኢሶንና ደርግ በሚለፈልፉበት ጊዜ ስለ ዓለም አቀፉ ጎብረተሰብም ሆነ በጅምላ በመረሸንና በመጠፍጠፍ ፀጥ ለማሰኘት ይረባረቡበት ስለነበረው ስለአገር ቤቱም ጎብረተሰብ አስተያየት ደንታ አልነበራቸውም። በ፲፱፻፸ ዓ.ም ወደ መጨረሻው አካባቢ በአዲስ አበባ የጅምላ ርሸናው እያበቃ በመላ ኢትዮጵያ ባሉ የገጠር ከተሞች ግን በእፍላኑት እየተጋጋመ በመምጣት ላይ ነበር። የጅምላ ግድያ ነበር የቀይ ሽብሩ ገጽታ፣ እንድ ትውልድ ጠርጎ ለማጥፋት ሆን ተብሎ የተነደፈ ፖሊሲ።

ነጻ እርምጃ፣ ይህ ሌላው የቀይ ሽብር ገጽታ ሲሆን፥ ስሙ በቀጥታ እንደሚያመላክተው በነጻ የመገደል መብት፥ በመያዝ አስፈላጊነት ሳይገቱ ተኩሶ የመምታት መብት ማለት ነበር። ለጥፋት ማስረጂያ ማቅረብ፥ ሕጋዊ መንገዶችን መከተል "በአብዮታውያን" ገዳዮቹ ዘንድ እንደ "ቡርዥዋው የሕግ ፍጽምና" ይቈጠራል። መኢሶን በተግባር ላይ እንዲውል ግፊት ያደረገበት ነጻ እርምጃ የተጀመረው በመስከረም ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ውስጥ ነበር። በዚህ ፖሊሲ መሠረት ስኳዶች "አናርኪስት" ነው ብለው የሚጠረጥሩትን ወይም መስሉ የተሰማቸውን ባዩበት እንዲገድሉ መብቱ ተሰጣቸው። ይኸው ፖሊሲ እንደሚፈቅደው በመንገዶች ላይ፥ በቢሮዎች፥ በፋብሪካዎች፥ የትም የት በማንኛውም ጊዜ ተኩሰ ሆነ። የስኳድ አባላቱ ከጂፖቻቸው ወይም ከፎንሞ መኪኖቻቸው ዱብ ዱብ ይሉና እንዱን ረሽነው ይቀጥላሉ፤ የሚጠየቅ ጥያቄ የለም። ስለባ ሁኖ የወደቀው ሕፃን፥

ሽማግሌ፥ ወይ ባልቴት፥ ቄስ ወይም ደግሞ ተማሪ ሊሆን ይችላል። ግድ አልነበረም።

ነጻ እርምጃውን የቀበሌ ስኳዶች የግል ቂም በቀልን ለመወጪያ፥ ውይም ለሌላ ለማንኛውም በቂ ገንዘብ ከፍሉ ጠላቱን ለማስወገድ ለፈለገ፥ ቅጠረኛ በመሆን ይጠቀሙበት ነበር። ኮረዳዎች ይደፈራሉ ይረሸናሉ፣ ነጋዴዎች ይዘረፋሉ ይረሸናሉ፣ ተቀናቃኞች ይገደላሉ። በዚያን ጊዜ የበላይነቱን ይዞ የነበረው አእምሮ ቢስነት በአንድ የሷሞንድ ጋዜጠኛ በሚከተለው መልክ ቀርቧል፤

> "አንድ ፒዮላ አካባቢ ያምትኖር ሕመምተኛ
> እናት አንድ ግምሺያ ላይ ያሳትን አንድ ሴኛ
> ወደ ፋርማሲ (መድሐኒት ቤት) ላከቻው።
> ወደ ቤቱ ሲመለስ ኩበሉ ከአደባባዩ ደረጃ ላይ
> በጥይት ራሱ ላይ ተመትቶ ሞተ። ገዳዮቹ
> ፈላውን በሚማ ገልፀተ አድርገው አይተው ያጯቸን
> እናት 'ይቅርታ ሴላ ሰው መስሉን ነው (ያገደልነው)'
> አሏት።" (7)

እነዚህ እንግዲህ ጠዋኑት ያላቸው ገዳዮች መሆናቸው ነበር፣ ከነጻ እርምጃው ይትበሃል ጋር የሚሄድ አልነበረም። አንድ የደርግ አባል ለተሰበሰቡ የቀበሌ መሪዎች (መስከረም ፭፱ ቀን አዲስ አባባ ውስጥ) "ነጻ እርምጃው ወጣቶች ላይ እንዲያተኩር የታሰበ ነው።" ብሎ እንደተናገረ ይታወቃል።(8) ከፋርማሲ ሲመለስ የተገደለው ኮበልም እንደማንኛውም ሁሉ ዒላማ ለመሆን የሚፈልገውን ያሟላ ነበር።

በመሠረቱ ጠቅላላው ፖሊሲ ጎሊናን ከመሰት የመነጨ ከመሆኑ የተነሣ የጉንደሩ አስተዳዳሪ ነፍሰ ገዳዩ የደርግ አባል ሻለቃ መላኩ ተፈራ የልዩ ኮማንዶ አሣሹን ይጠራና በጉንደር ከተማ "ለግማሽ ሰአት ነጻ እርምጃ!" ብሎ ያዝዘው ነበር። ይህንንም ተእዛዝ ተከትለው ኮማንዶዎች ከተማ ውስጥ ይገቡና የተተመነው ሰአት እስኪሞላ ድረስ ያሻቸውን ማንኛውንም መንገድ ላይ ያገኙትን ይገድሉ ነበር። እንደዚህ ባሉት ጊዜያት

ቤት ሰብረው የሚገቡ ቢሆንም ኑሮ የሚቹ ቍጥር የላቀ በሆነ ነበር። ኻለቃ መላኩ እርምጃውን የሚያዝዘው ባሰኘው ጊዜ ሲሆን፥ የግድያው ፈንጠዚያ ለምን ያህል ጊዜ መቈየት እንዳለበትም የሚወስነው እንደፈቀደው ነበር።(በወቅቱ የነበሩት አቡን"ከመልዓኩ መቅሠፍት ይሠውራቸሁ" ብለው ያሳረጉት ያለ ምክንያት አልነበረም)[1]

መኢሶን ይሀን ፖሊሲ ከግፍቀሩ የተነሣ ከደርግ ጋር ተጣልቶ ሲለያይ ከደርግ ጥፋቶች አንዱ "ከውስጡ ያሉ አድኀርያን ነጻ እርምጃውን ለማስቆም መሞከራቸው ነበር፣" ብሎ ይከራከር ነበር። ከቤት እቤት ፍተሻ፣ እንደገና የዚህ እርምጃም ሐሳብ የመነጨው ከመኢሶን መሪዎች አፍላቂ ምናብ ነበር። ፖሊሲው በአዲስ አበባው የሕዝብ አደራጅ ጽቤትና የዚያም መሪ በነበረው በከበደ መንገሻ ተጽፎ በማስታወሻ መልክ ለደርግ የቀረበ ነበር። ከ"ቀይ ሽብሩ" መንገሻ ተጽፎ በፊት ከቤት እቤት ይደረግ የነበረው ፍተሻ ያን ያህል የተጠናከረና በሚገባም የተደራጀ አልነበረም።

በ"ቀይ ሽብሩ" ሥር ከቤት እቤት ፍተሻ በዕውቱ "አልሸሹም ዞር አሉ" ዓይነት ነገር ነበር። የተፈለገው ለደንቡ ያህል የሚደረገው ፍተሻ ሳይሆን ይበልጥ ሥፋት ላለው ግድያ ሽፋን እንዲሆን ነበር። ፍተሻዎቹ በዘፈቀደ የሚደረጉ ርሽናዎችን ነጻ እርምጃዎችን ያስከተሉ ነበሩ። ተጠርጣሪው ከተገኘ ይገደላል፤ ካልተገኘም ቤቱ ውስጥ የተገኙት በጅምላ ይገደላሉ፤ ቢያንስ አንድ ወይም ሁለት አይቀርም።

የመጀመሪያው ፥ እኔ ነኝ ያለው ከቤት እቤት ፍተሻ መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም. ተጀምሮ ፱ ቀናት ቆየ። ሌላ ደግሞ ሚያዚያ ፭፱ ቀን መጣና ሁለት ቀናት ቆየ። መስከረም ፴ ላይ መርካቶ (አዲሱ ገበያ) የሌሊት ፍተሻ ተደርጎ የበርካታ ሰዎችን ሞት አስከተለ። ፍተሻው መጀመሩ ሲገለጽ ቡና ቤቶች በሙሉና የሲኒማ ቤት አዳራሾች ይዘጋሉ፤ የስካዶችና የፀጥታ

[1]ትርጉም ላይ የተጨመረ

ኀይሎች መኪኖች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎች መኪኖች መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድላቸውም። ሰው ቤቱ ውስጥ እንዲቆይ የግቢ በሮችና የቤት በሮች ክፍት እንዲሆኑ ይታዘዛሉ። በፍርሐት የሚወመድድ ፀጥታ ከተማዋ ላይ በሚረብበትና ሰው ጥሏት እንደሸሸ ወና በምትመሥልበት ጊዜ ስኳዶችና የፀጥታ ሰዎች ከቤት እቤት እየተንቀሳቀሱ ግድያቸውን ይያያዙታል። የከተማዪቱ መውጫዎች ሁሉ በታጠቁ ወታደሮችና እዚህም እዚያም አሰሁ የምትሰውን ካላሺንኮቭ እንግበው የ ሰምንት መቶ ያህል "ተጠርጣሪ አናርኪስቶች" የመታወቂያ ፎቶግራፎችን ይዘው ኪላዎቹን በሚቆጣጠሩ የሰደድና የመኢሶን ስኳዶች ይዘጋሉ።

ፍተሻው በእፊሴል የሚታወቀው የኢሕአፓ ተጠርጣሪዎችን የጦር መሣሪያን፥ የዲሞክራሲያ እትሞችን፥ የኢሕአፓ የሙዝሙር ካሴቶችን፥ የማባዣያ መኪናዎችን፥ ....ወዘተ ለማግኘት ነበር። ሬድዮው ግን በድል አድራጊነት መንፈስ ይገልጽ የነበረው በፍተሻው ወቅት " የቅቤ፥ የማር፥ የማሪያ ቴሬዛ ብሮች፥ ...ወዘተ" መያዝን ነበር። ይህ ሁሉ ደግሞ እንደ "ኢሕአፓ ክዝን" ተደርጎ ነበር የሚቀርበው። በሌላም አንጋገር እየተካሄደ የነበረው የጠራ የጎጣ ዝርፊያ ነበር ማለት ነው። ሁሉም ነገር በቅቤ በበርበሬ በጥንታዊ የጥሬ ብር ገንዘብ ስርቆት ላይ ብቻ ተወስኖ ቀርቶ ቢሆን ኑሮ ምናልባት ሰው ብዙም ባልገደደው ነበር። ፍተሻዎቹን አሸባሪ ያደረጋቸው በዘፈቀደ የሚደረገው ግድያ ነበር። ከቤት ሳልተገኙ ልጆቻቸው ምክንያት ማቅረብ ያልቻሉ ይገደላሉ፤ አንድ የዲሞክራሲያ እትም ከአንድ ሰው ቤት ከተገኘ ምን ያህል ሰው መገደል እንዳለበት የሚወስነው የፍተሻው ቡድን መሪ በታየው ነው። በሁሉም ሁኔታ ግን አንድ ሰው መገደሉ አይቀርም። ፈታሹ ቡድን ኮረጻዎቹን ይደፍራል፤ አንዳንዶቹን ሲገድል ሌሎቹን ይምራል። ቤት ውስጥ ገንዘብ ከተገኘ ባለቤቱ ላይ ነፃ እርምጃ ይወሰድና ገንዘቡ በወራሪዎቹ ይወረሳል። የሚቹ ቍጥር ከፍ ያለ ነበር። መንግሥት በየቀኑ በሬዲዮ "እጅ ያልሰጥም ያሉ ፀረ አብዮተኞች ተደመሰሱ" እያለ በማውራት በተፈፀሙት ግድያዎች ይፈነድቅ ነበር።

ኢሕአፓ ፍተሻ የሚካሄድበትን አለት ቀደም እያለ ለማወቅ ይችል ስለነበር ከቤት እቤት ይደረግ የነበረው ፍተሻ መዋቅሩን ከግምት ውጭ የሆነ ጉዳት አላደረሰበትም:: ሁኖም በአሰላው ወቅት በርካታ የኢሕአፓ አባላት ተገድለዋል፡ በማጋቢቱ ፍተሻ የኢሕአፓ አባልና የኢሠማ ሊቀመንበር የነበረው ማርቆሥ ሀነስ ከወታደሮች ጋር ተታኩሶ የሞተ ሲሆን የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው ተሥፋዬ ደበላይ በመንግሥት ስኳዶች በመከበቡ ከርቅ ሕንፃ በመዝለል ራሱን ገሏል:: (9)

በኬላዎች ላይ የሚደረጉ ግድያዎችም በዘፈቀደ የሚካሄዱ ነበሩ:: ከእንዲህ ዓይነቶቹ ኬላዎች አንዱ ከነበረው ከአታቂው ኬላ ላይ ነበር:: ኑጋ አየለ፥ መላኩ ማርቆስና ዮሐንስ ብርሃነ ከአንድ እንግሊዛዊ የዩኒቨርሲቲ መምሕር ጋር የተገደሉት:: (10)

መላዪቱ ከተማ በነፍሰ ገዳይ ስኳዶች ተወርራ ትንፍሽ ልውሽ የማትልበትና እኒሁ ስኳዶች ቢያጠፏትም ቢምሯትም ቀልባቸው በመራቸው የሚወስንበት ሁኔታ ምናልባት በዚህ ደረጃ በሌሎች ብዙ ሀገሮች የማይታወቅ ይሆናል:: የሆነው ሁኖ ከቤት እቤት ፍተሻው ኢትዮጵያ ውስጥ የ"ቀይ ሽብሩ" ዘመቻ አካል ሁኖ በመምጣት ቁጥር የሌላቸውን ሰዎች በጭፍን ለመግደል መጠቀሚያ የሆነ አዲሱ ገበያ (መርካቶ) አካባቢ የኢሕአፓ ስኳዶችና ኑጋዲዎች የመንግሥትን ሰው በላ ስኳዶች በሚጋተሩበት ጊዜ ተከሱ ብርቱ ይሆናል፡ ሁኖም የሚቹ ቁጥር በዚያን ሁኔታም ቢሆን ከፍ ያለ ቢሆን እንዲፈለጉት ቢሆንም ለመግደልና ለመዘረፍ እንዳይችሉ ያደርጋቸው ነበር::

ግብረ ሰይል ፣ (Torture) በኢትዮጵያ ውስጥ በፖሊስ ወይም በፀጥታ ሰዎች የሚደረግ ምሪመራ ለረጅም ጊዜ ከግብረ ሰይል ጋር ተመራራሽ ሁኖ ኑሯል :: ጥፋቱን ወዲያውኑ የሚያምን ትንሽ መቅመሱ አይቀርም ፣ የማይቀመሱ ጥቂቶች ናቸው ::ግን የግብረ ሰይልም ዓይነት

ዓይነት አለው ፣ ኃይለ ሥላሴ የፖለቲካ አፈንጋጮችን ወይም የተያዙ የሽምቅ ተዋጊዎችን ምሥጢር እንዲያወጡ ለማድረግ በዚሁ ዘዴ ይጠቀሙ ነበር :: የተጠረጠረ ሌባ በምርመራ ጊዜ ልምጭ ይቀምሳል :: ግን በፖለቲካ ምክንያት እንደታሰሩት የከፋ ግበረ ሰይል አይደርስበትም ነበር :: ይሀን ሁሉ " ቀይ ሽብር " ቀየረው :: በመሠረቱ ባጠቃላይ የደርግ የግፍ እገዛ ነው ይሀን ሁሉ የቀየረው :: እያንዳንዱ ÷ ለግብረ ሰይል ይደረጋል ፣ ከዚህ ቀም ስቅል ለማምለጥ ያለው ዕድል አስቀድሞውን አለመያዝ ብቻ ነበር::

ግበረ ሰይል የሽብሩ ዘመቻ የማይነጠል አካል ነበር :: በጣም ጥቂቶች ነበሩ ለማምለጥ በርግጥ ዕድለኞች የነበሩት :: ሽማግሌ ወይም ወጣት ሳይባል ማንኛውም ሰው ነበር ግበረ ሰይል የሚፈጸምበት :: ንጹሕ ሆን ጥፋተኛ ለውጥ አልነበረውም ፣ ምክንያቱም ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹ እሥረኛውን ብለው ብለው በሚወጣላቸው ጊዜ እሥረኛው ወይ ሙቷል ፡ወይም ደግሞ " ጥፋቱን " እያወጣ ነው :: " ጥፋቱን " ስላወጣም ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹን ያስቆማቸዋል ማለት አይቻልም ፣ ጥፋትን እምኖም መደብደብ ነበርና :: ከጥያቄ በፊትም በኋላም አይቀርም :: በሚከረፋውና በጣም በተጨናነቀው የቀበሌና የፀጥታ እሥር ቤቶች ክፍሉች ውስጥ በመበስበስ ላይ ያለ የሰው ሥጋ ÷ የተቈረጡ እጅ እግሮች ÷ የተመጻመጹ ጀሮዎች ÷ የተፎነኑ አፍንጫዎች ÷ የተመዘዙ ጥፍሮች ÷ የተጉለጉሱ ዓይኖች ÷ የተጨፈለቁ ቈለጦች ÷ የተብጣጠሱ የሴት ብልቶች ÷ የተቃጠሉ ጀረባዎች ÷ የተቃጠለ ፀጉር .....ምኑ ቅጡ ÷ ምስክርነታቸውን እነሆ ይላሉ :: እነዚህን የግዳርና የዋይታ ክፍሉች ነበር ካስተሮ " ዕውነተኛው አብዮት " ብሉ ያሞገሡው ዕውነተኛው ገጽታ ::

በልዩ ልዩ እሥር ቤቶችና የቀበሌ ማቆያ ማዕከሎች የሚከተሉት የግብረ ሰይል ዘዴዎች እሥረኞች ላይ ውለዋል፡

ግርፋት፡ ይህ አብዛኛውን ጊዜ ወፌ ኢላላ ተብሉ የሚጠራውና እንዲሁም እሥረኛው ከመገረፉ በፊት ከሚታሠርበት የአስተሣሰር ዓይነት ተነሥቶ ቁጥር ፭ ወይም ፮ ተብሎም የሚታወቀው አበር :: አለንጋው አኮርማጅ ወይም ከውስጡ ብረት ያለበት ጎማ አበር :: ግርፋቱ የሚፈጸመው አብዛኛውን ጊዜ ውስጥ እግሮች ላይ ሲሆን፥ ጀርባም ጭምር ይደርሰዋል :: በአንዳድ ሁኔታ እሥረኛው ውኃ በሞላ በርሜል ውስጥ በጭንቅላቱ ተዘቅዝቆ እንዲዘፈቅ ይደረግና በዚያው ሁኔታ ላይ እንዳለ ይገረፋል :: (ይህ በጉንደር እሥር ቤት ያለማሠለስ ለሞት ያበቃ ቅጣት አበር)

ሕመሙ ይበልጥ እንዲያሠቃይ ግበረ ሰይል አድራጊዎቹ የውስጥ እግር (የጫማ)ቆዳውን በካራ ይሸነታትፉና ያንን ቁስሉን ከመግረፋቸው በፊት እንዲነፈርቅ ለሁለት ቀናት ያህል ያቆዩታል :: በሌላ ሁኔታ ደግሞ ግርፋቱ የእሥረኛውን ቆዳ ሲሰነጣጥቀውና ሲቈስል ጥሬ ጨውና በርበሬ ይነሰንሰብታል :: ወይንም ሽንት ቀሰሉ ላይ ያፈሰብታል :: ጭንቅላት ደግሞ ሥለታም ጠርዝ ባለው ማሥመሪያ ይመታል ::

ግበረ ሥጋዊ ሰይል ፡ ትላልቅ ሴቶችንና ልጃገረዶችን መድፈር የተለመደ አድራጎት አበር:: ከተደፈሩት አንዳንዶቹም የዘጠኝ ዓመት እምቦቃቅላዎች አበሩ:: ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሴት እሥረኞች ለ"ጥያቄ" ተጠርተው ከተወሰዱ አብዛኛውን ጊዜ ጥሬው ÷ ለመድፍር የሚደረግ አበር :: ምንም እንኳ ግበረ ሰይሉ የተፈጸመባቸው ሐፍረት እየተሰማቸው ለመግለጽ ፈቃደኛ ባይሆኑም ደፋሪዎቹ እንደሚፈራረቁባቸውና ግበረ ሰዶም እንደሚፈጽሙባቸውም ይታወቃል ::

ወንድ እሥረኞችም ፍም እስኪመስል የጋለ ብረት በፊንጢጣቸው በመስደድና ቈለጣቸው ላይ ወይ እባለ ዘራቸው ላይ ውኃ ወይም እሸዋ የሞላበት ጠርሙስ ፡ በማንጠልጠል ግበረ ሰይል ይፈጸምባቸዋል :: ወታደራዊ

ፖሊስ ጠቅላይ ሠፈር ውስጥ ቈለጥ በመወፍለትና በማምከን የተካኑ አበሩ ::

የሴቶች ሐፍረተ ሥጋ ÷ ረጅምና ወፍራም ዘንግ እየተሰደደበት ÷ ጠርሙስ እየተከተተበት ÷ (ጠርሙሱ ወደ ውስጥ ይመታና እዚያው ውስጥ ይሰበራል) ወይም የደቀቀ የጠርሙስ ስፋጭ እየተወመረበት ብጥስጥሱ ይወጣል::

ሸንጠላ ፡ በሥለታም ካራ የከንድና የጭንን ቆዳ መገፈፍን÷ ጥፍሮች መዝዞ ማውጣትን÷ ጣቶችን በትንንሹ መከታተፍን ÷ እፍንጫና ጉንጭን በጥንሳ መበጠስን÷ የብልት አካባቢ ፀጉርና ቆዳን በጥንሳ መንጨትን ÷ የሴትን የጡት ውልብልቢት (ጫፍ) መቍረጥን ÷ ፀጉርን ÷ ጀርባን ÷ ሆድን ÷ በእሳት መለብለብን ያጠቃልላል :: በአንዳድ ሁኔታዎች እጅ እግር መቁረጡ በተራ የእናጢ መጋዝ በመገዝገዝ የሚካሄድ ይሆንና እጅግ ዝማ ያለ ይሆን አበር :: እሥረኞችን የፈላ ዘይት ውስጥ መዝፈቅና ከዚያ አውጥቶ ደግሞ ቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ መጨመርም አበር ::

አዳዲስ እሥረኞችን ለማስፈራራትና ቁስለኞቹም ጠንብተውና የገዳር ቀናት አሳልፈው እንዲሞቱ ምን ጊዜም ለቍስል የሚደረግ የሕክምና እንክብካቤ አልነበረም ::

በላዔ ሰብእንት ፡ እስደንጋጭ ይመስል ይሆናል ፡ (ነውም) ይህም ጭምር በነዚያ ደናቁርት እንደ ሽብሩ ዘመቻ አካል ተደርጎ በሥራ ላይ ውሏል:: የሰው ሥጋ የሚበሉት ግበረ ሰይል ፈፃሚዎቹ ሳይሆኑ እነሱ አስገድደው እሥረኞቹን ነው የሚያስበሏቸው:: መግቢያው ላይ የጠቀስነው የልጃቸውን የተከታተፈ አባለ ዘር እንዲበሉ የተገደዱ እናት ታሪክ አለ :: (ጎንደር ነው ታሪኩ የተፈጸመው) በአዲስ አበባው የፀጥታ እሥር ቤት ውስጥ ብዙዎች የራሳቸውን የተከተፈ ሥጋ እንዲበሉ ተገድደዋል ::

ተገድዶ መብላቱ የሰው ዓይነ ምድርን (ሠገራን) ይጨምራል :: (እንደገና ይህም በአዲስ አበባ የፀጥታ

ማዕከላዊ እሥር ቤትና ወታደራዊ ፖሊስ ጠቅላይ ሠፈር ውስጥ ይደረግ የነበረ ነው ::) እሥረኞች የሰው ደም እንዲጠጡና አክታ እንዲውጡም ይደረግ ነበር::

ለአምሯዊ ግበረ ሰይል ፣ ይህ ፣ በሥፋት ሥራ ላይ የዋለ ነበር:: ሰውነታቸው የተዘንጣጠለ ፥ ቁስላቸው አመርቅዞ የሚከረፉት እሥረኞች አዲስ መጥ እሥረኞች ውስጥ ይወረወራሉ :: አዲስ መጥ እሥረኞች ሌሎች ላይ ግበረ ሰይል ሲካሄድባቸው እንዲመለከቱ ይገደዳሉ :: " ቀይ ሽብር " በተጋጋመበት ወቅት የቀበሌ ነዋሪዎች ባጠቃላይ እንዲመጡ ይደረግና በአደባባይ የሚካሄድ ግበረ ሰይል እንዲያዩ ይደረጋል :: ፍንክች አልል ያለ እሥረኛ ወላጆች ከፊቱ ቀርበው ግበረ ሰይል ሲፈጸምባቸው እንዲመለከት ይገደዳል :: እሥረኞችን ለማደናገጥ የማስመሰል ርሽናዎችም ይካሄዳሉ :: (በዚህ የአዲስ አበባው ወታደራዊ ፖሊስ ጠ/መምሪያ የተራቀቀበት ነበር ::) በግብረ ሰይል ቁም ስቅላቸውን የሚያዩ ሰዎች የጣር ጩኸት ሆን ተብሎ አዲስ መጥ እሥረኞች እንዲሰሙት ይደረጋል :: ሌሊት ሌሊት የሚፈጸመው ግበረ ሰይል በጣም የከፋ ስለነበርና ርሽናዎችም አዘውትረው የሚካሄዱት በዚሁ ጊዜ ስለነበር እሥረኞች እንቅልፍ አጥተው ያድራሉ :: ጭካኔ ያገበራቸው ዘበኞች በሩን የከፈቱ በማስመሰል በሚፈጸመው ማታለል ሥቃያቸው ይባባሳል :: አንዳንድ ጊዜም መኩንኖች የሰም ዝርዝር ያለው ወረቀት ይዘው ይመጡና የእሥረኞቹን ስም ከጠሩ በኃላ ፥ ልንገደል ነው ብለው ያሰቡትን ሰዎቻቸው የተጠሩ ሰዎች ትተው ይሄዳሉ :: እሥረኞች በተሰይ የቅርብ ዓደኞሞች፥ አንዱ በሌላው ላይ ግበረ ሰይል እንዲፈጽሙ ይገደዳል::

የእሥር ቤቶች ሁኔታ ራሱ የሚቻል አልነበረም:: አራት ተኩል ሜትር በአራት ተኩል ሜትር ስፋት ባላት ክፍል ውስጥ ከሃ በላይ የሚሆኑ እሥረኞች ጀርባ ለጀርባ ገጥመው ታምቀው፥ ለመጋደም በቂ ቦታ አይገኝም:: ለመጸዳጃ እገልግሉት የምትውለው፥ አብዛኛው አብዛኛውን ጊዜ ሞልታ የምትፈስ ጥማ ይዛ የምትገኝ አንዲት ትንሽ ባሊ

ናት:: የክፍሏ መጠንባት፥ የሽንቱ፥ የትውከቱ ግብረ ሰይል የተፈጸመባቸው እሥረኞች ቁስል ሽታ ...አይጣል ነበር::

ግብረ-ሰይል የሚፈጸመው የትም ነበር:: እጅግ አረመኔነት ይታይባቸው የነበሩ ቦታዎች፥ የቀበሌ እግቶ ማቆያ ማዕከሎች (በመኢሶን ወይም በደርግ አባላት ይስተናበሩ የነበሩ) ምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ግቢ ውስጥ የሚገኘው የፀጥታ ዋና መ/ቤት፥ የድሮው ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል አጠገብ፥ አዲስ አበባ የሚገኘው የወታደራዊ ጠ/ፖሊስ መምሪያ ነበሩ:: ግብረ-ሰይል ፈጻሚዎቹ የፀጥታ ፖሊስ አባሎች፥ የቀበሌ ባለሥልጣኖች ወታደሮች (በተለይም በጎንደር ደግሞ ልዩ ኮማንዶዎች) ነበሩ:: ሰዚህ አመፃ የተዳረጉት ደግሞ ከልዩ ልዩ የጎብረተ ሰብ ክፍል የወጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች፥ ሽማግሌዎች፥ ሴቶች፥ ወንዶች ነበሩ:: ብዙዎች አካላዊ ጉዳቶች ደርሰውባቸዋል:: ብዙዎች አእምሯቸውን ነሥቷቸዋል:: ብዙዎች ያበዱም ጭምር በጥይት ተገድለዋል፤ በደርግ ዓይን ዕብደት " ከትክክለኛ ፍርድ ለማምለጥ ምክንያት አይሆንምና:: ሁኖም ብዙዎችም ተርፈዋል፤ አንዳንዶቹ አሁንም ከእሥር ቤት ናቸው:: አንዳንዶች "ነጻ" ተለቀዋል፤ ሌሎች ደግሞ ሰደት ላይ ናቸው::

ከግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የተገደሉ ሌሎቹ ሰላማዊ ሞት የሞቱ ቢሆኑም አሁንም እንዳሉ አሉ ማለት ይቻላል:: ከግብረ-ሰይል ፈጻሚዎቹ ጥቂቶችም፥ ፍዳ ሲያበሏቸው እንደነበሩት ጥቂቶች ሁሉ እነሱም ለስደት በቅተዋል::

የስምንት ዓመቷ ልጅ ዋሳቸው መንግሥቱ በኢሕአፓ አባልነት ይጠረጠሩ የነበሩ ወንድሞቹ ያኖሯቸውን ሰንዶች ደብቀሃል በሚል ክስ ጎንደር ውስጥ ተያዘ:: ዋሳቸው፥ ታውቃለህ ብለው ችክ ያሉበትን (የሰነዶቹን) መደበቂያ ቦታውን ለማሳየት ባለመቻሉ በሚያሰቅቅ ሁኔታ ለቀናት ግብረ-ሰይል ተፈጸመበትና በሥቃይ ላይ እንዳለ ሞተ::

ዓለማየሁ፥ ዕድሜው ፭፪ መኖሪያው ኮልፌ አካባቢ (አዲስ አበባ) የነበረ ተማሪ ሲሆን ሚሳይ ዓለሙ ደግሞ ዕድሜው ፭፯፥ መኖሪያው አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ የነበረ ሠራተኛ ነበር። ሁለቱም የተያዙት የኢሕአፓ አባላት ናችሁ በመባል ነበር። በተደጋጋሚም ማብረ-ሰይል ከተፈጸመባቸው በኋላ፥ ሚሳይ ላይ ቤንዚን ተርከፍክፎ እሳት ተለኮሰበትና ወዲያውኑ ተቃጥሎ ሞተ። የዓለማየሁ ሥቃይ ግን ተራዘመበት። ጠቅላላ ልብሱን እንዲያወልቅ ከተደረገ በኋላ ዕርቃኑ ሥጋው ላይ ቤንዚን እንዲርከፈከፍበት ተደረገና በእሳት ጋየ። ለተቃጠለው አካሉ ምንም ሕክምና ሳይደረግለት ተትቶ ከሞቂት ቀናት በኋላ ሞተ። ባሕር ዳር፥ ብርሃኔ ኪዳኔ የተባለ ዕድሜው ፭፩ ወጣት የነበረ ልክ እንደ ሚሣይ በቤንዚን ተቃጥሎ ሙቷል።

መኖሪያዋ ቄራ አካባቢ፥ ዕድሜዋ ፭፪ የነበረ ሂሩት በአሰቃቂ ሁኔታ ማብረ ሰይል ተፈጽሞባታል። ሁለቱ ጡቶቿ ትንሽ በትንሽ ከተቆረጡ በኋላ ፍም የመሰለ የጋለ ብረት በብልቷ ተሰድዶባት ሙታለች።

ሀሰኑ አልቃሲም ጉንደር እሥር ቤት ውስጥ ማበረ ሰይል ሲፈጸምበት ሙቶ የተዘጓጠለ ሬሳው ለትርዒት እንዲታይ አውራ ጉዳና ላይ ተወረወረና አስር ዓመት ያልሞላው ትንሽ ወንድሙ የወንድሙን ሬሳ በተመለከተ ጊዜ ውሽቱን ለቀቀው። የመንግሥት ስኳዶች " ለሞተ አናርኪስት " ማልቀስ ክልክል መሆኑን የሚያዝዘውን ትእዛዝ ጣሰ በሚል ወዲያውኑ ተኩሰው ገደሉት።

ዕድሜው ፭፭ ዓመት የነበረ ጎይሉ አስፋው የተባለ ተማሪ በማብረ ሰይል ባለሟሎች ክፉኛ ተደብድቦ ሕክምና ባለማግኘት በደረሰበት ቁስል ለሞት በቅቷል።

ዕድሜዋ ፭፭ ፥ መኖሪያዋ ጸባት የነበሩ እታገኝ ብርሃኑ የአምስት ወር ነፍሰ ጡር ነበረች ስትያዝ። ማበረ ሰይል ተፈጽሞባት ከመገደሏና አውራ ጉዳና ላይ ከመጣሏ በፊት በርግጥ ሕይወት ነበራት ብሎ ለመናገር አያስደፍርም ነበር

። ከዚ ሬሳ ጋር ፈንቱ ገላው የተባለ የሴላ እሥረኛ የተቈራረጠ ሬሳ አብሮ ለትርዒት ቀርቧል።

ጉንደር ውስጥ መምህር የነበረው የ፴፬ዓመቱ ዮናስ አዲሱ ለዘብ ያለ የፖለቲካ አመለካከት ነበረው። ታዲያ ተያዘና " የኢሕአፓ ከፍተኛ መሪ " ነህ በሚል ተከሰሰ። ለሳምንታት ፥ ስሞች መዋቅርና የመደበቂያ ቦታዎች እንዲያወጣ ማበረ ሰይል ተፈጸመበት ፤ ግን ሊያወጣ አልቻለም። በኋላም ከወገቡ በታች ሽባ ሁኖ ከተለያዩ የሕመም መንሤዔዎች ይሥቃይ ጀመር። ባለ ሥልጣናት ለሽልማት የሚያበቃውን ዋናውን ይዘናል ብለው አስበው ነበርና ወደ ሆስፒታል ወሰዱት። እዚያም እጆቹና እግሮቹ ከአልጋው ጋር ተጠፍረው ሕክምና ተደረገለት። ቆየት ብሎም ሴላ እሥረኛ ዮናስ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር እንዳልነበረ የፀጥታ ሰዎቹን ሊያሳምናቸው ቻለ። ጥቅምት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ዮናስ ከሆስፒታል በቃሬዛ እንዲወጣ ተደርጎ መቃብር ውስጥ ተወረወረ ፤ በሕይወታቸው ከተቀበሩት ጥቂት የሽብር ሰለባዎችም አንዱ ሆነ።

ኢብራሂም ዘለቀ ፥ ሀሰን ሞሐመድ ፥ አሠፋ ጀማነህ፥ ሞገሥ በላይ ፥ ታደሰ አያሌው ፥ሰርጎ ሙሔ ፥ ሺታሁን አስጢፋኖስ ፥ መላኩ ወልደ ትንሣኤ ፥ ገብረ ጻድቃን ጎይሌና ቱጥር የሴላቸው ሌሎች አረመኔያዊ ማበረ ሰይል ተፈጽሞባቸው ተረሽነዋል። የሴፍ አዳን አከርካሪ አጥንቱ በማብረ ሰይል ከተሰበረ በኋላ፥ አያሌ የቁም ስቅል ተቀብሉ " መዳረሻው እንደጠፋው " እንደ ፍቅሬ ዘርጋው ፥ አሱም የት እንደደረሰ የሚያውቅ የለም። እንደ ሀብታም አንዳርጋቸውና እንደ አልማዝ ታደሰ ያሉ ልጃገረዶች እጅግ ጭካኔ በተመላበት ማበረ ሰይል ከተፈጸሙ በኋላ ሞት ገላግሏቸዋል።

ሽብሩ ፥ በመንግሥቱ የዓመፃ አውታራትና በስኳዶቹ ውስጥ ታምቆ የነበረውን ጭካኔና አውሬነት እንዳሰ በእደባባይ እንዲወጣ አደረገው። ለትርዒት ተብሎ ሬሳዎች አውራ ጎዳና ላይ ሲወረወሩ የማብረ ሰይል ፈጻሚዎቹን

አውሬነት ማየት ይቻል ነበር :: ይኸው አሲቃቂ ግበረ ሰይል አሁንም በ" ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ው" መንግሥት እሥር ቤቶች ውስጥ እየቀጠለ ነው:: (11)

የራሳ ትርጒት ፡ ይህ " የቀዩ ሽብር " የብቻው የሆነ የራሱ ፈጠራ ነበር :: ሐሣቡ ከሶቪየቶችና ከምሥራቅ ጀርመን አማካሪዎች የመጣ ነው የሚሉ አሉ ፡ ለሁሉም ግን መንግሥቱ ያን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋሉ ራሱ አረመኔነት ነው ::

እሥር ቤት ውስጥ የሞቱ ÷ ግበረ ሰይል ሲፈጸምባቸው የሞቱ÷ በነጻ አርምጃ የሞቱ ሰዎች በደም የተበከሉና ዝንጥልጥላቸው የወጣ ሬሳዎች ÷ በመስቀልኛ መንገዶች ላይ ÷ በዋና አውራ ጎዳናዎች ላይ ÷ እቤቶች አጠገብ ይጣሉና ለአንድ ቀን ትርዒት ሁነው ይታያሉ :: ማንም ወላጅ ÷ የዘመዱን ÷ የልጁን ሬሳ ማንሣት አይችልም :: ማንም ሰው ማልቀስ አይችልም ፡ እንዲያውም የቀበሌ ነዋሪዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጎ እንዲህ እያሉ መዝፈን ይገደዳሉ ፡

" እቤት እቤት ደስ ማለቱ
የአናርኪስት ደም ሲፈስ ማየቱ!"

በሌላ ጊዜ ደግሞ መኢሶን ያሠለጠናቸው ወጣቶች ከትርዒቱ ቦታ እንዲመጡ ይደረግና ከላይ የተጠቀሰውን ወይም እሱን መሰል ዘፈን እንዲዘፍኑ ይደረጋል ::

ሬሳ ለትርዒት ይቀርብ የነበረበት ምክንያት ሕዝቡን ቀልብ ለመግፈፍ ÷ ውርደት ለማልበስና ምንም መፈናፈን የማይቻል ደካማ አድርጎ ራሱን እንዲመለከት ÷ የመንግሥትን ኃያልነት ደግሞ አግንኖ እንዲያይ ለማድረግ ነበር :: በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ከአውራ ጎዳና ላይ ወድቀው ተበጣጥሰውና ሙተው በማየት አእምሯቸውን ስተው እብዶች ሁነዋል ፡ ለሞቱት ሊያለቅሱም ሆነ ሬሳቸውን ሊቀብሩ ባለመቻላቸው ከባድ ኀዘን ውስጥ

ወድቀዋል ፡ ተገድለው መንገድ ላይ ተጥለው ይሆናል በሚል ወገኖቻቸውን ፍለጋ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ በመኳተን ወላጆች ከፉኛ ተሠቃይተዋል ::

ይበልጥ አስደንጋጭ እንዲሆን ሬሳዎች ሆን ተብሎም ይበጣጠሱ ነበር ፡ አንዳንዶቹ እንገታቸው÷ ሌሎች ደግሞ እጅ እግራቸው ይቁረጣል :: በአንዳንድ ሁኔታዎች ÷ የተቁረጡ እጆች ከግንባር ላይ በምሥማር ይቸነከራሉ :: በአብዛኛው ሁኔታ " አናርኪስት ነበርኩ " ወይም " ቀይ ሽብሩ ይፋፋም !" የሚል መልእክት ያለው ጽሑፍ ሬሳዎቹ ላይ ይቸነከራል :: ውሾችም ተገድለው " እኔም አናርኪስት ነበርኩ " የሚል መልእክት የያዘ ጽሑፍ ለማሾፊያ ተቸንክሮባቸው በሰው ሬሳ አጠገብ ይጣላሉ::

ማታ ማታ የማዘጋጃ ቤት መኪኖች ሬሳዎችን ሰብስበው በማይታወቅ የጅምላ መቃብር ውስጥ ይድፏቸዋል ::

የተበጣጠሰ ሬሳን ለትርዒት ማቅረብ ÷ የአረመኔያዊ ሽብር አንዱ አስፀያፊው ገጽታው ሲሆን ግልጽ በሆነ መንገድ የመንግሥቱ ኃያልነትን አምባገነናዊ መንግሥትና የመኢሶን ባልደረቦቹን ኢሰብአዊና አረመኔያዊ ባሕርይ አመልክቷል ::

የሬሳ ሽያጭ÷ ከመስከረም ፲፱፻፷፰ ጀምሮ ምኒልክ ሆስፒታል ውስጥ አዲስ አበባ ÷ በሽብሩ የወደቁ ሰዎች ሬሳ ላይ በላዩ ይቁለል ነበር :: የተጠነቁ ወላጆች ÷ የልጆቻቸውን ሬሳ ከቁልሉ ውስጥ ለመፈለግ ከውጭው በር ይሠለፋሉ ፡ ተለይቶ የታወቀውን ሰው ሬሳ ለማውጣት ቁልሉን ለሚያወርዱ አዲስ የሥራ መስክ ተከፍቶ ነበር ::

ማንም ሰው የሚፈልገውን ሬሳ በነጻ አይወስድምና ገዳዮቹ " መንግሥት ጥይቱን በነጻ ያገኘዋል ?" የሚል አባባል ነበራቸው :: የሚፈልገውን ሬሳ ከእጁ ለማስገባት የሚፈልግ ሰው " የጥይት ዋጋ " እየተባለ የታወቀውን መክፈል ይገደዳል :: የተቁረጠ ዋጋ አልነበረም :: ግን

ባጠቃላይ ክፍያው የሚያሰላው ራሳውን በበሳሳው የጥይት መጠን ነበር:: "ፅድለኛ"አባት ልጁ በእንዲት ጥይት የሞተበት/የሞተችበት ነበር:: በፀሐፊው በኩል የሚያስነውር ቀልድ ውስጥ ለመግባት ሳይሆን ፥ ወላጆች በልውጉ ይሰግቸው የነበረውን ለመግለጽ ነው :: ምንም እንኳ የራሳ ሽያጩን ሕግብ ያቀረበው ባይታወቅም እንኳ ፈጠን ያለ ገቢ ያመጣ የንግድ ሥራ ነበር :: ውሉ እድሮ ወላጆች መክፈል እምቢ ሲሉና (ብዙዎች "የገደሳችኋቸው እናንተ ናችሁ ፤ ብሏቸው " እሉ) ራሳ ለትርዒት ማቅረብ ሠፋ ያለ ትኩረት እየሰበ ሲመጣ ሽያጩ ቀነሰ ::

አጋልጥ ተጋለጥ ፥ የሶቪየት ሰበካ ሀገሮች የሽብር ጠበብት በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ የማጋለጡ ተግባር የቀይ ሽብሩ ዓይነተኛ ገጽታ መሆኑ አጋጣሚ አልነበረም ::

በ"ቀይ ሽብሩ" ወቅት የሚከተሉት መልኮች ነበሩት ፤

1.) ራስን ማጋለጥ ፤ ይህ በእሥር ቤት ውስጥ ግበረ ሰይል በሚፈጸምበት ወቅት ወይም ሕዝብ በተሰበሰበበት የሚደረግ ነበር::

የተያዙ ተጠርጣሪዎች በልዩ ልዩ ወንጀሎች ይከሰሱና የኢሕአፓ አባል ወይም መሪ መሆናቸውን እንዲያጋልጡ ይጠየቃሉ ::"ተጋልጠሃልና ራስህን አጋልጠህ ከሞት ብትተርፍ ይሻልሃል" የሚል ነበር የተለመደ ማግባቢያቸው:: ቀደም ሲል ያስለፈለፏቸውን የተረቱ እሥረኞች ፥ ወይም ከኢሕአፓ ተገንጥለው ወደ ደርግ የገቡ አንጃዎችን ያመጡና ያጋልጥ ዘንድ እንዲያግባቡት ያደርጋሉ :: የዚህ ሁሉ ምፅት ግን ከግብረ ሰይል የዳኑ መስሏቸው ራሳቸውን ያጋለጡ ፥ በኋላ በግብረ ሰይል መሠቃየታቸውና እንዲያውም መረሸናቸው ነበር::

በሕዝባዊ ስብሰባዎች የተሰበሰበ ሕዝብ በለደድና በመኢሶን በታጠቁ ቡድኖች ተከብቦ፥ የደርግ ወይም የመኢሶን ካድሬ እየተነሣ ሰው ራሱን እንዲያጋልጥ ለረጅም ጊዜ ይደነፋበታል

ከማጋለጥ የተቆጠቡ ሞት እንደሚጠብቃቸው እየተገለጸ ይዛትባቸዋል:: "ራስህን ካጋለጥክ ግን በኋላ ከተጋለጥክ ወይ ስምህ እሮ በያዝነው ዝርዝር ላይ ከተገኘ ነጻ እርምጅ ይወሰድብሃል?" ይባላል:: ካድሬዎቹ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ወይም ዲሞክራሲያን እንድ ጊዜም እንኳን ያነበቡትን ሰዎች ዝርዝር ያላቸው በማስመሰል ያሞኛሉ:: ሰውም ደንግጦና ግራ ተጋብቶ ራሱን ያጋልጣል:: "ዲሞክራሲያ እንድ ጊዜ እንብቤያለሁ!" ጀ የኢሕአፓ ደጋፊ ነው ብዬ ጠርጥሬያለሁ፣ ግን ምንም አላልኩም፣" "ከአናርኪስት ጋር ተንጋግሬያለሁ" ወዘተ....ወዘተ.... እንዚያ ራሳቸውን ያጋለጡ ተይዘው በፍጥነት ይወሰዳሉ:: በአንድ ቀን ብቻ (ግንቦት ፲፱፻፸ ዓ.ም.) ጉንደርና ጥቂት ሌሎች ከፍለ ሀገር ከተሞች ውስጥ ፮ ሺህ ሰዎች ራሳቸውን አጋልጠዋል!

2.) ሌሎችን ማጋለጥ፤ አንድ እሥረኛ የሚያውቃቸውን የሌሎች "አናርኪስት" ሰምች እስኪሰጥ ድረስ ግብረ ሰይል ይፈጸምበታል:: ብዙዎቹ እሠቃቂውን ግብረ ሰይል መቻል ያቃታቸው ሌሎችን ያጋልጣሉ፤ ከራሳቸው መከራ ለመላቀቅ ዝም ብለው ዕውቂያ ይሰጣሉ:: በሌሎች በመጋለጣቸው የተነሣ የተያዙ ሰዎች ግብረ ሰይል ይፈጽሙባቸዋል፤ ሌሎችን እንዲያጋልጡ ይገደዳሉ፤ እንዲያ እያለ ዙሪያ ጥምጥም ውስጥ ይሽከረከራል:: ሌሎች የማጋለጥ ተግባር በቀበሌዎች፥ በፋብሪካዎች ...ወዘተ. የሕዝብ "የማጋለጥ ስብሰባዎች" ም ይካሄዳል:: ሕዝቡ "አናርኪስቶችን" እንዲያጋለጥ ይታዘዛል!

ይገፋፋል። ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲወነጅሉ ተደርገዋል፤ እንዳንዶች የግል ጠላቶቻቸውን፥ በንግድ ወይም በፍቅር ጉዳይ ወደረኛ የሆኗቸውን ለማጋለጥ ሁኔታውን ተጠቅመውበታል። ከዚህም የተነሣ ቍጽጠር የሌላቸው፥ ከኢሕአፓ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲህ ዓይነቱ ወጥመድ እየተጠመደባቸው ተመትተዋል።

በሕዝብ ውስጥ የፍርሐትና የርስ በርስ መጠራጠር መንፈስ ረበበ። ማንም ማንንም ሊያመን አልቻለም። ዉሮቱ ልጅ እናቱን ሊያጋልጥ ይችላለ፥ ሠራተኛዋ ቀጣሪዎቿን ልተወነጅል ትችላለች፤ ምርጫው ከባድ መጨነቅ መጠበብ የነበረበት ነበር። ራስህን ካላጋለጠክ ሌላው ያጋልጠሃል፤ ሌሎችን ካላጋለጥክ ግብረ ሰይል ወይም ሞት ይጠብቀሃል። ተማሪው ችግር ደግሞ ሌሎችን ስታጋልጥ ራስህም የነሱ አባሪ ተደርገህ ስለምትወሰድ ከቅጣት እታመልጥም። የጀነኑቱ መላ በመምታት ለሚደረገው ማጭበርበር ራሳችንን እናዋርድም ብለው ሌላውን እያጋልጡም። እንዳንዲም -ሌሎችን ለማዳን በመሞከር በራሳቸው ላይ ይደፈድፋሉ። - በእንጻራዊ ደረጃ ደከም ያሉቱ (እዚህ ላይ ዳኝነት መስጠታችን አይደለም፤ "ማን ይናገር? የነበረ " ነውና እዚያው ነበልባል ውስጥ ከነበረው የበለጠ ማን ሊዳኝ ይችላል?) ሌሎችንም ራሳቸውንም ያጋልጣሉ፤ እንዲያም በማድረጋቸው የሌሎችንም የራሳቸውንም ግዳር ያስረዝማሉ። ሌሎችን አጋልጠው ርሸናቸው እንዲፋጠን ያስደረጉ ብዙ እሥረኞች እስከ ፲፱፻፹፱-፲፱፻፺፩ ዓ.ም. እንኳን ከእሥር ቤት የተወሰዱ በምስጢር ተገድለዋል። ለምሳሌ፦ በአዲስ አበባ፥ በጎንደር፥ በደሴ፥ በጅማ፥ በመቀሌና ሐረር።

"ቀይ ሽብሩ" መላ ሀገሪቱን ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ የማይችል ፍርሐትና በቀላሉ የማይሽር የአእምሮ ቍስል ቁራኛ አድርጓታል። "ሽብር" የሚለው ቃል አሁን ብዙ ሰው ላይ ፍርሐት ይለቃል፤ ሽብር ሲባል የሚታያቸው "ቀዩ ሽብር" ነውና። የደረሰው፥ ሞት ቢሉ ሞት አይደለም፤ ሕመም ወይም ውርደት ብቻም አይደለም፥ ከዚህ ሁሉ በላይ

ነበር። የሕዝብን መንፈስና ቅስሙና ሰብሮ ወኔውን ሰልቦ፥ አሜን ብሎ መታዘዝን ብቻ ከሚያውቅ ከግዑዝ ፍጥረት ደረጃ ለማውረድ ሆን ተብሎ የተደረገ ሙከራ ነበር። አንድ ሰው " ቀዩ ሽብር የተነጣጠረው፥ ሕይወት ባላቸው ላይ ነው፤" ብሎ የጻፈው እውነት ነበረው። ዓላማው ለተቃውሞ፥ አሻፈረኝ ለማለት የሚከፍሉትን ዋጋ ለማሳየት ሕይወት ያላቸውን መጸመጥ ነበር። ለብዙ ጊዜ ብዙ ዓመታን ላየች ኢትዮጵያ እንኳ "ቀይ ሽብር" ከልክ ያለፈ ነበር። የተካሄደበት መንገድ፥ መጠኑ፥ አረመኔያዊነቱ ሊታሰብ ከሚችለው ውጭ ነበር።

"ቀዩ ሽብር" ሲተረጎም፥ የግፍ የግድያ፥ አረመኔያዊ ግብረ-ሰይል የራሳ መበጣጠስ ጭፍጨፋ፥ ግብታዊ ርሸና፥ እስከነ ሕይወት መቅበር፥ አባትን በልጅ፥ ልጅን በአባት ማውገጀል፥ ጥርጣሬን ማሠራጨት ፍርሐትና ተሥፋ መቁረጥ ነበር። እነዚያ ይህን ሁሉ ፀዋትወ ሙከራ የተቀበሉት፥ በውስጡ ተቀቅለው ያለፉት ናቸው በአእምሮ ላይ የቀረፀውን፥ ሽብር ቢያንስ በይፋ አቁሟል ከተባለ ብዙ ዓመታት በኋላ እንኳ ሕዝቡ ጨምድዶ የያዘውን ትክክለኛ ስሜት ሊገመግሙ የሚችሉ። በሽብሩ ወቅት ሞት ድንገት ከመጣ ትልቅ ግልግል ነበር። የብዙ እሥረኞች ወላጆችና ቤተሰቦች ራሳቸውን ገለዋል። በርካታ የኢሕአፓ አባላት የመርዝ (ሳይኑድ) እንክብል በመዋጥ ራሳቸውን አጥፍተዋል፤ ሌሎቹም የተባይ መርዝ በመጠጣት ሙተዋል። ከመያዝና በርኃጥም ተከትሎ በሚመጣው በተጎተተና በተራዘመ ግዳር ከመሞት ፈጣን ሞት የተመረጠ ነበር። "ደጉ" ግብረ-ሰይል ፈጻሚ ደብድቦ አእምሮን የሚያስትና ፈጥኖ የሚገድል ነበር። ክፉው ደግኖም እንደ ሃምሳ አለቃ ተሾመ ዓይነቱ፥ ግደልን ብለው እንዲለምኑት የሚያደርግና ይበልጥ እንዲሰቃዩ በሕይወት ጠርዝ ላይ የሚያቆየው ነበር። ቋሚ ይበልጥ ሰለሚሠቃይ ሞት ግልግል ነበር። ባንድ ቀን ወይም በሳምንት ውስጥ ልጅ አልባ መሆናቸውን ያዩ ወላጆች፥ እንድጹ ልጂ ቁም ስቅሉን ሲቀበል የተመለከተች እናት፥ ወንድሟን በአሠቃቂ ሁኔታ ለገደለው መንግሥት የውሸሲ መዝሙር እንድትዘምር የተገደደች እንት፥ እጅ እግራቸውን

አጥተው ዱሻቸውን እያሳዩ እሥር ቤት ያሉት፥ ለፅውርነት የተዳረጉት፥ በግብረ-ሰይል አእምሮዋቸውን የሳቱትን ወጣቶች የሚንከባከቡ ወላጆች....ወዘተ ..ወዘተ የቁም ሥቃይ ለቋሚዎች "ቀዩ ሽብር" ከሞት የከፋ ትርጓሜ ነው የነበረው።

("ቀዩ ሽብር") ጨቋኙ ገዥዎች የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት እስከምን ያህል የዝቅጠት ደረጃ ሊወርዱ እንደሚችሉ አሳየ። የለእዉሱና ሌሎችን ጠቁመው ወደ እርግጠኛ ሞት የሰደዱ ብዙዎቹን ሐፍረት አለበሳቸው፤ ጥቂቶች ምሁራን በመንግሥት ከተቀጠሩት ማህይማን ገዳዮች ያልተሻሉ ..... ያውም ባይብሱ ..... ሁነው በመገኘታቸው ለምሁራን የነበረውን አክብሮት አጉደፈው። "ቀዩ ሽብር" በተግባር ሲውል ሀገሪቱ ልትወጣውና ልትፍቀው ብዙ ዓመታት የሚፈጅባትን ጉዳት አደረሰባት።

፪

ምን ያህል?

ምን ያህል ኢትዮጵያውያን/ ኢትዮጵያውያት ሞቱ በ"ቀይ ሽብሩ" ወቅት? ዕውነታው እንደሚያሰየው እንዲት ሀገርንና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦቿን በስንት የተለያዩ መንገዶች ጉዳት ላይ የጣለን ነገር በቁጥር አስልቶ ማቅረብ መቼም ተገቢ አይመስልም። ግን ኡታላይ ጭብጥ ጉዳዩንና የሚቹንም መጠን ሊያቃልሉ የሚሞክሩትን ሀይ! ለማለትም እንኳ እንድ መልስ ሰጠት አለበት።

ምን ያህል? ለሚለው ለዚሁ ጥያቄ ብዙ ኢትጵያውያን የየራሳቸው መልስ አላቸው። ምን ያህል ሞተ? ተብለው ሲጠየቁ፥ እንጸንጹች "ማን አልሞተም?" ብለው ይመልሳሉ፤ ሌሎች ደግሞ "እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው፤"ብለው ይመልሳሉ:: የሞተው ያን ያህል ነበር ::

ሽብሩ በብዙ ረገድ ሁሉን ያስተካከል ነበር:: ያልጉበኘው የሀገሪቱ ክፍል አልነበረም ማለት ይቻላል:: (ቢያንስ ከተሞችን እስከ ወረዳ ድረስ) በያታ፥ በሃይማኖት፥ ወይም በብሔር ላይ የተመሠረተ ልዩነት አላደረገም:: የደርግ ኑፍሰ በላ ወሮበሎች በተለይ ሴቶች ላይ የተለየ አውሬነት ያሳዩ ነበር:: አስፈሙም ጭፍጨፋ የተፈጸመው እግሮች በነበሩበት አካባቢ ነበር:: ደርግ ጸር እስከ ለነበረው ተቃውሞ መገለጫ ኢሕአፓን አድርጎ ስለወሰደ ሽብሩ በኢሕአፓና ከሱ ጋር ዝምድና ባላቸው ላይ አተኩረ (12) ነገር ግን ሽብሩ ከኢሕአፓ ጋር ትሥስር ከነበራቸው በላይ ነበር የፈጀው:: የግደያውን መጠን መገመት የሚቻለው ድምፁን ያሰማ ተቃውሞውን ሁሉ ጠርጎ ለማጠፋትና አክሎ አክሎም ለመግደል፥ ያለምንም ማማረጥ ሆን ብሎ ለመጨፍጨፍ፥ ሕዝብን ሽብር ውስጥ ለመክተትና ቀልቡን ለመግፈፍ መንግሥት ታጥቆ የተነሣበት ዕቅዱ እንደነበር ተገንዝቦ አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ብቻ ነው:: ጭብሩ

ደርግ መንግሥቱ ጽኑ እንዲሆንለት ማረጋገጫ ይሆንልኛል ብሎ የመጠው መንገድ ነበር። ይኸው ሥሌት የብዙ ሺህ ሰው መሞትን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብን መማረክን በሚዛን ያስቀመጠ ነበር።

የቁጥር ነገር ከተነሣ ሽብሩ ሥያሜውን እማኝቶ የጀመረበትን በትክክል ማስቀመጥ ይጠይቃል። "ቀዩ ሽብር" በወጣ ተሠይሞ የጀመረው የካቲት ፲፱፻፷፱ ሲሆን ከዚያ በፊትም በተለይም ከመስከረም ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. በኋላ ሽብርና ግፍ ይፈጸም ነበር። ነገር ግን ጭብሩ በይፋ እስከ የካቲት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ድረስ የቀይ ቀጸላ አልደረሰም ነበር። መኢሶን፥ የደርግ ሽብር በመሠረቱ የጀመረው ከነሐሴ ፲፱፻፷፱ በኋላ ነው ብሎ ይከራከራል። ይህ ግን ማሻሸን ከደርግ ጋር የተቈራረጠበትን እጉልቶ የሚያሳየው ነው። በግልጽ እንደታየው መኢሶን ከደርግ ጋር ለመቆራረጡ በፊት የነበረው አረመኔያዊ በሆነ መንገድ ሙሉ በሙሉ የተሳተፈበት ሽብር፥ አብዮታዊ ነበር፣ ስለሆነም መደገፍ ነበረበት ባይ ነው። በወንጀል ያደፈ ያለፈ ታሪኩን ነጭ ቀለም ለመቀባት የሚደረገውን እንደዚያ ዓይነት ሙከራ ወደጉን ትተን፥ ስል "ቀይ ሽብሩ" ስናነሣ ይህን ሥያሜ ይዞ በተፈጸመው ግፍና ከየካቲት ፲፱፻፷፱ እስከ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. ድረስ በቀጠለው ላይ ራሳችንን እንወስናለን ማለቱ በቂ ይሆናል።

በግፍ ስለ ወደቁት ሁሉ የተመጣጠነ ግምት ላይ መድረስ እንዲት ይቻላል? ግደያው በጣም በተጧጧፈበት ጊዜ የነበረውን የግምት መጠን፥ ደርግ ያወጣውን ዝርዝር በመደመር፥ አንዳንድ ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ ከሞት የተረፉ ሰዎችን በመጠየቅ፥ የቀኑንና የግድያውን የሞት መጠን [(ኢይወርድ/ኢይዐርግ) /minimum/maximum)] ከግምት በማስገባት፥ አዲስ አበባ የሆነው በሌሎችም በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ትላልቅም ትናንሽም ከተሞች እንደሚደገምና እንደሚባዛ ባለርሳት ለመገመት መሞከር ይቻላል ብለን እናምናለን። መነሻ ምክንያታቸው ጥያቄ ላይ ሊወድቅ የሚችል አንዳንድ ወገኖች "በቀይ ሽብሩ" ለደረሰው ኡቃላይ የሰው ሞት ፰ ሺ የሚለውን አኀዝ ለማቅረብ ሞክረዋል። (ሰምሳሌ በረከት

ሀብቴ ሥላሴ እንደ. ጽሑፍ ላይ ይህንን አኀዝ ጽፍ፥ በአሜሪካ ባለሥልጣኖች፥ በተባበሩት መንግሥታት የቀድሞ የአሜሪካ አምባሰደር በተባበሩት መንግሥታት ጂን ከረክ ፓትሪክ ጭምር ተወስዶ ተስተጋበቷል።(13)

የሆነ ሁኖ ይህ አኀዝ ከሚያዚያ ፲፱፻፷፱ እስከ ግንቦት ፲፱፻፷፱ የተፈፀመውን ግዶያ እንኳን ግምት ውስጥ ለማስገባት እንዳልቻለ ማየት ይቻላል። በእንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከ ፰ ሺህ ያላነሱ ሰዎች ተገድለዋል። ፩ ሺህ ፰ መቶ አዲስ አበባ ውስጥ በሜይ ዲይ ዋዜማ ሰላማዊ ሰልፍ ተገድለዋል፤ ደርግ ራሱ በስድስት ክፍለ ሀገሮች ወስጥ በገጠር አካባቢ ከግንቦት ፮ እስከ ፯ ፩ ሺህ ፯፻፲፫ መግደሉን ገለጿል፣ አንዲሁም የስዊድሽ ሴቭ ዘ ቺልድረን ፈንድ ዋና ፀሐፊ በቀን በቀንብቀን በትክክል ለማስቀመጥ በየሌሊቱ) ከ ፻ እስከ ፻፶ ሰዎች አዲስ አበባ ብቻ ይገደሉ ነበር ብሎ ዘግቧል። ኢሠርዱን ፻ አድርገን እንሠኳን ብንነግ የተፋፋመ ግድያ ከተካሄደባቸው ወራት እንዱ በሆነው በግንቦት ፲፱፻፷፱ ውስጥ ፫ ሺህ ያህል ሰዎች ተገድለው ነበር ማለት ነው። በግልጽ እንደሚታየው ፰ ሺህ የሚለው አኀዝ አንድም መረጃ አለማግኘትን ያሳያል፣ አንድም ደግሞ ከፍ ያለ ቁጥር መጥቀሱ ጠንከረፍ ያለ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ትግል መካሄዱን በማመልከት ለኢሕአፓ ሰ.መ. ያተርፍለታል በሚል የተሳሳተ እምነት፥ ሆን ተብሎ እልቂቱን እቃልሉ ለማቅረብ የተደረገ ሙከራ መሆኑን ያመለክታል። (14)

እስቲ አንዳንድ ግምቶችን እንመልከት፤

አምንሊቲ ኢንተርናሽናል ቢያንስ ፲ ሺህ ሰዎች በየካቲትና በታህሣስ ፲፱፻፷፱ መካከል ተገድለዋል ማለት ይቻላል።

በኛ በኩል በግንቦት ወር ብቻ እንኳ ከ፰ ሺህ ሰዎች በላይ መገደላቸውን አላይተናል። የተፋፋመ ግድያ የተካሄደባቸውን ብንወስድ፥ ከየካቲት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. እስከ ሰኔ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ቀዩ ሽብር በጣም ግሞ ነበር። ደግሞ "ትንሽ ቀዝቀዝ" አለና እንደገና ከጥቅምት ፲፱፻፷ እስከ ታህሣሥ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ድረስ

ተጋጋመ። ሬውተር የካቲት ፳፰ ዓ.ም. በዘገበው ላይ በጥርና በየካቲት መክክል ፪ ሺህ ሰዎች እንደሞቱ መገመቱን ይገልጻል።

የሚች ብዙት በጣም ከፍ ያለ እንደነበር ጥርጥር የለውም። "የተለዩ ግንፌላዎችን" (በሚይ ዴይ ዋዜማ፥ በታሕሳስ ውስጥ አዲስ አበባ፥ በሌሎች ወራት በናዝሬት፥ በጎንደር በደሴና በሌሎች ከተሞች) ነጠላ ምሳሌዎች ብንወስድ ከላይ ከጠቀስነው ልቆ የሚሄድ አኀዝ ላይ እንደርሳለን።

በአዲስ አበባ በራፂ ሽብሩ በተፋፋመባቸው ወራት ውስጥ በየሌሊቱ ከደያ ያላነሱ ሰዎች መሞታቸውን እናረጋግጣለን። ለምሳሌ እነደ ታህሣስ ..... ባሉት የተለዩ ጊዜያት ደግሞ አኀዙ ከፍ ይላል። ከዚያ በላይ ደግሞ ግድያው በየቀኑና በየሌሊቱ በልዩ ልዩ የህገሪቷ ክፍሎች ውስጥ ይፈጸም ነበር። በተለይም በሸዋ፥ በጎንደር፥ በሐረርጌ፥ በሳሸምና በወሎ) ይህን ሁሉ በግምት ማስገባትና የቀን የሌሊቱን ግድያና ከፃ እስከ ፪፫ አካባቢ የሚደርስ ብዛት ያላቸውን፥ በቋርጥ በቋርጥ እየተከፈሉ የሚረሽኑትን እሥረኞች ከሥሌታችን ውስጥ ማከል ያስፈልጋል።

ፕርፌሰር ሪቻርድ ግሪን ፈልድ፥ ሁለት ሚሊዮን ያህል ወንዶችና ሌቶች የሽብሩ ዘመቻ በተፋፋመበት ወቅት እሥር ቤት ውስጥ እንደነበሩ የሚገልጽ ዘገባ አቅርበዋል (15) ነገር ግን ጀይ ሲ ጊልቦድ ከቪ ሺህ እስከ ፪ ሺህ እሥረኞች "ከትክክለኛው ቁጥር ዝቅ ያለ ይሆናል" ብሎ ከዘገበው ጋራ እንስማማለን። (16) የሽብሩ ዘመቻ በመላ አገሪቱ በተለያዩ እሥር ቤቶችና ማቆያ ማዕከሎች በተፋፋመበት ወቅት ከ ፪ሺ፬ ሺህ ያላነሱ እሥረኞች ነበሩ ብለን እንገምታለን። ከነዚህም ጥቂት ተቆንጥሮ ተፈትቶላቸዋል፤ ታዲያ ባሁኑ ጊዜ ከ ፴ ሺህ የማይበልጡ የፖለቲካ እሥረኞች ናቸው እሉ ተብሎ የሚገመተው፤ ሌሎች የት ደረሱ?

በኛ ሥሌት መሠረት "ወደ ፪፬ ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያዊያን በ"ቀዩ ሽብር" ተገድለዋል እንላለን።

ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ "ቀይ ሽብሩን" እስካጠፉበት እስከ ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ድረስ በአጠቃላይ የተገደለው ሰው መጠን ከ ፪፫፬ ሺህ አያንስም።

ይህ አኀዝ በመሠረቱ ሪፕተ አድርጎ የያዘ ግምት ሲሆን አጠቃላይ ቁጥሩ ላይ ለመድረስ የሚቻልበት ሁኔታዕውን ሲሆን ከትክክለኛው ቁጥር እጅግ ዝቅ ያለ ሁኖ እንደሚገኝ እርግጠኞች ነን። ደራሲውያንጋገራቸው የተወሰኑ ኢትዮጵያዊያን ፪፫፬ ሺህ የሚለው አኀዝ ከ"ቀይ ሽብር" በፊት የነበረውን ግፍና ግድያ ሳይጨምር "ለቀይ ሽብሩ" ወቅት ብቻ የሚስማማ ነው ይላሉ። የኛ ግምት ከሽምቅ ውጊያው ጦርነቶች ጋራ የተያያዘውን በገጠሩ ውስጥ የደረሰውን የሕይወት መጥፋት አይጨምርም።

ያቀረብነው አኀዝ መንግሥቱ ኢሕአፓንና በከተሞች አካባቢና በከተሞች ውስጥ በዋናነት ተከማችቶ የነበረውን ወታደራዊ አገዛዝ ላይ የተነሳ ተቃውሞ ለማጥፋት እርምጃ ሲወስድ የሞቱትን የሚመለከት ነው። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ውስጥ በሽብሩ ያልተጻበሰ ቤተሰብ የለም ለማለት ያስደፍራል። በርግጥም ከላይ ከተጠቀሱት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት "የጠፉ" በሚል ፈርጅ ውስጥ ይቀመጡ ይሆናል፤ ግን ሁሉም እንደሞቱ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ ሊኖር አይችልም። እንዲህ ዓይነቱ ግፍ በሌሎች አገሮችም ተፈጽሟል፤ (አርጀንቲና፥ ኡራጋይ....ወዘተ) ግን ከደርግ ሽብር ጋር ሲመዛዘን ደብዛዛ ይሆናሉ። ደርግ የቺሊውን ፒኖሼ ፋሺስት እምለ ይወርድበታል፤ ግን ሲወጻደሩ የሳንቲያጎዎቹ ነፍስ ገጸዮች "ለዘብተኞች" ሁነው ይታያሉ።

ዙሮ ዙሮ፥ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ምን ያህል ሞቱ የሚለው ጥያቄ ይህን ያህል ክብደት ያለው ሁኖ አይታይም። በዚህም ሆነ በዚያ የህገሪቷ አንድ ወጣት ትውልድ እንዳልነበር ሆነ። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በፍርሐትና በሽብር እእምሯቸው ተነካ፤ ባጠቃላይ ህገሪቱ ደማች፤ በታሪካዊው የየካቲት አብዮት የተወሰደው አመርታዊው እርምጃ መቆም አይደለም፥ እንዳለ ታጠፈ። የደርግ ሽብር ኢትዮጵያዊያን

የንጉሰትን አብዮት ደመሰሰው። አሁን በቦታው ላይ የሚወላወሰው ይበልጥ ያለፉትን መንግሥታት የሚመስል፥ እንደውም ከነሱ የከፋ ሐሣዊ መሲሐዊ ምሥል ነው። ሽብሩ ደርግን እዚያው ከቀማው ሥልጣን ላይ ተንጠልጥሎ እንዲቀርና በሂደት ውስጥ ግን ከሥሩ የረገጠውን መሬት ከመሸርሸሩ የተነሳ መቼም ሰላም እንዳያገኝ፥ መቼም ሕዝባዊ ሕዝባዊ ድጋፍ እንዳያገኝ በጠመንጃ አፈ ሙዝ ሲያመጣ የፈለገውን ምንም ዓይነት መረጋጋት እንዳይገኝ አድርጎታል። የዐመጹ ዑደት እየቀጠለ ነው፤ ምናልባትም ምን ያህል? ብለን ብንጠይቅ በመሠረቱ ሽብሩ በይፋ አበቃ ከተባለ በኋላ እንኳ አሁንም በመሞት ላይ ያሉትን ሊጨምር ይገባዋል።

፫

የተፈጸሙቱ ይናገሩ

"ማን ይናገር?- የነበረ፤ ማን ያርዳ? የቀበረ፤"

ከሁኔታው ገንጠል ካለና ደረቅ ከሆነ የትኞት ዓውድ ወጣ ብለን ከነገሩ ልብ ውስጥ ካልገባን አስደንጋጭ የሆኑትን የ"ቀይ ሽብር" ዝርዝር ሁኔታዎች ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። በዓይናቸው ካዩት፥ የቁም ስቅላቸውን ከተቀበሉት፥ አሁንም የአስፈሪ ቅዠት ትውስታ ከሆነባቸው የበለጠ ማን ሊያቀርበው ይችላል።

ለዚህ መጽሐፍ ካደረግነው አጠቃላይ ጥናት እንደ አንድ ክፍል አድርገን ልንሰበስብ ከቻልነው የምስክርነት ቃልና ዘገባ ጥቂቱን ከዚህ በታች እናቀርባለን። እንዳንድ የምስክርነት ቃል አሳጥረን ነው ያወጣነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ግልጽ በሆነ ምክንያት ስሞች፥ ወይም ተገድፈዋል፤ ወይም ደግሞ በምሕፃር ብቻ ሠፍረዋል። እዚህ የምናቀርባቸው ታሪኮች እጅግ አስደንጋጭ የሆኑትን ነው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሽብሩን ብሩህ አድርገው ሊያሳዩ የሚችሉ ከመሆናቸውም ጋር አንባቢው፥ የኢትዮዕያ መንግሥት " አብዮት ለማካሄድ መግደል አለብን፤" ሲል ምን ማለትቱ እንደነበር በውል እንዲጨብጠው ይረዱታል የምንላቸው ናቸው።

ደብረ ማርቆስ

"መስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ተያዝሁ፥ የመኢሶን አባል የነበረ ነገር አቀባይ ሹክ ባላቸው ተነሥተው ፖሊስና የቀበሌ ዘበኞች ሊይዙኝ መጡ። ወደ ደብረ ማርቆስ ማዕከላዊ እሥር ቤት ወሰዱኝ፥ ከተወረወርኩበት ክፍል ውስጥ 41 እሥረኞች ነበሩ፤ በሌብነት ከተከሰሱት ሁለት እሥረኞች በስተቀር የሁሉም ክስ የኢሕአፓ አባላት ናቸሁ የሚል ነበር። ከፍሉ

ጠባብና የተጨናነቀ ሲሆን ከሁሉም የከፋው ግን ሽታው ነበር። የሽንት ሽታ፥ ያደፈ ገላ ሽታ፥ እንዲሁም በጣም የሚያምስ ከርፋት ነበር። በኋላ ልደርስበት እንደቻልኩት ለካስ ያ ጥንባት በግብረ ሰይል ከተፈጸፀሙት እሥረኞች ቁስል የሚተነፍግ ኑሯል። ከእሥረኞቹ ስድስቱ(ሽታውን፥ መልእክ፥ እስጢፋኖስ፥ ገብረ መስቀል፥ ታደሰ፥ አያሌውና ሰርጎ ሙሄ) ከወገባቸው በታች ሽባ ሆነው ስለነበር ለሽንት መውጣት ሲፈልጉ በእንፉቅቅ ወይ ደግሞ በሰው ሽክም ነበር። ደግሞም ጡሽቱን የሚለቅ፥ ወይም በድንገት ዘለግ እድርጎ የሚሰቅ፥ እጆቹም ላይ ሽንቱን የሚሸና ያበደ እሥረኛም ነበር።

ግታ ጠሩኝና ወደ አንድ አጻራሽ ወሰዱኝ፣ የግብረ ሰይል መፈጸሚያው አጻራሽ መሆኑ ግልጽ ነበር። መርማሪዎቹ ግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ እምስት ነበሩ። አንዲትም ጥያቄ ሳይጠይቁ፥ እንደኛው ዝም ብሎ በርግጫና በጡጫ መታኝ፣ ከዚያም እጆቼን ወደ ኋላ አሥረው፥ ከርኖቼን አንድ ላይ ግጥም አድርገው፥ እግሮቼ ከወለሉ በላይ በሚወዛወዝበት ሁኔታ ከጣራው ላይ አንጠለጠሉኝ። አንደኛው እንደ ኤሌትሪክ ማራገቢያ ወይም እንደ አውሮፕላን ቢልቢላ ያሽከረክረኝ ገባ።

"አናርኪስት ነህ ተብለህ ተጋልጠሀል" አለ አንደኛው፣ "ግበረ አበሮችህን ልታጋልጥ ዝግጁ ነህን?" ብሎ ቀጠለ። ፈጽሞ የኢሕአፓ አባልም ደጋፊም እንዳልነበርሁ ካድሁ። ይህንኑ መልስ ይጠብቁ ወይም ለዚሁ መልስ የጓጉ ይመስልበጥድፊያ ሱሪዬንና ሙታንታዬን አወለቁ። ሁለቱም የተራቆተ ቂጤን ገረፉኝ። አንደኛው በእሾካም ለበት ሌላው በእጭር ወፍራም አለንጋ ተያያዙኝ። ሲበቃቸው ገመዱን ቁልቁል ቢጎትቱት ወርጄ ወለሉ ላይ ተዘረርሁና እሪ አልኩ። ከዚያም እጆቼን ፈትተው ሸሚዜን አወለቁና እጆቼን እንደገና አሠሩ። በሆዴ እንድተኛ አስገደዱኝና የተራቆተው ጀርባዬንና ቂጤን ይደበድቡ ገቡ። አእምሮዬን ብስት ወይም ብሞት ምኞቴ ነበር፣ ግን አልሆነም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወረቀት ብጥስጣሽ በክብሪት ለኩሱና ደም በሚያዘንበው ጀርባዬ ላይ ጣሉት። በእጃቸውና በሚማቸው ከመሬት ጋር ሠፍተው ስለያዙኝ ልንቀሳቀስ አልቻልኩም። እሪታዬ በጣም ሲጎላ ግዜ ቆሻሻ ጨርቅ እፈ ውስጥ ወተፉበት በመጨረሻም

ራሴን ሳትሁ። ከክፍሌ ውስጥ ሆኜ ስንቃም፣ በደምና በትውከት ጻክራ ነበር።

በሁለት ሳምንታት ውስጥ ሁለት ጊዜ ግብረ ሰይል ደረሰብኝ። እያንጻንጹ የግብረ ሰይል ዙር ወደ ሁለት ሰዓት ያህል የፈጀ ይመስለኛል። ከፖሊስ እሥር ቤት በነበርኩበት ወቅት በርካታ እሥረኞች ሌሊት ሌሊት ተጠርተው እየተወሰዱ እንጻቸውም ጨርሰው ሳይመለሱ መቅረታቸውን አይቻለሁ። በእንደዚያ ዓይነቱ ሌሊት ነበር እነዚያ የጠቀስኳቸው ሽባ ሁኑው የነበሩቱ የተገደሉት ውሎው እድሮ በዚያን ጊዜ እንድ ሺህ አራት መቶ እሥረኞች ወደነበሩበት ማዕከላዊ እሥር ቤት ተወሰዱ። በጥቅምት ፲፱፻፷፱ በታኅሣስ ፲፱፻፷፱ እንዲሁም በሠኔና በነሐሴ ፲፱፻፷፱ (August 1978) ቁጥራቸው በርከት ያለ እሥረኞች በማንኛውም ጊዜ በየቋርጡ ከሃያ እምሥት ያላነሱ እየተወሰዱ ይረሸኑ ነበር። እንድ ጊዜ በታኅሣስ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ሌሊት ስሙ ሲጠራ ከክፍሌ አልወጣም ብሎ እሻፈረኝ ያለ እንድ እሥረኛ እዚያው ክፍሉ ውስጥ በዘበኞቹ ታንቆ ተገደለና ሬሳውን ይዘው ውልቅ አሉ። የዚያ ሰውዬ ስም አሁን ጠፍቶኛል፥ ነገር ግን በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. (Early 1977) መጀመሪያ አካባቢ የተያዘ ወጣት ተማሪ ነበር።

እኔ ላይ ከስ አልተመሠረተብኝም ወይንም ለፍርድ አልቀረብሁም፣ እንድ ሌሊት ለመጠራትና ለመሞት እጠበበቅ ነበር፣ ግን ተረፍኩሁ፣ ከአራት ዓመታት በኋላ መስከረም ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ተሰቀቅሁ"።

ጎንደር፣

"ጎንደር ከተማ ውስጥ በታኅሣስ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ነበር በልዩ የኮማንዶ ወታደሮች የተያዝኩት። ነገር አቀባዩ ሰደድ የገባ "ባንዳ" ነበር። በቀጥታ ወደ ጎንደር ቤተ መንግሥት ወሰደው፣ በሁለት ቀናት ውስጥ ለሁለት ጊዜ ግብረ ሰይል ተፈፀመብኝ። ግብረ ሰይሉን የውስጥ እግርን በደንጻና አለንጋ መገረፍን፥ ከጣራ ላይ ጭንቅላት ወደ ቁልቁል ተዘቅዝቆ መሰቀልንና እንደ ኤሌትሪክ ማራገቢያ መሽከርከርን የአጥንት መጋጠሚያዎችን በውፍራም ቆመጥ መደብደብን

ወሌ

" ኮረም፡ ደሴ፡ ኮምቦልቻ፡...ወ.ዘ.ተ ውስጥ ብዙዎች መከራ ተቀበሉ፣ ብዙዎች ሞቱ። እንደኛ ደረጃ ትቢት ውስጥ መምህር ስለነበረው አስማድ እሻግሬ ልንግራችሁ እችላለሁ የካቲት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ውስጥ ከሞገሥ በላይ፡ ጋሻው በዛ፡ መኩሪያና ከሌሎችም በርከት ያሉ መምህራንና ተማሪዎች ጋር ተያዘ። ሁሉም በኢሕአፓ አባልነት ተወንጅለው ሞካኔ በተመሳበት ሁኔታ ግበረ ሰይል ተካሄደባቸው፣ ነገር ግን ማንኛቸውም ያመኑት ነገር አልነበረም፡ ሞገሥ፡ ወንዳይ፡ ተካ፡ ጋሻውና በርከት ያሉ ሌሎች ወደ ሸዋ ሮቢት በርሐ ተወስደው ተገደሉና የጅምላ መቃብር ውስጥ ተቀበሩ። ይህ የሆነው የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ነበር።

አሠግድ ለስድስት ወራት ከታሠረ በኋላ ተለቀቀ። ግንቦት ፲፱፻፷ ዓ.ም.ያሸብር ስኳዶች እንደገና ሊይዙት ሲመጡ፡ ቀደም ሲል ራሱን ለመግደል ማላታይን (የተባይ ማጥፊያ መርዝ) ጠጣ፣ ነገር ግን ወታደሮች እርጎ እንዲጠጣ አስገድደው፡ የጠጣውን እንዲያስታውክ አደረጉትና ወደ ደሴ ሆስፒታል ወሰዱት። ኑፍሱን ሲያውቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። በመካከሉ እረፍት ሳይሰጠው በተደጋጋሚ ጊዜ ለበርካታ ቀናት ግብረ ሰይል ተፈጸመበት። ከዚያም ተረሽነና ሬሳው ከደሴ አውራ ጎዳናዎች በአንዱ ላይ ግንቦት ፲፱፻፷ ዓ.ም. ተጣለ።

ከአሠግድ አሻግሬ ሬሳ ጋር አብሮ የተጣለው የጎይሉ ገብሩ ሬሳ ነበር። ይህ ተማሪ፡ እነዚያ የፍዳ እቢጋዞች ያለ የሌላቸውን የግብረ ሰይል ዘዴ ሁሉ ተቀብሏል። ጎይሉ በዕውነቱ የሞተው ከሱው ጋራ እዚያው ክፍል ውስጥ የነበሩትን አሥራ ሁለት ሌሎች ወጣቶች ለማዳን ነበር። ልጆቹ፡ እንዳቸውም ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ ያለነበሩ ሲሆኑ በእሥር ቤቱ ሁኔታና በግብረ ሰይሉ እጅግ ተሸብረው ነበር። ታዲያ ጎይሉ፡ ልጆቹን የመለመለን እሱ ነው ብለው እንዲያጋልጡት ነገራቸውና፡ እሱም ለግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ፣ ልጆቹን "ሊጠቀምባቸው" ሞክሮ እንደነበርና "በመሠረቱ ምንም እንደማያውቁ፡ ምንም እንዳላደረጉ" ገለጹላቸው። ልጆቹን ትተው ጎይሉን ለአሥራ አምስት ቀናት በግብረ ሰይል አፈጻጸት፡ ከዚያም የሕይወት ምልክት ምንም ያህል የማይታይበትን ሥጋውን በጥይት ደብድበው

አውራ ጎዳና ላይ ጣሉት። እንደሚጠበቀው በኋላ ከልጆቹ አራቱ ተገደሉ። የቀሩት ሰምንቱ ከሞት ተርፈው እሥር ቤት ውስጥ ነበሩ፡ እስከማውቀው ድረስ።

ጎዳር ፲፱፻፸ ዓ.ም. ከኔዱቱ ____ጋር ወልድያ ውስጥ የተያዘች አልማዝ ታደሰን አውቃለሁ። አልማዝ እሥር ቤቱ ውስጥ አረመኔያዊ ግብረ ሰይል ተፈጽሞባታል። ሐፍረተ ሥጋዋን በካራና በጠርሙስ እንዳልሆነ አድርገውታል፡ ጡቶቿን ቆርጠዋል። በቁስሉ ጠንቅ ብቻ በሞተች ነበር፣ ነገር ግን ከካሣች በርሄ (መምህርት) ከተሻገር አያሌው፡ ከይመር ከበደና ከሌሎች እሥር እሥረኞች ጋር ከእሥር ቤት አውጥተው ረሽኗት። እንደተለመደው፡ ሬሳቸው ለትርጒት አውራ ጎዳና ላይ ተጣለ። ወልድያ ከተማ ውስጥ በ፲፱፻፸ ዓ.ም.(ጎዳር ፲፫ ቀን፡ መጋቢት ፭ ና፡ ታኅሣሰ ፲፭ ቀን) እኔ ራሴ " የቀይ ሽብሩ" የዐይን ምስክር ሁኛለሁ። አርባ ዘጠኝ የተበጣጠሱ ሬሳዎች አውራ ጎዳና ላይ ተጥለው ቆጥሪያለሁ።

አወቀ አስማማው፡ (የግል ድርጅት ውስጥ ይሠራ የነበረ) ደስታ ሚሳይ (ተማሪ) ከበደ (መምህር) ና አሥራ አራት ሌሎች ተማሪዎች ነሐሴ ፲፱፻፸ ዓ.ም. ከአላማጣ እሥር ቤት ጫካማ ወደሆነ አካባቢ ተወስደው የራሳቸውን መቃብር እንዲቆፍሩ ከተደረጉ በኋላ ተገድለው ተቀብረዋል። ከወሎ እሥር ቤቶች ውስጥ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የጠፉ ሰዎች ቁጥር በእርግጥ በጣም ብዙ ነው።"

አዲስ አበባ፡

"ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም. ተያዝኩ። ስያዝ ሁለተኛ ጊዜዬ ነበር። በመጀመሪያው ጊዜ ጎዳር ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ባፈሳ ተይዤ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ተለቀቅኩ። በሁለተኛው ዙር ከጠቋሚ ባገኙት ፍንጭ ተነሥተው የቀበሌ ዘበኞችና ካድሬዎች ከቤቴ ያዙኝ። ከመጀመሪያው የጥቂት ጊዜ እሥራቴ በኋላ ወደ ሲኒማ ቤት ጨርሶ አልሄድም ነበር፣ ምክንያቱም ከሲኒማ ቤት በሚወጣበት ጊዜ የታጠቁ ዘበኞችና ፊታቸውን የሸፍፈኑ ጠቋሚዎች ይጠብቁና ሰውን እየጠቁሙ ያስይዛሉና ነበር።

ቀበሌ ፵፫ እሥር ቤት ውስጥ እንድቆይ ተደረገ። ከዚያም ከፍ ወዳለው ወደ ከፍተኛ ፪ እሥር ቤት ተዛወርኩ። ቀበሌ እሥር ቤት ውስጥ ወደ ፭፻፵፭ ግድም ነበርን፣ ከፍተኛው ውስጥ ግን ከሯ መቶ የምናንስ አልነበርንም። ሁሉም የተወነጀለው በኢሕአፓ አባልነት ነበር ብሉ ለመናገር የሚያስደፍር ሲሆን፥ ጥቂቶች ከትጥቃቂ እርምጃ ጋራ በተያያዘ የተያዙ ነበሩ። ከነዚህኞቹ የተረፈ አልነበረም። ምርመራው ትጥ ያልያዘ ሲሆን ግበረ ሰይሉ ግን ዝንፍ የማይል ነበር። ግበረ ሰይል ከፈጸሙብኝ በኋላ፥ የኢሕአፓ የከተማ ትጥቅ ስኳድ፥ አባል መሆኔን እንዳምን ጠየቁኝ፣ ግን የራሴን የሞት ብያኔ መፈረም ስለሆነ እሻፈረኝ አልኩ። በቀበሌም በከፍተኛም እሥር ቤቶች ግበረ ሰይል ተቀብያለሁ።

የሚከተሉት የግብረ ሰይል ዓይነቶች በቀጥታ በኔ ላይ ወይም በእሥር ቤቱ የከፍል ባልደረቦቼ ላይ የዋሉ ነበሩ፣

- ወፌ ኢላላ(ፈላጋ)፥
- የኤላክትሪክ ንዝረት በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች መልቀቅ፥
- ጣቶች ላይ ምሥማር መምታት፥
- የተራቁተ ጀርባን መግረፍና ሽንት በላዩ ላይ ማፍሰስ
- ወይም በቁስሉ ላይ መሽናት፥
- በካራ/ሳንጃ የሰውነት ክፍልን መቁረጥ፥
- በቢንዚን የተራሰ ጨርቅና የተቀደዱ ወረቀቶች አድርጎ ማቃጠል።

በልብስ ካውያ ጀርባን የመተኩስ የግብረ ሰይል ዘዴም እንደነበረ ሰምቻለሁ፥ እኔ ላይ አልደረሰብኝም። ብልቶቻቸው የተበላሹ፥ እጅ እግሮቻቸው የተቆራረጡ፥ .....እሥረኞች ነበሩ። እዚህ በነበርኩበት ጊዜ ሌሊት ሌሊት ሰም ይጠራና እሥረኞች ተወስደው ይገደላሉ፣ .... ከፍተኛ እሥር ቤቶች ውስጥ የሚካሄደውን አጠቃላይ የማፍ እድራጎት የሚቆጣጠሩት እነዚያው ባለ ሥልጣኖችና ካድሬዎች ያሉባቸው " የቀይ ሽብር ኮሚቴዎች " የሚሏቸው ነበሩ።

ኮሚቴዎቹ በተወሰነ ጊዜ፥ የተወሰኑ እሥረኞችን _ ምንም እንኳ ጥቂቶቹ አስቀድሞ የተረሸኑ ቢሆንም _____የሞት ፍርድ በፊርማቸው ያፀድቃሉ። ለአዲስ መጦች፥ በግብረ ሰይል የተፈጸዩት እሥረኞች ሁኔታ ብቻ እንኳ ራሱን የቻለ ሰይል ነበር :: የማታ ማታው ጭንቀትም ሁለንተናን እንኩትኩት የሚያደርግ ነበር :: ሚስቱም ጭምር የታሠረች እሥረኛ ትዝ ይለኛል፣ በየጊዜው ዘበኞቹ በኛ ፊት "ሚስትህ እንጂ መልካም.....አላት፥ እንተ ብቻ ልትደሰትበት መፈለግህ የሚያሳፍር ነው " እያሉ ያፈዙበታል :: ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ አሉት ፥ "እትሥጋ፥ ስንገድልህ (ሚስትህን) ልክ ከሳንህ ሁና እንድታቅፍህ እናደርግልሃለን ::" በኋላም ሁለቱም ባልና ሚስቱ ተገደሉ ::

ፍጻሜው ሞት ባይሆንም ፥ ሌላም ተመሳሳይ ታሪክ አውቃለሁ። ሰውዬው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ማኅበር ውስጥ ይሠራ ነበር። ከያዙት በኋላ ሚስቱንና የስድስት ዓመት ልጁንም ወደ እሥር ቤቱ አመጧቸው ::መቶ አለቃው ሴትዮዋን ደፈራትና አረገዘች ::ልጁን ወታደሮቹ ኢሕአፓን የሚቃወም መፈክር እንዲሥህ አስተማሩትና አባቱ ፊት እነዚያን መፈክሮች እንዲያነበንብ ይደረጋል። ከሦስት ወራት በኋላ ያ ያልታደለ ሰውዬ ካረገዘች ሚስቱ ጋር ዓይን ለዓይን እንዲገጣጠሙ ሊደረግ፥ መቶ አለቃው ደግሞ እዚያው እያንጓበበ በሰውዬው ውርደት ይፍነከነክ ገባ። ሰውዬው ለረጅም ጊዜ ከተቀበለው ግበረ ሰይል ይልቅ ይህን ማየቱ እጹቀው። በኋላ እንደተፈታ ሰማሁ። ከዚያ በኋላ በሚስቱና በሱ መካከል የሆነውን ግን አላወቅኩም።

እፀደ ወይን ስለምትባል የእቴጌ መነን ትቤት ወጣት ተማሪም አውቃለሁ። ከደረሰባት እሥቃቂ ግበረ ሰይል የተነሣ ያልሟሟ ነገር መቅመስ አትችልም ነበር። ለቁስሏ ሕክምና ካለማግኘትና ከረሐብ የተነሳ ሞተች። ነገር ግን ራሳዋን በጥይት ደብድበው ጥቅምት ፲፱፻፷፱ ዓ.ም እሠፈሯ ወስደው ጣሏት። በትግራይ እረኛ ልማት ዩኒቲ (TADU) ይሠራ የነበረው ገብረ ጻድቃን ጎይሌ መቀሌ ተያዘና ግበረ ሰይል ተፈጸመበት። እንዲያወጣ ሊያደርጉት (የኢሕአፓ አባልነትን) ስላልቻሉ ወደ አዲስ አበባው የፀጥታ ክፍል ላኩት። እዚያም እንዲሁ በተከታታይ ለቀናት በግብረ ሰይል ተፈጸይቶ በዚያው ሞተ።

ብዙዎች የእሥር ቤት የክፍል ባልደረቦቼ ፍጻሜያቸው ተገድሉ እውራ ጉዳና ላይ መጣል ሆነ። እኔ እለም በታኝ ከተሰደድኩ በኋላ መስከረም ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ተለቀቅሁ። ከሰ ፈድሞ አልተመሠረተብኝም፣ወይም በወግ አልተፈረደብኝም።

ሽዋ

በዓይኔ ያየሁትን ነው የምጽፍላችሁ። የመጀመሪያው ታሪክ በዋናነት የሚያተኩረው በደፋትና ጥሙጋ እውራጃ በማፉድ ወረዳ ወደሚገኘው ወደ ሞራ ሜዳ ከአዲስ አበባ መጥቶ ስለነበረው ታሪኩ ስለተባለ ታጋይ ነው። ወደ ሽዋ ሮቢት የምርመራ ማዕከል ይዘው ያመጡት ዕለት በወሬ ኢሳላ ዓይነት ይደበድቡት ጀመር። ያ የመጀመሪያ ቀኑ ነበርና እንደሁላችንም ሚማምቹ ይደሙ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን እንደገና ድብደባው ቀጥሉ "ግበረ አበሮቹንና የግንኙነት መሥመሩን" እንዲያወጣ ተጠየቀ። እንድ የሚገናኘው ባካባቢው እንዳለና እንደሚያሳያቸው ነገራቸው። የምሣ ሰአት ስለተቃረበ ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹ ፖሊሶቹን ወደ ክፍሉን እንዲመልሱት እዝዘው ወደየቢታቸው ሄዱ። ታሪኩ በዚህን ጊዜ በጣም ተጸከሚል፣ ሰውነቱም በየቦታው ይደማ ነበር። ወደ ክፈሉ ተራምዶ በቀጥታ መግባት ስላቃተው፣ ወደቀ። ዝብረ እግዚአብሔር የተባለ፥ መንታ ምላስ ያለው አለንጋ የያዘ ፖሊስ ታሪኩን በአለንጋው ራሱ ላይ ሲመታው ያለንጋው እንዱ ምላስ ዓይኑን ክፉኛ መትቶ ሰነጠቀውና የታሪኩ ዓይን "ፈሰሰ"። ተሸክመው ወደ ክፍሉ ውስጥ ሲወረውሩትም በጣዳር ሙሽ። ሌሊት እውጥተው ሲወስዱት ፈልገው ነበር፣ ነገር ግን በሞት አፋፍ ላይ ነበር፣ እንድ ዓይኑ አብጧል፣ እንዱ ጠፍቷል፣ የውስጥ እግሮቹ ተበጥሶው ደም ያዘንባሉ፣ ጀርባውና ፊቱ አባብጠዋል።

ማለዳ ሊወስዱት መጡ። የመርማሪዎቹ አለቃ፥ የደርግ አባል ነው የሚባል መቶ አለቃ ሰሎሞን ነበር። ታሪኩ ቅሾት ውስጥ ያለ ይመስል ነበር። " ዓደኞችህን ታሳየናለህ"

አሉትና ፕገሮ መኪና ውስጥ ከትተው ወሰዱት። በኋላ እንደሰማነው ታሪኩ እንድ ዓደኛውን ጠቁሞ አስይዟቸው፥ ሌላም በመንገድ ላይ አመላክቷቸው ይህ "አደገኛ ነው" ብሎ ገለጸላቸው ኑሯል። ስለዚህም፣ ታሪኩን አዲስ ካከያዘው ሰውና ከመኪና ነጂው ጋር ትተዋቸው "አደገኛ ነው" የተባለውን አጥምደው ለመያዝ ሄዱ። በሆነ መንገድ፥ ታሪኩና ሌላው ሰው የመኪና ነጂውን ሽጉጥ ነጥቀው ጭኑ ላይ አቁስለውት አመለጡ። በኃላ ልንረዳ እንደቻልነው፥ ያ ሌላው ሰው ታሪኩን በጀርባው እዝሎት ነው ያመለጡት።

የፀጥታዎቹ ሰዎች ተመልሰው መጡና ታሪኩ ማምለጡን ሳይነግሩን "ቀይ ሽብር" እንደሚፋፋምብን ተገዘቱብን። አንዳንዶቻችን ታሪኩ ተገሎ ይሆናል ስንል፥ ሌሎች ደግሞ ወይ እምልጠ ይሆናል፥ ወይም ደግሞ መኪናው እየተንቀሳቀሰ በመዝለል ራሱን ገድሎ ይሆናል ብለው ጠረጠሩ። ከጥቂት ቀናት በኋላ የደርግ ኑፍሰ ገዳዮች ያልታሰበ ዕድል ገጠማቸውና ባካባቢው በጣም ይፈለግ የነበረው ጌታነህ በዛ የተባለ ታጋይ ሊያመልጥ ሲሞክር በተኩስ ተያዘ።

ጌታነህ፥ ሽዋ ሮቢት የምርመራ ማዕከል እንደመጣ፥ ከመርማሪዎቹ የግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ እንዱ ንጉሤ የተባለ ጠብደል ሰው ዘሎ አፈፍ አደረገውና በዓይናችን እያየን ሁለት እጆቹን ሰበራቸው።ከዚያም ጌታነህን ከሲሚንቶው ወለል ላይ ዘረሩት :: ንጉሤ እንደገና ጌታነህን በዚያ በከባድ የወታደር ጫማ እፍ አፉን በርግጫ መታውና አፉን ደም ሞላው ፥ ከጥርሶቹም ጥቂቱ ተሰበሩ :: "ደም ከፈለግህ ይህን ተቀበል ፥" አለና ጌታነህ ንጉሤ ሱሪ ላይ ተፋበት።ንጉሤ እክሎ መታውና ልብሱን ሊቀይር ሄደ:: ከዚያም ሲመለስ እጆቹን አሥሮ በወሬ ኢሳላ ደበደበው:: እንደገና ወለሉ ላይ ሲጥሉት፥ ንጉሤ እነሱን መስደቡን ቀጠለ፣ እንደገናም ንጉሤ ከሲሚንቶ ወለሉ ጋር አጋጨው:: በዚህን ጊዜ የጌታነህ መላ ሰውነት በደም ተበከለ:: የተገባበጠና የተቀጠቀጠው ፊቱ ከማይታወቅበት ደረጃ ላይ ደረሰ:: እጆቹና እግሮቹ ከመዘንጣጠላቸው የተነሣ እጥንቶቹን አግጠው መጥተው እናያቸው ነበር:: ያም ሁኖ እጆቹን በሠንሰለት (አሥመራ ካቴና ብለን በምንጠራው) እንዳሠሯቸው ነበር::

ሌሊት ከክፍላችን ውስጥ እንዳለ፥ ጌታህ እንደመቀወስ አለ። ደጋግሞም ውኃ ይጠይቅ ነበር። ግለጻ እንደገና መጡና እንደተለመደው የክፍሉን በር አስከፍተው፥ ከርፋቱ እንዳያምሳቸው አንድ አምሥት ደቂቃ ያህል ቈይተው ገቡ። ጌታህ ደግሞ እንደገና በአንድ ቀን ሙሉ ግበረ ሰይል ቁም ስቅሉን ካየ በኋላ መደበቂያ ዋሻውን ሊያሳያቸው ተስማማ። መራመድ የማይችል ስለነበርም ተሸክመው ወሰዱት። እዚያም ጥቂት ቋንጣ፥ የተሰበረ ኡዚ ጠመንጃና በርበሬ አገኘ ። በንዴት ይዘውት ተመለሱና ቁሻሻ ውኃ በተሞላበት በርሜል ውስጥ ዘፈቁት ። መዝፈቅንና አሠቃቂ ድብደባን ያፈራርቁበት ነበር።

ሌሊት ክፍላችን ውስጥ፥ ጌታህ እንድንገድለው ጠየቀን፣ ግን ማን እንዳደረገው እንጹ ግበረ ሰይል ሊፈጸምበት ሊያወጣ ይችላል ብሎ ሁሉም ስለፈራ የማይሆን ነገር ነበር። እንድ አሥረኛ ችግሩን ዘርዝሮ፥ በገዛ ራሱ ሕይወቱን እንዲያጠፋ መከረው። በመከከላችን ሰላጮችና ነገር ለማውጣጣት የተተከሉም ነበሩ ጌታህ እንጹን አሥረኛ ግድግዳውን አስደግፎ እንዲያቆመው ጠየቀው፣ ከዚያም እጁ የታሠረበትን ኩቴና ታሳላቅ መሸጎሪያዎች ወደ አፍንጫው አስጠጋና በሲሚንቶው ወለል ላይ ተፈጠፈጠ። በማም የሚያስደንግጥ አስተርዕዮ ነበር። እንደገና ያንኑ ደገመና ከፈሉ ደም ተረጨበት። እንዲህ ሆኖ ሲሞት አየን። ግለጻ፥ ግበረ ሰይል ፈጻሚዎች ሲመጡ ሙት ጌታህና እና አሥረኞች የተሞሉባት፥ ፀጥታ የሰፈነባት ክፍል ቈዮአቸው። አሥረኞች ክፍሉን እንድናፀዳ ታዘዝን፣ እነሱም የጌታህን ሬሳ ጭራ ሜዳ ወስደው፥ በኋላ እንዳወቅነው የፍየል ደም አፈሰሱበትና በጥይት ደብድበው መንገዱ ላይ ወረወሩት።

ታሪኩም ከጥቂት ቀናት በኋላ እንደገና ተይዞ ወዲያው ተገደለ። ሽዋ ሮቢት አሥር ቤት ውስጥ እንደነዚህ ዓይነት ብዙ ታሪኮች ነበሩ። ምንያህል ሰዎች እንደተረሸኑ አላውቅም፣ ነገር ግን እጃቸው ላይ የወደቁ እንዳሻቸው የሚያደርጓቸው በቂ ሰዎች የነበሯቸው እንደመሆኑ መጠን ገዳዮቹ ምን ጊዜም በግድያ ላይ የተጠመዱ እንደነበሩ በመሐላ ማረጋገጥ እችላለሁ።

አዲስ አበባ

"ዕድሜዬ ሰላ ሲሆን የሚዘገንኑ ነገሮች ገጥሞኛል፣ ግን ከ" ቀይ ሽብሩ" ጋር የሚወዳደር የለም።ያየሁትን እንድንግራችሁ ከጠየቃችሁኝ በ ___ መምህር ስለነበረውና ስለተገደለው ልጁ ልነግራችሁ እችላለሁ፣ ግን ራሳውን አላየሁም። ቀበሌያችን ውስጥ በተደረገ ሰላማዊ ሠልፍ ፲፩ ዓመት የሆናት የእኅቴ ሴት ልጅ በጥይት ስትገደል አይቻለሁ። እንዲህ ዓይነት ታሪክ ብዙ አውቃለሁ። ሾላ አካባቢ ቀለመወርቅ ትሪቤት አጠገብ በቀይ ሽብሩ ወቅት ከመቶ ያላነሰ ራሳ አውራ ጐዳና ላይ ተጥሎ አይቻለሁ። በማም የሚዘገንን ስለነበር እዚያ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ዘመዶቼን መጠየቅ ማቆም ነበረብኝ። ጎረቤቶቼስ ቢሆኑ? የዘ _____ ቤተሰብ? የዘ____ ሴት ልጅ ወንድ ልጆቿን በሙሉ ለቀይ ሽብሩ ገብራለች። ኤልያስ ለስድስት ወራት በግብረ ሰይል ተፈጻይቶ በዚሁም የፍጻ ጠንቅ ከታወረ በኋላ ከሌሎች ጋር ሰበታ ተወስዶ ተገደለና ከጅምላ መቃብር ውስጥ ተጣለ። ሌላው ልጇ ብርሃን ለሁለት ወራት ግበረ ሰይል ከተቀበለ በኋላ (በፈላ ዘይት ውስጥም ተንከሮ ነበር) ተገድሎ እዚሁ ቀበሌያችን ጎጻና ላይ ከማላውቃቸው አሥር ልጆች ጋር ሬሳው ተጣለ። የታወቀችው የቀበሌ ባለሥልጣን የሽዋ ልዑልና ምክትሏ ቡሩክ የተገደሉ ዕለት ቀበሌዎች በእካባቢያችን ብዙ ወጣቶችን ሲገሉ ሦስተኛው ልጇ ተገድሎ ጎጻና ላይ ሬሳው በመኪና ተጎተተ። ያን ዕለት ከናቷ ጋር ቤተክርስቲያን ሄደን ፀሎት እያደረስን ነበር። ከሩቅ ሬሳ በመኪና ሲጎተት አየንና ላልታወቀው የፈረደበት ሰው አለቀስን። ከኔ ጋር የነበረችው ዓደኛዬ ያ የሚጎተት ሬሳ የልጅ ልጇ መሆኑን አላወቀችም ነበር።

እጅግ ዓየሁና ወሰኔ በውጋና ፈላሽ ባለ ሥልጣን ሕንፃ ውስጥ በቤት ጠራጊነት ሥራ ተቀጥራ የነበረች ሴት ልጆች ነበሩ። እጅግ ዓየሁ ተይዛ አረመኔያዊ በሆነ መንገድ በግብረ ሰይል በማም ከመጐዳቷ የተነሣ ቀበሌው በሙሉ ሞቷ እንዲፋጠንላት ይፀልይላት ነበር። ከአሥራ ሁለት ቀናት ግበረ ሰይል በኋላ ገድሰው ሬሳዋን ____ በቀበሌ ነዋሪዎች ቁራ እየተባለ መታወቅ በጀመረው ____ መስቀልኛ መንገድ ላይ ጣሉት። አንጹ ተማሪ፥ ሌላው የመንግሥት ሠራተኛ የነበረ፥ ሁለት ልጆች የነበሯት ቀበሌያችን ውስጥ ትኖር የነበረ የአንዲት ሴላ ሴት ስም ጠሩኝ። እንድ ሌሊት ስኳዶች ተማሪውን ፍለጋ መጡና ጠፍቶ ቆየ። ታዲያ በሉ

ቁጭት የመንግሥት ሠራተኛውን መደብደብና ለመውሰድም ሲያሥሩት ጀመሩ:: በንዴት የተቃጠለችው እናት እንዴን የስኳድ አባል በጠርሙስ አለችው:: ከዚያም ሁለቱንም እናትና ልጁን ወዲያውኑ እዚያው ገደሏቸው:: ቤቱንም እንዳለ ዘረፉት፥ የወንድ ሚቹንም ልብስ አልተው::

የቀበሌ ዘበኞች ፥ የተጠርጣሪዎች ጓደኞች እየመሰሉ ወደየቤቱ ስልክ ይደውላሉ :: አንድ ጊዜ እንዲት እናትን በዚሁ መንገድ አታለሏትና ፥ ልጇ ከቤት እንዳለ ነገረቻቸው ::እነሱም መጡና ልጁን ጎትተው አውጥተው በራሱ ላይ ገደሉት :: እናትየዋ እሪ እያለች ብትወጣ እሷንም ጭኗ ላይ በጥይት መቷት :: አንድ ቤት ደግሞ ሁለት ልጆች ገድለው ውሾችን ለቅቀው ደሙን እንዲልሱ አደረጉ ፤ ይህ ሁሉ በልጆቹ እናት ፊት ነበር :: እናትዮዋ ተንበርክካ ሬሳዎቹን እንዲተዉላት ብትማፀንም እምቢ ብለው ይዘውባት ሄዱ :: "አብዮቱ ኩትኩቶ የሚያሳድጋቸው ሌሎች ልጆች ውለጂ " ብለውም አፈዙባት :: ሴትዮዋን እንደ ዕብደት አድርጓት የልጆቿ አስከሬን ለትርዒት ከቀረበበት ሥፍራ ላይ በየቀኑ ትቀመጥ ነበር :: ለሚሊሺያ ራሽን እንድናሰናዳ ስንታዘዝ እሷም እንዲሁ ታዝዛ አሻፈረኝ ስላለች አንድ ዘበኛ እጇን ሰበረው :: እንዲያም ሁኖ ራሽን ወደምናሰናዳበት ወደ ቀበሌው አዳራሽ አምጥተዋት የግድ እንድትሠራ ተደርጎ ነበር::

የ_____ ልጅ ትእግሥት፥ ሊያገባት ሞክሮ እምቢ በተባለ የቀበሌ ዘበኛ ተያዘች:: አካባቢዋ ፒያሳ አቅራቢያ ከ _____ ሠፈር አጠገብ ነበር:: ፍም እስኪመስል የጋለ ብረት በብልቷ በመስደድ አረመኔያዊ የሆነ ግበረ ሰይል ፈፀሙባት:: " ያለተወለደ አናርኪስት ተሸክመሽ እንደሆነ ለመፈተሽ ነው" እያሉ ዘበኞች ሆዷ ላይ ይዘሉባት ይጨፍሩባት ጀመሩ:: በዚሁ ሥቃይ ውስጥ ሙታ ከተለመደው ከቀለመ ወርቅ ትቤት አጠገብ ለትርዒት ተጣለች:: ነፉስ ስልክ ውስጥ፤ የሌሎችን ልጆች እያደነ ሲገድል የነበረ የቀድሞ የመቶ አለቃ ማምሻውን ቤቱ ሲገባ በሌሎች እስኳዶች የራሱ ስድስት ልጆች በመትረየስ ታጭደው አገኛቸው:: እንደሚታወቀው በዚያን ጊዜ ስኳዶች ደካማ ቀበሌዎችን ለመርዳት ወይም ትብብር ለማሳየት ከራሳቸው ውጭ የነበሩ ቀበሌዎችን ይጉበኙ ነበር:: ታዲያ ያ (የሟቾች) አባት እንደነሱ ሁሉ ሰው ገዳይ መሆኑን አላወቁም ነበር::

አንድ ሽማግሌ ሰው የተገደሉ ሦስት ልጆቻቸውን ሬሳ ከምኒሊክ ሆስፒታል አስወጥተው ለመውሰድ የጥይት ዋጋ ከፈሉ ቢሏቸው፥ በንዴት፥ "ብሏቸው ከፈለጋችሁ አሉ::በድብደባና በአንድ ዓመት እሥራት ብቻ ማምለጣቸው ዕድለኛ ነበሩ:: "ጥይት በነጻ ይገኝ ይመስላችኋል? የአምቡላንሱስ ቤንዚን?" እንዲህ ነበር የሚሉን ሬሳ ለመውሰድ ስንሄድ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማንኛውም ሰው ሬሳ መውሰዱን ወይም ሰሬላ መክፈሉን አቆመ::

በቀበሌዎች ሁሉ ይኸው ታሪክ ይደጋገማል:: እሑድ እሑድ ቤተክርስቲያን እንገናኝና (ፈጣሪያችን) እንዲታደገን እንፀልያለን:: ያለተነካ ቤተሰብ የለም፤ ገዳዮች ይኸው አብረውን ነው ያሉት፤ በየቀኑ እናያቸዋለን፤ እንደምንጠላቸውም ያውቃሉ:: ሁሳችንም ያን የፍርድ ቀን እየጠበቅን ነው:: ሙሉ ታሪኩን ማወቅ ከፈለጋችሁ ቤተሰቡን ሁሉ ማነጋገር ይኖርባችኋል፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ቤተ ሰብ በልቡ ያመቀው ስንት፥ ሐዘን፥ ሕመም አለውና::"

አዲስ አበባ

"የቀድሞው ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ወታደራዊ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ተይዤ ተወሰድኩ:: ይህ እሥር ቤት ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የሚገኘው የፀጥታ እሥር ቤትን ያህል መጥፎ ሲሆን በአረመኔያዊ አሠራሩ ከማይጨው ወታደራዊ ሠፈር እሥር ቤት ጋር ይወዳደራል:: (ጃን ሜዳ አጠገብ የሚገኘው ትልቅ እሥር ቤት ክፍሎቹ የተሠሩት ከሥሩ ቆሻሻ የሚወርድበት ቱቦ በተዘረጋበት ላይ ነው:::)

በእሥር ቤቱ ዙሪያ ሦስት ሜትር ርዝመት ያለው ግድግዳ አለ፤ ከግድግዳው ፊት ደግሞ በእሥረኞቹ የተቆፈረ ርዝመትና ሥፋት ያለው ቦይ አለ:: ስለዚህ ማምለጥ በጣም ከባድ ነው:: ከውስጥ፥ ክፍሎቹ 1 1/2 ሜትር በሁለት ሜትር ሲሆኑ የሚጠቀሙባቸው ለብቻ ገልለው ለሚያሥሯቸው እሥረኞች ነው:: ግድግዳው ላይ ከፍ ብለው ያሉት መስኮቶች የሚከፈቱት ክፍሎቹን በግራና በቀኝ ወደሚለየው መተላለፊያ ነው:: ወለሉ ከሲሚንቶ የተሠራ

እንደመሆኑ መጠን ተዝቃዛ ነው። እሥር ቤቱ አርሞ ያለ፥ ዐጥታውም የሚያስፈራራና የሚመፈግግ ነው።

እሥር ቤቱ ስንደርስ ሚማዎቻችንን እንድናወልቅ አዘዙን፣ ዕቃዎቻችንንም አስረከብን፣ ከዚያም "ሬሳችንን" ለመረከብ የሚነገራቸው የዘመዶቻችን ስሞችና አድራሻዎች ዝርዝር የሚጻፍበት ፎርም እንድንሞላ አስገደረጉን። ከዚህ በኋላ እቦዩ አጠገብ አመለቱን ጠመንጆቻቸውን አቀባብለው "ምላሮቹን ሳቡ።" ይህ የማሞኛ ርሽና የገደሉን ያህል ነው የተሰማን።

የሚያስፈራራ ፀጥታ በሠፈነባቸው ክፍሎቻችን ውስጥ ሁል ጊዜ ኮረንቲ ስለሚበራና መስኮቱም ወደ እሥር ቤቱ ውስጥ ስለሚከፈት ቀንና ሌሊቱን የምናሳልፈው የትኛው ቀን የትኛው ሌሊት መሆኑን ሳናውቀው ነው ምርመራና ግብረ ሰይል አብረው ሣይነጣጠሉ ነው የሚያካሂዱት። የውስጥ እግርህን ከደበደቡ በኋላ ከጠንካራ ገመድ ከተሠራ ወንበር ላይ እንድትዘል ያደርጉሃል። ይህ እንደያውም የውስጥ እግርህን የበለጠ ሕመም እንዲሰማው ያደርገዋል። የተራቀቀበት አንድ ነገር ቆለጥን በጭኳ በመደብደብና ለዚሁ ጉዳይ በተሠራ መሣሪያ በመጨቆን (በመጭቀጥ) ማድቀቅን ነው። ግብረ ሰይል እያካሄዱ "እንገልሃለን፥ መሞትህንም የሚያውቅ አይኖርም" ይሉሃል። ግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ "ሰአት አክባሪ" ናቸው። የምሣ ሰአታቸው ሲደርስ ወዲያው አቁመው ይሄዳሉ። ከሰአት በኋላ እሰኪመለሱ ከጣራ ላይ እንዳንጠለጠለህ ይተውሃል። አዘውትሬ የተቀበልኳቸው የግብረ ሰይል ዓይነቶች ግርፊያ፥ የኤሌትሪክ ንዝረት፥ የብልት ፀጉርን በፕንላ መንጨት፥ ጭንቅላትን ሥስታም ጠርዝ ባለው ማሥመሪያ መምታት፥... ጣቶቻቸውን ቀስ በቀስ የቀረጣጠፏቸው ሌሎች ነበሩ፤ ሌሎች ደግሞ የሰው ዓይነ ምድር እንዲበሉ፥ የሰው ደም እንዲጠጡ የተደረጉ ነበሩ።

ዓርብ ዓርብ የርሽና ጊዜ ነው። (የወታደሮቹ) ኮቴ አንተው ክፍል በራፍ ላይ ደርሶ ይቆም ይሆናል በሚል ሥጋት ሌሊቱን መጠበቅ እያድርስ ነው። .... አብሬያቸው ከመጣሁት እሥረኞች ሁለት ብቻ ነን የተረፍነው። ..ሌሎቹን ወርሶ አይቻቸው አላውቅም፣ ተገድለዋል ብዬ እገምታለሁ።

ናዝሬት (ሽዋ)

"የተያዝኩት ጥቅምት ፲፱፻፷፱ ከቤቴ ከሌሊቱ በ ፫ ሰአት ነው። የወሰዱኝ በጊዜው እንደ "መኢሶን አባላት" ይታወቁ የነበሩ በኋላ ወደ ሰደድ የተሳቡ ሲሣይ ወልደዮሐንስና (አሁን ሃምሳ አለቃ የሆኑና በኤርትራ ውስጥ አንድ ቦታ የሚኖር) ብዙህ እንዳይላሉ ናቸው የያዙኝና ቤቴን የፈተሹኝን ስኳድ የመሩት።

እሥር ቤት ውስጥ መሐርነት መብራቱን አገኘሁት። ቤቱ ውስጥ አንድ የዴሞክራሲያ እትም ተገኝቶበታል። በተደጋጋሚ ከማሐርነት ጋር "ድርጅታዊ" ግንኙነት እንደነበረኝ ጠየቁኝ፣ ነገር ግን ፊጽሞ ኑሮኝ አያውቅም ብዬ ካድኩ።ከመርማሪዎቹና ከግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ የማስታውሳቸው ተሥፋዬ መንግሥቱ (የወንጂ አብዮታዊ መከላከያ ኮሚቴ ሊቀ መንበር፥ ዮናስ አራሮ (ካድሬ)ና አባተ ተሰማ የተባለ የመኢሶን አባል ናቸው። አንድ ቀን መሐርነትን ጠርተው አወጡት፣ ከዚያ በኋላ ታይቶ አይታወቅም። ሙሉጌታ የሚባል ሌላ እሥረኛ ነበር በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደጠፉ የቀረ። እኔን አንድ ወር አቆይተው ለቀቁኝ፣ ግን እንደነተሾመና (የወንጂ ሥኳር ፋብሪካ ሠራተኛ) ሰሎሞን (ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ውስጥ ኮረንቲ ሠሪ) በአሠቃቂ ሁኔታ ግብረ ሰይል ተቀበልኩ ማለት አልችልም። እነሱ ላይ ያልተጠቀሙባቸው የጭካኔ ቅጣቶች አልነበሩም። በጣም ከከፉት ግብረ ሰይል ፈጻሚዎች የማስታውሳቸው፥ የወዝ ሊግ አባል የነበረውን ሚልኪሶ አንጀሉን ሲሆን ይኸው ሰው በጭካኔው የታወቀ ከመሆኑ የተነሣ፥ የአቃቂ ሠራተኞች ሌላው ገዳይ ጣም ያለው እሸቴ (አሁን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል) ለእርዳታ ይጠራው ነበር። ሚሠለጰኪሶና ጣም ያለው ሁለቱ በእንድነት ልክ የሌለው ሠራተኛ ወርሰዋል።

በየካቲት 1970 ብቻ ናዝሬት ውስጥ (ከአዜ ገላውዲዮስ ትሪቤት ውጭ፥ ግምብ ገቢያና ቅድስት ማሪያም አጠገብ) 21 የአስተማሪዎች የተማሪዎችና የሌሎች የማላውቃቸው የኢሕአፓ አባላት ናቸው የተባሉ ሰዎች ሬሳዎች አይቻለሁ። ከወንጂ ብዙ ሰዎች ታሥረው ነበር፣ እስካሁን የደረሰበት ምልክቱ የለም።

ሐረርጌና አዲስ አበባ

"ስለገዛ ራሴ ተመክሮ ከመጻፌ በፊት ሌላ ስለማውቀው ብጽፍ ጠቃሚ ይመስለኛል፡- ስልተያዙ፥ ግበረ ሰይል ስለተቀበሉና ስለተገደሉ መስከረም 1969 ሐረር ውስጥ የመድኃኔ ዓለም ት/ቤት መምህርና ርእሰ መምህር የነበረው ነጋሽ ሙሳ ተያዘና አረመኔያዊ በሆነ መንገድ ግበረ ሰይል ከመቀበሉ የተነሣ ጫማዎቹ እንዳልሆኑ ሁነው ደም ያንቆረቁሩ ነበር፣ ሽንቱንም ደም ያቀለመው ነበር። በዚሁ ዓመት በጎዳር ወር ፭፮ እሥረኞች ወደ ኤረር (በሐረርና ጂጂጋ መንገድ ላይ) ተወስደው በቅጽበታው ውሳኔ ተገድለው ተቀበሩ። ከነዚህ ፭፮ ውስጥ የማስታውሳቸው ያታሪክ መምህርና የተነሥ (የሐረር መምህራን ማኅበር ልሳን) አዘጋጅ የነበረው ዓለማየሁ፥ ከፈሌ (የሂሳብ መምህር) ዘውዴ (የመድኃኔ ዓለም ት/ቤት ተማሪ የነበረች) ባሸንኩር (ተማሪ የነበረች) አሸብር ጎይሉ (የዩኒቬርስቲ ተማሪ ከአዲስ አበባ) ተማሪዎች የነበሩ ሰሎሞንና የሺጥላ ናቸው።

ቅጽል ስሙ ለንደን የነበረ ግርማ ከተረሸነ በኋላ "የሰማሌ ሰርጎ ገብ" ተብሎ ሬሳው በመኪና እየተጎተተ እንዲታይ ተደረገ። እዚያው ሐረር ውስጥ ጥፁመልማን የተባለ ወጣት ስኳዶች ሊይዙት ሲመጡ አልያዝም በማለት ሁለት ገድሎ እሱም ተገደለ። እናቱ ከገበያ ስትመለስ በስኳድ ታፍና ተወሰደችና መድረሻዋ ጠፋ።

እሥር ቤት ውስጥ ሁኜ፥ አሰበተፈሪ እሥር ቤቶች ውስጥ ግብረሰይል የተቀበሉ ብዙዎችን አግኝቻለሁ፥ እንደነገሩኝም እንድ የኢሕአፓ አባል ሰባት ጊዜ ከተደበደበ በኃላ ኢሕአፓንቱን ስላመነ ግብረ ሰይል ፈጻሚዎች " ሰባቶች" በተባለ የተራዘመ ድብደባ ያምናሉ። ቁጥር 8 ወይም 6 እየተባለ በሚታወቀው አስተሳሠር ያሥሩሀና ሰረጅም ሰአታት ጫማዎችህ እስኪደሙና አጥንቶቹ እስኪታዩ ድረስ ይደበድቡሃል። አሥረኛን ከረሸኑ በኋላ፥ ሬሳውን ከመኪና ጋር አሥረው ከተማውን እያዙሩ መጎተት ደስ ይላቸዋል። የሱልጣንን ሬሳ እንዲህ ነው ያደረጉት በ ፲፱፻፷፰ ውስጥ፥ የደርጉ አባል ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ ነበር በዚህ ከተማ ውስጥ የተካሄደውን ግደያ የመራው። የጥቃ ፋብሪካ ሠራተኞች በጅምላ ነው የተረሸኑት። የገለምሶ አርሶ አደር ማኅበር

አባላት፥ ጥቂት ተማሪዎችና የመንግሥት ሠራተኞች እንዲሁም የአውራጃው አስተዳዳሪ (የቀድሞ የአየር ኀይል መቶ አለቃ የነበረ) በሻለቃ ጌታቸው እንዲታፈሱ ከተደረጉ በኋላ በገለምሶና በበዲሳ መካከል ባለው ሜካ ውስጥ በጅምላ ተረሸኑ። በዚያን ጊዜ ፴ የሚሆኑ ተማሪዎች ከአሰበ ተፈሪ ታፍሰው ወደ ሚኤሶ በመወሰድ ተረሽነዋል።

እኔ ራሴ አዲስ አበባ ውስጥ ተይዤ ሲኢማ አምፒር አጠገብ ከሚገኘው ቀበሌ ፲ ከፍተኛ ፪ ውስጥ ታጉቼ ቆይቻለሁ። በመጀመሪያ ተገረፍኩ፥ ተደበደብኩ፥ ግብረ ሰይል ይፈጽሙብኝ የነበሩት ማሰረሻ ከበደ ፥ ፍሬው(የቀድሞ ኪስ አውላቂ) ታደሰ (የፀጥታ ጆሮ ነው) ፀጋዬ(የቀበሌ ዘበኛና የስፖርት ፌዴሬሽን መኪና ነጂ) እንዲሁም ፈለቀ የሚባል የከፍተኛ ፭ ካድሬ የነበሩ ናቸው።- በዚህ ቀበሌ ውስጥ ከየሬሳዎች ውስጥ (ታምራት የተባለ የቀበሌ መሪን ገደላቸው በሚል በዚያው አንድ ወንጀል በተለያየ ጊዜ የተገደሉ) የዓለማየሁን የሳሙኤልን የግርማ ታፈሰን አውቃለሁ።

በቀበሌ እሥር ቤት ውስጥ የተለያዩ የግብረ ሰይል አይነቶች የሚከተሉት ነበሩ፣ ቁጥር ፭ ስቅላትና ግርፋት፥ ውኃ ውስጥ ዘፍቆ መግረፍ፥ ጀርባን ከገረፉ በኋላ የጋዜጣ ወረቀት በላዩ ላይ ማቃጠል፥ ፀጉርን አቃጥሎ ፀመጉን በደም ለውሶ አስገድዶ ማስበላት፥ ሲጋራ ምላስ ላይ መተርከስ፥ አሥረኛው፥ የግብረ ሰይል ፈጻሚውን አክታ እንዲውጥ ማድረግ፥ አሥረኛው ጣቱን ከፊንጢጣው እንዲከትና ያንኑ ጣቱን አፉ ውስጥ፣ እንዲዶል ማስገደድ፥ የጀርባና የጫማ ቁስልን በእግር መደፍጠጥ፥ ጀርባን በኮረንቲ ካውያ መተኩስ ናቸው።

ጎዳር ፲፱፻፷፱ አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከእሥር ቤት ተወስዶ ተገድሎ ቴዎድሮስ አደባባይ ላይ ለትርዒት ተጥሎ ነበር። አንድ የመጠጥ ሱስ የተጠናወተው ወጣት ራሱን ከተጨማሪ ግበረ ሰይል ያጸነ መስሎት እምስት ጓደኞቹን አጋለጠ! ሁኖም ግን ከአምስቱ ጋር ተወስዶ ተገደለና "ሱማሌ ተራ" ተብሎ በሚታወቀው ቦታ የስድስቱም ሬሳ ለትርዒት ቀረበ። ሰምንት ወጣት ልጆችም ወደ ከፍተኛ ፭፩ እንዲመጡ ተደርጎ ከተገደሉ በኋላ ራስ መኩንን ድልድይ አካባቢ ተጥለዋል። ወደኛ ቀበሌ እሥር ቤት ከኛ ጋር ለታሠረ አንድ ዘመዴ ምግብ ታመላልስ የነበረች እንዲት

የ፲፱ ዓመት ወጣት ነበረች፣ ታዲያ ከዘበኞቹ እንዱ፥ ዓይኑ ስላረፈባት አንድ ቀን እሷም ከኛ ጋር ታሠረች:: ታደሰ የተባለ ይህ ዘበኛ ደፈራትና አረገዘች፣ ማርገዟንም እንዳወቀ ገደላት:: ውሉ አድሮ ታደሰ በሌላ ወንጀል ሲያዝ ይህም (የልጅቷ ግድያ) ከወንጀሉ ዝርዝር ውስጥ ተደመረ:: ነገር ግን የተወሰነበት ቅጣት የጥቂት ዓመታት እሥራት ነበር::

የቀበሌ አለቆችና ዘበኞች ይደፍራሉ፣ ይገድላሉ፣ ይዘርፋሉ፣ ለምሳሌ ሃጅ በድሩ የተባለ የቀበሌ ፲፩ ሊቀመንበር፥ ከቀበሌ ፱ ተረፈና ከቀበሌ ፲፫ አወቀ በዚህ ረገድ የታወቁ ነበሩ:: ሰዎችን ያሥሩና ዘመዶቻቸውን አስፈራርተው ገንዘብ ይቀበሉ ነበር፣ ገንዘብ ይዘርፉና ባለቤቶቹን ይገድሉ ነበር:: መርካቶ አካባቢ የነጻነት ጎን ቡና ቤት ባለቤት ዕጣ ይኸው ነበር:: የቀበሌ ፱ ሊቀመንበር ተረፈ የግራር ሆቴል ባለቤትን ሚስት ወሽመና ከዚያም ባልዬውን ገደለ:: ገ _____ የተባለ የቅቤ ነጋዴ "አናርኪስት" ተብሎ ሲገደል ከሚችልበት ሁኔታ ለመጻን ፲፭ ሺህ ብር መክፈል እንደነበረበት ዐውቃለሁ ::

" በእንድ ወንጀል " በርካታ ሰዎችን መግደልም የታየ ነበር :: ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ታምራት የተባለውን የቀበሌ ሊቀመንበር "ገደላችሁ በመባል" ምስት ሰዎች ተገድለው ነበር :: ጥር ፲፱፻፫፭ ዓ.ም. በቀበሌው ውስጥ የሕዝብ ስብሰባ ተደርጎ ቀርዋሬ የተባለ በወጣትነት ዕድሜ ያለ ሰው የታምራት ገዳይ ተብሎ ለሕዝቡ ተጋለጠ :: እዚያው ቦታ በሕዝቡ ፊት እንድ የቀበሌ ዘበኛ ቀርዋሬን ገደለው ፣ ከዚያም አናርኪስቶች ሲሞቱ ማየት እንዲት እንደሚያስደስት የሚገልጸውን የተለመደ ዘፈን እንዲዘፍን ሕዝቡ ታዘዘ :: ከሳምንት በኋላ ሌላ ስብሰባ ተጠራና አሁን ደግሞ የቀበሌው ኗሪ የሆነ ገብረ መድኅን ሽምዬ እንደ ታምራት "ገዳይ" ሁኖ ተጋለጠ :: በዚህ ጊዜ ሰው ለመቃወም ደፈረ፣ "ታምራትን ለመግደል በሠልፍ ቁመው ነበርን ወይስ ምንድነው ነገሩ ?"ነበር ብዙዎች ያሉት :: ገብረ መድኅን በዚህ ሁኔታ ከሞት ተረፈ ፣ ከመለቀቁ በፊት ግን ሦስት ዓመታት ዓለም በቃኝ ታሠረ ::

ሀጅ በድሩ ፥ ሬሳቸው ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ለተጣለው ብዙ ሰዎች መገደል ተጠያቂ እሱ ነበር :: ለምሳሌ ጥር ፲፱፻፫ እሥረኛ በማምለጡ በንዴት

የተቃጠለው በድሩ ሰምንት አዳዲስ እሥረኞች እውጥቶ ረሽኖ ሬሳቸው ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ተጥሏል :: የቀበሌ ፲፮ አለቃ የነበረው በትረ እሥረኞችን ማቃጠልና የራሳቸውን የበሰበሰ ወይም በደም የተጨማለቀ ሥጋ እንዲበሉ ማስገደድን ሙያዬ ብሎ የያዘ ሌላ የታወቀ ገዳይና ግበረ ሰይል ፈጻሚ ነበረ:: የእሥረኞችን አባለዘርና ፊንጢጣ በሊጋራ መለኩሻ ያቃጥል እንደነበርም ተነግሮኛል:: ፖለቲካ ትቤት ውስጥ የመኢሶንና የሌሎች ካድሬዎች፥ ለእሥረኞች መዝፈቂያ ሲሉ የፈላ ዘይትና ውሃ፥ ገላ መታጠቢያ ግንዳ ውስጥ መሙላት ይወዱ ነበር::

ሠኔ ፲፱፻፫፫ ዓ.ም. በተለያዩ እሥር ቤቶችና የማቆያ ማዕከሎች ኮሚቴ ተዘዋውሮ በኢሕአፓ የመከላከያ ስኳድ አባልነት የተወነጀሉትን በሙሉ ሰብስቦ ወደ ደርግ ዋና መሥሪያ ቤት ወስዷቸው ከተመረመሩና በግብረ ሰይል ከተሠቃዩ በኋላ ብዙዎች ተገደሉ::

እኔ ስድስት ዓመታት በእሥር ቆየሁ፣ በወግ ክስ አልተመሠረተብኝም፣ወይም አልተፈረደብኝም::

አዲስ አበባ (17)

" እሑድ ዕለት ከሌሊቱ በ፱ ሰአት ትንሽ ጋጠ ወጥነት ያለው ሁኔታ ቀሰቀሰኝና የጸጉሬንነውን የቀይ ሽብር ዕውነታ እነሆ አለኝ:: ስድባቸውን እያዘነቡ ቤቱን ሰብረው ለመግባት ይሞክሩ በነበሩበት የሽብር ስኳዶች ሦስቱም የቤታችን በሮች ይደቁ ጀመር:: ወዲያው የታየኝ በመኝታ ክፍሌ መስኮት ዘልዬ በቤታችን መስኮትና በመሠረቱ መካከል በሚገኘው መተላለፊያ ላይ እጅግ ራቅ ካለውና ጠባብም ከሆነው ጥግ መደበቅ ነበር:: የሚያሳዝነው ግን ከቻኩላዬ የተንሣ የመስኮቱን ከእንጨት የተሠራ ብርሃን ከላ (Shutter) መልሼ ሳልዘጋው ቀርቼ ኑሯል::

ከተደበቅኩበት ሁኜ የወራሪዎቹን ውሽት፥ ስድብ እሰማ ነበርና የሁለት ሴቶች ድምፅ (ያለጥርጥር ጠቋሚዎች) እንዳለ ለየሁ:: እነሱ ነበሩ ' ግድግዳዎቹ ላይ ልዩ ምልክት ፈለጉ!'

ጣራውን ዘንጥሶ'ነርቶግራፍች የተከፈፈጠበትን ገንጥሶ፣ 'ፍራሾቹን ተመልከቱ!' ....ወዘተ እያሉ እነዚያ ደደቦች ቤቱን እንዳለ እያመሳቀሉት ነበር። እስከዚያች ሰአት ድረስ ለረጅም ጊዜ ቤታቸው ደብቀውኝ ወደነበሩት ..... ወደ ተባሉት ባልቴት ልጆችሽ የት አሉ? የት ነው የምትደብቂያቸው? እያሉ ጥያቄዎች ሲወረውሩባቸው ሰማሁ። ያስፈራሯቸው፣ እዚሁ እንገልሻለን እያሉም ይዝቱባቸው ነበር። በድንገትም ከኔጲቱ መስኮት ብርሃን ቦግ ሲል አየሁ። ራሴን ጥያቄ ጠይቄ ሳልጨርስ መልሱን አገኘሁት። የእንጨቱን ብርሃን ከላ ከውጭ በኩል ሳልዘጋ ረስቼው ነበር። አንድ ፍርሐት የጨመደደው ድምፅ "በመስኮት አድርገው እምልጠዋል። ተደብቀው መሆን አለበት፣ ተጠንቀቁ፣" ሲል ሰማሁ። የጀርባውን መስኮቶች በሙሉ ከፈቱት፣ የክፍሎቹ መብራቶች በሙሉ ስለበሩ የነበርኩበትን ፍጹም የሆነ ጨለማ ዋጠው። ከነሱ አንዱ 'የተደበቁትን' ለመፈለግ የኛኑ ደካማ ባትሪ (ይመስለኛል) ተጠቀመ። ትንፋሼን ውጬ፣ ጀርባዬን ግድግዳው ላይ ልክክ አድርጌ ሰጥፌ ራቴን መልሼ በድን መስዬ ቆምኩ።

'ውጣ ተይዘሃል!' ብሎ ጮኸ። ቆየት ብዬ፥ አንድ ዐይነት ሲኢግ ዓይተን መሆን አለበት፥ ብዬ አሰብኩ። ፍንክች አላልኩም፣ እሱም ወደ ክፍሉ ውስጥ ተመለሰ። እዚህ ላይ የወራሪዎቹንና የጠቋሚዎቹን ማንነት መለየት ታሰበኝ። እንደማልታይ እርግጠኛ ነበርኩ። ስለዚህም ቅርብ ወደነበረው መስኮት (የኔ መኝታ ቤት) እያመሳሁ ተጠጋሁና ወደ ውስጥ እሾልቄ ተመለከትኩ፣ አንድ ሰው ብቻ ነበር ካሴቶቼን ቴፖቼንና የውስጥ ሱሪዎቼን ከሺሶቹ ውስጥ ያጭት የነበረው። ከዚያም ወደ መካከለኛው መስኮት ለመረማመድ ወሰንኩ። ከእንጨት የተሠራው የመስኮቱ ብርሃን ከላ አመቺ ስለነበር የተሻለ ዕይታ እንዳገኝ ረዳኝ። መስኮቱ እኛ እንደመኝታ ቤት ወደምንጠቀምባቸው በመጋረጃ ወደተከለሉ የተጣመሩ ማረፊያ ቤትና ምግብ ቤት ያመራል።

በርካታ የታጠቁ ሰዎች እየተተራመሱ ሲገቡ ሲወጡ ይታያሉ፣ የተከናነቡት ጋቢ ፊታቸውን የደበቀው ሁለት ያልታጠቁ ሴቶች ነበሩ፣ ጠቋሚዎቹ እነሱ መሆናቸው ነው። ራዲዮ፥ ልብስ፥ የወጥ ቤት ቁሳቁስ (ማሀን ቂንቆራ) .....ወዘተ የታጠቁት ወንበዴዎች ያጉላሉ። ባልቴቷ

ያንገታቸውን ልዩ የወርቅ ሀብል ሊሞጨልፍ ከሚሞክረው ዘበኛ ጋር ጭቅጭቁን ተያይዘውታል። በኋላም መንጭቆ ይወስድባቸውና የተሠራ ፀጉራቸውን በጭካኔ ጨምድዶ ይዞ የጆሮ ጌትቻቸውንም እከሱ ከእጅ ያገባል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዋነኞቹ ካድሬዎች ቦታውን በደንብ እንዲፈትሹ ለበታች ካድሬዎች ትእዛዝ ሰጥተው ጥለው ይሄዳሉ። በድንገት ድምፅ ከመስማቴ ጋር ከቤቱ የኋላ ግድግዳ ላይ ከመስኮቱ ፊት ለፊት የአንድ ሰው ጥላ ታየኝ፣ በጣም ቅርቤ ነበር። አልጋውም ላይ እየወጣ ነበር። ታዲያ በእቅራቢያዬ ወደሚገኙት የቤት ክዳን ቆርቆሮዎችና ጥቂት የተሰባበሩ እንስራዎች እጠገብ ወይም በሥራቸው ለመደበቅ ወደዚያ ቸር አልኩ። ለነገሩ እርቀቱ ከመስኮቱ በክንድ የሚለካ ነበር።

'አሁንም ይህንን የተከፈተ መስኮት አጠረጥረዋለሁ' ፥ ሲል ሰማሁት። ' ክብሪት ያለህ ስጠኝ' አለና ወረቀቶች ጨባብጦ ክብራቱን ሲሞር ወረቀቱን ሲለኩስ አዳመጥኩት፥

ሁለታችንም ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አልን፣ እሱ ዓይኑን ሰበረ፣ እኔም እንዲሁ በድንጋጤ ደነዘዝኩ። እሱም እንደደነገጠ ይታየኝ ነበር፣ ግን ፈጥኖ አደብ ገዛና ፀጉሬን አፈፍ አደረገው። በዚያም ቀይ ሽብር መዳፍ ውስጥ ወደቅኩኝ። ድምፅ አሰማና ሌሎች ተጯሩጠው መጡ። በመስኮቱ አድርጎ ግማሽ ሰውነቴን ያህል ጎትቶ አወጣኝ። ከሩቅ የሚጣራ ይመስል ' ይህች ውሻ መሣሪያ ይኖራት ይሆናልና ተጠንቀቅ' ሲል የሆነ ሰው ሰማሁ። ጉትተው ካስገቡኝ በኋላ በጥፊ ተጠፈጠፍኩ፣ በቡጢ ተመታሁ፣ ተተፋብኝ፣ ወለሉም ላይ ተወረወርኩ። እንዳንዶቹም ሲገድሉኝ ያሰቡ በማስመሰል ሽጉጦቻቸውን አቀባበሉ።

'.....ነሽ?'ብሎ እንዱ ጠየቀ፣ አልጋዬ አጠገብ ትቼው የነበረውን መታወቂያ ወረቀት ይዞ ' አዎ እኔ ነኝ ' ብዬ አለቀስኩ። መታወቂያዬ ግሪድ ናት የሚል ነው። እንባዬ በጉንጮቼ ላይ ዱብ ዱብ እያለ ነበር። ' ጉሪቤታችን ያሉ ቁስ ፖሊሶች መስለው ከሚመጡ አናርኪስቶች ተጠንቀቁ ብለውኝ ነበርና ለዚህ ነው የተደበቅሁት' ብዬ ሳላስበው ተናገርኩ።

' እዚህ ይኖሩ የነበሩ እናርኪስት ልጃገረዶች የት ነው ያሉት?' ብሎ እንደኛው ጠየቀ:: ' እንድ የውሽት መልስ ትሰጭኝና ናሳሽን ነው የምጠረምሰው' የሚል ተከተለ::

'እዲሱን ልብሷን ለብሳ ማለዳ ቤተክርስቲያን ሂዳለች፣ በቶታል ቤንዚን ማደያ መንገድ በኩል ነው የሄደችው' ብዬ መለስኩ:: ተጨማሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ዕድል ሳልሰጣቸው የልዩ ልዩ ጸድቃን ሰማእታትን ስም በመጥራት ፡ ስለወንድ ልጅ እምላክ፡ ስለ እምዬ ማርያም፡..... ወዘተ እያልኩ በመግፀን ልመናውን እጉርፍኩባቸው፣ ግን እኔን የፈለጉ አልመሰለም፣ ስለሌሎቹ ሴቶች መጠየቁን ደጋግሙ፣ እያንዳንዱን ጥያቄ በጥፊ ወይም በርግጫ እያጀቡ፡ መልሴ እንዲት ነበረች:: ጉትተው እነሱኝና 'መደበቂያ ቦታዎችን' እንዳሳያቸው ከክፍል ክፍል አዞሩኝ::

በ ሰ..... ገጽ ላይ የሰውን ትኩረት የሚስቡት፡ ወደሚቀጥለው ክፍል ወርውረው በከተቱኝ ጊዜ ከጉድጓዳቸው ተወርውረው ለመውጣት የከጀላቸው ታላላቅ ዐይኖቹ ነበሩ:: ሰ.....ግልጥጥጠጡ ከወጣው አልጋው እጠገብ እዕርቃኑን ቁሞ መላ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ነበር:: ከእንድ ዓመት ተኩል በፊት ይኸው ቤት ሲበረበር፡ አባቱም እጁን በካቴና ታሥሮ ሲወሰድ አይቷል:: ሰ ..... ዕድሜው ስድስት ዓመት ተመንፈቅ ነበር:: ክፍሉ ምስትልትሉ ወጣ፣ ትራሶችና ፍራሾች ተቀዳደዱ:: ከበርካሪዎቹ አንዱ መጻሕፍቱን ከመደርደሪያው ላይ እያወረደ፡ ' ከተማው ውስጥ መጽሐፍ አለመኖሩ እያስደንቅም! እናርኪስቶቹ እዚህ ደብቀዋቸዋል' ብሎ ጮኸ :: ሌላው ደግሞ መጽሐፍ መደርደሪያው እናት ላይ ቁሞ ጠመንጃ ወይም የሆነ የተደበቀ ሰንድ እጂ ላይ ይወድቅልኛል ብሎ በመገመት ኮርኒሱን በካራ ይቀድ ነበር:: 'የት እንዳለ አሳዩን!' እያሉ ጮሁብኝ:: ድምጼን ከፍ አድርጌ 'ከግድ ቤት ውጥቼ አላውቅም፣ እባካችሁ አትግደሉኝ፣...ወዘተ' እያልኩ ለመንኳቸው:: የእጋቾቼ ብሽቀት እየጨመረ መጣ:: ጥቂት ተጨማሪ ጥፊ አላሱኝና ወደ ማረፊያው ክፍል ገፈተሩኝ:: እዚያም ዓይነተኛዎቹ ሰዎች ሶፋዎቹ ላይ ተቀምጠው አየሁ:: የቴሌፎን መሥመሩ እንደተላቀቀ ማየት እችል ነበር:: በበረንዳው በኩል የማረፊያ ቤቱ በር ተበረገደና ወዲያውም የከፍተኛ ፪ ቀበሌ ፲ አብዮታዊ ዘብ ሊቀ መንበርና የአሳሹ ቡድን ምክትል አዛዡ ገቡ:: አየር

ወለድ ውስጥ የቀድሞ ባለ ሌላ ማዕረግ የነበረ፡ እሳት የሚተፋ ድራጎን ብጤ ሰው በቀጥታ ወደኔ ተወረወረና ባንድ እጁ ጉሮሮዬን እንቀኝ::፡ በሌላው ፀጉሬን ጨመደደኝ:: ከዚያም ብድግ አድርጎ ተሸከመኝና ቅድም ውጭ ሁኜ ወደ ውስጥ እመለከተው ከነበረው ክፍል ወሰደኝ::

'እንኝ _____ ! ልክ እዚያ ፍግም እንዳለችው እንደዚያች ውሻ ጓደኛሽ ቀይ ሽብር ልናፋፍምብሽ ነው' ብሎ ደነፋ::

ወደ ጥግ ስመለከት ባልቴቷ ወለሉ ላይ ቁጭ ብለው ጭናቸው ላይ እረፋ፡ የሚደፍቀውን የመ .....ን የተገመደ ሰውነት ታቅፈው እየታቸው:: እንዚያ ደደቦች እንዳሰቡት ሳይሆን የልብ መታወክ እንዳልነበራት ባለቴቷ አሳምረው አውቀዋል:: እኔም መ..... እንገቷ ላይ ከተንጠለጠለው ከታብ ውስጥ የምታኖረውን የመርዝ እንክብል (ሳይናይድ) እንደዋጠች አውቄያለሁ:: ቱጥር እንደሌላቸው ሌሎች ጓደኞቿ ሁሉ መ.....ም ተንዘፈዘፈችና ሞት እያሸለባት ጸጥ ስትል እየተመለከትኩ ሳለ ባልቴቷ ሙቷቸውን እያንጉራጌሩ በሞት ድምፅ ዋይ አሉ::

መ ..... ለእምነቷ የቆመች የተባች ታጋይ ነበረች ማለት እችላለሁ:: ዩኒቨርሲቲ በነበረችበት ጊዜ፡ ምንም እንኳ በዚያ ጊዜ ብዙ ሴቶች የተማሪውን እንቅስቃሴ ባይደግፉም እሷ ግን ድጋፍም የተባ ተሳትፎም ነበራት:: በየካቲቱ አብዮት ወቅት በሴቶች ሠራተኞች ውስጥ ምስጢራዊ ሕዋሳትን በማደራጀት ተግባር ውስጥ ትሣተፍ ነበር:: ደርግ ሥልጣን ከያዘም በኋላ በዚሁ ተልዕኮ ቀጥላለች:: ለወታደራዊው መንግሥት የነበራት ተቃውሞ ፍጹም ሲሆን የግል ተመክሮዋም ይበልጥ ጥላቻን እንድታተርፍ ፡ ንቃትን እንድትጨምር አድርጎታል:: ለመጀመሪያ ጊዜ መ ..... ን ያገኘኋት የነበሪ ኑሮ ውስጥ ገብታ እንድ ጓደኛ ቤት አሥራ አራት ዓመት ዕድሜ ከነበራት እኅቷ ጋራ ሁና ነበር:: ይህች ትንሽ እኅቷ በመስከረም ፲፱፻፷፰ በተደረገ ሰለማዊ ሠልፍ ላይ ተይዛ በእንድ የእሥር ቤት ዘበኛ ተደፍራለች:: ይህችን ልጅ ከመ .....ጋራ ሳያት ገና ድሮ የአራት ወር ፅንስ ይዛ፡ ትልቅ እኅቷን ' እንድ ነገር' እንድታደርግ እየንዘነዘቻት ነበር::

እናታቸው ሐረር ለሕክምና ሂደው በአጋዴን ጦርነት ምክንያት መጓጓዣ አጥተው እዚያው ቀርተዋል። ወንድማቸው ደግሞ 'እናርኪስት' ተብሎ ታሥሯል። በርግጥ ሙ .....ወታደራዊውን መንግሥትና የቆመበትንም ዓላማ ለመጥላት በቂ ምክንያት ነበራት። እነዚያ ደደቦች፥ በሥቃይዋ እየተደሰቱ በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ስትሞት ማየት ልቤን ቆሳው። አጋቼም ከክፍሉ ውስጥ ጉትቶ አወጣኝ።

በኔም በዘር ማንዘሬም ላይ ፀያፍ ስድብ እያወረደብኝ ከቤት አውጥቶ ቁሻሻና ስብርባሪ በተመላበት ጣባብ መተላለፊያ ውስጥ ጉተተኝ። የጠርሙስ ስብርባሪም የውስጥ እግሬን ይቀዳድደው ገባ። አልፎ አልፎም ይህ አውሬ የሆነ ሰው ሊደበድበኝና ሆዴ ላይም ጹብ ጹብ ሊልብኝ ቆም ይላል። ጉረሮዬንም ረግጦ ይዞ ለመግደል ያስፈራራኝ ነበር። ደሜ እየፈሰሰ፥ ህመሙም እየበረታብኝ እንምሮዬን ወደመሳቱ ደርሼ ነበር። የ እንድ መቶ ሜትር ርቀት ያህል እንደሄድን አስፋልት ከተነጠፈው መንገድ ላይ ደረስን። እዚያም የአላሽ ቡድኑ አዛዥ መሪውን ይዞ የተቀመጠባት የቀይ ሽብሩ ቮልክስ ቫገን መኪና (የሠሌዳ ቁጥሯ 9502 አ አ) ቁማ ነበር። አዛዡ ከመኪናዋ ወርዶ የኋላ በሩን ከከፈተ በኋላ የውኃ ቀለም መልክ ያለው የቀይ ሽብር ሠሌዳና ጥቂት ታሳላት ምሸግሮች ለምክትሉ አቀበለው። ድኃ ስለመሆኔ ደንቆሮ፥ ገረድ ስለመሆኔ፥ ያች የሚፈልጓት በቶታል ቤንዚን ማደያ መንገድ አድርጋ መሄዷን የሚገልጸውን ትኑት ምልኛዬን (ሊጦኔን) በመድገም በጉልበቴ ተንበረከኩና ለመንኳቸው። ምክትሉ ከመንገዱ ባሻገር ወደነበረው ትንሽ ሣርማ ቦታ ጉትቶ አሻገረኝና ወደመሬት ከገፈተረኝ በኋላ ክላሺንኮቭ መሣሪያውን አቀባበለ። እኔም የመጨረሻዋ ሰአት መሰለችኝና የመታዩይ ስድብ ልወረውርበት ካሰብኩ በኋላ እንደምንም ተገታሁና የተለመደውን ትሁት ልመናዬን ደገምኩ። አልባሌዎቹን ቃላት ሰመጨረሻዪቱ ጊዜ ቈጠብኳቸው። በጣም ረጅም ጊዜ መስሎኝ ከነበረው፥ በተጨባጭ ከአንድ ደቂቃ ከማይበልጥ ጊዜ በኋላ እንደገና ሆዴ ላይ ረገጠኝና እንድንሣ አዘዘኝ። ያ እርግጫ ከቶውንም አልተሰማኝም።

ደብዘዝ ያለ ብርሃን ወደሚታይበት ሰርጥ መንገድ ሲጉትተኝ ጊዜ የመድፈር ሐሣብ የነበረው መስሎኝ ነበር፥ ግን ተሳስቻለሁ። ከጥቂት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ 'ማ ነህ በዚህ የምትሄድ?' እያሉ በመርሣህ ጠመንጃቸውን ባቀባበሉ ሰዎች እንድንቆም ተገደድን። እኔን የሚያሠቃየው ሰውዬ የይለፍ ቃል ነገራቸውና እንድቀጥል ተፈቀደልን። በድምድማቱ ላይ የብርጭቆና የጠርሙስ ስባሪ በሲሚንቶ ተጠናክሮ ተትረፍርፎ የተተከለበት ረጅም የግንብ አጥር ካለው በአቅራቢያው ከሚገኝ ትልቅ ቅጽር ግቢ መሰዳኝ። ሕንፃው በአንድ የንግድ ቡድን የተመሠረተ ማኅበር የግል ማኅበራዊ ክበብ እንደነበር አውቃለሁ። በግቢው ውስጥም በውጭም ብዙ የታጠቁ ሰዎች ነበሩ። የተወሰኑት ደማቅ ብርሃን ወደ በራበት ትልቅ አዳራሽ አጀቡን።

ትልቁ አዳራሽ እንደገባን፥ ዓይኖች በሙሉ.....ከሦስት መቶ ጥንድ የሚበልጡ ወደኛ ዞሩ፥ እንድ፥ አለንጋ የያዘ ሰው የቀይ ሽብር አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት (ቀሽአኮ) ወደተቀመጡባቸው ሁለት ሞላላ ጠረጴዛዎች እናልፍ ዘንድ መንገድ እንዲለቁልን በተጣበበው የሲሚንቶ ወለል ላይ ተንቆራጥጠው የተቀመጡትን ወጣቶች ሸንቈጣቸው። በአንጻራዊ መንገድ ሲታይ በጣም ያለተጣበበ ጥቂት ሜትር ካሬ ቦታ ነበረ። ምክንያትም እንደነበረው አየሁ። ቀረብ እንዳልኩ የማውቀውና በአካባቢው የአንድ ቀበሌ የተመረጠ ፀሐፊ የነበረ ሰሎሞን የተባለ ወጣት ግበረ ሰይል እየተፈጸመበት ነበር። ተንጠልጥሎ በመገረፍ ላይ ነበር። ግበረ ሰይል ፈጻሚው ሲያየኝ መደብደቡን አቆመ። አዲስ ሰለባ ተገኘና ፥ ከአጃቢዎቹ አንዱ ሆን ብሎ ጠለፈኝና ግበረ ሰይል ፈጻሚው አጠገብ ስወድቅ፥ ሰሆነ ሠልፍ ራሱን የሚያሟሙቅ ይመስል ባለፈሮ የሆነውን የወታደር ጫማ በማንሣት የእጅ ጣቶቼ ላይ አሳረፈው። አንድ ሰው ለቀሽአኮ ሊቀ መንበር መታወቂያ ወረቀቴን እቀበለውና ስሜን እንኳ ከመጥራቱ በፊት 'ምንም የማላውቅ ገረድና በቶታል መንገድ አድርጋ ሄደች ' የሚለው ዝብዝብ ውስጥ ገባሁ። 'እዮረኝ ልወድቅ ነው' አልኩና ተዝለፈለፍኩ። ድካም እንደተሰማው የሚነበብበት ሊቀመንበርም 'ይህችን ደንቆሮ ገረድ አስወግዱልኝ' እንደማለት ዓይነት ጥላቻ በተመላበት መንገድ በእጁ ምልክት ሰጠ። ወለሉ ላይ ወርውረው ጣሉኝና ከፉኛ የተጉዳ ሰው የሚሆነውን በመምሰል ለሰስ ባለ ድምፅ እቃትት ጀመር።

ዓይኖቼን ስከፍት፥ ከዚያው ከተጋደምኩበት የለመድኩትን የወይዘሮ ጽጌን ቀሚስና መልክ አየሁ።

እሳቸው እነባቢያቸው በሚኖረው ሕዝብ በማም ተወዳጅ ከመሆናቸው የተነሣ በተደጋጋሚ ጊዜ የቀበሌ ሊቀመንበር ሁነው የተመረጡ ፱፩ ዓመት ዕድሜ ያሳቸው ባልቴት ታጋይ ናቸው። ያውቁኛል። እሳቸው ቤት በርከት ያሉ ጎበዕ ስብሰባዎች አድርገን ስለነበር ስለእንቅስቃሴያችን ያውቃሉ። አንድ ዓይነት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሁለታችንም እንደማንገኝ ሁሉ፥ ለኔ ሐዘን ተሰምቷቸው በሐዘኔታ መልክ ወደኔ እየተመለከቱ ነበር። በኋላ እንደሰማሁት እዚያ አዳራሽ ውስጥ በተሰበሰቡት አሥረኞች ሁሉ ፊት ግብረ ሰይል ተፈጽሞባቸው ያወጡት እንዳችም ነገር አልነበረም ::

የመኢሠማ ወኪል የነበረው ሞላ (ጌታቸውም በሚባል የሚታወቅ) የተባለው የለየለት ነፍሰ ገዳይ ወደባልቴቷ ቀርቦ እንዲነሡ አዘዛቸው።

'በዚህች አሮጊት ውሻ አናርኪስት ላይና በእምሥት ሌሎች ላይ ቀይ ሽብር ሳፋፍም ነው ' ብሎ ተንጨረጨረ። አምስት ሌሎች አሥረኞችን በኔሊብ መረጠና ይዟቸው ወጣ። ይሆን ጊዜ ከጠዋቱ ፲፩ ሰአት ሁኗል። አብዛኞቹ አሥረኞች በ፲ __ ፲፩ ዕድሜ ክልል ውስጥ እንደነበሩ ተመለከትኩ፣ ሁኖም ዕድሜያቸው ከአስር ዓመት በታች እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ቁጥራቸው የማይናቅ አሥረኞችም ነበሩ።

ጠዋት ዘበኞቹ የተኙትን የሚያሥነሱት በአሥረኞቹ ውስጥ እየተረማመዱ በመርሀና እያንዳንዱን በመግረፍ ነበር። ሞላም 'እነዚያን ስድስት አናርኪዎች በእንዲት ጥይት መግደል ነበረብኝ፣ በነሱ ላይ ስድስት ጥይቶች ማጥፋቴ ያሳዝነኛል፣' ብሎ እየጮኸ በተንቀባረረ አረማመዱ ዘው ብሎ ገባ። ከዚያም ኤኬ 47 ን ወደኛ አንጣጠረና ምላውን ሳበ። ጠመንጃው ቀጭታ እንዳሰማ ባሳየነው ፍርሐትና ራሳችንንም ለመቅበር ባደረግነው ቅጽበታዊ ሙከራ ዘበኞቹ በሣቅ ፈነዱ። ቀሽእኮዎች እሁን ወደዳር ወጡና መድረኩ እንደ ንግርታ፥ ግደይ፥ አሠፋና ጀጄአላ በመሳሰሉት ተያዘ። እነዚህ የቀድሞ የኢሕአፓ አበላት የነበሩና 'የአብዮቱን ካምፕ' በመቀላቀል 'ራሳቸውን የለወጡ' ናቸው፣ ተባለ።

ግደይ ሽሚዙን አወለቀና ገና ያልጠገገውን የግብረ ሰይል ጭስሉን ሲያሳየን፥ ማርታ ደግሞ ቤል በተም ሱሪዋን ከፍ አድርጋ ሰንበሮች የተጋደሙበትን እግሮቿን አሳየችን።

አሠሩ ድምፅ ማጉያ በመጠቀም (ምንም እንኳ አስፈላጊ ባይሆንም) ' እንደናንተው አናርኪዎች ነበርን፣ በዲሞክራሲያ ተታለን ነበርን። ይህ ሁሉ ቀሀል የደረሰብን በሽንቱ ነበር፣ አትሞኙ፣ አብዮቱን ተቀላቀሉ' ብሎ እኛ ላይ አምባረቀብን። ከሃዲዎቹ ተራ በተራ ከመናገራቸውም በላይ ኢሕአፓ ያዋጠንን የ 'ዲሲፕሊን ኪኒን'- እንድናስታውከው አስጠነቀቁን። አድማው ጥያቄ እንዲጠይቅ ቢገፋፉም ማንም ለመድፈር አልሞከረም።

'ዝም ማለት ራሱ የዲሞ ኪኒን' እንደዋጣችሁ የሚያሳይ ምልክት ነው፣ ' ብሎ ካስተባባሪዎቹ አንዱ ጮኀ። አንዱ ወጣት ልጅ በ 'እናሸንፋለን' ና በ 'እናቸንፋለን' መካከል ልዩነቱ ምን ነበር ብሎ በመጠየቅ ፀጥታውን ገሠሰው። (18) ሌላ ልጃገረድ ደግሞ (ዲሞ ወይም ኢሕአፓ ለምን በሴት አንቀጽ እንደሚጠሩ ጠየቀች። ይህ ለጥቂት ጊዜ ቀጠለና ራሳችንን ሌሎችንም 'ለማጋለጥ' ጊዜ እንድናገኝ አረፍት ተሰጠን።

ለራስ ማጋለጡ ጥሪው ሲደረግ እንደገና ፍጹም ፀጥታ ሆነ። ሞላ በንዴት ተቃጠለ። ' ራሳችሁን ማጋለጥ ብትጀምሩ ይሻላችኋል፣ ያለበለዚያ በሁላችሁም ላይ ቀይ ሽብር አፋፍምባችኋለሁ!' ብሎ ጮኸ። እዚህ ላይ ጠቅሼ ማለፍ ያለብኝ እኔ ፎርም እንድሞላ ባይሰጠኝም ሌሎቹ አሥረኞች አሥር ላይ በዋለሱበት በመጀመሪያው ቀን ስምንት ጥያቄዎች የያዘ ፎርም ሞልተዋሉ። ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፣ ስም፥ አድራሻ፥ ምስጢራዊ ስም፥ ማን መለመለህ? ማንን መለመልክ? ከኢሕአፓ ሥራቶች (ድርጅቶች) አንተ የየትኛው አባል ነህ? (ወጣት ሊግ፥ ፓርቲ፥ የሌቶች ድርጅት፥ ኢላአማ፥ዲሞክራሲያዊ ግንባር ....ወዘተ) ና በእጅህ የሚገኙ ዕቃዎች ወይም ሰነዶች፥ ወይም ደግሞ የተደበቀበትን ቦታ የምታውቀው?

አንዳንዶቹ ካድሬዎች የተሞሉትን ፎርሞች እየተመለከቱ መረጃዎቹን ወደ ሌላ ትልቅ ሠንጠረዥ ላይ በመሙላት ተጠምደው ነበር። ሞላን ትእግሥቱን ወረሱበትና ጥቂት ፎርሞች ብድግ አድርጎ "እያንዳንዳችሁን እጠራለሁ፣ መልሶቻችሁ ትክክል መሆን አለባቸው፣ ካልሆኑ ግርፋትና ቀይ ሽብር ነው የሚከተላችሁ፣" አለ። በእውነቱ ችግሩ ማነው የመለመለህ የሚለው ጥያቄ ላይ ነበር።

የሞቱትን ወይም ጎቡዕ ኑሮ ውስጥ የገቡትን፣ ወይም ደግሞ ገጠር የወጡትን ስሞች ከሰጠህ÷ ዕርቃንህን ተደርገህ ግበረ ሰይል ትቀበላለህ። " የ"ዲሞ"ን ልንይዛቸው የማንችላቸውን ሰዎች ስም የመስጠትን መላ እናውቀዋለን ፤" ይሉሃል ። አዳራሹ ውስጥ ካለው ሰው ስም ብትሰጥ የሞላው ፎርም ይወጣና ይነጻጸራል ። መልሶቹ ካልተመሳሰሉ ÷ ሁለቱ እርስ በርሳቸው ÷ አንዱ ባንዱ ላይ ግበረ ሰይል እንዲፈጽም ፡ ይደረጋሉ ። ያልተያዘ ሰው ከጠቂምከ ወራሪ ቡድን መርተህ የጠቃምከው ሰው ወደተደበቀበት ቦታ እንድትወስድ ትጠየቃለህ ።

ግብረ ሰይሉ የሚፈጽመው እዚያው ሁሉም እሥረኛ በተሰበሰበበት ነበር ። እሥረኛው እስከ ሙታንታው ድረስ እንዲያወልቅ ይደረግና ጉልበቱን ወደ ደረቱ ሰብስቦ ÷ እጆቹን ወደ ቁርጭምጭሚቱ ዘርግቶ እንዲቀመጥ ይደረጋል ። ከዚያም እጆቹና እግሮቹ በፕላስቲክ ገመድ ጠብቀው ይታሠራሉ ። ጠግማ ዘንዘና ብጤ ወይም የሆነ እንጨት በታጠፉት ጉልበቶቹና በተዘረጉት እጆቹ መካከል ይከተታል ። ሁለቱ የዘንዘና ወይም የእንጨት ጫፎች በሁለት ሬዳቶች ብድግ ይደረጉና ሁለት ወምበሮች ላይ ይቀመጣሉ እንደ ግብረ ሰይል ፈጻሚው ውቃቢ በሮቲሰሪ ሽቦ ላይ ተሸብልላ አስፈላጊውን ማጣፈጪያ እቃምመው ያደርጉበት ዘንድ እንደሚያሽከረክሯት ደሮ እሥረኛውም በዚሁ መንገድ እንዲንቀሳቀስ ይሆናል በዚህ ሁኔታ (እሥረኛው) ለልዩ ልዩ የግብረ ሰይል ዓይነት ይዳረጋል ። የሸብሩ ዓዝ ግሳንግስ የሚከተሉትን ያጠቃልላል ፤ አለንጋዎች÷ ልዩ ልዩ ቅርጽና መጠን ያሳቸው ዱላዎች ÷ ሁሉ ዓይነት መጠን ያሳቸው የፕላስቲክ ገመዶች ÷ ከባድ የብረት ዘለበት ያሳቸው ቀበቶዎች ÷ ከትልቅ መኪና ወይም ከትራክተር ጎማ ተቀድደው የወጡ ረጃጅም የጎማ ቁራጮች ጎራዴዎችና ካራዎች ÷ ክብረት ÷ የሲጋራ መለኮሻ ÷ የፕላስቲክ ከረጢቶችና÷ የቆሸሹ የእግር ሹራቦች (ካልሲዎች) ። ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹ በሰው ገላ ላይ የሚመርጧቸው ተወዳጅ ሥፍራዎች ÷ የውስጥ እግር ÷ ብብት ÷ የጀርባ አጥንት ÷ ጡትና የጡት ውልብልቢት (ጫፍ) ÷ ጭን ....መዘተ ነበሩ ።

አካላዊ ግበረ ሰይሉ ደግሞ በአእምሯዊ ግበረ ሰይል የተደገፈ ነበር ። እንቅልፍ መንሣት ÷ ሳያሠልሱ ማስፈራራት ÷ የፈዝ ርሽናዎች ÷እስገድዶ መፈክር

ማስለፍለፍ ÷.....ይሄ ከግብረ ሰይሉ ጋር ደም ያሰረበ አስተርዕዮ ነበር ። ሌሎቹ ÷ ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹን እያሞገሡ ሲዘፍኑ ÷ (የሥቃይ እበጋዞቹ) እኒያ ደደቦች ሲስቁም ሲናደዱም ÷ ጠመንጃዎች ሲያቀባብሉ ÷ ሲያንጣጥሩ ÷ አለንጋዎች በአየር ላይ እያፏጩ ያጋጠማቸው ላይ ሲያርፉ ÷ የፈረደባቸው ዳግመኛ በሕይወት ላይታቱ በአሊብ እየተለቀሙ ሲወሰዱ÷ _____ምንም እንኳ ሰርሸና ከወጡት እንጻንዶቹ ዘመዶቻቸው ለቀሽአኮ ብዙ ሺህ ብር ከፍለው በድብቅ እንዳስፈቷቸው የደረስንበት ቢሆንም ።

ካድሬዎቹ ያስሞሉትን ፎርም በመጠቀም የኢሕአፓ ድርጅታዊ መዋቅሮችን ይዘዋል ያሏቸውን ሰባት ሠንጠረዦች አበጁ። እያንዳንዱ ትልቅ ሠንጠረዥ በተሰያዩ መዋቅሮች ውስጥ ማ ምን እንደሆነ አሥፍሮ የያዘ መሆኑ ነበር። በግብረ ሰይል የተገኘው እያንዳንዱ መረጃ ሠንጠረዡ ውስጥ ይታከል ነበር። በተጨማሪም ካድሬዎቹ እንደነዚህ ካሉ የዚህ ዓይነት ሠንጠረዥ ካሳቸው ሌሎች የእሥረኛ ማቆያ (ሙዓል) ማዕከላት ጋር በስልክ በመነጋገር መረጃ ይለዋወጡ ነበር ።

የግብረ ሰይሉ ከንዋኔ ÷ የአጋልጡ ማታለያ ÷ ቀኑን ሙሉ ያካሂዳል ። ዕረፍት የምናገኘው ለምግብና ለሽንት ስንወጣ ብቻ ነበር ። አዳራሹ ውስጥ የነበረው የአዳት ሁኔታ የሽንት ቤቱን ያህል የከፋ ነበር።

ቤተ ዘመዶች ናቸው ምግብ የሚያቀብሉት ። ታዲያ ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹ መጠኑ በዛ ያለ ምግብ እንዲመጣ ያስደርጉና የተሻለውን መርጠው ለራሳቸው ይበሳሉ። ባጠቃላይ ሁሉም ተዳምረው ÷ አስተዳዳሪዎች ÷ ዘበኞች ÷ ግበረ ሰይል ፈጻሚዎችና ካድሬዎች እንዲሁም የቀሽአኮ አባላት ጅ ይሆኑ ነበር ። ምንም እንኳ እሥረኞቹን ባጠቃላይ ፍርሓት ጨምድዶ የያዛቸው ቢሆንም እንጻንዶች ÷ ወሮበሎቹ ምግብና ሲጋራ ላይ (ያውም ከገዛ ዘመዶቻቸው የመጣ) ለቀቅ ሲሉላቸው በማየትና ጊዜ ሰጥተውም ከሴት እሥረኞች ጋር ሲዳሩ በመመልከታቸው የተታለሉና ÷ የተሳሳተ የደኅንነት ስሜት የአሳደሩ ነበሩ ። እንጻንድ የሴት እሥረኞች ሕይወታቸውን ለማጻን ራሳቸውን ሲያዋርዱ÷ እንጻንዶች ደግሞ እዚያው አዳራሹ ውስጥ ነገር አቀባዮች ይሆኑ ነበር ። ያም ሁኖ ብዙዎች በአሊብ እየተወሰዱ

ይገደላሉ ፤ እንዳንድ ጊዜም በፍትወታዊ ችርታቸው በተደሰተው በዚያው ሰው ግድያው ይፈጸምባቸዋል :: ከዘመዶቻቸው ለእሥረኞች የሚመጣውን ሲጋራ በሚመለከት ካድሬዎቹ እንዲህ እያሉ ያፈዙ ነበር ፤ " አብዮቱ ነጻ አውጥቷችኋል ! ተደብቃችሁ ማጤስ ቀርቶላችኋል ፤ አሁን ዘመዶቻችሁ እንደምታጤሱ አውቀው ሲጋራ ይገዙላችኋል::"

ሳሆኖቹ ከወጡ በኋላ ሞላ እንደገና እየጤሰና እየማለ እየተገዘተ በርግዶ ገባና "እናንት ቁሻሻ አናርኪስቶች ወደ እናት አብዮት ተመልሰናል እያላችሁ እስካሁን ስታታልሉን ነበር ፥ እናንት የናት ጡት ነካሽ ውለታ ቢሶች ! በቴርሞስ ፍላስክ ውስጥ ከትታችሁ ውጭ ላሉት አናርኪስት ጓደኞቻችሁ የጻፉችሁትን የምስጢር መልእክት ደርሰንበታል :: ከናንተ አምስታችሁ እንዳላችሁበት እናውቃለንና አውጡ!" አለ:: ራሳችንን ለማጋለጥ አምስት ደቂቃ ሰጠን፤ ሰአቱን አውጣና በጣቶቹ ደቂቃዎቹን መቃጠር ጀመረ :: ጠቅላላው ነገር የሞላና የጓደኞቹ ፈጠራ ነበርና ማንም ራሱንም ሆን ሌላ ለማጋለጥ የተነሣ አልነበረም:: የሞላ የደቂቃ ቁጠራ ዜሮ ላይ አቁልቁሎ ደረሰ :: አምስት ሰዎች ጠራና አምስቱ ተቃውሟቸውን እያሰሙ ወደ ውጭ ተወሰዱ :: በኋላ እንዱ ፒኛማ ከለበሰ፥ የወጣቱ ልጅ አባት ነው ብለን ከጠረጠርነው ሽምገል ካለ ሰው ጋር ተመለሰ:: ከሞላ ጋር የወጣው የልጁን ሕይወት በማትረፉ ምክንያት ስለ ገንዘብ ክፍያ ለመነጋገር እንደነበር ጥርጥር የለውም ::ምናልባትም ገድለውትም ይሆናል፤_____አላውቅም ::

አዳዲስ እሥረኞችን በየደቂቃው ወይም በየሰአቱ እያመጡ ነበር :: አዳዲሶች ሲመጡ የሚያውቋቸው ወይም ያጋለጧቸው እንዲቀርቡ ይደረግና እንዲቀበላቸውና እንዲያወጡም እንዲያግባቧቸው ይደረጋል :: ከካድሬዎቹ እንዱ፥ እንግዳ የተባለው አራት እሥረኞች አመጣና ሁለቱን ይዞ ወደኔ ቀረበ :: "እነዚህን ሁለት አናርኪስቶች እንዲያወጡ አሳምኖቸው፤ አለበለዚያ ሁላችሁም ለቀይ ሽብር ትዳረጋላችሁ !" አለ ::አዲስ መጠቹን ያጋለጡት ሁለት እሥረኞች ሁለቱን ለማሳመን ቀጠሉ :: ይህ ሁሉ ሲሆን የግብር ሰይሉ መፈጸሚያ ዓውድ ሥራ አልፈታም :: ከሌሊቱ 7 ሰአት አካባቢ ወንዶቹ ባንድ ወገን ፥ ሴቶቹ በሌላው ሁነን እንድንተኛ ተፈቀደልን :: እንደሚጠበቀው

ሴቶቹ የተኙበት ቦታ በዘበኞችና በካድሬዎች ተጎብኝቶ ነበር::

ማክሰኞ በማለዳው በደንጊያ ከተገነባው እጥር ውጭ ብዙ ግርግር ታየ :: ከተለመደው የቤተሰብ ጉብኚ ቀጥር በላይ መሆኑ ግልጽ የሆነ ሕዝብ ከመንገዱ ባሻገር ባለው፥ የእጥሩን ግረጌ ባክበበው ደፍ ላይ ለመቆም እየተጋፋና እየተገፋተረ ነበር :: ልንሰማው የቻልነው የዘበኞችን ጮክ ያለ ድምፅና የሴቶችን የሰለለ ድምፅ ብቻ ነበር :: ከቀይ ሽብሩ ኮሚቴ አባላት አንዱ ገባና ለከፍተኛው የእሥረኞች ማቆያ ካምፕ ስለሁኔታው ለማስረዳት ስልክ ደወለ :: ተጨማሪ ዘበኞች ጠየቀ ፤ ተጨማሪ የመከላከያ መሰናክሎችንም እንደሚያደርግ ተናገረ:: ትንሽ ለማሸለብ ይሞክር የነበረው ሞላ ነቃና ' ልጆቻቸውን ያባልጉና የሚያማርሩ የአናርኪስቶች እናቶች ' ብሎ ከተበሳጨ በኋላ ሴቶቹን አካባቢውን ለቅቀው እንዲሄዱ ያለበለዚያ ' በራሳቸው ልጆች ላይ ቀይ ሽብር ሲፋፋም ' እንደሚያዩ እንዲነገራቸው ሌሎችን አዘዘ :: ረብሻው እሰከ ጠዋቱ አጋማሽ ቆየ :: ከዚያም ብዙ የተጠበቀው' ንቃተ ኅሊናን ከፍ የሚያደርገውና ከማንኛውም የአናርኪስት ጋጠአት የሚያጸዳው' መጣ:: እሱም ከደርግ ጋር አጋር ከሆኑት ድርጅቶች የአንዱ ካድሬ ነበር :: ስለ ኢሕአፓ ከሰረት ንግግር ካደረገልን በኋላ በንብረት የሚከተለውን ባለ አዝማች መዝሙር እንድንዘምር አደረገን::

ሰይ እሰይ ደስ ማለቱ ፥
ምንደኛ የኢሕአፓ ቅጠረኛ ትሮስካይቱ
በመንገድ ላይ ተዘርሮ ማየቱ
በቀይ ሽብር ተመትቶ መመልከቱ
እሰይ እሰይ ደስ ማለቱ!

(ካድሬው) ለመዝሙሩ ያሳይ የነበረውን ጽኑ ሰሜት እኛ የምንጋራው ባይሆንም ሁላችንም እስኪረካ ድረስ ደጋግመን ዘመርልንትና ኢሕአፓ እንዲት ' ትሮስካይት' እንደሆነ ወደ ማስረዳቱ ገባ::

ይሽውም በመካሄድ ላይ እያለ በላይ በላዩ ተጨማሪ እሥረኞች እየመጡ ነበር ::በነሱ ዓይን ሲታዩ እነ ሞላን ጉና ጀግሬዎች የሚያስመስሉ፥ ሁሉም የመግደል ሰብ

የተጠናወታቸው እነ እረገጤ መድበው ÷ ሰሙ ንጉሥ ÷ ቀልቤሳና ዓለማየሁ ÷ ለየት ያለ የእሥረኛ ስብስብ ይዘው መጡ :: እሥረኛን ሠገራ ውስጥ ማጥለቅ የሚያፈቅረው የግብረ ሰይል ዘዴ የነበረው የከፍተኛ ፲፬ ዓለማየሁ እንዲያውም ለመንግሥትም እንኳ አሳሳቢ ስለሆነ በ፲፱፻፫ ዓ.ም.ተረሽኗል::

እነዚህ ጭካኔ ያንበራቸው አረመኔዎች እንደ ግል ሥራቸው አድርገው የተፈለጉ ሰዎችን መታወቂያ ለማረጋገጥ ከአንድ እሥር ቤት ወደ አንዱ ይዘዋወሩ ነበር :: አዳራሹ ውስጥ ካመጡት እሥረኞች አንዱ ራሱን ለማጋለጥና ኢሕአፓ ላይ እርግማኑን ለመቁለል መድረኩ ላይ ወጣ:: አቀራረቡ በጣም ስላስደሰታቸው ከነሱ ጋር መልሰው ሊወስዱት ፈለጉ :: ነገር ግን የሞላ ጓደኞች የተያዘው በራሳቸው አካባቢ መሆኑን በመግለጽ አንስተዋም አሉ:: የተሟሟቀ ጭቅጭቅ በወረበሎቹ መካከል ተነሣና ሞላ ራሱ ወጣቱን ለነ እርገጤ ሲያስረክብ ነገሩ በረደ ::ይህም÷ ከደርግ ጋር ባበሩት በተለያዩ ድርጅቶች መካከል ከሃዲዎችን ወደራሳቸው ድርጅት ለመመልመል ያደርጉት የነበረው የተፋፋመ ውድድር ነጸብራቅ እንደነበር እናውቅ ነበር ::

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ተለይቼ እንዳልታወቅ ለማድረግ በመሞከር የተለያዩ ጥጎች እየያዝኩ ነበር:: ማንም ሰው ምግብ ስላላመጣልኝ ማንም ምንም ስላልሰጠኝ ርቦኝ ነበር :: ላለመታወቅ እንድሞክር በተጨማሪም የገፋፋኝ እሥራ ከነበረበት ሚኒስቴር ውስጥ ያውቁኝ የነበረውን ይኸና አምላክ የተባለውን ከቀበሌ ዘበኞች አንዱን ለመለየት በመቻሌ ነበር:: ይኸና የቢሮ ዘበኛ የነበረ ሲሆን እዚያ ሚኒስቴር መቤት ውስጥ እሱን ቤት ጠራጊዎችንና ተሳላኪዎችን ለተሻለ የደሞዝ ክፍያና የሥራ ሁኔታ ለመታገል እንዲችሉ ልናደራጃቸው ሞክረን ነበር :: ሁኖም በኋላ የቀበሌው ሥራ የተሻለ ገንዘብ የሚያስገኝ ሁኖ አገኘው:: ወራሪዎቹን ወደ ቤታችን እምጥታቸው ከነበሩት እንዲ ነገር አቀባይ ጠጋ አለችኝና እቤታችን መጥቶ 'አናርኪስት ልጃገረዶችን' ለመገናኘት ይመጣ የነበረው አዳራሹ ውስጥ ካሉት ወጣቶች አንዱ እንደሆነ አድርጌ እንዳጋልጥ መከረችኝ :: ከማድ ቤት የመጣሁበት ጊዜ እነስተኛ ነው ፤ ግን እንጀራ እወስድላቸው የነበር የሁለት ልጃገረዶች ቤት አውቃለሁ አልኳት :: በጣም ተፍነከነከችና

የሚወር ቡድን ለማደራጀት ሞክረች፡ ግን ልክ በዚያን ጊዜ ይበልጥ የሚያስመረቅን 'ሚሳይ' ተገኘ መሰለኝ ወደ ሌላ ሄደች :: የጠቀሰኩት ቤት ባዶ ሲሆን ዕቅዱም ከተቻለ ለማምለጥ÷ ያም ካልሆነ 'ታማኝነቴን' ለማሳየት ነበር ::

ከምላ በኋላ በኢላአማ አባልነት የተጠረጠሩ ጥቂት ሠራተኞችን አመጡ :: ግበረ ሰይል ፈጻሚው ወደ አዳራሹ ያመጣኝ ታደሰ የተባለው የቀድሞ አየር ወለድ አባል የነበረው ነበር:: እንድ በእንድ በእሠቃቂ ሁኔታ ግበረ ሰይል ፈጸመባቸው:: እንዳንድ ጊዜ የትንፋሽ ቧንቧዎቻቸው ላይ ይረግጣቸውና እእምሯቸውን እንዲስቱ ያደርጋል፤ ደግሞ ትንፋሻቸው እንዲመለስ ያደርግና መልሶ ይረግጣቸዋል:: ግበረ ሰይሉ በሚካሄድበት ጊዜ ባቅራቢያው ትንፋሻቸው እንዲመለስ ያደርግና መልሶ ይረግጣቸዋል:: ግበረ ሰይሉ በሚካሄድበት ጊዜ በአቅራቢያው ከሚገኘው ሆቴል ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች መጥተው እንዲመለከቱ ተደርጎ ያዩትን ለ'መሐል ሠፋሪዎች' እንዲናገሩ ተነገራቸው ::

ከእራት በኋላም የተለመደው ሽብር ቀጠለ ....እጅ እግር እንደ ብራና ተወጥሮ ቁም ስቅል የሚታይበት የግብረ ሰይል መሣሪያ ሥራ ያለፈታ ሲሆን ÷ 'እዚህም አዳራሽ ውስጥ እንኳ እባላት የሚመስምሉ ቢያንስ አምስት አናርኪስቶች እንዳሉ ስለደረስንበት ' በሚል ራሳችሁን እንደገና አጋልጡ ተባልን :: ሁለት ወጣቶች ግብረ ሰይል የተቀበሉትን የአንዳንዶቹን ወኔ እንድቀን ተወያይተን ነበር ሲሉ ራሳቸውን አጋለጡ :: ከዚያም የሽብር መልእክተኞቹ የሰም ዝርዝር አነበቡ :: ባጠቃላይ የአስራ አምስት እሥረኞች ሰም:: እነዚሁ የተጠሩ ሰዎች በሠልፍ እንዲቆሙ ተደረገና 'ጠቃሚ ዕቃዎቻቸውን ' አዳራሹ ውስጥ ላሉ ዘመዶቻቸው እንዲያስረክቡ አዘዟቸው :: ከዚያም በታጠቁ ዘበኞች ታጅበው ወደ ውጭ ተወሰዱ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ከነሱ ከማማሸ በታች ያሀሉን መለይቸውና እንድንተኛ ተፈቀደልን::

ከሌሊቱ ፱ ሰአት ላይ ደብዘዝ ያለው መብራት ሙሉ በሙሉ ቦማ እንዲል ተደርጎ ÷ እየተሬገጥንና እየተገረፍን ተቀሰቀስን :: ጥቁር መነጽር አድርገው ÷ ፊታቸውን በግለክ (ski masks ሸፍነው የታጠቁ ሰዎች ÷ እነ እረገጤ ÷ ቀልቤሳና ዓለማየሁ ገቡ :: በአሊብ እሥረኞችን እየለቀሙ

በመካከላችን ወዲያ ወዲህ አሉ ። ልጆች ሳይቀሩ ተለቀሙ ። የተመረጡት በሙሉ የነዚያ አራዊት የሆኑ ነፍሰ ገዳዮችን የማድያ ሱስ ለማርካት ተወሰዱ።

ረቡዕ ጠዋት ለመጀመሪያ ጊዜ ከእዳራሹ ወጥተን ንጹሕ አየር እንድንተነፍስ ተፈቀደልን ። እኔ በነበርኩበት ቀረሁ ። በኋላ እኛ በቡድን ተከፋፍለን የፖለቲካ ውይይት እንድናደርግ ታዝዘን ሳለ ካድሬዎቹና ዘበኞቹ ጫት እምጥተው ይቅሙ ነበር ። ባለ ጓንንቸር ቁልፍ ከሆነና ቀጫሉ በብርሃኔ (ከካድሬዎቹ አንዱ) ጥይት ከተሰበረ ሳጥን ውስጥ መጻሕፍት አወጡ። ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት ያላቸው መጻሕፍትና ጎን ጋዜጣ ባንድ በኩል ተቈለሉና የአንድ ከፍተኛ ም/ሊቀ መንበር የሆነው ብርሃኔ 'የማይነበቡ ' ለማድረግ በጥይት ደበደባቸው ። የደርግና የመኢሶን /የሕዝብ አደራጅ ጽ/ቤት ጽሑፎች እንድናነብና እንድንወያይ ተሰጡን ። እነ ሞላና እነ ብርሃኔ ጫታቸውን እያኘኩ በመረጧቸው ልጃገረድ እሥረኞች ጭኖች ላይ አረፍ ብለው ነበር።

ለሞላ ዕርፍት ካደረግን በኋላ እሰከ አራት ድረስ ውይይቱ ቀጠለ። ከአራት በኋላ በርከት ያሉ ፀረ-ኢሕአፓ መፈክሮች ተዜሙ ፥ መዝሙሮች ተዘመሩ ። ሁሉም ደስተኛ የሆነ መሰለ። ወሮበሎቹም በጫቱ መርቅነው ነበር። ከቀሽኦ አንዱ በድንገት አፈፍ ብሎ 'ፀጥታ ' ብሎ አምባረቀና አሁን ' የኢሕአፓን የከተማ ስኳድ አባላት ' ማጋለጫ ጊዜ ነው አለ። ከሞላ ጎደል ዘና ብሎ የነበረው ስሜት ድራሹ ጠፋ ። ወደ ፊት ብቅ ለማለት ማንም አልቃጣም ፤ ነገር ግን አንድ ዐይን አፋር የሚመስል የ ፲፯ ዓመት ልጅን ተተናኩሉት ። እውቀው ነበር ። የናቱ አንድዬ ልጅ እንድመሆኑ መጠን ልዩ ፍቅር ታሳየው በነበረችው እናቱ ተንቀባር ነበር ያደገው ። ይህችው እናቱ (ወይዘሮ ጽጌ ቤት ቡና ላይ ስንገናኝ) ' ልጄ ከመንግሥት ጋር እየተጣሉ ሲራወጡ እንደሚውሉት ሌሎች ልጆች አይደለም ፤ ሁል ጊዜ ከቤቱ አይለይም ' ብላ ሳትንማረኝ ቀርታ አታውቅም ነበር ። ይኸውና ያ ንጹሕ ምንም ያለተዘጋጀ ልጅ ዕርቃኑን ተደርጎ ማሰሪ ሰይል መወጠሪያ ላይ ተዘረጋ ። አንድ ስም ሰጣቸውና ወዲያውኑ አውርደው አብዮቱን በመቀላቀሉ አበጀህ አሉት ። እንዲያውም የሆነ

ፈላሽ መድኃኒት ቀሳሉ ላይ አፈሰሱለት ። መልእክቱ ግልጽ ነበር፣ አንዱን አጋልጥ ' የተለየ አስተያየት ' ይደረግልሃል።

እንደሚባለው የእናት ማህፀን ዝንጉርጉር ነውና ፣ ሰዎች በተለያዩ ብዙ ሽፋኖች ይመጣሉ። በዚህን ጊዜ አንድ ሐሞተ ቢስ እሥረኛ ብድግ አለና እዚያው ጎረቤት የሚገኘውን እናጢ ቤት፥ በመደበቅ ላይ ያሉ የኢሕአፓ አባላት እንደመጠለያ እንደሚጠቀሙበት ነገራቸው። ፈነጠዙ። አሳሽ ቡድን በፍጥነት ከጠቋሚው ጋር ሁኖ ወደቦታው እንዲሄድ ተደረገ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጠቋሚው ከንዱን ካንገቱ ላይ ታብቶ በወረደ የጨርቅ ቀለበት ውስጥ አሳቅፎ ተመልሶ መጣ። ተደብቀው የነበሩ ታጋዮች ወራሪው ቡድን ላይ የእጅ ቦምብ ወርውረው አንድ የቀበሌ ዘበኛ ገድለው ሌሎችን እሱን ጭምር አቁስለው እንዳመለጡ ነገረን።

ማክሰኞ ጠዋት በግለዳ ፥ ጠዋት ለሥራ የሚመጡትን ሠራተኞች በደፈጣ በመያዝ ሌሊቱን ሲጠብቅ ያደረው አሳሽ ቡድን 5 የእናጢውን ሠራተኞች ይዘው መጡ። እነዚህኑ ልብሳቸውን አስወልቀው ከቀዝቃዛ ቤት ከተቷቸው። ካድሬዎቹ ለሞተው ዘበኛ ቀብር ስለሄዱ እዳራሹ ጠዋቱን ወጥ ያለ ሆነ። ስለ ኢሕአፓ ትሮትስካይትነት ንግግር ሊያደርግልን የመጣ አንድ ካድሬ ብቻ ጎን የተባለው 'በኢሕአፓ የሚካሄደው' መጽሄት እንዲት ስታሊንን እንደተቸውና ስለዚህም (ኢሕአፓ) የለየለት ትሮትስካይት መሆኑን እንዳረጋገጠ ...ዓይነት አንቶ ፈንቶ ንግግር እያሰለቸን እዚያው ቆየ። እቀብር የሄዱት ወሮበሎች ሲመለሱ ንግግሩ ተቋረጠ። የተዘጋባቸውን ሠራተኞች ለማውጣት ምንም ጊዜ አላጠፉም።

እዚያው ሱቅ ውስጥ ይኖር ፥ እዚያም ይሠራ ነበር የተባለ ከሠራተኞቹ አንዱ አስቀድሞ መወጠሪያው ላይ ተደረገ። ከፍርሐትና ከብርድ የተነሣ ጥርሱ እየተንቀጫቀጨ ሲጋራ ጠየቀ። ከካድሬዎቹ አንዱ ለኩሰና አፉ ላይ ወተፈለት፣ ግን ወደቀበት። ሞላ በርግጫ መታውና ሲጋራው ላይ ቆመበት። አዳራሹ ውስጥ ካየናቸው እጅግ አሠቃቂ ከነበሩት የግብረ ሰይል እድራጎቶች አንዱ ነበር። እዚህ ሰውዬ ላይ የደረሰው ፊቱ ላይ ፥ ሰውነቱ ላይ፥ ጫማዎቹ ላይ ተደበደበ። የጎንለ ደም ከጀሮዎቹ ላይ ዘለላ ዘለላ እያበጀ ተንጠለጠለ። ያለ ውኃ ወይም ሳሙና የራስ ፀጉሩን

ላጨት ፡ ከጦርሶቹ እንዱን በጢንሳ መንግለው አወጡና አፉን ደም ሲሞላው እንዲጠጣው በማስገደድ አጥብቀው ያዙት። እንዲያም ሆኖ ወለሉን የደም ኩሬ አጥለቀለቀው። ያን ሁሉ ደም በማየታቸው አንዳንድ እሥረኞች አእምሯቸውን ሳቱ። ሰውዬው እሪ አለ፡ ታዲያም ጩኹቱን ለማፈን ሲሉ አፉ ውስጥ ቁሽኛ የሆነ፡ በዚህን ጊዜ ደግሞ በተጨማሪ በደም የተጨማለቀ የእግር ሹራብ አፉ ውስጥ ጉስጉሱ። ይህ እንዲህ እየተደረገ ሳለ፡ 'እቢት ማስደሰቱ' የሚለውን ዘፈን እየግረፉ ሮክ ብለን እንድንዘፍን አደረጉን። (ካድሬዎቹ) በኛ መካከል ተሰራጭተው ማን ሮክ ብሎ እንደሚዘፍን ማን እንደማይዘፍን ይመለከቱ ነበር። እያንዳንዱ ሰው ዘለግ አድርጎ ዘፍኗል ማለት እችላለሁ። የፐላስቲክ ከረጢት ለክሱና ጭኖቹና ከንዶቹ ላይ ጠብ ጠብ እንዲልበት አደረጉ። አንዳንድ ጊዜ ጉራዴ ያነሡና ከጭንቅላቱ በላይ ከፍ ያደርጉታል፡ በኛ ሁሉ ድንጋጤ ይደሰቱና ዝት አድርገው በጠፍጣፋው ወገን የታሠረውን እሥረኛ ይመቱታል። ምሰኪኑ ሰውዬ ከቁጥጥሩ ውጪ ዓይነ ምድሩን ለቀቀው። በመጨረሻም ጎሊናውን ሳተ።

ከዚያ በኋላ 'ምሣ 'ቀረበ'። ምንም እንኳ ለመሸሩፈን ብንሞክርም ብዙዎቻችን ልንበላ አልቻልንም። አዳራሹ ፀጥ አለ፡ እያንዳንዱ እሥረኛ ተደበረ፡ ሽብር ሠፈነ።

ከምሣ በኋላ አዳራሹ ይፀዳ ዘንድ በተለይም የግብረ ሰይሉ ዓውድ አካባቢ ወደ ውጭ እንድንወጣ ታዘዝን። ካዳራሹ ውጭ በጣም ወጣቶች የሆኑት እሥረኞች እርስ በርሳቸው መጫወት ጀመሩ።እንድ ሦስተኛ ክፍል የደረሰ የ ዘጠኝ ዓመት ልጅ ከጓደኞቹ ጋር እየተራወጠና እየተራገጠ መልካም ጊዜ እያሳለፈ ነበር፡ ታዲያ ከጓደኞቹ እርግጫ ለማምለጥ ሲሞክር በተደጋጋሚ ከአዳራሹ በር ጋር ተጋጨ። እሸልበት የነበረው ሞላ ነቃና በሩንሲክት ትንሹን ልጅ እዚያ አገኘው። ብድግ አድርጎም ውስጥ አስገባውና አሥር ትልቅ የብረት ዘለበት ባለው ቀበቶ ይደበድበው ገባ። ቀበቶው አሁንም አሁንም ገላው ላይ እንዳረፈበት ሲሙሀና ሲንሰቀሰት ሁላችንም ሰማነው። ሁላችንም ወደ አዳራሹ ስንገባ ሞላ አሁንም በሌላ ጩኽት ተቀበለን። 'ይህ ትንሽ አናርኪስት እንኳ አስካሁን የሰምንት አናርኪስቶችን ሥም ሸሸጎ ነበር፡ ግን ሽብሩ ምላሱን ፈታለት። ትላልቆቹማ ምን ያህል የደበቃችሁት ይኖር?' አለ።

በትንሹ ልጅ የተጋለጡትን ለማምጣት ሄዱ። ለኛም በዚያን ጊዜ፡ በኛ በኩል ስለሚጠበቀው ማጋለጥ አስመልክቶ እንድንጽፍ ወረቀት ተሰጠን። (ወረቀቶቹ ለተመረጡ እሥረኞች እንጂ ለሁሉም አልተሰጡም) አሳሹ ቡድን ጥቂት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይዞ ተመለሰ። ትልልቆቹ አልተገኙም ሲሉ ሰማናቸው። ብርሃኔ የአዲሶቹን እሥረኞች ምሪመራ ተረከበ። አባቷ ማረክ፡ እናቷ ኢትዮጵያዊት በሆነች አሊፍቴሪያ በምትባል ልጅ ጀመረ። ስለ ክልስቷ ትምክህታዊ ስድብ እየወረደባት ልብሷን እንዲታወልቅ ተደረገች። የአሥራ ሁለት ዓመት ልጃገረድ እንደመሆኗ መጠን በዚያ ሁሉ የወንድ እሥረኛ ፊት ዕርቃኗን መቆሙ አሳፈራት። ብርሃኔ ሥራዬ ብሎ ያጉጠጉጡ ጡቶቿ ላይ ይደበድባት ገባ። ፊጽሞ ኢሕአፓ እንዳልነበረችና የጠቁመባትን ልጅ ከትንሽ ወንድሟ ጋር ሲጣላ ለወንድሟ ረድታ እንድ ጊዜ ደብድባው ስለነበረ በዚህ የተጎሣ ይጠሳት እንደነበር ገለጠች። ልጁም ሲጠየቅ እሷ ያለችው ትክክል እንደነበረ ተናገረ። የሆነ ሆኖ ብርሃኔ ከኢሊፍቴሪያ ጋር የመጣችውን ትዝታ የተባለች ልጅ ተከቶ ደበደባት።

ዓርብ ጠዋት ከደርግ ጋር ካበሩት ድርጅቶች አንድ ካድሬ መጣና ያጠናናቸውን መዝሙሮች መረመረ። ከዚያም መዝሙሮቻችሁ ብስለት የላቸውም፣ ምክንያቱም ኢሕአፓ ትሮትስካይት ሳይሆን 'አናርኮ ሲንዲካሊስት ነው' አለና በዚያው መሠረት አዳዲስ መዝሙሮች አስጠንቶን ተመለሰ። ቀኑን ብዙ እሥረኞች መጡ። አንዳንዶቹ በጣዛ ራሳቸው መጥተው እጅ የሰጡ ነበሩ። ነገር ግን እነሱም ከግብረ ሰይል አላመለጡም። 'ዙሮ ዙሮ ቀይ ሽብሩ ከናታችሁ ማንፀን ላያወጣችሁ አይቀርም ነበር፣' ይሏቸው ነበር ግብረ ሰይል ፈጻሚዎቹ። ግምሻውን ብዙ ካድሬዎች ባካባቢው አልነበሩም፣ በጊዜም እንድንተኛም ተነገረን። ሁኖም ተረኛ መኩንኑ ብርሃኔ እንቅልፍ የሚነሣ ሕመም (ኢንሶምንያ) ነበረበትና ጊዜ ለማሳለፍ ሲል እንቅልፍ ወስዷቸው ወደነበረ የተወሰኑ እሥረኞች እድብቶ ሄደና በጣት እየተንከተከተ ይገርፋቸው ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሁላችንም ነቃን። ከዚያ በኋላ ፲፩ እሥረኞች (ኢሕአፓን የሚደግፈው የጉራጌ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላት ናችሁ በሚል የተወነጀሉ) መረጡና የጉራጌን ብሔራዊ ሙፈራ እንዲወጡ ገረፉቸው። በዚህ ደግሞ ተሰላቹና እንዲት ልጃገረድ መርጠ

" 'ቀይ ሽብር' እንደሚያፋፍምባት በመግለጽ ተኩሳተረባት:: እጎት ስለነበራት እንዲሰነባበቱ አድርጎ እየሳቀ ወደውጭ ጎትቶ አወጣት:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልቡ እስኪፈርስ እየሣቀ፥ ከኋላው ልጆቹ ፀጉሯ ተንጨብርሮ እያለቀሰች መጣ:: የተሰቀለው ልባችን መለሰ ብሎ በረጅሙ ተነፈስን:: ከሞት ጋር ሲወዳደር መደፈር ክብደት ተሰጥቶት የሚታይ አልመሰለም::

ቅዳሜ ዕለት ከፍ ከፍ ያሉት የቀሽአኮ አባላት የቀበሌ ባለሥልጣኖችና ካድሬዎች አለመኖራቸው ግልጽ ሁኖ ይታይ ነበር:: የኑሱ ቦታ በአጠቃላይ ሲታይ ወንጀል አደግና የአካባቢው ወሜኔዎች በሆኑ የበታች ሹማምንት ተይዞ ነበር:: እነዚህ አጭበርባሪዎች ጊዜያቸውን ያሳለፉት እኛን ሥጋትና ፍራቻ እንዲሰማን በማድረግ እኔ ሞሳና ብርሃኔን ለመምሰል በመሞከር ነበር:: ከኑሱ እንዱ እንዲት ልጃገረድ ከሌተሰቦቿ ጋር በስልክ እንድትነጋገር አደረጋትና መጥቼ ሂጫሌን እቀበላለሁ ሲል ሰማነው:: ሌላው ደግሞ የአካባቢው ባለ ጸቦ ቤት ልጆች የሆኑ ሁለት ልጃገረዶችን ገላቸውን እንዲታጠቡና ልብስ እንዲቀይሩ እቤታቸው ወሰዳቸው :: ሲመለስም ፖስቴ ብጤ ለቀሩት ዘበኞች ይዘላቸው መጣ:: የአንደኛው አጭበርባሪ ሚስት የነበረች ተይዛ መጥታ ' ከአናርኪስቶች 'ጋር ግንኙነት አለሽ በሚል ተመረመረች :: ሰውዬው ፥ስለፈታችው መበቀሉ መሆኑ ነበር::

እሑድ ዕለት በ፲፱ ሰአት ከቻሬ ከጠዋቱ ሳይ ዘገየ ብቻ ነበርና የነበረው ተነሥቼ ወደሱ ቀረብኩ:: የቀሽአኮ አባልና የከፍተኛ ዘበኞች አለቃ ነበር:: ' የቅድሥት ሥላሴ ቤተክርስቲያን የዓመቱ ክበረ በዓል ዛሬ ነው፤ ካድሬ እንግዳን ሐሙስ ዕለት ጠይቄው ትሂጃለሽ ብሎ ተሥፋ ሰጥቶኝ ነበር፤ ግን አልተመለሰም፤ ቅዳሴው እንዳያመልጠኝ እባክህ ሰደደኝ::' አልኩት 'ሞላን ጠብቂ' ግለት ሲጀምር አቋረጥኩና 'እነዚያ የጠፉ ቀጣሪዎቼን በሚመለከት እዚያው ተመልሼ መሥራት እቀጥልና የሚካሄደውን እንግርህለሁ፤ እኔን ምንም የማላውቅ ገረድ በኑሱ ወንጀል እንድሠቃይ አድርገውኛል' በማለት ንዴትን ያንፀባርቃል ብዬ በገመትኩት የድምጽ ቃና አክዬ ተናገርኩ::

'ማሩም ነው!' አለ ዘገየ:: 'ይህ ነው የሠራተኛ መንፈስ፤ የተቻለውን ያህል መረሻ እየሰበሰብሽ ከኔ በለተቀር ለሌላ

እንዳትነግሪ:: አስታውሺ፥ ለኔ ብቻ፤' ብሎ ከዚያ በደም ከተበከለ አዳራሽና ካጦር ጊቢው አውጥቶ ሸኘኝ.."

ይህን ክፍል ከመደምደማችን በፊት ባሕር ዳር ውስጥ መስከረም ፲፱፻፩፱ ዓ.ም. ተይዞ ከወር በኋላ ስለተገደለው ዕድሜው ፴ ዓመት ስለነበረ መምህር ብርሃኔ ቢሆንኝ እንጥቀስ:: ልዩ ልዩ ተፈጽሞበት እጅ እግሮቹም ተቁርጠው ነበር:: ግበረ ሰይል ፈጻሚዎቹ እጅ እግሮቹን የቁረጡት በተራ መጋዝ ሥጋውን ቁርጠው ገብተው እጥንቶቹን በመገዝገዝ ነበር ::

ጅማ ውስጥ ፥ ረኛነ ሰኣድ ውስጥ የነበረ አንድ ፖሊስ የራሱ ልጅ ከግድግዳ አጠገብ ተሠልፈው ለርሽና ከሚጠባበቁት አንዱ ሁኖ አገኘው:: ርሽናውን እንዲያስተውል የተጠራው ሕዝብ በፀጥታ ተመለከተ:: ፖሊሱም እዙን ፈጸመና በማግሥቱ ራሱን ገደለ::

እነዚህ እዚህ ያቀረብናቸውን የምስክርነት ቃሎች በሺዎች ስታባዛቸው የቀይ ሽብሩ አሠቃቂና በጣም አሳዛኝ ገጽታ ይበልጥ ቦግ ብሎ ይወጣል::

ማስታወሻዎች

ክፍል ሦስት

1. ቀይ ሽብሩ እንዲካሄድ በመወትወትና መጠየቂያም በማትረብ የተጻፉ ስሜት የፈነቀላቸው ጽሑፎችን በሚመለከት የመኢሶንን የሠፈው ሕዝብ ድምፅ የየካቲትና መጋቢት ፲፱፻፷፱ እትሞችን በሙሉ ይመለከቷል።
2. Korovikov, ibid,p. 94.
3. አንድ ተመልካች፣ "The Ethiopian Revolution" Monthly Review NY, July-August 1977, pp. 46-47.
4. Times, London, May 16, 1977.
5. Daily Telegraph, London, September 13, 1977.
6. Times, ibid.
7. J.C. Guilleband, "The Dergue's Red Terror" Guardian, London, Feb. 26, 1978.
8. Abyot vol. 2, no.6.
9. ተስፋዬን ለስኳዶቹ ያመላከታቸው የመኢሶን ካድሬ በራሁን ___ አሁን በስደት ፓሪስ ፈረንሳይ አገር ይኖራል። ተስፋዬ ራሱን በገደለበት ወቅት በተከፈተው ተኩስ በራሁን ማርዬ የሚባል ሌላ የኢሕአፓ አባል ተገድሳል።
10. ነጋ አየለ ከJohn Mrkakis ጋር Class and Revolution in Ethiopia, Nottingham: Spokesman,1978 የተባለውን መጽሐፍ በጋራ የጻፈ፣ የኮንሰ ብርሃኑ መንግሥት በአስከሬኑ ሊለየው ያልቻለ የኢሕአፓ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበረ።
11. እሥረኞች ሁነው ግዘረ ሰይል የተቀበሉና አሁን ተፈትተው በስደት ያሉ ሰዎች የምስክርነት ቃል።
12. የአምንስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት በኢትዮጵያ ላይ 1977 (G.C)
13. Selassie, Bereket H. "Political Leadership in Crisis" Horn of Africa, New Jersy (USA), vol.3 no.1,1980.

14. ለብሔርተኛ ግንባሮች ግልጽ የሆነ ወገንተኛ ድጋፍ ያላቸው በረሀትና ሌሎች፡ ለመግጠል ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ከመሣል ከእምብርቱ ወይም ለመላዋ ኢትዮጵያ ለማምጣት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያውያን ጎደሎች ያደረጉትን ትግል (የተከፈለውንም ዋጋ) ለማቃለል ከብዙ መጨነትና መጠበብ ውስጥ ይገባሉ። በረሀትና ጓደኞቹ ለብሔርተኛ ትግሎች የብቻቸው የሆነ ከብደት ይሰጧቸዋል፡ ከዚያም ዘንድ ለሌሎች ድርጅቶች ተገቢ ድርሻቸውን መስጠት የነሱን ፍቁር ድርጅቶች ከብደት ይቀንስ ይሆናል የሚል ስሜት ያደረባቸው ይመስላሉ። እንዲያውም በረሀት፡የኤርትራ ችግር ቢፈታ ኑሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ሌላ ችግር ባልነበረ ነበር! እስከማለት መድረሱ ዘገባ የጨለጠ ነው። (ታሰ ምልልስ፡ በVOA Focus Program, September 22,1984)

15. VOICE, British Review of Arab Affairs, August 10, 1979.

16. Guilleband, ibid.

17. ይህ የምስክርነት ቃል በቅድ መልክ፡ (በደራሲው ፈቃድ) ገና ካልታተመና እንድ መጽሐፍ ከሚወጣው በT.K. በእንግሊዝኛ ከተጻፈ ረቂት ተቆንጽሎ የተወሰደ ሲሆን ጊዜያዊ ርእሱ "ሙታንታ ካሳት፡ ግደላት! ___ ሴቶች በደርግ ላይ፡" 1985 (GC)

18. እናቨንፋለንና እናቸንፋለን የተለያየ ትርጉም ባይኖራቸውም፡ እናቨንፋለን፡ የደርግና የመኢሶን እናቸንፋለን የኢሕአፓና የደኃፈምቹ ተደርጎ ስለተወሰደ፡ በቀዩ ሽብር ጊዜ እናቸንፋለን ያለ ሁሉ እንደ "አናርኪስት" ይቁጠር ነበር። ጎብ አደርና ወዝ አደር የሚሉትም ቃላት የዚያው ብጤ ነበሩ። የተለያዩ የቃላት አጠቃቀምና አኮብ የአድኀሪነት ወይም የተራማጅነት አንድምታ ነበረው። ደርግም በቀላሉ የሚያልፈው አልነበረም። ሁለት የማተሚያ ቤት ፈደል ለቀማ ሠራተኞች በኢትዮጵያን ሄራልድ (Ethiopian Herald) የእንግሊዝኛ ጋዜጣ የመጀመሪያው ገጽ ራስጌ የሚጻፈውን ኢትዮጵያ ትቅደም፡ ፈደል ተዛውሮባቸው በትቅደም (tikdem) ፈንታ ትድከም (tidkem) ብለው በማሥራራቸው ተይዘው የቁም ሥቅላቸውን ካዩ በኋላ፡ የት እንደደረሱ አልታወቀም። በደርጊቱ ኢትዮጵያ የፈደል ግድፈት የሁለት ሰው ሞት።

ክፍል አራት

መደምደሚያ

ቀዩ ሽብር
ዋጋው የከበደ ድል

"ምንም እንኳ አንድ ሰውን መደምሰስ ቢቻልም፥
በመደምሰሱ ሀልውናው አይጠፋም፥ እንዲያውም
በአንጻሩ ...ገሳውን ሰድዶ ህልው መሆን ይጀምራል።
እኒህን እርስ በርሳቸው ይቃረኑ የሚመስሉ ሁቆችን
ነው ፈላሞ ቆራሞ ግዥዎች ሊጋተሯቸው
ያልቻሉት። - ግሞዱ እያጨደ ይጥላል፥
ወዲያውም ግር ማደግ ይጀምራል።"

ርይስዘርድ ካፑቺንስኪ (ሻህ አቭሻህ
ከተባለው መጽሐፍ ውስጥ)

"የትግላችን ግብና ዓላማ የጭቁኑንና የሠራውን ሕዝብ
ሰብአዊ መብቶች መረጋገጥ ነው።"
መንግሥቱ ኃ/ማርያም የካቲት ፲/ ፲፱፻፰

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ለሞት በዳረገና አካለ ስንኩላን ባደረገ፥ መላ ሀገሪቱንም በመዘበረ የሰው እልቂት ውስጥ አቸናፊዎችና ተቸናፊዎች ሊኖሩ ይችላሉን? መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ጓደኞቹ አቸናፊዎች እንደሆኑ፥ ቀይ ሽበሩም የወሳኝ ውጊያ ፍቱን መሣሪያቸው እንደነበረ አድርገው ያስባሉ። ከዚህም የተነሣ ያን ክፉ ቀን በዘፈን ያሞጋግሡታል፥ በድሳቸውም ይንበሣረሩበታል። ይህ መጠንከ የማይባል ዋጋ የተከፈለበት ድል ፣ እንዲህ ዓይነት ድል ነበር ተብሎ የሚታወቅ ከሆነ!

አሁን የጓላውን መለስ ብለን ለመማተር የሚያስችለንን ተጨማሪ ዕድል ይዘን ስንመለከተው፥ ዓላማው ለማሸበርና ለመግደል እስከሆነ ድረስ ሽብሩ አቸንፎ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን መንግሥቱ ኃ/ ማርያምም አላቸነፌም፣ ተቃዋሚው ወገንም

አልተረታም። ፲፱ኛውንም የተያያዘችው ኢትዮጵያ አሁንም በሽምቅ ወጊያዎችና በዓመፆች የታመሰች ናት፣ መንግሥቱም የአንጻራዊ ጥንካሬ አፍአዊ ምልክቶች ቢያሳይም በውስጡ ሥረ መሠረቱ የተዳከመ ነው። ሕዝባዊ ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም፣ ተቃዋሚውን ሁሉ ለመደምሰስ አልሆነለትም።

ከንገረ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለው ዓይነት የሆኑ መንግሥታት ለሕዝብ ፈቃድና ስምምነት መች ቦታ ሰጥተውት ያውቃሉ? የሚል ከርከር ሊነሣ ይችላል። እነሱ ዋና ሥራቸው አድርገው የሚጠመዱት ሕዝብን በጎይል ቅስሙን በመስበርና ሥልጣናቸውን በመከባከብ፥ ለዚህም ደግሞ ወታደራዊ ጎይላቸውን ለመጨመር ጥረት በማድረግ ላይ ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ሀቁ ይህ ይመስላል። ወታደራዊው መንግሥት በማሳመን ድጋፍ የሚያገኘበትን መንገድ አልተከተለም። ተጠቃሚዎቹን ለማሰባሰብና መደላድሉንም ለማጠናከር የታወጁትን ሥር ነቀል ለውጦች እንኳን ሊጠቀምባቸው አልተቻለውም የተወሰዱት የመሻሻል እርምጃዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ የማይጨበጡ ሕልሞች ሁነው ቀሩ። ይበል ፥ይበል፥ የተባለለት የመሬት ይዞታው መሻሻል ፈውዳላዊ ዝርፊያን ምሕረት በሌለው የወታደራዊ መንግሥት ምዝበራ ተክቶት አረፈ።

ቅሬታ እንደሚሥፋፋ፣ የተረጋገጠ ተሥፋፋም። ይኸውም ሕዝብን ሊያሳምን ወይም ሊማርክ በሚችል መንገድ ለመሠረታውያን ችግሮች መፍትሔ ሊሰጣቸው ስላልቻለ፥ ወይም ሊፈቱ በሚችሉበት አቅጣጫ እርምጃ ስላልተደረገ ነበር። በመጀመሪያው ወቅት ኢሕአፓና በጣም የነቃው ክፍል ነበር የአዲሱን ገዥ አምባገነናው እርምጃዎችና የጋለ ተምኔት የተቃወሙት። ባሁኑ ጊዜ አብዛኛው ሕዝብ ወታደራዊውን መንግሥት ይቃወማል ፣ በሺዎች የሚቆጠሩም በወህኒ ቤት፥ በስደት ላይ ናቸው ወይም ጫካ ገብተው ትግሉን በመቀጠል ላይ ይገኛሉ።

ምንም እንኳ የሥር ነቀል አቀንቃኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ያካሄደው ትግል ሌሎች ቦታዎች የተካሄዱትን ትግሉች

አካሄድ የተከተለ እንደሆነ አድርገው ስለዚሁ በቃላት የተዋቡ ንግግሮች ያንቋረቁሩ ቢሆንም ያንን መልክ የያዘ አልነበረም። ምናልባትም ከዚህ የተነሣ ኢሕአፓና ታግለው ራሳቸውን መሥዋዕት ያቀረቡ፥ ዕውቀት የጠለቃቸውን የውጭ አገር ማእምራን ምክር ባለመስማታቸው "ጥፋተኛ" ነበሩ ማለት እንችል ይሆናል። ቀበሌዎች፥ ሶቪየቶች(ወይስ ኮሚዩኖች ነበር?) ያስታውሱኛል፣ ያለውን የጣሊያን ኮሚዩኒስት ፓርቲው (፲.ሲ.አይ) ፓጂታን መስማት እንጂ እነዚሁ የተባሉት ቀበሌዎች ቢገድሏቸውም በገዛ ዓይናቸው ያዩት ብቻ ተጸዕኖ ሊያደርግባቸው ባልተገባ ነበር። በሃሲዲይና በሞሲኔ እንጋገር እነዚሁ ነፍሰ ገዳዮችና ማብረ ሰይል ፈጻሚዎች ነበሩና አብዮቱን በማራመድ ላይ የነበሩት እንዲያውም በእነሱ ላይ ጠመንጃ ማንጣት አልነበረባቸውም :: ለአውሮፓ የአባታዊነት አመለካከት ቢመስልም ለኢትዮጵያ ደረጃ፥ ደርግ ዴሞክራሲያዊ ነበር ብሎ የጻፈውና ግልጽ ያደረገው የእንግሊዙ ኮሚዩኒስት - ጆን ማሪትንስም እስ አክ። ወይስ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ዲሞክራሲን መጠየቃቸው ጨረታን ገቸብ እያዩ እንደማናፋት የሚቆጠር ነው ብሎ ያስጠነቀቀውን የፐሲኢውን ኤስ ካሪሉ አልሰሙትም?

ደግነቱ ኢሕአፓም ሆነ ሕዝቡ ለእንዲህ ዓይነቱ "ዕፀብ ድንቅ ዕውቀት " ጆሯቸውን አልሰጡም :: በራሱ መጣኝነትና ክትትል ሥር ሁኖ ዲሞክራሲ በትንሽ በትንሹ ተመጥኖ መስጠት አለበት ብሎ ሊመክራቸው የተነሣውን መኢሶንንም እንኳ አልሰሙትም። ራሱን ሞግዚት አድርጎ ሳቀረበውም መብታቸውንና አብዮታቸውን አሳልፈው ለመስጠት አሻፈረን አሉ። በዚህም አዋቂነታቸውን፣ ግልጽነታቸውንና ንቃታቸውን አስመሰከሩ። ለንጉሣዊ የተባለው መንግሥት የራሳቸው እንዳልሆነ ለነሱ ጥቅምም እንደማይሠራ አሳምረው አውቀዋል። ይህንን ለማረጋገጥ ከሌኒን ወይም ከሆን ሌላ ሰው ጥቅስ መጥቀስ አላስፈለጋቸውም፣አረመኔያዊ ከሆነ ጎይል ጋር ያደረጉት ጀግንነት የተመላበት ትግል በቂ ማስራጃ ነበርና።

ዋጋው ከፍ ያለ ነበር፣ ነገር ግን ሌላ ሊሆን ይችል ነበርን? ኢሕአፓ የተጠቀመበትን ሥልት፥ ጉዳትን ለመቀነስ በሚቻልበት መንገድ ለመለወጥ ይቻል እንደነበር ግልጽ ነው።

ሁኖም ተቃዋሚ ወገን እስኳልጠፉ ድረስ ግድያዎቹ አይጠፉም ነበር። ለዚህም ነው "መተንኮሱስ" በሚል ጆሮ ላይ በሚንጠለጠል ቃል ዙሪያ የሚሽከረከሩ ረቀቅ ያሉ ክርክሮች ሁሉ ግልጽ የሆኑ የመንበርከክና የመግዛት መመሪያዎች ሁነው ቁጭ የሚሉት አንድ ሥልጣንን የቀማ እምባገነናዊ መንግሥት በጎይል ልግዛችሁ ብሎ አፈፍ ሲል ሕዝቡ በተቃውሞ ለመነሣት መብት የለውምን? ብለን እንጠይቃለን። የተቈጣ ጅብ መላወሻ አሳጥቶ ቢያጣብብህ ፊት ለፊት ሂዶ መላተሙ ብልኀኑት ያለው ሥልት ላይሆን ይችላል፤ ግን ግብ ግቡ የማይቀር ነው።

በኢትዮጵያ ሁኔታ ጅቡ ከመጀመሪያው ቁጡ ነበር፤ እንዲያም ሁኖ ቀጠለ። እራት ለመሆን ራስን ከማቅረብ በስተቀር ቁጣውን የማብረጃ መንገድ አልነበረም። እዚህ ላይ የሚከተለውን የሀገራችንን ተረት ያስታውሷል። እንድ የእሀያ መንጋ፥ ከእካባቢው ጅቦች ጋር በሰላም ተስማምቶ ለመኖር ፈለገና ከጅቦቹ እንዱ ሲሞት አክብሮት ለመስጠትና ኀዘኑን ለመግለጽ ወደ ጅቦቹ ዋሻ ሄደ። ጅቦቹም የተደሰቱ መሰሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጅቦቹ፥ ለተሰበሰበው ኀዘንተኛ መሸኛ ይሆን ዘንድ የላይ የላይ ከንፈሮቻቸውን እንዲሰጡ ጠየቋቸው፤ በሁኔታው የተደናገጡት፥ ግን ቢሆንም ቅር ማሰኘት ያልፈለጉት እሀዮች የላይ የላይ ከንፈሮቻቸውን እበረከቱና ጅቦቹ አያጣጣሙ ሰለቀጡ። ከዚያም ጅቦቹ እሀዮቹ ላይ አፈጠጡና ጥርሳቸውን ገልፍጠው የማንገራገር ድምፅ በማሰማት" እኛ በኀዘን ተጠምደን ላለን እንዲት እዚህ ተቀምጣቸሁ ትግለቁብናላችሁ?" አሉና፥ እነሆም "ተተንኩሰው" እሀዮቹ ላይ ጉብ ጉብ አሉባቸው።

በመሠረቱ ይህ ጉዳይ እጅግ ገላጭ ከሆኑ ተረቶችና የስብከት ድርሳናት ክልል እንኳ አልፎ አልፎ የሚሄድ መሠረታዊ ነጥብ ነው። ፍጹም ሥልጣንን የታገሉት ሕዝባውያን ከፍሉት ሁሉ ሥልጣን ከእጃቸው እንዲሰርፅ፥ ዲሞክራሲ እንዲሠፍን ፈለጉ። ሥልጣን የቀሙቱ ደግሞ ሕዝቡ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የተባ ተሣትፎ እንዳይኖረው በማግለል የዚሁ ሥልጣን ሞግዚቶች መሆንን ፈለጉ። ሕዝቡ የተሰጠው ዕድል ፈንታ ጭብጨባውን ማቅለጥና በሚሹጉዳጉድለት ስሜት ቀስቃሽና ተራማጅ ዲስኩር መርካት ሆነ። ሕዝቡ

እምቢኝ ብሎ ሰላማዊ ተቃውሞ እደረገ፣ ደርግ ይህንን ተቃውሞ ሊያከሽፈው አልቻለም፤ ታዲያም እንድያውን ለመደምሰስ ይችል ዘንድ በትሩን ወደ መምዘዝ ተራመደ።

እነዚያ ዕውቀት የጠለቃቸው ማዕምራን ሊያከቸለችሉና "ይህማ የመደብ ትግል ነው፤ ከዚህ ሌላ ምን ይጠበቃል?" ሲሉ ድማፃቸው ሊሰማን ምንም አይቀረውም። መልካም። ግን ግን ነበር ለአብዮቱ የቆመው? እንድ አብዮት በአብዮቱ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን እነዚያኑ መደቦችና ሕዘቦች በመጨፍጨፍ ሊከናወን ይችላልን? ምን ዓይነት አብዮት ነው ወጎጻን በብዙኀኑ ጭቁን ሕዝብ ላይ የሚያስነሣ? ይህ መንግሥት የሕዝብን እምነት ያፈዘበት ማደንገዣው ሲከላ የፀረ አብዮት ወኪል መሆኑ ቦግ ብሎ ይወጣል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የጉሮ ሁኔታ መለኪያ መስፈርታችን ካደረግን የተደረጉት የማሻሻል ለውጠች ያለምንም ጥርጥር ባዶ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ሀገሪቱ ሰላም ይሁን በሔራዊ ልዕልና የላትም። እንደገና ዕውኃው እንደሚያሳየን ንጉሠ ነገሥታዊውን መንግሥት ተቃውመው ቁመው የነበሩቱ እነዚያው ሰዎች አሁን ደግሞ ይህንን ወታደራዊ መንግሥት ተቃውመው ቁመዋል። አንድ ዉደት አድርገን ስንመለስ ምሁራዊ፥ ዘረኛና የአደግዳጊዎች ከርከሮች በሚያስጸይፍ አኳኋን መሠረተ ቢስና ዋጋ የሌላቸው መሆናቸውን ያረጋገጣሉ።

መለኪያችን፥ ዕውነታ ወይም አስመሳይ ተራማጆች ያሚለጠጡን ሌላ ቃል ለመጠቀም ተግባር ነው። ወታደራዊው መንግሥት ራሱን ሶሻሊስት ወያም ዲሞክራሲያዊ አድርጎ ሊለፍፍ ይችላል፤ ነገር ግን ሕዝቡ አሱን የሚመለከተው በነፍስ ገዳይ ግልባብ ውስጥ ነው። በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰው የገደለ ከዚያ በላይ የሆነውን አካል ስንኩላን ያደረገ ነውና። "ሰው በጸቦ ብቻ አይኖርም" የሚለው አንጋገር ራሱ ብቻ በረሐብ አለንጋ በተገረፈች ኢትዮጵያ ውስጥ የኅለደፈ አንጋገር ይሆናል፤ ግን እዚህ ላይ ማከል የሚቻለው ማንም ቢሆን ከማርክሲያውያን ብሉያን መጻሕፍት ጥቅሶችን እየተመገበ ለረጅም ጊዜ መኖር እንደማይችል ነው። ለኢትዮጲያውያን፥ የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን መንግሥት የጭራት ገጽታ ውበት ሰጥቶ ሊያቀርብላቸው የሚችል ነገር የለም። ግራ ለሆኑ ቱሪስቶች፥

ቀበሌዎች የአብዮቱን ጊዜ የሩሲያን ሶቪየቶች ሊያስታውሷቸው ይችላሉ፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያውያን ቀበሌዎች የአብዮቱን ጊዜ የሩሲያን ሶቪየቶች ሊያስታውሷቸው ይችላሉ፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያውያን ቀበሌ ማለት ሞትና የፖሊስ ቁጥጥር ማለት ነው። ሶቪዮቶችና ኪዩባውያን ለአንጻንዶች እንደ ዓለም አቀፋውያን፣ እንደ እንድሩ ያንግ ለሚያስቡት ደግሞ እንዲያውም መረጋጋትን እንደሚፈጥሩ ጎይሉች መስለው ሊታዩ ይችላሉ። ለኢትዮጵያውያን ግን እኒህ ፈረንጆች የበላይ ገዥነትን የሚያመላክቱ ነበሩ፤ ናቸውም። የኑናስ ገጸዩ መንግሥት መቀጠል ምክንያቶች ሁኑው ያታዩታል። ኢትዮጵያውያን ኋላ ቀሮች ናቸው ማለት ይቻላል፤ እንደማንኛውም እንዲህ ዓይነት ሕዝብ ሁሉ የሚያምኑት በመጽሐፍት ላይ የተጻፉትን ወይም በሠሉ የምሁራን እንደበቶች የሚገለጹትን ሳይሆን የራሳቸውን ተመክሮ ነው። ለዚያውም ሮሮ ከመቶ ማንበብ አይችልም፤

ሽብሩ የወታራዊው መንግሥት ችንፈት መገለጫው ነበር። የጎይል እርምጃ ሳይወስድ፥ ወይም ከውጭ ቅጥረኞች ሳይጋብዝ ሥልጣን ላይ ሊያቆየው የሚችል ሕዝባዊ መሠረት መጣል ላለመቻሉ ማስረጂያ ነበር። በተጨማሪም ሽብሩ የየካቲት አብዮት መክሸፉን፥ ለዲሞክራሲና ለነጻነት የሚደረገው ሕዝባዊ ንቅናቄ መቐንፉን እጉልቶ አሳይቷል። ዝቅ ባለ ደረጃ ሲታይ ሽብሩ፥ ኢሕአፓን አጸከመ ፤ (ምንም እንኳ ፓርቲው ባይጠፋና ትጥቅ ትግሉን ቢቀጥልም) መንግሥቱን አጠናከረ፤ (ምንም እንኳ ለመግዛት የሚያስችለውን መረጋጋት ገና ማግኘት ቢኖርበትም) ማለት ይቻላል። ግን ይህ ነጥቡን እንዳለ መሳት ይሆናል። አዲስ አበባ ውስጥ ፀጥታ ሠፍኗል፤ ግን ያ ፀጥታ ከመካሰ መቃብር ፀጥታ ጋር እንደሚመሳሰል ማን ይክዳል? መንግሥቱ የተወደደም የተረጋጋም አይደለም፤ ርኮሳን መናፍስት እንዳኾበበት ነው ያለው።

ሽብሩ አረመኔያዊ ነበር፤ ግን ኢትዮጲያን ወደፊት ለማራመድ ሌላ መንገድ ነበርን? ይህ፥ ኋላ ቀር ሕዝቦች (በኑሉ አባባል) በዱላ ካልተገዙ በስተቀር ሊለወጡ አይችሉም ብለው በሚያምኑት የቀረበ ሌላ የክርክር ዘርፍ ነው። እንዲህ

ለሚሉት ይኸው መድኃኒት በእገራቸው ውስጥ ቢሰጣቸውስ? ብሎ የሚያስጠይቅ ነው። ኢትዮጵያ ትንቀሳቀሳለችን? ወዴት የሚለው አሁንም ተገቢ ጥያቄ ነው። ያለምንም ጥርጥር አሁን ኢትዮጵያ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካው መስክ እሥጊ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ይታያል። ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ምሕረት የለሽና ዲስኩረኛ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ካለፈው መንግሥት ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነት የቅርፅ ብቻ ነው። ሕዝቡ እየተራበ ነው፤ ብዝበዛ የተሥፋፋ ነው፤ ጦርነቶች የተሰያዩ የሀገሪቱን ክፍሎች እምሰዋታል፥ ዲሞክራሲያውያን መብቶች የሉም፤ ብሔራዊ ጭቆናና ከሉም ለመላቀቅ የሚደረጉት ጦርነቶች የሀገሪቱን እንድነት እየተፈታተኑ ነው።የምሥራቁ ለዕል ኃያላን መንግሥት ሀገሪቱን በሱ የበላይነት ሥር አስገብቷታል ፤ ሕዝቡ ወደ ስደት እንዲሸሽ ተገድዷል። በእርግጥ ኢትዮጵያ የአብዛኞቹ ዜጎጀ እሥር ቤት ሁናለች። አሲስ ኢን ዘ ወንደርላንድ በተባለው መጻሐፍ ውስጥ ያለ እንድ ገፀ ባሕርይ እዚያው ከነበሩበት ቦታ ላይ ለመገኘት ያለማቋረጥ መሮጥ ያስፈልጋል ይላል። የኢትዮጲያ መንግሥት በብዙ ረገድ ወደ ኋላ ለመሄድ እየርጠና እየገደለ ነበር። በተጨፈጨፉት በሺዎቹ የሚቈጠሩ አስከሬኖች ላዩ አዲስ ኢትዮጵያ አልበቀለችም። የምናየው "ያችኑ አሮጌይቱን ኢትዮጵያ" ነው። በፍጹም ሥልጣን ሥር የተከደኩኗች፥ ግፍ ረሐብና ሞት የሠፈነባት ኢትዮጲያ። በርግጥ የተከናነበችው ማልባብ እንደተተከሉት ሐውልቶች ሁሉ አዲስ ነው።

ወታደራዊዉ መንግሥት የየካቲትን አብዮት ገደለው፤ ሽብሩ ደግሞ አፈር አለበሰው። ተመቃብሩ ላይ ሲጸፉ የሚገቡ የ"ቀይ ሽብሩ" ነክነት ያላቸው ተስማሚ ቃላት ናቸው። ገሃዎችንና ሕዝቡን የሚያካልል የደም ጅረት በመካከላቸው አለ። ይህም የመንግሥቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅዶች ከንቱ ያደርጋቸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የወትሮው የደም መመሰሻው መንገድ ደምን በደም መበቀል ነወ፤ ባሁኑ ጊዜ ዕውነታው የሚያሳየው ግጭቱ በገዢዎችና በተገዢዎች መካከል ባለው የተፋፋመ ጦርነት የሚፈታ መሆኑን ብቻ ቢሆንም፥ ከዚህ ተለየ ሁኔታ ቸርነትና ይቅርታን በተከተለ መንገድ እንዲፈታ ተሥፋ ማድረግ የተገባ ነው። የየካቲት አብዮት በኢትዮጲያ ዜጎች ላይ የተጣበቀውን ዐመፅ እያላቀቀው ነበር፤ ነገር ግን

ደርግ መልሶ ሊያጠቃቀው ችሏል። እንደገና ለማላቀቅ ደግሞ ዐመፅን መጠየቁ አልቀረም። እንዲያ አያለ እየተጥመለመለ ይቀጥላል፤... መጨረሻውን መመኘት ተገቢ እንጂ ነው።

ምንም ዓይነት ሁኔታ ፣ ምንም ዓይነት ማጠየቂያ ይምጣ እንደዚያ ዓይነት ዘዴ ተእንግዲህ ፈጽሞ መደገም እንደሌለበት ተቃውሚዎቹንና በሕይወት የተረፉትን በማስተማር ሽብሩ ራሱን እንዳቸነፈ ተሥፋ ይደረጋል። ደርግ ለእንዲም ለሁሌም የሚቸነፍበት መንገድ፥ ሽብሩም ለዳግመኛ ትንሣዔ ምንም ዓይነት ዕድል የማያገኝበት ዘዴ ይህ ብቻ ነው። እስከዚያ መቼስ ምን ይደረጋል ሮ"ቀይ ሽብሩ" መስተጋብራን በእንድ አብዮታዊ ገጣሚ የተሳለፈውን መልእክት ከልባቸው ቢጥፉት የሚበጃቸው ይሆናል፤

"በሚቀጥለው ዙር በመጪው ጊዜያት፥
ተውት አትድከሙ ይብቃ የናንት ምጣት፥
በድቅድቅ ጨለማ በደረቁ ውድቀት
መዝጊያዎቻችንን ለመስበር ለማንኮት
እኛ ነን ምንመጣ ተንግዲህ እታክቱ
ቢኛን በማለዳ ቢኛን በሌሊቱ
ለናንተውም መዝጊያ ይድረሰው ሪድኤቱ፤"

ማጭዱ አጭዶ አጭዶ ጥሏል፤ ነገር ግን ሣሩ መልሶ አድጓል፤ ይበልጥ ለምልሞ፥ ይበልጥ ዛላው አምሮ፥ ይበልጥም ተጀንኖ።